ሰር አርተር ኮናን ዶይል

# ሼርሎክ ሆልምስ

## የአጸፋው ሙሽ እንቦቅልሽ እና ሌሎች ሥራዎች



ትርጉም፦ መጋቦ በለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰር አርተር ኮናን ዶይል

# ሼርሎክ ሆልምስ

## የአዳኙ ውሻ እንቆቅልሽ

## እና

## ሌሎች ሥራዎች

ትርጉም፡- ወ/ሃዋሁ በለው

t.me/OLDBOOKSPDF

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
All Rights Reserved

የመጀመሪያ ዕትም ሐምሌ 2003

ቀደምት ትርጉም

እና ካረኒና

ለአስተያየት

መጋየሁ በለው
ፖ.ሣ.ቁ 31774
አዲስ አበባ
E-mail:- wegayehu.belew950@gmail.com

t.me/OLDBOOKSPDF

# ማውጫ


ጨዋው ወንደላጤ---------- 7

ጥቁር እንግዳ---------- 38

የአዳኙ ውሻ እንቆቅልሽ---------- 63

የወጣቷ ቢስክሌተኛ ፈተና---------- 155

ሞገደኛው መርማሪ---------- 187


t.me/OLDBOOKSPDF

# ሰር አርተር ኮናን ዶይል

አርተር ኮናን ዶይል ከ1859-1930 (እ.ኤ.አ) የኖረ እንግሊዛዊ የህክምና ባለሙያ እና ዕውቅ የረጅምና የአጫጭር ልቦለዶች ደራሲ ነው። ሰር አርተር ኮናን ዶይል በሼርሎክ ሆልምስ የወንጀል ክትትል የፈጠራ ሥራዎቹ ይታወቃል። ዶይል የሥነ-ጽሑፍ አቀራረብ ስልቱን ለመቀየር ሲል በ1893 ሼርሎክ ሆልምስን ለመግደል ቢሞክርም ከአንባቢያን በተረበበት ከፍተኛ ግፊት *The Hound of the Baskervilles* በተሰኘው ድርሰቱ የሼርሎክ ሆልምስን ትንሣኤ ለህዝብ አብሠረ።ል። ይህ ድርሰቱም ከሁሉም የላቀ መሆኑ ይነገርለታ።ል።

አርተር ኮናን ዶይል ሚያ. 22 ቀን 1859 *ለክትላንድ* ውስጥ ኢድንበርግ በተባለ ቦታ ተወለደ የከፍተኛ ትምህርቱን በሰቶኒ ሀርስት ኮሌጅና በኢድንበርግ ዩኒቨርስቲ ተከታትሏ.ል። ከ1882-1890 በእንግሊዝ አገር ሳውዝ ሲ፣ በህክምና ሙያው አገልግሏ.ል። ሼርሎክ ሆልምስን እንደ ዋና ገጸ-ባሕሪ አድርጎ ከጻፋቸው ስልሳ ያክል ድርሰቶቹ *A Study in Scarlet* የተሰኘውን የመጀመሪያ መጽሐፉን ለንባብ ያበቃው በ1887 ነበር። ሆልምስ ጠቅሰል ያሉ ሃሳቦችን በታ-ትኖ በመመርመር የንጥሮችን መነሻ ለማወቅ የሚያደርገው ጥረት የአንባቢን አዕምሮ ሰቅዞ የመያዝ ምት-ሓታዊ ሃይል አለው። በድርሰቶቹ ውስጥ ተራኪና ሆልምስ የቅርብ አጋር ሆኖ የተሳሰው ዶክተር ዋትሰንም የራሱ የሆነ ታላቅ ድርሻ ያለው ገጸ-ባህሪ ነው። ዶይል የደራሲነት ሥራው ተሳክቶለት የመጀመሪያ ሥራዎቹን ካሳተመ በግምት አምስት ዓመታት በኋላ የህክምና ሥራውን ትቶ መሉ ጊዜውን ለሥነ-ጽሑፍ ሰጠ።

ሼርሎክ ሆልምስን እንደ ዋናው የወንጀል ተከታታይ አድርጎ ለንባብ ካበቃቸው ሥራዎቹ መካከል በዚህ ትርጉም ውስጥ የተካተተው፣ *The Hound of the Baskervilles (1902)* እና አጫጭር ልቦለዶችን ያሰባሰቡት *The Sign of Four (1890)፣ The Adventure of Sherlock Holmes (1892)፣* እንዲሁም *His Last Bow (1917)* ይገኙበታ.ል። እነዚህ በወንጀል ክትትል ላይ ያተኮሩ ሥራዎቹ ዶይል ዓለም አቀፍ ዝናን እንዲጎናጸፍ አድርገውታ.ል። ሆልምስም ከገጸ-ባሕሪነት ባለፈ ግሉ-ሰብዕናው በብዙዎች ዘንድ የሚታወቅ የቤከር ጎዳና አካባቢ ኗሪ ተደርጎ እስከ መቆጠር ደርሷ.ል። ከበቦች በስመ ተሰያመውሉታ.ል።

ሰር አርተር ኮናን ዶይል በዚህ ብቻ አላበቃም። በታሪክ ተመስ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎቹም ይታወቃል። ከነዚህም ውስጥ Micah Clarke (1818)፣ The White Company (1890)፣ Rodney Stone (1896)፣ Sir Nigel (1906) እና A Story of Waterloo- ታሪካዊ ድራማ (1894) ይገኙበታል።

ኮናን ዶይል በቦር ጦርነት (1899-1902) በህክምና መደብ ያገለገለ ሲሆን ከጦርነቱ መልስ ኢ-ልቦለድ የሆኑ- ታላቁ የቦር ጦርነት(1900)፣የደቡብ አፍሪካ ጦርነት፡-ምክንያቱና ባሕሪው የሚሉና ሌሎችንም የታሪክ መጻሕፍት ጽፏል።

1880ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ የመንፈሳዊ አስተሳሰብ አራማጅ የነበረ ሲሆን ይህ አመለካከቱ ልጁ በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ከሞተ በኋላ አየጨመረ መጣ። የኮናን ዶይል ግለ-ሪክ፣ትዝታና ጉድለ ታትሞ ለንባብ የበቃው በ1924 ነው። ዶይል ጁላይ 7 ቀን 1930 ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

በዚህ ትርጉም ውስጥ የተካተቱት አጫጭር ወንጀል-ነክ የፊጠራ ታሪኮች ደራሲው በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በሀያኛው መጀመሪያ ካሳተማቸው የተለያዩ መድበሎች የተመረጡ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ The Adventure of the Noble Bachelor- ጨዋው ወንደላጤ በሚል፣ The Adventure of the yellow Face- ጥቁር አንግዳ እና The Adventure of the Solitary Cyclist- የወጣቷ ቢስክሌተኛ ፈተና በሚል የተረቡት ትርጉሞች፣Selected Works of Sir Arthur Conan Doyle:-Sherlock Holmes በሚል ርእስ አራቱን የደራሲው ሥራዎች ባቀፈውና በእያንዱ አሳታሚዎች(ሕንድ) ከታተመ ትልቅ መድበል የተወሰዱ ናቸው። የአፋኙ ውሻ አንቆቅልሽ (The Hound of the Baskervilles)፣ በAlan Ronaldson በተሳለ አቀራረብ ተዘጋጅቶ በ1976 ከታተመ መጽሐፍ፡ የተተረጎመ ሲሆን ምጎደኛው መርማሪ (The adventure of the Dying Detective)፣ His Last Bow በሚል ርእስ አ.አ.አ በ1917 ከታተመ መድበል የተወሰደ ነው።

መልካም ንባብ!!

t.me/OLDBOOKSPDF

# ጨዋው ወንደላጤ

ጋብቻየን ልፈጽም ጥቂት ሳምንታት ብቻ ቀርተውኛል። በቤከር ጉዳና ሆልምስ በሚኖርበት አፓርታማ ከእሱ ጋር ተዳበዩ ነው የምኖረው። አንድ ቀን ከሰዓት ዠኋላ ሆልምስ ወጣ ብሎ ተናፍሶ ሲመለስ ጠረጴዛው ላይ ደብዳቤ ተቀምጦ ያገኛል። በነፋስ የታጀበው የመኸር ወቅት ገናብ በዕለቱ ቀኑን መሉ ከቤት እንዳልወጣ አድርጐኝ ነው የዋለው። በአፍጋኒስታን ዘመቻ ላይ ሰውነቱ ውስጥ ገብታ የቀረችው ጥይትና የቀኑ ቅዝቃዜ ተባበረው ምቾት ነስተውኛል። በመሆኑም በአንድ ወንበር ላይ ተቀምጬ በሌላው ላይ ዕግሮቼን ዘርግቻለሁ። የዕለቱን ዜና በያዙ ብዙ ጋዜጦች ዙሪያየን ተከበቤ አንዱን ሳነሳ ሌላውን ስጥል ቆየሁና ሁሉንም አገላብጬ ስጨርስ ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ትልቅ ኢንቨሎፕ አየሁት። ማን እንደጻፈው በማሰላሰልም ተስ ብየ ሄጀ ተመለከትኩት።

"በጣም ደስ የሚል መልዕክት" አልኩት ገና ወደ ቤት በመግባት ላይ እያለ ። "በትክክል የማስታውስ ከሆነ የጧት ደብዳቤዎችህ ከዓሣ ነጋዴ ወይም ከመርከብ ውስጥ አስተናጋጅ ሳይሆኑ አይቀሩም።"

"እውነት ነው፣ ደብዳቤዎቼ የተለያዩ ናቸው። ልዩነት ደግሞ ውበት ነው" አለ ፊገግ እያለ። "በጣም ደስ የሚሉት ትሕትና የተለባሱት ናቸው። ይኸኛው ግን የምፈልገው ዓይነት አይመስለኝም። የተሰመደው ዓይነት ተራ ህበራዊ ውጥንቅጥ፣ የስርቆትና የቅሦፊት ጠማር ነው።"

የፖስታውን እሽግ ቀዶ አነበበው።

"አ! ይኸ የሆነ ደስ የሚል ነገር ሳይኖረው አይቀርም"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ማህበራዊ ጉዳይ አይደለም?"

"የተለየ የመደያ ችሎታን የሚጠይቅ"

"እናስ ከባለሥልጣን ደንበኞችህ?"

"በእንግሊዝ ውስጥ ካሉ ከፍተኛ ባለሥልጣናት አንዱ"

"ውድ ጓደኛዬ አንካን ደስ ያለህ!"

"አሁን የማረጋግጥልህ ዋትሰን፣ እኔ ትልቅ ግምት የምሰጠው ለደንበኛዬ የሥልጣን ደረጃ ወይም ማዕረግ ሳይሆን ለጉዳዩ ፈታኝነት ነው። የሚያስደስተኝም ይኸው ነው። ይሁን እንጂ አዲስ ምርመራ ላያስፈልገው ይችላል። የሰሞኑን ጋዜጦች ልብ ብለህ አንብበሃቸዋል?"

"በመጠኑ" አልኩት በሀፀት ስሜት በማዕዘኑ አካባቢ ወደ ተቆለለው የጋዜጣ ክምር እያመለከትሁ። "ምንም አይሠራልኝም።"

"ጥሩ አጋጣሚ ነው። ምናልባትም መረጃውን ለእኔ ልታስተላልፍልኝ ትችላለህ። ወንጀል ነክና ጋዜጣን የሚመለከቱ ዜናዎችን ከማንበቤ በስተቀር ሌላውን አላየሁትም። ሁለቱውም ትምህርት ሰጪ ስለሆነ ነው። በትርብ ጊዜ የተፈፀሙትን ድርጊቶች ተከታትለህ ከሆነ ግን ስለ ሎርድ ሳይመንና ጋብቻው የተሳፈውን አንብበህ መሆን አለበት።"

"እሱንማ በሚገባ፣ በስሜት ተውጨ ነው ያነበብኩት።"

"በጣም ጥሩ። በእጅ የያዝኩት ደብዳቤ ከሎርድ ሳይመን የተላከ ነው። አንብልሃለሁ። አንተ ደግሞ እነዚህን ወረቀቶች በደንብ ተመልከተህ ምን ማድረግ እንዳለብን ትነግረኛለህ። ደብዳቤው እንዲህ ይላል---



t.me/OLDBOOKSPDF

"ውድ ሚስተር ሸርሎክ ሆልምስ፡ በሚሣዊ አስተሳሰብህና ነፃ ውሳኔ አስጣጥ ችሎታህ ሙሉ አምነት እንድጥልብህ ያደረገኝ ልዑል ባዘወተር ነው። በመሆኑም ጋብቻዮን ከተመለከተ ስለተፈሀመው አሰቃቂ ድርጊት የአንተን መደዊ ምክር ለመጠየት ውሳኔ ላይ ደርሻለሁ። የስኮትላንድ ያርዱ ሚስተር ሌስትራድ ጉዳዩን ይዘታል። ይሁን እንጂ የአንተ ትብብር ቢታክልበት ምንም ተታውም እንደማይኖረው አስረግጦ ነግሮኛል። እንዲያውም ተጨማሪ ድጋፍ ከአንተ እንደሚያገኝ ያስባል። በአሥር ሰዓት እደውልልሃለሁ። ጉዳዩ በጣም አሳሳቢና ቅድሚያ የሚሰጠው ስለሆነ ሌላ ቀጠሮ ቢኖርህ እንኳን ታስተላልፈዋለህ ብሎ ተስፋ አደርጋለሁ።

ያንተው ታማኝ፣
ሳይመን

በአሥር ሰዓት ነው ያለው። አሁን ዘጠኝ ሰዓት ሆኗል። ከአንድ ሰዓት በኋላ ይደርሳል ።"

ስለዚህ ከአንተ ጋር ለመነጋገር ጊዜ አለኝ። ጉዳዩን በጥሞና ለማጤላት ታግዘኛለህ። አንተ ጋዜጦችን በቅደም ተከተል እያዘጋጀህ ሃሳቡን አሳጥረህ ማስታወሻ ትይገልኛለህ። እኔ ደግሞ ስለደንበኞችን ማንነት መረጃዎችን አጠናቅራለሁ" አለና ከመቅረዙ አጠገብ ካለው የመጻሕፍት መደርደሪያ አንድ ቀይ ሽፋን ያለው ዳጉስ ያለ መጽሐፍ አወጣ።

"ይኸውና" አለ ቱጭ ብሎ መጽሐፉን ጭኑ ላይ እያስቀመጠ። "ሎርድ ሮበርት ዋልሲንግ-ሃም ሳይመን የባልሞራል-ሐውም ሁለተኛ ወንድ ልጅ። በ1846 የተወለደ የአርባ አንድ ዓመት ጉልማሳ ነው። የሥራ ሃላፊነቱ በቅርቡ የተዋቀረው የቅኝ ግዛቶች አስተዳደር ሚኒስትር ነው። መስፍን (ዱክ) የነበሩት አባቱ በአንድ ወቀት የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ነበሩ። ለእኛ ሥራ ጠቀሚታ አለው ባይባልም የትውልድ ሐረጉ ከፍተኛ ከሚባለው የነር ግንድ የሚመዘዝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው። አሁን ተጨበጭ የሆነ ነገር ለማግኘት ወደ አንተ ልመለስ።"

"የምፈልገውን ለማግኘት ብዙም አልተቸገርክም" አልኩት። "ምክንያቱም መረጃዎቹ የቅርብ ጊዜ ስለሆኑና በጉዳዩም ስለተመሰጥክ ነው። ሆኖም በእጅህ ላይ ሌላ ያላለቀ ጉዳይ ስላለ ወደ አንተ ለማስተላለፍ አልደፈርክም። አንተም በጀመርከው ጉዳይ ላይ ሌላ ጣልቃ ሲገባብህ አትወድም።"

"እ፣ ስለ ዕቃ መጫኛ መኪናው ጉዳይ! አሱማ ቀላል ነው። ችግሩም ተፈቷል። ከጋዜጦች ያገኘኸውን መረጃ መርጠህ አምጣልኝማ!"

"የመጀመሪያው ይኸውና። የግል አስተያየት በሚለው የሞርኒንግ ፖስት ጋዜጣ ላይ ያገኘሁት ነው። አንደምታየው ከጥቂት ሳምንታት በፊት የተጻፈ ነው። 'የጋብቻ ዝግጅት እየተደረገ ነው' ይላል። 'የሚሰማው ጭምጭምታ እውነት ከሆነ በባልሞራል መስፍን ሁለተኛ ልጅ በሎርድ ርበርት ሳይመኝ በአሶይሲየስ ዶራን ብቸኛ ሴት ልጅ (ሳንፍራንሲስኩ ክሊፎረኒያ) በወይዘሪት ሐቲ ዶራን መካከል የጋብቻ ሥርዓት ይፈጸማል' ይልና ያበቃል።"

"እጥር ምጥን ያሰና የሚፈለገውን ሃሳብ የያዘ" አለ ሆልምስ ረጅምና ቀጭን እግሮቹን ወደ እሳቱ እየዘረጋ።

"በተመሳሳይ ሣምንት ይኸንኑ አንልቶ የዓፈ አንድ የሕዝብ ጋዜጣም አለ። እሱ ደግሞ እንዲህ ይላል። 'የዘመኑ የነፃ ንግድ መርህ የአገር ውስጥ ሃብታችንን እያሳደደ ስለሆነ የጋብቻውን ገበያ የሚቆጣጠር ደንብ እንዲወጣ ጥሪ እንደሚቀርብ ታውቀ። በመላው አትላንቲክ የሚገኙ ቡነጃጂት ቀስ በቀስ የታላቋ ብሪታንያን መሳፍንት በእጃቸው እያስገቡ ነው። ለዚህም ይመስላል፣ ሎርድ ሳይመን ከክሊፎርኒያው ሚሊየነር ብቸኛ ሴት ልጅ ከወይዘሪት ሐቲ ዶራን ጋር ጋብቻ ለመፈፀም መወሰኑን በይፋ አሳውቋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሱርድ ሳይመን በቶንጀዋ ልጃገረድ ፍቅር ተንበርክኳል። የቱጃሩ ነጋዴ ልጅም በብዙ ሺህ የሚቆጠር የጥሩሽ ገንዘብ እንደምትሰጥ ይጠበቃል። ሱርድ ሳይመን ከተወሰነ የርስት መሬት ያለፈ የራሱ የሆነ ሀብትና ንብረት የለውም። እናም ተጠቃሚው አሱም ጭምር እንጅ እሷ ብቻ አይደለችም። ከእንዲህ ዓይነቱ ጥምረት እሷ የምታተርፈው ነገር ቢኖር ከሪፖብሊካንነት ወደ አቻ የእንግሊዝ ወግ አጥባቂነት ለመሸጋገር ያስችላታል።"

"ሴላስ?" አለ ሆልምስ እያዛጋ።

"ሴላም አለ። በሞርኒንግ ፖስት ጋዜጣ ላይ ጋብቻው ብዙም ጋጋታ የሌለበት፣ ጫጫታና ሁካታ በማይበዛበት ሐኖቨር አደባባይ በሚኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን እንደሚፈፀም፣ የቅርብ ግንኙነት ያላቸው በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ በሥነ ሥርዓቱ ለይ እንደሚገኙና መሽሮቹ ላንካስተር አካባቢ ወደተዘጋጀላቸው ቤት እንደሚገቡ ተገልጿል። ከሁለት ቀናት በኋላ ሮብ ቀን መሆኑ ነው፣ የጋብቻው ሥነ ሥርዓት እንደሚፈፀምና የጫጉላ ጊዜያቸውንም የሚያሳልፉት ፒተርስፊልድ በሚገኘው በልዕል ባከውተር መናፈሻ እንደሚሆን ታውቋል። እነዚህ ሁሉ ማስታወቂያዎች መሽራዋ ከመጥፋቷ በፊት የተነበቡ ናቸው።"

"ከ... ከ... ከምን በፊት?" ሲል ሆልምስ ጠየቀ።

"ከሴትዮዋ መጥፋት በፊት"

"መቼ ነበር የጠፋች?"

"የጋብቻው ዕለት ቁርስ ላይ"

"በጣም የሚደንቅ ነው። ያልታሰበ፣ አስገራሚ ድራማ!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እም፣ እኔንም እጅግ ያስደነቀኝ ጉዳይ ነው-እስከ አሁን ከሰማነው ሁሉ ጥቂት ፈንጥጦ ያለ።"

"እንደዚህ ዓይነት ነገር ብዙ ጊዜ የሚሆነው ከጋብቻ በፊትና አንዳንዴም ጫጉላ ላይ ነው። የዚህ ዓይነት አጋጣሚ አይቼም ሰምቼም አላውቅም። እስቲ ዝርዝር ሁኔታውን አስረዳኝ።"

"ጋዜጣው ላይ ያሉ መረጃዎች ሁሉንም ያጠቃልላሉ ብለህ ማሰብ የለብህም--ተጠንቀቅ"

"ትናንትና ጠዋት በወጣ ጋዜጣ ላይ ያገኘሁት አንድ መጣጥፍ ነው። ላንብልህ። ርዕሱ 'በታወቀ ሠርግ ላይ ልዩ ድራማ ተፈፀመ' ይላል።

"የለ-ርድ ሮበርት ሳይመን ቤተሰብ ከጋብቻው ጋር ተያይዞ በተፈፀመው ድርጊት ከፍተኛ ድንጋጤ ላይ ወድቋል ። የጋብቻው ሥነ ሥርዓት በትናንት ጋዜጦች ላይ እንደታወጀው በቀዳሚው ቀን ሚት ተፈጽሟል ቢባልም ውስጥ ለውስጥ ሌላ ተባራሪ ወሬ እየተዛመተ መሆኑ የታወቀው ግን በኋላ ነው። ለዚህ የአደባባይ ምሥጢር ለሆነው ጉዳይ ጆሮ ባለመስጠት ወይም በመደበቅ የሚገኝ ጥቅም እንደሌለ ሁሉም ይረዳል።

"በሐኖቨር ቅዱስ ጊየርጊስ ቤተክርስቲያን በተፈፀመው የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ከቅርብ ቤተሰብ አባላት ማለትም ከመ·ሸራዋ አባት፣ ከመ·ሸራው ታናሽ ወንድምና እህት በስተቀር ማንም የታደመበት አልነበረም። ከዚያ በኋላ የሁሉም ጉዞ ላንክስተር ወደሚገኘው ወደ መ·ሸራት አባት ቤት ነበር። በዚህ ሁኔታ ውስጥ አንድ ስሟ ያልታወቀ ሴት ከመ·ሸራው ጋር የሆነ ጉዳይ እንዳላት በመግለጽ ወደ ቤት ካልገባሁ በሚል ግርግር ፈጥራ ነበር። በእልፍኝ አሽከሮችና በአስተናጋጅ ሃይል ነው ተገፍትራ እንድትወጣ የተደረገው። ቀድማ ወደ ቤት የገባችው መ·ሸራ ብዙም ላትቆይ ጥሩ ስሜት



t.me/OLDBOOKSPDF

እየተስማት እንዳልሆነ በመግለጽ ለዕረፍት ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። ያቀደታዋ ጊዜ መራዘም ሴላ አሰባልታ ሊያስከትል እንደሚችል የሠጋው አባት ወደ ልጅቷ መኝታ ክፍል ሲሄድ ለአጭር ጊዜ ብቻ ንበታ ልብስ ቀይራና ባርኔጣዋን አድርጋ ተጣድፋ መውጣቷን ከደነገጡርዋ ይረዳል። በር ላይ ከሚያስተናግዱት ጥበቃዎች አንዱ፣ የሆነች ሴት ከቤት ወጥታ ስትሄድ ማየቱን ቢናገርም ማንነቷን መግለጽ አልፈለገም። አባቷና መ·ሽራው የጠፉች መሆኗን በማረጋገጥ ለፖሊስ ሪፖርት አድርገዋል። ጉዳዩን ለማጣራት ጠንክራ ክትትል እንዲካሄድም ጠይቀዋል። እስክ ትናንትናው ምሽት ግን የልጅቷ አድራሻ ሊገኝ አልቻለም። ሆኖም በክተማው ውስጥ አንዳንድ አለባልታዎች ይናፈሱ ስለነበር ቀደም ሲል ረብሻ የፈጠረችው ሴትዮ በቅናት መንፈስ በመ·ሽራዋ ድንገት መሰወር እጇ ይኖርበታል በሚል ጥርጣሬ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር እንድትውል ተደረገ።"

"ጨረስክ በቃ?"

"በሌላ ጋዜጣ ላይ የወጣ አንድ ነገር ብቻ ይተረፍል። እሱም ግን የግል አስተያየት ነው።"

"ምንድነው እሱ?"

"ረብሻ የፈጠረችው ወይዘሪት ፍሎራ የምትባለው ሴት በፖሊስ መታሠሯ እውነት ነው። ከመ·ሽራው ጋር ለተወሰነ ዓመታት የቅርብ ግንኙነት እንደነበራቸው ታውቋል። ዝርዝር ሁኔታው አልተገለፀም። በመገናኛ ብዙሃን የተገለፁት ሁሉም መረጃዎች በእጅህ ላይ ያሉ ይመስለኛል።"

"በጣም ጥሩ! ይኸን ጉዳይ ከግቡ ሳላደርስ ወደ ኋላ አላፈገፍግም። የሉርድ ሳይመን መምጫ ሰዓት እየደረሰ ነው። እንዲያውም በእኛ ስዓት ጥቂት ደቂቃዎች አልፈዋል። የመጥሪያ ደወሉ እየጠራ ነው። የተከበረው ደንበኛችን



t.me/OLDBOOKSPDF

መጥታል። ለመውጣት እንዳታስብ ነገሮችን ለማስታወስ ያመች ዘንድ የአንተ መኖር ወሳኝ ነው።"

"ሎርድ ሮበርት ሳይመን" አለ ተላላኪው በሩን ቦግ አድርጐ እየከፈተ ። ደስ የሚል ቁመና ያለው ረጋ ያለ መልክ መልካም ጐልማሳ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ቢሆንም ለማዘዝም ሆነ ለመታዘዝ ዝግጁ ሆኖ ቀርቧል። ነቃ ያለና አለባበሱ ያማረ ነው። ከትከሻው ጐበጥ፣ ከፀጉሩ ሽበት ማለቱ ዕድሜውን ለመገመት ያስችላል። ግራና ቀኝ እየተመለከተና በቀኝ እጁ መነጽሩን እያስተካከለ ገባ።

"ጤና ይስጥልን ሎርድ ሳይመን!" አለ ሆልምስ ተነስቶ እጅ እየነሳለት። "እባክህ ወንበሩ ላይ አረፍ በል። አሱ ዶክተር ዋትሰን ይባላል፣ ጓደኛየና የሥራ ባልደረባየ ነው። ወደ ምድጃው ጠጋ በልና በጉዳዩ ላይ በሰፊው እንነጋገራለን።"

"አንተም እንደምትገምተው ጉዳዩ በጣም ልብ የሚያቆስል ነው ሚስተር ሆልምስ። እንደዚህ ዓይነት ነገር በተለይ በከፍተኛው የማሕበረሰብ ክፍል አካባቢ ይፈፀማል ብየ ባልገምትም እጅግ አስከፊ የሆኑ አያሌ ችግሮችን እንደፈታህ አገነዛባለሁ።"

"እንዲያውም ከዚህም በላይ "

"ምን አልክ?"

"በተመሳሳይ ጉዳይ ከከፍተኛ ባለሥልጣናት መካከል የመጨረሻ ደንበኛዬ ንጉሥ ነው"

"እውነትክን ነው? እንደዚያ መሆኑን አላውቅም። የየት አገር ንጉሥ?"

"የስካንዲናቪያ ንጉሥ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ሆኖ ነው? ሚስቱ ጠፍታበት?"

"የደንበኞቼን ምሥጢር የመጠበቅ ሥነ-ምግባራዊ ግዴታ እንዳለብኝ ታውቃለህ። ለአንተም ቢሆን እንደዚሁ ለማድረግ ቃል እገባልሃለሁ።"

"እውነት ነው! እውነት ነው! ይኸን ስለጠየቅሁህ ይቅርታ። የእኔን ጉዳይ በተመለከተ ግን ላንተ ሊያግዝ ይችላል የምትለውን መረጃ ሁሉ ለመሥጠት ዘግጁ ነኝ።"

"አመሰግናለሁ። ማግኘት የሚገባኝን መረጃ ከጋዜጦች አግኝቻለሁ። ከዚህ በላይ አልፈልግም። ለምሳሌ እዚህ ጋዜጣ ላይ የወጣው ትክክል ነው ብየ አገምታለሁ። ስለመ·ሽራዋ መጥፋት ማለቱ ነው።"

ሱርድ ላይመን ጋዜጣውን ተመለከተው። "አዎ፣ እዚህ ላይ የማየው ትክክል ነው።"

"ወደዚያ ድምዳሜ ከመድረሳችን በፊት ብዙ ተጨማሪ ማስረጃዎች ያስፈልገናል። አንተን በቀጥታ በመጠየቅ የማገኛቸው መልሶች ወደ እውነታው ያደርሱናል ብየ አስባለሁ።"

"እንደዚያ እንድታደርግ ነው ምኞቴ"

"ወይዘሪት ሐቲ ዶራ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኛችሁት የት ነው?"

"ከአንድ ዓመት በፊት፣ ሳንፍራንሲስኮ"

"አሜሪካ ሄደህ ታውቃለህ?"

"አዎ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ቀለበት አሥራችኋል?"

"አላሠርንም"

"ጓደኞሞች ነበራችሁ?"

"ቤተሰቧን አይቼ ተደሰትሁ። እሷም መደሰቱን አውቃ ስለነበር ተግባባን።"

"አባቷ በጣም ሐብታም ነው?"

"በፖስፊክ አካባቢ ተወዳዳሪ የሌለው ቱጃር ነው ይባላል።"

"ሃብቱን እንዴት ነው የሰነው?

"በወርቅ ማዕድን ሥራ ተሠማርቶ። ከጥቂት ዓመታት በፊት ያጣ የነጣ ድሃ ነበር።"

"እሺ፣ ስለ ወጣቷ ልጅ ባህሪ ያለህ ስሜት ምን ይመስላል- ስለ ባለቤትህ ጠባይ?"

ሎርድ መነጽሩን አስተካከለና ጥቂት እንደማሰብ ብሎ "ትሰማኛለህ ሚስተር ሆልምስ?" አለው። "ባለቤቱ አባቷ እንዳሁኑ ሃብታም ከመሆኑ በፊት የሃያ ዓመት ዕድሜ ነበራት። በዚያን ጊዜ በማዕድን ማውጫ ካምፖች፣ በዱርና በገደሉ በነፃነት ትዘዋወር ነበር። እናም ዕውቀቷን የሸመተችው ከትምህርት ቤት ሳይሆን ከተፈጥሮ ነበር ማለት ይቻላል። እሷ በአገራችን አባባል ወንዳወንድ የምትባል ዓይነት ሴት ነበረች። ጠንካራ፣ ሃይለኛና ነፃ ናት። ምንም ዓይነት ባሕላዊ ተዕእኖ አይበግራትም። በጣም ብርቱ ናት። ሐሳቧን ለመለወጥ ፈጣን ፣ ውሳኔዋን ለመተግበርም ደፋር ናት ለማለት ፈልጌ ነው። በሌላ በኩል በጨዋነቷ ባላምን ይሽን ሁሉ ክብር ባልሰጠኋት ነበር። ክብሯን የሚነካ ነገር ከመጣ ውርደት ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላለመውደቅ የጀግንነት ሞክን እንደምታስቀድም አልጠራጠርም።"

"ፎቶግራፉ አለህ?"

"የያዝኩት ይመስለኛል።"

ማስታወሻውን ከፍቶ የቆንጆ ሴት ልጅ መልክ አሳየን። ፎቶግራፍ አይደለም። ውበትን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ሥዕል እንጅ። ረጅም ፀጉሯ፣ ትላልቅ ዓይኖቿና እምቡጥ ከንፈሮቿ እጅግ ማራኪ ናቸው። ሆልምስ አስተውሎ ተመለከተና ማስታወሻውን ለሎርድ ሳይመን መለሰው።

"ከዚያ ወጣት ወደ ሎንደን ስትመጣ ትውውቃችሁን አደሳችሁ፣ አይደል?"

"አዎ፣ ባለፈው ዓመት ከአባት ጋር ወደ ሎንደን መጣች። በተደጋጋሚ ተገናኘን፣ ተለበት አሠርን፣ ከዚያም አሁን ተጋባን።"

"ያመጣችው ጥሎሽ ብዙ እንደነበር አገምታለሁ።"

"መካከለኛ ነው።ይህን ያክል ጥሎሽ በእኔ ቤተሰብ ውስጥ ያልተለመደ አይደለም።"

"በእርግጥ ጋብቻው ያለተለት ስለሆነ ጥሎሹ አንተው ጋ የሚቀር ነው?"

"ይህን ጉዳይ በሚመለከት ጥያቄ አላቀረብኩም።"

"አስፈላጊም አይደለም። በሠርጉ ዋዜማ ላይ ከወይዘሪት ዶራን ጋር ተገናኝታችሁ ነበር?"

"አዎ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ስትገናኙ የነበራትስ ስሜት ምን ይመስል ነበር? ጥሩ ነበር ትላለህ?"

"የተለየ ነገር አልነበረም። እንደተለመደው ስለወደፊቱ ኑሯችን ምን ማድረግ እንዳለብን ነበር የምትናገረው።"

"በጣም ጥሩ። የሠረገ ዕለት ጠዋትስ?"

"በተቻላት መጠን ድምቅ ብላ ነበር--ቢያንስ እስክ ሥነ ሥርዓቱ ፍፃሜ ድረስ።"

"ከዚያ በኋላ ያየኸው ለውጥ ነበር?"

"እውነቱን ለመናገር ከዚህ ቀደም አይቼባት የማላውቀውን የመቆጣት ስሜት ያየሁባት ከዚያ በኋላ ነው። የተፈጠረው አጋጣሚ ግን ያን ያክል ኩበደት ያለውና ለምክንያትነት የሚበቃም አይለደም።"

"ለሁሉም መረጃውን እንወቀው"

"አ! የሕፃን ሥራ ነው ። ወደ ቤተክርስቲያኑ ስንገባ የፊት ለፊቱን በር አልፋ በመሄድ ላይ እያለች የያዘችው እቅፍ አበባ ወደቀባት። ባጋጣሚ ዘለግ ያለ ቁመት ካለው ባለ ድጋፍ አግዳሚ ወንበር ላይ ነበር የወደቀው። በግምት ከአንድ ደቂቃ በኋላ አንድ የሆነ ሰው አንስቶ በእጁ ላይ አደረገላት። ምን ሆና እንደነበር ስጠይቃት የሰጠችኝ መልስ አጋጣሚ ነው የሚል ቢሆንም በሠረገላ ወደ ቤት ስንሄድ በሰበብ አስባቡ የመነጫነጭ ስሜት ይታይባት ነበር።"

"መደገፊያ ባለው አግዳሚ ወንበር ላይ የሆነ ሰው እንደነበር እየነገርከኝ ነው። ሌሎች ጥቂት ታዳሚዎችም እዚያው አካባቢ ነበሩ አይደል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እም። ቤተክርስቲያን ክፍት ስለነበር እነሱ አላዩም ማለት አይቻልም።"

"ይህ ሰው ከባለቤትህ ጓደኞች አንዱ ሊሆን አይችልም ትላለህ?"

"በጭራሽ! ሰውየው እዚህ ግባ የማይባል ተራ ሰው ነው። ልብ ብየም አላየሁትም። አሁን ግን ከዋናው ነጥብ ያፈነገጥን ይመስለኛል።"

"ወይዘሮ ሳይመን ከሠርጉ ስትመለስ መጀመሪያ ይታይባት የነበረው የተረጋጋ የጨዋነት መንፈስ መቀነሱ እንዳለ ሆኖ ወደ አባታ ቤት ስትመለስ ምን አደረገች?"

"ከደንገጡርዋ ጋር ስትነጋገር አይቻታለሁ"

"ደንገጡሯ ማን ትባላለች?"

"አሊስ ትባላለች። አሜሪካዊትና ከካሊፎርኒያ አብራት የመጣች ናት።"

"የምሥጢር ሠራተኛ ትሆን?"

"ትንሽ የሚበዛባት ይመስለኛል። አመቤታ ትልቅ ነፃነት ስለሰጠቻት ሊሆን ይችላል። አሜሪካ ውስጥ ለእንደዚህ ዓይነት ነገሮች የተለየ አመለካከት ነው ያላቸው።"

"ከዚች አሊስ ከምትባል ሴት ጋር ለምን ያክል ጊዜ ነው የተወያዩት?"

"ለጥቂት ደቂቃዎች። እኔ ግን ሌላ ነገር እያሰብኩ ነበር።"

"ምን እንደተባባሉ አልሰማህም?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ወይዘሮ ሳይመን ስለ ይገባኛል ጥያቄ ጉዳይ የሆነ ነገር ተናግራለች። ባልተለመደ የአነጋገር ዘዴ ትናገር ስለነበር የተናገረችው አልገባኝም።"

"የአሜሪካኖች አነጋገር አንዳንዴ ይፈጥናል። ባለቤትህ ከሠራተኛዋ ጋር ተነጋግራ ስትጨርስ ምን አደረገች?"

"ቱርስ ወደተዘጋጀበት ክፍል ገባች።"

"እሮህን ይዛ?"

"ብቻዋን። በእንደዚህ ዓይነት ነገሮች ላይ በጣም ነፃ ሆና ነው የምትንቀሳቀስ። አሥር ደቂቃ ገደማ ተቀምጠን እንደቆየን ቸክላ ተነሳችና የሆኑ የይቅርታ ቃላት እያጉረመረመች ክፍሉን ጥላ እንደወጣች አልተመለሰችም።"

"እሊስ የምትባለው ደገጡርዋ እንደምትለው ግን ወደ ክፍሏ ገብታ በመሸራ ልብሷ ላይ ረገፎም ካፖርት ደርባና ባርኔጣ አድርጋ ነው ወደ ውጪ የወጣች።"

"እውነት ነው። ከዚያ በኋላ በሐይድ መናፈሻ ከፍሎራ ሚላር ጋር ስትሄድ ታይታለች። ፍሎራ ሚለር ማለት ረብሻ ፈጠርሽ ተብላ ተይዛ እስክእሁን በአሥር ላይ ያለች ናት።"

"በዚች ወጣትና በእንተ መካከል ስላለው ግንኙነት ዘርዘር አድርገህ ብትነግረኝስ?"

ሎርድ ሳይመን ትክሻውን እንደመነቅነቅ አደረገና ራሱን አነቃቃ። "ለጥቂት ዓመታት በጓደኝነት ቆይተናል። በጣም የተቀራረበ ግንኙነት ነበረን ማለት አችላለሁ። በጣም እንክባክባ ስለነበር እኔን ለመውቀስ በቂ ምክንያት የላትም። ግን የሴቶችን ባሕሪ ታውቃለህ ማስተር ሆልምስ ። ፍሎራ በጣም ጥሩ ልጅ ብትሆንም ግልፍተኛነቷም የዚያኑ ያክል ነው። ግንኙነታችን በጣም የጠበቀ ከመሆኑ የተነሳ ሊሆን ይችላል፣ ለማግባት



t.me/OLDBOOKSPDF

በዝግጅት ላይ መሆኔን እንደሰማች በጣም አሳፋሪ የሆነ ደብዳቤም ጽፋልኛለች። ጋብቻው ላይ ብዙ ታዳሚ እንዳይኖርና በቤተሰብ ብቻ እንዲወሰን ያደረግሁትም ቤተክርስቲያን ውስጥ ብጥብጥ ሊነሳ ይችላል በሚል ፍራቻ ነው። ከቤተክርስቲያን ተመልሰን ዶራን ቤት ስንደርስ ገፈታትራ ለመግባት ሞክራ ነበር። በባለቤቴም ላይ ብዙ የስድብ ናዳ አውርዳለች። ለመምታትም ታጥታለች። እኔ ግን ይህ ሊሆን እንደሚችል ተጠራጥሬ ስለነበር ሲቪል የለበሱ ፖሊሶች እንዲጠብቁ አደረግሁ። እነሱ ናቸው ገፈታትረው ያስወጧት።"

"ባለቤትህ ይኸን ሁሉ ሰምታለች?"

"በጣም የገረመኝ ይኸው ነው፤ አልሰማችም።"

"ግን እኮ ከዚያ በኋላ ከሴትዮዋ ጋር ስትሄድ ታይታለች።"

"አዎ፤ የስኮትላንድ ያርዱ ሚስተር ሊስትራድ ይህን ጉዳይ በጥሞና እየተከታተለው ነው። ፍሎራ ባለቤቱን አታላ ካስወጣች በኋላም አስከፊ በሆነ ወጥመድ ውስጥ ልትከታት ትችላለች የሚል ፍራቻ አሳድሯል።"

"አዎ፤ መጠርጠሩ ተገቢ ነው።"

"አንተስ የሚሆን ይመስልሃል?"

"ከመጠርጠር ያለፈ አይደለም። አንተስ ይሆናል ትላለህ?"

"ፍሎራ እንካ ንስ በእሷ በዝንብም ላይ ጉዳት አታደርስም።"

"ቅናት የማያስደርገው ነገር የለም። ትልቁ የባህሪ መገለጫ ነው። አንተ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለህ አመለካከት ምንድ ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ ሃሳብ ለማግኘት አንጂ ሃሳብ ለማፍለቅ አልመጣሁም። ያሉትን መረጃዎች ሁሉ ሰጥቻለሁ። ይሁን አንጂ ለጠየቅኸኝ ጥያቄ ድርጊቱ በውስጣ ትንሽ የፀጸናጥና የመረበሽ ስሜት አሳሰደረባትም ለማለት አይቃጣኝም።"

"በአጭሩ ድንጉኛ መረበሽ ታይቶባታል እያልከኝ ነው?"

"አዎ፣ ፊቷን ስለማዞሯ ሳስብ፣ ያዞረችብኝ በእኔ ላይ አይመስለኝም። በሌሎች ያልተሳካ ምኞትና ድርጊት እንጅ ከዚህ በተሻለ ልገልፀው አልችልም።"

"ይሁን፤ ይህም ግምት ውስጥ የሚገባ አባባል ነው" አለ ሆልምስ ፈገግ እያለ። "ሎርድ ሳይመን አሁን መረጃዉን አሰባስቤ ለመጨረስ የተቃረብክ ይመስለኛል። አንድ ጥያቄ ልጨምር። ቱርስ ለመብላት ስትቀመጥ የፊት ለፊቱ መስኮት ወደ ውጭ ለማየት ያስችል ነበር?"

"ከጐን በኩል ያለውን መንገድና መናፈሻ ነበር ማየት የምንችለው።"

"ጨርሻለሁ ። ከዚህ በኋለ አንተን እዚህ አሥራ ማቆየት አልፈልግም። እደውላለሁ።"

"ጉግሩን የመፍታት ዕድል የሚኖርህ ይመስልሃል?" አለ ደንበኛችን ከመቀመጫው እየተነሳ።

"ፈትቼዋለሁ።"

"ኧ፣ ምንድነው?"

"ፈትቼዋለሁ -አልክህ"

"ታዲያ ባለቤቱ የት ነው ያለችው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዝርዝር ሁኔታውን በቅርቡ እንግርሃለሁ።"

ሎርድ ሳይመን ራሱን ነቀነቀና፣ "ከእኔና ከአንተ የተሻለ አስተዋይ · አዕምሮ ያላቸውን ሰዎች ሊጠይቅ ይችላል የሚል ግምት አለኝ" ሲል ሥጋቱን ገለፀና ግርማ ሞገስ ባልተለየው የቆየ ባህላዊ ሥርዓት ጉንበስ ብሎ እጅ በመንሳት ወጥቶ አብስ አለ።

"ሎርድ ሳይመን የእኔንና የእሱን አዕምሮ በአዕል ሚዛን ላይ ማስቀመጡ ለእኔ ትልቅ ነገር ነው" አለ ሼርሉክ ሆልምስ እየሳቀ። "ከዚህ ሁሉ አድካሚ ከሆነ መስቀለኛ ጥያቄ በኋላ ውስኪና ሶዳ እንዲሁም ሲጋራ የሚያስፈልገኝ ይመስለኛል። ጉዳዩን በተመለከተ ምን መደረግ እንዳለበት ደንበኛችን ወደ ቤት ከመግባቱ በፊት ውሳኔ ላይ ደርሻለሁ።"

"በራቸ ሆልምስ!"

"የዚህን ያክል ባይሆኑም ተመሳሳይ ጉዳዮች ብዙ ጊዜ አጋጥመውኛል። ሰፊ ምርመራ ማካሄዴ በነገሮች ላይ የነበረኝን ብቸኛ አጣርቼ ለማወቅ አስችሎኛል። ሁልጊዜም ባይሆን፣ ዘርዘር ብለው የሚቀርቡ መረጃዎች አሳማኝ ናቸው--"

"ግን እኮ አንተ የለማኸውን ሁሉ ሰምቻለሁ።"

"ለተሞክሮ የሚያግዙ ቀደምት የምርመራ ሃይሎችን ያላገለበጥሁ ቢሆንም፣ከጥቂት ዓመታት በፊት ተመሳሳይ የሆነ ድርጊት አበርዲን በሚባል ከተማ፣ከዚህም የባሰ ደግሞ መኒክ ውስጥ ተፈጽሞ ያውቃል። ከነዚህ ውስጥ አንዱ... ሴስትሬድ መጣ! እንደምን ዋልክ ሴስትሬድ! ከብፈው ላይ ብርጭቆ ይዘህ ና፣ ሲጋራም ከፖኮው አውጣ!"

ዕውቁ የመንግሥት መርማሪ አጭር የመርከበኛ ጃኬት ለብሶ ክራባት አድርጓል። አለባበሱ መርከበኛ ይመስላል። ጥቁር ሼራ ቦርሳ በእጁ ይዟል። አጭር ሠላምታ ለጥቶን



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁጭ ከማለቱ የተጋበዘውን ሲጋራ አቀጣጠለ።

"ምን አዲስ ነገር አለ?" ሲል ሆልምስ ዓይኑን እያቁለጨለጨ ጠየቀው። "ደስ ያለህ አትመስልም።"

"በጣም ከፍቶኛል። የዚህ ጉደኛ፣ የሎርድ ሳይመን ሠርግ ጉዳይ ፋታ አሳጥቶኛል። ምኑንም ልጨብጠው አልቻልኩም።"

"እውነትክን ከሆነ ታስገርመኛለህ!"

"እንደዚህ ዝብርቅርቅ ያለ ነገር ተሰምቶ ያውቃል? ቁንን መሉ በዚሁ ሥራ ተጠምጂ ነው የዋልኩት።"

"ገናብ ያበሰበሰህ ትመስላለህ" አለው ሆልምስ እጁን መርማሪው ከለበሰው የመርከበኛ ጃኬት ላይ ጣል አድርጉ።

"ወንዝ ለወንዝ ስንከራተት ነዋ!"

"እስቲ ስለ እግዚአብሔር፣ ለምንድነው ወንዝ ለወንዝ የምትንከራተተው?"

"የወይዘሮ ሳይመንን አስከሬን ፍለጋ።"

ሼርሎክ ሆልምስ ከተቀመጠበት መንበር ላይ ወደ ኋላ ተለጥጦ ከት ብሎ ከልቡ ሳቀ።

"የትራፋልጋርን አደባባይ ኩሬውን ዞረኸዋል?"

"ምን ለማለት ፈልገህ ነው?"

"ምክንያቱም ሴትዮዋን የማግኘት ዕድሉ እዚያም ሊኖር ይችላል ብየ ስላሰብኩ ነዋ!"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሌስትራድ ጓደኛዬን በቁጣ ገላመጠው። "ስለ ጉዳዩ ከ'ሀ' እስከ "ፐ" የምታውቅ መስለኝ።" አለ ግንባሩን አኮሳትሮ።

"አዕምሮየ ተጨባጭ መረጃዎችን ብቻ እንዲቀበል ዝግጁ አድርጌዋለሁ።"

"እንዲያ ነው! ስለዚህ መንኩራኩቱ ምንም ፋይዳ አያመጣም እያልከኝ ነው።"

"የሚያመጣው ፋይዳ ያለ አይመሰለኝም።"

"እንደዚያ ከሆነ እነዚህ ነገሮች እንዴት እንደተገኙ ብትገልጽልኝ?" አለና ቦርሳው ውስጥ ያሉትን ነገሮች አያወጣ አስተመጣቸው። በውሃ የተነከረ የሙሽራ ልብስ፣ ጥንድ የሙሽራ ጫማ፣ የሙሽራዋን አክሊል ከነመሸፈኛው፣ ሁሉም በውሃ ተነክረዋል። "ተመልከት!" አለ የሠርግ ቀለበት አውጥቶ ከሌሎች ዕቃዎች ጋር እየጨመረ። "ከዚህ በላይ የምታደርገው ብዙ ነገር ያለ አይመሰለኝም። ትሰማኛህ ማስተር ሆልምስ?"

"እየሰማሁህ ነው" አለ ጓደኛዬ የሚያጨሰው የሲጋራ ጭስ ሰማያዊ ቀለም ያለው ቀለበት እየሰራ ሲወጣ እየታየ። "ከወንዙ ውስጥ ያወጣኻቸው ናቸው?"

"እንዲያውም! የመናፈሻው የጥበቃ ሠራተኛ ነው ወንዙዳር ሲንሳፈፉ ያገኛቸው። የእሷ ልብሶች መሆናቸው ተረጋግጧል። እኔ እንደማመስለኝ ልብሶቿ እዚህ ከሆነ አስከሬኗም ከዚህ ብዙ የማርቅ አይመስለኝም።"

"...እንዴት ከዚህ ድምዳሜ ሰይ ልትደርስ ቻልክ?"

"ከአንዳንድ መረጃዎች የፍሎራ ማሳረ እጅ ያለበት ስለማመስል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"አስቸጋሪ ይሆንብሃል ብየ አሰጋለሁ።"

"እውነትክን ነው?" አለ ሌስትሬድ ምርር እያለው። "ሆልምስ፣ ትንታኔህና የደረስክበት ድምዳሜ የምትመስደውን ርምጃ የተሳሳተ ያደርገዋል ብየ እፈራለሁ። በደቂቃዎች ውስጥ ሁለት ስህተቶች ሰርተኻል። ይኽ ቀሚስ ከፍሎራ ሚላር ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑ አያጠራጥርም።"

"እንዴት ሆኖ?"

"ቀሚሱ ውስጥ ኪስ አለ። ኪሱ ውስጥ የመታወቂያ መያዣ አለ። በመታወቂያ መያዣው ውስጥ ማስታወሻ አለ። ማስታወሻው ደግሞ ይኽውና" አለና አውጥቶ ፊት ለፊት አስተመጠለት። "አዳምጠኝ! 'ሁሉም ነገር ሲያልቅ እንገናኛለን። ቶሎ አንድትመጭ ።ኤፍ. ኤች.ኤም' ። ስለዚህ የእኔ ሃሳብ ሌዲ ሳይመን ፍሎራ ሚላር ወጥመድ ውስጥ ስለገባች ለመ·ሽራዋ መጥፋት ተጠያቂዎቹ እሷና ተባባሪዎቿ ናቸው የሚል ነው። ይህ የተፈረመበት ማስታወሻ ያለምንም ጥርጥር በር ላይ ስትደርስ በሚስጢር በእጇ እንዲገባ ተደርጓል—"

"ጉበዝ ሌስትሬድ፣" አለ ሆልምስ ሳቅ እያለ። "በእውነት ትልቅ ሥራ ነው የሠራኸው። እስቲ አምጣው ልየው።" እንደዋዛ የተቀበለውን ወረቀት ሲመለከት በጣም ደስ አለው።

"ያን ያክል አስደሳች ሆኖ አገኘኸው?"

"በጣም እንጂ እንኳን ደስ ያለህ?"

ሌስትሬድ የድል አድራጊነት ስሜት እየተሰማው ተነስቶ ለማየት ጉ·ንበስ አለ። "ለምን?" አለ ድምፁን ከፍ አድረጉ።

"መነበብ ያለበት እሱ አይደለም"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ትክክለኛው መረጃ ያለው ከዚህ ላይ ነው። በቶኝ በኩል"

"በቶኝ በኩል? አብደኻል! በአርሳስ የተፃፈው ማስታወሻ እኮ እዚህ ጋ ነው።"

"እዚህ ጋ ደግሞ የሆቴል ሂሳብ የተከፈለበት ቱራጭ ወረቀት ነው። በጣም አፈልገዋለሁ።"

"ቀደም ሲል አይቼዋለሁ። ምንም ነገር የለውም" አለ ሌስትሬድ። "አክቶበር 4፣ክፍል ቁጥር 8፣ቁርስ ምሳ፡ ምናምን የሚል ነው። ጠቃሚ ነገር የለውም።"

"ላንተ ምንም የሌለው ሊመስልህ ይችላል። ግን በጣም ጠቃሚ መረጃ ነው። ማስታወሻውም እንዲሁ። ፊርማው ተፈላጊ ነው። ስለዚህ አሁንም ደግሚ እንካ.ን ደስ ያለህ አልሃለሁ።"

"በቲ ጊዜ አጥፍቻለሁ" አለ ሌስትሬድ ከመቀመጫው እየተነሳ። "ጠንክሮ በመሥራት እንጅ ምድጃ ዳር ቁጭ ብሎ ነገር በማጠንጠን አላምንም። ደህና ዋል ሚስተር ሆልምስ። የችግሩን ምንጭ ማን ቀድሞ እንደሚደርስበት ወደፊት እናያለን" አለና ልብሶችን ሰብስቦ ቦርሳው ውስጥ አስገባና ወደ በሩ አመራ።

ሆልምስ እንደማቅማማት አደለ "አንድ ፍንጭ ልስጥህ" አለው ሌስትሬድን በሩን ከፍቶ ከመውጣቱ በፊት። "የችግሩን ትክክለኛ መፍትሄ አነግርሃለሁ። ወይዘሮ ሳይመን የምትባል ሴት የለችም። የተረት ተረት ስም ነው። እንደዚህ የምትባል ሴት የለችም። ወደፊትም አትኖርም።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሴስትሬድ ጓደኛዬን እያዘነ ተመለከተው። ከዚያ ወደ እኔ እያየ ግንባሩን ሦስት ጊዜ ተምተም አደረገና ርጋታ በተሞላበት ሁኔታ ራሱን እያወዛወዘ ወጥቶ ጥርግ አለ።

ሆልምስ በሩ በቅጡ አለመዘጋቱን ያስተዋለው ካፖርቱን ለመልበስ ሲነሳ ነው። "ሰውየው ከቤት ውጭ ስለሚደረግ የምርመራ ሥራ የተናገረው ቁም ነገር ያዘለ ነው" ሲል የራሱን አስተያየት ሰጠና "ዋትሰን ወረቀቶችህን ለማገላበጥ ትንሽ ጊዜ እንድታገኝ ትቼህ መውጣት አለብኝ።"

ሼርሎክ ሆልምስ ትቶኝ ሲወጣ አሥራ አንድ ሰዓት አልፏል። ብቻዬን የምሆንበት ጊዜ ግን አላገኘሁም። በአንድ ሰዓት ውስጥ አንድ የምግብ ቤት ሠራተኛ ትልቅ ጠፍጣፋ ሳጥን የሚመስል ነገር ይዞ ከች አለ። ሳጥኑን አብሮት በመጣው ወጣት አጋዥነት ከፍቶ በመኖሪያ ቤታችን ካለው ጠረጴዛ ላይ ልዩ የሆነ ራት ተደርድሮ ሳይ በጣም ተገረምኩ።

ከመጠጡ አስከ ምግቡ፣ ከሠላጣው እስከ ዶሮ አሮስቶው፣ከትኩስ እስከ ቀዘቃዛው ምንም የቀረ ነገር የለም። ሁለቱ ሰዎች የምግቡ ዋጋ የተከፈለ መሆኑንና በቤታችን አድራሻ የታዘዘ መሆኑን ከመግለጽ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር ሳይተነፍሱ ማዕዱን አቅርበው ተመልሰዋል።

ገና ዘጠኝ ሰዓት ሳይሞላ ሼርሎክ ሆልምስ ፈጠን ባለ አርምጃ ወደ ክፍላችን እየገባ ነበር። ፊቱ ላይ የመከላተር ምልክት ቢታይም ዓይኖቹ ፈክተ ብለዋል። እናም በያዘው ገዳይ ላይ የሚያበሳጭ ሁኔታ እንዳልገጠመው ገምቻለሁ።

"ምግቡን አቅርበውታላ" አለና እጁን ጠራረገ።

"እንግዳ ያለብህ ትመስላለህ። የአምስት ለው ራት እኮ ነው የቀረበው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"አዎ፣ ጥቂት እንግዶች ሊመጡ ይችላሉ" አለ። "ሎርድ ሳይመን እስከአሁን እዚህ ባለመድረሱ ተገርሜአለሁ። እ! በደረጃው ላይ የጫማው ኮቴ እየተሰማኝ ነው።"

እውነትም ጠዋት አብሮን የነበረው ጓደኛችን መነጽሩን እያስተካከለ የመረበሽ ሁኔታ ቢታይበትም ከምንጊዜውም በላይ ራሱን ኮፍሶ እየመጣ ነበር።

"መልዕክቱ ደረሰህ?" ሲል ሆልምስ ጠየቀው

"አዎ፣ እውነቱን ለመናገር የመልእክቱ ይዘት በጣም ነው ያስደነገጠኝ።"

"አንተ የምትለውን ለማድረግ ሥልጣኑ አለህ?"

"በጣም እንጂ!"

ሎርድ ሳይመን ግንባሩን በእጁ ይዞ ወንበር ላይ ተቀምጧል።

"መስፍኑ ምን ይለኛል?" ሲል አጉረመረመ። "እንድ የቤተሰቡ አባል ሲዋረድ፣ በሐፍረት ሲሸማቀቅ፣ ምን ይሰማው ይሆን?"

"የአጋጣሚ ጉዳይ ነው። አሳፋሪ አይደለም።"

"አንተ ነገሮችን የምታየው በሌላ መልኩ ነው። እኔ ደግሞ በተለየ..."

"— አድራጎት ድንገተኛ መሆኑ ቢያሳዝነንም ፣ ሴትዮዋ ከዚህ የተለየ ማድረግ የምትችል አይመስለኝም። እናት አልባ በመሆኗ የዚህ ዓይነት ችግር ሲደርስባት እንዴት እንደምትወጣው አትጠጪ የሚያሳይ መላ መች የላትም።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጌታየ፣ ይሄ ቅሌት ነው፣ የአደባባይ ወርደትም አለ ሎርድ ሳይመን ጠረጴዛውን በእጁ እየመታ።

"በዚህ ከፍተኛ ሃላፊነት ላይ ተቀምጠህ ለዚች ምስኪን ልጅ ይቅርታ ማድረግ ነውር አይደለም።"

"ምንም ዓይነት ይቅርታ አላደርግም። በጣም ተናድጀለሁ። ለህፍረትም ተዳርጌአለሁ።"

"የደወል ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ" አለ ሆልምስ።

"አዎ፣ የዕግር ኩቴም ይሰማኛል። ገዳዩን ቀስል አድርገህ እንድታየው እፈልጋለሁ። በዚህ መተማመን ካልቻልን ሎርድ ሳይመን እነሆ ችግሩን በተሳካ ሁኔታ ሊፈታ የሚችል ጠበቃ አምጥቻለሁ።" በሩን ሲከፍተው አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ተከታትለው ገቡ። "ሎርድ ሳይመን" አለና በመቀጠል ሚስተርና ሚስዝ ፍራንሲስ ሔይ ሞልተንን ለማስተዋወቅ ይፈቀድልኝ፣ ከሚስዝ ጋር የምትተዋወቁ ይመስለኛል።"

ደንበኞችን እነዚህን ሁለት እንግዶች፣ ሲያይ ከመቀመጫው ዘሎ ተነሳና እጆቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ አንገቱን አቀርቅሮ ቆመ። ወይዘሮዋ ፊጠን ብላ ሄዳ እጆቿን ለሰላምታ ዘረጋችለት። እሱ ግን ቀና ብሎ ለማየትም ፈቃደኛ አልሆነም። የእሷ ተማጽኖ ልብ የሚሰብር ስለነበር ያንን ላለማየት ሆን ብሎ ያደረገው ሊሆንም ይችላል።

"ተበሳጭተሃል ሮበርት" አለችው። "ልትበሳጭም ይገባል።"

"ከእንቺ ምንም ይቅርታ አልፈልግም" አለ ሎርድ ሳይመን ምርር ባለ ስሜት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"አውነት ነው። በድየኻለሁ። ከመሄዴ በፊት ሳናግርህ ይገባ ነበር። ግን ያኔ ፍራንክን ሳየው ስውነቱ እየተንቀጠቀጠ ነበር። የማደርገውንም ሆነ የምናገረውን አላውቅም። ከሁሉም ደግሞ እንዴት ቤተክርስቲያን ውስጥ ተገለፍልፌ ሳልወድቅ እንደቀረሁ ሳስብ ተአምር ይሆንብኛል።"

"ሚስዝ ሞልተን፣ እኔና ጓደኛዬ ብንወጣላችሁና እናንተ በግልጽ ብትወያዩ ምን ይመስልሻል?"

"እንድናገር ከተፈቀደልኝ አለ እንግዳው ጉልማሳ። "ጉዳዩ ከሚገባው በላይ ምሥጢር ሆኖ ቆይታል። በእኔ በኩል መላው አውሮፓና አሜሪካ ስለዚህ ጉዳይ ሐቁን እንዲያውቅ እፈልጋለሁ።" ሰውየው አጭርና ቀጭን ቁመና አለው። መልኩ አድርጎ ከተላጨው ፊቱ ላይ ንቃትና ድፍረት ይነበባል።

"ስለዚህ ታሪካችንን ልናገር" አለች ወይዘሮዋ። "ፍራንክና እኔ በ1884 ሮክ. ተራራ አጠገብ ማክካየር ካምፕ ውስጥ ነው የተገናኘን። አባቴ የማዕድን ማውጫ ቦታ ተሰጥቶት ይሠራ ነበር።

"እኔና ፍራንክ እዚያው እያለን ቃል ተገባባን። ከዕለታት አንድ ቀን አባቴ በሃብት ተንበሸበሸ። ምስኪኑ ፍራንክ ግን በሚቆፍረው ቦታ ላይ ምንም ማዕድን ሳያገኝ ቀረ። አባቴ በሃብት ላይ ሃብት እየጨመረ ሲሄድ ፍራንክ ግን ድህነት እጐሳቆለው። አባቴ የእኔንና የፍራንክን ቃል መገባባት አያውቅም። እናም እኔን ፍረስኮ ወደሚባል ቦታ ወሰደኝ። ፍራንክ በእጁ ምንም ነገር ባይኖረውም እኔ ወደ ሄድኩበት ተከትሎ መጣ። አሁንም አባቴ ስለ ግንኙነታችን የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ቢለማ በጣም ከመናደድ በስተቀር የሚያተርፈው ነገር ስላልነበር እንዲሁ ለመቆየት ተስማማን። በመጨረሻም ሠርቶ ለመክበር ሲል ወደ ሴላ አገር እንደሚሄድ ነገረኝ። እንደ እኔ አባት ሃብታም እስካልሆነ ድረስም እንደማይመለስና የእኔን እጅ ለመጨበጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደማይቃጣው ገለፀልኝ። እኔም እስክመጨረሻው እንደምጠብቀውና እሱ በሕይወት እያለ ማንንም እንደማላገባ ቃል ገባሁለት። 'ታዲያ ለምን እሁኑኑ እዚህ አንጋባም?' አለኝ። 'ከዚያ አንችንም እምንሻለሁ፤ እስክመመለስ ድረስም የአንቺ ባል መሆኔን አልናገርም።' በጉዳዩ ላይ ተነጋግረን አንድ ቁስ አባት በተገኙበት የእሱን ሰናይ ሃሳብ ተግባራዊ አደረግን። እዚያው እያለን ነው ሁሉም ነገር ያለቀው። ከዚያ ፍራንክ ወደ ሃበት ፍለጋ ሲሄድ እኔም ወደ አባቱ መጣሁ እላችኋለሁ።

"በቀጣይ ስለ ፍራንክ የተሰያዩ ወሬዎችን ሰማሁ። ሞንታና በተባለ ቦታ ይሠራ እንደነበር፤ ወደ አሪዞና፣ ቀጥሎም ኒው ሜክሲኮ ሄዶ እንደነበርም ሰማሁ። ከዚህ ሁሉ በኋላ በአንድ ጋዜጣ ላይ በወጣ ሰፊ ጽሑፍ የአጋቹ ሕንዶች በአንድ የማዕድን ቁፋሮ ካምፕ ላይ አደጋ ጥለው አያሌ ሰዎች መሞታቸውን አነበብኩ። ከሞቱት ሰዎች የሰም ዝርዝር ውስጥም የእኔውን ፍራንክ አገኘሁት። እኔም በድንጋጤ የተነሳ ራሴን ስቼ ወደቅሁ። ለወራትም ህክምና ላይ ቆየሁ። አባቱ አዳልጦኝ የወደቅሁ መሰሉት ፍሪስኮ ውስጥ ወደሚገኝ አንድ መለስተኛ ሐኪም ቤት ነበር የወሰደኝ። ከአንድ ዓመት በላይ ለሚሆን ጊዜ ስለፍራንክ ምንም ሳልሰማ ቆየሁ። እናም ያለምንም መጠራጠር ሞቷል ብየ ደመደምኩ። ቁርጤን አወቅሁ። በዚህ አጋጣሚ ሎርድ ላይመን ወደ ፍሪስኮ መጣ። እኛም ወደ ሎንዶን መጣን። ጋብቻችን ሲፈጸም አባቱ በጣም ደስ ብሎት ነበር። እኔ ግን ለእኔ ምስክን ለፍራንክ በልቤ ውስጥ የሰጠሁትን ቦታ ማንም በዓለም ላይ እኔ ነኝ የሚል ወንድ ቢመጣ መውሰድ እንደማይችል ይሰማኝ ነበር።

አሁንም ሎርድ ላይመንን አግብቼ ቢሆን ኖሮ በእሱ ላይ ሆኜ የራሴን ሥራ ነበር የምሠራው። ሥራ እንጅ ፍቅር በትእዛዝ ይሆንም። ከእሱ ጋር ወደቱርባን የሄድኩት እሱ ጥሩ ባል እንደሚሆነኝ እኔም ጥሩ ሚስት እሆነዋለሁ ብየ ነበር። ግን ወደ መቃረቢያው እየሄድኩ ሳለ ዞር ብየ ስመለከት ፍራንክ ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጨን። መጀመሪያ ላይ የእሱ ጣዕረ-ሞት እንጅ እሱ አልመሰለኝም።እንደገና አስተውየ ስመለከተው አሁንም



t.me/OLDBOOKSPDF

እዚያው ነው። ላሰተዋለው ሰው እኔን በማየት ተደስታ ወይስ ተከፍታ ይሆን? እያለ የሚጠይቅ ይመስላል። አለመውደቴ ይገርመኛል። ሀረብኝ። ቁሱ የሚያነበንባቸው መንፈሳዊ ቃላት ጥዙጉዙ የሚል የንብ ርግብግቢታ መሰለው ነበር የሚሰሙኝ። ምን እንደማደርግ ግራ ገባኝ። አገልግሎቱን አቋርጨ ዘልዬ ወደ እሱ በመሄድ መጥኝ ሰማለትም ታጣኝ። እንደገና አየሁት ። ምን እንደማስብ ያወቀ ይመስል ጣቱን አውጥቶ ከንፈሩ ላይ በማድረግ እንድረጋጋ በምልክት ነገረኝ። ከዚያ በቁራጭ ወረቀት የሆነ ነገር ሲሞነጫጭር ሳየው ለእኔ ማስታወሻ እየፃፈ መሆኑን ተረዳሁ። እሱ በቆመበት የድጋፍ መቀመጫ በዙል ላልፍ የታቀፍከትን አበባ ጣልከት። እሱም አበባውን አንስቶ ሲሰጠኝ ማስታወሻውን ጨምሮ በእጁ አስጨበጠኝ። በአንድ መስመር ጽሑፍ እንድንገናኝ ብቻ ነው የጠየቀኝ። አውነት ነው፤ የመጀመሪያው ሥራዬ አሱን ማግኘት እንደሆነ ቅንጣት ታክል አልተጠራጠርኩም። እናም እሱ የሰጠኝን መመሪያ ለመፈፀም ቆርጨ ተነሳሁ።

"ስመለስ ሁኔታውን ካሊፎርኒያ በነበርንበት ጊዜ ለሚያውቃትና በጣም ለሚቀርባት ሠራተኛዬ ነገርኳት። ለማንም እንዳትነግር ትዕዛዝ ሰጥቼ ጥቂት ዕቃዎችንና ካፖርቱን እንድታዘጋጅልኝ አደረግሁ። ስሎርድ ሳይመጣ መነገር እንደነበረብኝ አውቃለሁ። ግን በእናቱና በለሎች ታላላቅ ሰዎች ፊት ይሸን ማድረግ በጣም ይከብዳል። በመሆኑም አሁን ጠፍቼ በመሄድ ሌላ ጊዜ አውነቱን አውጥቼ ብናገር የተሻለ እንደሚሆን ራሴን አሳመንኩት። ፍራንክን በመስኮት በኩል ቁም እስከማየው ድረስ ሰአሥር ደቂቃ ያክል ቁርስ ላይ አልተቀመጥኩም። ከውጭ ጠቀሰኝና መኖፈሻው ውስጥ ቀስ እያለ ይንሸራሸር ጀመር። ሹልክ ብዬ ወጥቼ የምፈልጋቸውን ዕቃዎች በመያዝ ተከተልኩት። የሆነኛ ሴት መጥታ ስለ ሎርድ ሳይመን የሆነ ነገር ነገረችኝ። ከሰማሁት ጥቂት ነገር መረዳት እንደቻልኩት ከጋብቻው በፊት የሆነ የግል ጉዳይ ከሴትዮዋ ጋር ሳይኖረው አይቀርም።... አሷን ተውኩና ፍራንክን በእጁ አደረግሁት። በሰረገላ ተሳፍረን ጉርድን አደባባይ አካባቢ መዳረፊያት ሆቴል አመራን። ከአያሌ ዓመታት በኋላ



t.me/OLDBOOKSPDF

የተፈፀመው እውነተኛ ሠርጌም ይኸ ነው። ፍራንክ ከአፖቹ ሕንዶች አሥር ቤት አምልጦ ወደ ፍሪስኮ ሲመጣ መሞቱን ሰምቼ ወደ እንግሊዝ አገር መምጣቴን ሲሰማ ተከተሉኝ ይመጣል። የሚገርመው እኔ ጋ የደረሰው የሁለተኛው ጋብቻዬ ዕለት ጧት ነው።"

"ከጋዜጣ ላይ እንበቤ ነው" አለ አሜሪካዊው። "ስሟንና የሠርጉ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምበትን ቤተክርስቲያን ይገልፃል። የመኖሪያ አድራሻዋ ግን አልነበረም።"

"ከዚያ እኔና ፍራንክ ምን ማድረግ እንዳለብን በግልጽ ተነጋገርን። እኔ ግን በጣም ሐፍረት ስለተሰማኝ ለአባቱ በሕይወት መኖራን የሚገልጽ የእንዲት መሥመር ማስታወሻ ጽፌ እነሱን ወደማላይበት አካባቢ ለመጥፋት ፈልጌ ነበር። እነዚያ ወይዛዝርትና መኳንንት በጠረጴዛ ዙሪያ ታድመው የእኔን መመሰስ ሲጠባበቁ እንደነበር ሳስብ አሰቃቂ ይሆንብኛል። ፍራንክ የሠርግ ልብሶቼንና ሌሎችንም ጌጣጌጦች በእንድ ላይ አሥሮ ወደማይገኙበት ቦታ መስዶ ጣላቸው፤ የእኔን ዱካ ለማጥፋት ። ነገ ወደ ፓሪስ ለመሄድ ስንዘጋጅ እንዴት አድራሻችንን እንዳወቀ ባይገባኝም ይኸ ወንድማችን ሚስተር ሆልምስ ዛሬ ምሽት ላይ ወደ አካባቢያችን መጥቶ የእኔን ጥፋተኝነትና የፍራንክን ትክክለኛነት ከመንገሩም በተጨማሪ ድብቅ መሆናችን ከስህተት ውስጥ እንደሚጥለን አስረዳን። እናም ከሎርድ ሳይመን ጋር ለብቻ ለመነጋገር ዕድል እንደሚሰጠን ሲገልጽልኝ ወዲያውኑ ነው ወደዚህ የመጣን። ሮበርት፤ አሁን ሁለንም ሰምተኸዋል። አናድደህ ከሆነ በጣም ነው የማዝነው። በእኔ ላይ ክፉ እንደማታስብ ተስፋ አደርጋለሁ።"

ሎርድ ሳይመን ከነበረው አቋም ፍንክች አላለም። ይሁን እንጂ ረጅሙን ትረካ ጥርሱን እየነከሰም ቢሆን በሞታ ነው ያዳመጠ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይቅርታ ይደረግልኝ" አለ። "የግል ሚሥጢራ በሆነ ጉዳይ ላይ በአደባባይ መነጋገር ባህሌ አይደለም።"

"እና ይቅርታ አታደርግልኝም? ከመሄዴ በፊት እንጨባበጥም?"

"እ፣ እንቺን የሚያስደስትሽ ከሆነ--" አለና የዘረጋችለትን እጇን ቀዝቀዝ ባለ ስሜት ጨበጠው።

"ራት አብረን እንድንበላ መልካም ፈቃዳችሁ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።" አለ ሚስተር ሆልምስ።

"ጥያቄህ እጅግ የበዛ ይመስለኛል" ሲል ሎርድ መለሰ። "በቅርብ ጊዜ የተፈጠረውን ሁኔታ ለመቀበል እገደድ ይሆናል። እንድደለት ግን አይጠበቅብኝም። እናም ሁላችሁንም ደህና እደሩ ብየ ለመሰናበት መልካም ፈቃዳችሁ ይሁን።" ሁላችንም በእንድ ላይ ዝቅ ብለን በማጉንበስ እጅ ነሳን።

"አንቺና ባለቤትሽ አክብሮት እንደምትሰጡኝ እምነቱ የሀና ነው" አለ ሼርሎክ ሆልምስ። "ሚስተር ሞልተን፣ ከአሜሪካዊ ጋር በመገናኘቱ ደስ ብሎኛል። ምክንያቱም ጥንት የተፈፀመው የነገሥታትና የባለሥልጣናት ክንቱ ድርጊት ልጆችንን ወደፊት የአንድ ዓለም ዜጐች ከመሆን አያግዳቸውምና-"

"ጉዳዩ በጣም ደስ የሚል ነው" አለ ሆልምስ እንግዶቹን ከወጡ በኋላ። "ለመግለጽ አይቻልም ብለህ የፈራኸውን ነገር በቀላሉ ማስረዳት እንደሚቻል ያሳየ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። ሴትዮዋ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል ሳታዛባ ስትተርክቸው ከማየት የበለጠ አሳማኝ ነገር የለም። በእንዳሩ የስኮትላንድ ያርዱ ሚስተር ሌስትሬድ የደረሰበትን ውጤት ከማየት የበለጠ አሳሳች ነገር አልነበረም።"

"እንተ ምንም ስህተት የለብኝም ትላለህ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከመጀመሪያዎቹ ሁለት እውነተኛ መረጃዎች ነገሩ ለእኔ ግልፅ ሆኖልኝ ነበር። አንደኛው ልጅቷ የሠርጉ ሥነ-ሥርዓት እንዲካሄድ ፈቃደኛ መሆኗ፤ ሁለተኛው ወደቤት ስትመለስ በመጀመሪያው ውሳኔዋ መፀፀቷ ናቸው። በእርግጥ ሃሳቧን እንድትለውጥ የሚያደርግ ነገር ጧት ተፈጽሟል። ያ ነገር ምንድነው? ከቤተክርስቲያን ስትወጣ ከመ-ሽራው ጋር ስለነበረች ማንንም ማናገር አልቻለችም። ታዲያ የሆነ ሰው አይታለች? ካየች ከአሜሪካ የመጣ ሰው መሆን አለበት። ለምን ቢባል እዚህ አገር ከመጣች ብዙ ጊዜ ስላልሆናት በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የጠበቀ ግንኙነት ሊፈጥር የሚችልና የእሷን አቋም የሚያስለውጥ ሰው አይኖርም ። ገባህ? አሜሪካዊ አይታ ሊሆን ይችላል ወደሚለው ሃሳብ የመጣነው ነገሮችን ነጣጥሰን በማየት ነው። ይህ አሜሪካዊ ግን ማነው? በእሷ ላይስ ይህን ያክል ተፅእኖ እንዴት ሊፈጥር ቻለ? ፍቅረኛ ሊሆን ይችላል፤ ባልም ሊሆን ይችላል። የልጅነት ጊዜዋን በጥሩ ሁኔታ እንዳላሳለፈች አውቃለሁ። ይኸን ሁሉ ያገናኙት የሶርድ ሳይመንን ገለጻ ከመስማቴ በፊት ነው። ከአግዳሚ ወንበሩ ላይ ስላለው ሰውና ስለመ-ሽራዋ የባህሪ መቀየር፤ ስለማስታወሻው፤ ስለመ-ሽራዋ አበባ መውደቅ፤ ከሠራተኛዋ ጋር ስለመነጋገሯ የተገኘው መረጃ ሁሉን ነገር ግልጽ ያደርገዋል። ከወንድ ጋር አብራ ከሄደች ሰውየው ፍቅረኛዋ ወይም የቀድሞ ባልዋ መሆኑን ይጠቁማል። ሚዛኑ ግን ወደ ሁለተኛው ያደላል።"

"ስለመሆኑ እንዴት ልታገኛቸው ቻልክ?"

"የሆቴሎችን የክፍያ ታሪፍ በማጥናት። ስምንት ፖውንድ ለአንድ አልጋ፤ ስምንት ሺልንግ ለአንድ ለስላሳ የሚያስከፍሉ ሆቴሎች ሎንደን ውስጥ ጥቂት መሆናቸውን ተረዳሁ። ሁለተኛ ናርዝ አምበርላንድ ጉዳና ወደሚገኝ ሆቴል ሄጄ የመመዝገቢያ ሰነዱን ስመረምር ፍራንሲስ ኤች ሞልተን አሜሪካዊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ከአንድ ቀን በፊት ሰኞ መሄዱን ከቀሪ የክፍያ ሠነዱ ላይ አየሁ። የሚላኩለት ደብዳቤዎች ወደ 226 ጉርዶን አደበባይ እንዲላኩለት



t.me/OLDBOOKSPDF

ተናግሯል። ወደዚያ ስሄድ ባልና ሚስቱን በክፍላቸው ውስጥ አገኝቸው። አባታዊ ምክር ለመስጠትም ድፍረት አገኘሁ። አቋማቸውን ለሕዝቡ በተለይም ለሙርድ ሳይመን ግልፅ እንዲያደርጉ ነገርኳቸው። እዚሁ መጥተው እንዲያነጋግሩት እሱም ቀጠሮውን አክብሮ እንዲመጣ አመቻቸሁ።"

"ግን ውጤቱ በጣም ጥሩ ሊባል የሚችል አይደለም" ስል የራሴን አስተያየት ሰነዘርኩ። "በባህሪው ላይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ይታያል።"

"አይ ዋትሰን!" አለ ሆልምስ ፈገግ እያለ። "አንተም ብትሆን ከዚህ የተሻለ ሥነ-ምግባር ላታሳይ ትችላለህ። ሁለችንም በእንደዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ብንሆንና በሠርጋችን ዕለት ሚስትና ሃብትን የሚያሳጣ ድንገተና አጋጣሚ ቢፈጠርብን ራሳችንን አሁን በምናስበው አቋም ውስጥ አናገኘውም።"



t.me/OLDBOOKSPDF

# ጥቁር እንግዳ

ሼርሉክ ሆልምስ አልፎ አልፎም ቢሆን የሰውነት ማጠንከሪያ ጂም ይሠራል። የሚሠራው ግን ስፖርቱን ስለሚወደው አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ጡንቻቸውን በማሳበጥ ለእይታ እንደሚዳርጉት አሱም እንደነሱ ለመምሰል ብሎም አይደለም። እንዲያውም ዓላማ የሌለው የስፖርት እንቅስቃሴ ጉልበትና ጊዜን በከንቱ ማባከን ነው የሚል አመለካከት አለው። እናም ሆልምስ የአካል እንቅስቃሴ ሲያደርግ ከታየ መሥያሚ ግዳጁን ለመፈፀም የሚያግዘው አካላዊ ብቃት ሲገነባ ፊልጓል ማለት ነው። በዚህ ረገድ ደከመኝ ወይም ሰለቸኝ ሳይል ያሰምንም ዕረፍት ይሠራል-ይንቀሳቀሳል። ምግብ ላይ ግን በጣም ቁጥብ ነው። ሕይወትን ተለል አድርጐ ነው የሚያያት። በድሎት መኖርን ብዙም አለመደውም። መሥያውን የሚፈትን ሥራ ካልገጠመው ሱስ አስያዥ ዕፆችን አስከመውሰድ ይደርሳል።

በሀደይ ወራት መግቢያ ላይ ነው። እኔና አሱ በአንድ መናፈሻ ውስጥ እንሽራሸራለን። ለሁለት ሰዓታት ያክል አብረን ስንንዘዛ ላየን የምንተዋወቅ አንመስልም። አልፎ አልፎ ነው የምናወራው። አሥራ አንድ ሰዓት ገደማ የሆነው ገና ቤከር ጐዳና ከመድረሳችን በፊት ነው።

"ይቅርታ ጌታዬ!" አለ የጥበቃ ሠራተኛው ፣በሩን እንደከፈተ። "አንድ አርስዎን የሚፈልግ ሰው መጥቶ ነበር።"

ሆልምስ በዓይኑ እየገላመጠኝ "የከሰዓት በኋላ ሽርሽር ትርፉ ይኸው ነው!" አለ። "እና ሰውየው ሄዷል ነው የምትለኝ?"

"አዎ፣ ጌታዬ"

"እንዲገባ አልጠየቅኸውም?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ግባ ብሃው፡ንብቶ ነው ሃቶየው"

"ምን ያክል ጊዜ ቆየ?"

"ግማሽ ሰዓት ያክል ቆይቷል ጌታዬ። ቁንጥንጥ ሰው ነው። ቁጭ ብድግ ሲል ቆይቶ ነው የወጣው። ከበር ውጭ ሆኜ ሳዳምጠው 'ሰውየው አይመጣም ማለት ነው' እያለ ሲያጉረመርም ሰማሁት፤ና 'ለጥቂት ጊዜ ታገስ፤ የመጨረሻ ጊዜያቸው ደርሷል' አልኩት። 'ከዚያም ትንሽ ስለወበቀኝ ወጣ ብየ እመለሳለሁ' አለና ወጣ።"

"ጥሩ፤ አንተ ማድረግ የሚገባህን አድርገሃል" አለ ሆልምስ ወደ ቤት በመግባት ላይ እያለ። "ዋትሰን፤ ሥራ ለመሥራት ቡተነሳሳህበት ጊዜ እንደዚህ መሆኑ ቢያናድደኝም የሰውየው ትዕግሥት ማጣት ደግሞ ጉዳዩን ከባድ ያስመስለዋል። ለመሆኑ ያ ጠረጴዛው ላይ ያለው ጂፓ የማነው የእንግዴው ሰውየ መሆን አለበት። አዲስ ባይሆንም ያምራል። አጫሽች የሚወዱት ዓይነት ነው። ለንደን ውስጥ የዚህ ዓይነት ጂፓ ያላቸው ሰዎች ስንት እንደሆኑ መገመት ያዳግተኛል። ሰውየው ይህን የመሰለ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ጂፓ ጥሎ መሄዱን ቢያውቅ የሚናደድ ይመስለኛል።"

"ከፍተኛ ዋጋ ማውጣቱን እንዴት አወቅህ?"

"መቼም በአዲስነቱ ከስድስት እስከ ሰባት ፖውንድ ሊያወጣ ይችላል። ሁለት ጊዜ ጥገና እንደተደረገለት ይታወቃል። ከመያዣው ላይና አፉ አካባቢ። እንደምታየው የብር ጥምጣም ተደርጎለታል። ምናልባትም ከአዲስነቱ የበለጠ ዋጋ አስወጥቶ ሊሆን ይችላል። ሰውየው ይህን ያደረገው ከአዲሱ ይልት ይሽን ስለሚመርጥ መሆን አለበት።"

ሆልምስ ጂፓውን በእጁ ይዞ ሲያገላብጥ ተመለከትሁትና "ሌላስ?" ስል ጠየትሁት።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ፒፓዎች አንዳንዴ በሰዎች ላይ የተለየ ስሜት ያሳድራሉ አለ። "የለዓትን ወይም የጫማ ማሠሪያን ያክል ግን ልዩ ትርጉም አይሰጡም። በእርግጠኛነት ግን ባለቤቱ ጡንቻው ፈርጠም ያለ፣ ግራኝ፣ ቆንጆ ጥርስ ያለው፣ ግድየለሽና ለገንዘብ የማይጨነቅ ሰው ነው።"

ጓደኛዬ ይህን መረጃ ሲሰጥ ብዙም ተጨባጭ ነገር አልነበረውም። የሰጠውን አመክንዮ መቀበሌን ለማረጋገጥ አፍጭልቆ ይመለከተኝ ነበር።

"አንድ ሰው በቀን የሰባት ሽልንግ ፒፓ ስላጨሰ ሃብታም ነው ብለህ ትገምታለህ?" አልኩት።

"ይኸ ሌላም ቅልቅል ስላለበት ስምንት ሺልንግ ነው የሚሸጠው" ሲል ሆልምስ መለሰ። በመቀጠልም "በግማሽ ዋጋ ቆንጆ ዓይነት ስለሚያገኝ የተለየ ቁጠባ አያስፈልገውም" አለ።

"ሌሎች ነጥቦችስ?"

"ፒፓውን በፋኖስና በጋዝ ነበልባል የማቀጣጠል ልማድ አለበት። በአንድ በኩል ክላይ እስከታች ተሰብልቦ ይታያል። ክብረት ቢሆን እንደዚያ አይሆንም። እንደምታየው በቀኝ በኩል ነው የተለበለበው። ከዚህ ማወቅ የሚቻለው ሰውየው ግራኝ መሆኑን ነው። የራስህን ፒፓ ያዝና ወደ መብራቱ አስጠጋ። ግራኝ ሆነህ የግራ ጉንጉን እንዴት እንደምትይዘው ትረዳለህ። ...ተሳስቼ ካልሆነ በደረጃው ላይ ኩቱውን እየሰማሁ ነው። ፒፓውን እያዩ እንዲህ ነው እንዲያ ነው እያሉ ከመመራመር የሰውየው መምጣት ይመረጣል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያው በሩ ተከፈተና ቱሙቱ ዘለግ ያለ ወጣት ገባ። ጠቆር ያለ ግራይ መሉ ልብስ ለብሷል። ስሜቱ ግን ጥሩ አልነበረም። ዕድሜው በግምት ሰላሳ ዓመት ይሆነዋል።

"ይትርታ" አለ ተንሽ እንደማፈር እያለ። "ማንካኒት እንደነበረብኝ ይሰማኛል። አም፣ ማንካኒት ነበረብኝ። ትንሽ ተናድጀ ስለነበር ነው። በተላሉ ትረዱኛላችሁ ብየ አስባለሁ።" ፍዝዝ ብሎ እጁን ግንባሩ ላይ እንዳደረገ ሂዶ መንበሩ ላይ ዘፍ ሲል የወደቀ እንጅ የተቀመጠ አይመስልም ነበር።

"አያሌ ሰዓታት ያለ እንቅልፍ እንዳሳለፍክ መገመት አያዳግትም" አለ ሆልምስ እንደመሳቅ እያለ። "ያኔ ነርቮቻችን ይደክማሉ። ባሕሪያችንም ባልተለመደ ሁኔታ ይነጫነጫል። ምን ልርዳህ?"

"የአንተን ምክር ፈልጌ ነው የመጣሁት ጌታየ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። መላ ሕይወቱ ተመሰቃቅሏል።"

"እኔን በወንጀል ምርመራ አማካሪነት መቅጠር ትፈልጋለህ?"

"እሱ ብቻ አይደለም። እንደማንኛውም በአመክንዮ የሚመራ ሰው ምክርህን እንድትለግሰኝ እፈልጋለሁ። ወደፊት ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማወቅ አሻለሁ። እንደምትንገረኝም እምነቱ የፀና ነው።"

በጣም በስሜት ስለሚናገር ስለ ጉዳዩ ዘርዝሮ ማስረዳት እንደተቸገረ መገመት አላቃተኝም።

"በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው" አለ። "ማንም ሰው የራሱን ገመና ብዙም ለማያውቀው ሰው ገልጦ መናገር አይፈልግም። የትዳር ጓደኛህን ውስጣዊ ባሕሪ ከዚህ በፊት አይተኸቸው እንኳን ለማታውቅ ሰዎች ዘክዝከህ መንገር በጣም አስነዋሪና



t.me/OLDBOOKSPDF

ለማድረግም የሚዘገንን ነው። ግን ነገሩ ጫፍ ላይ ስለደረሰ ምክር ማግኘት አለብኝ።"

"ወንድሜ ሚስተር ግራንት መ·ንሮ" በማለት ሆልምስ ንግግሩን ጀመረ።

እንግዳው ከ·ቀመጠበት ዘሎ ተነሳና "ምን?" አለው ድምፁን ጮክ አድርጉ። በመቀጠልም "ስሜን ታውቀዋለህ?" አለው።

"ማንነትህን መደበቅ ከፈለግህ" አለ ሆልምስ እንደመሳቅ እያለ። "ስምህን በባርኔጣህ ላይ መጻፍ እንደሌለብህ አመክርሃለሁ። ያለዚያ ... እኔና ጓደኛዬ በዚች ክፍል ውስጥ ለጆሮ እንግዳ የሆኑ በርካታ ምሥጢሮችን አዳምጠናል። የአያሌ ሰዎችን ችግር የመፍታት ዕድልም አግኝተናል። አንተም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ እንደምትሆን አልጠራጠርም። ስለዚህ ወቀታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘቱ ወሳኝ መሆኑን አውቀህ ሳትዘገይ ፍሬ ሃሰቡን እንድታስረዳኝ አማወንሃለሁ።"

እንግዳችን አሁንም ግንባሩን በእጁ ያዘ። ለመናገር የከበደው ይመስላል። ከሁኔታው የተረዳሁት ቢኖር ሰውየው በጣም ቁጭብ፣ድብቅና ኩራተኛ ነው። ያም ሆኖ ድንገት ሳይታሰብ ወደ ዝርዝር ጉዳዩ ገባ።

"እውነቱን እነሆ፣ ሚስተር ሆልምስ" ሲል ጀመረ። "እኔ ለሦስት ዓመታት ያህል በትዳር የቆየሁ ነኝ። በእነዚህ ዓመታት እኔና ባለቤቴ እንደማንኛውም ባለትዳር ተዋደንና ተሳሳረን የደስታ ሕይወት አሳልፈናል። በመካከላችን ምንም ዓይነት አለመግባባት ተፈጥሮ አያውቅም። ካለፈው ሰኞ ጀምሮ ግን ያልታሰበ ችግር ስለተከሰተ ተራርቀናል። የችግሩን ምንነት ማወቅ አፈልጋለሁ።

"ሚስተር ሆልምስ፣ ብዙ ከመናገሬ በፊት አፅንኦት እንድትሰጠው የምፈልገው ጉዳይ አለ። ኢፌ ትወደኛለች። በዚህ ላይ ምንም ጥርጣሬ አይግባህ። ከልቧ ትወደኛለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

እድግም ታፈቅረኛለች። ይሆን እኔም በሚገባ አውቀዋለሁ- ይለማኛልም። በዚህ ላይ መከራከር አልፈልግም። አንድ ወንድ አንዲት ሴት የምትወደው መሆኗን በቀላሉ ማወቅ ይችላል። አሁን ግን አንዳች ምሥጢር ተከስቷል። ምስጢሩ መገለጥ አለበት።

"እውነቱን እንድናገር መልካም ፈቃድህ ይሁን ሚስተር ሆልምስ" ሲል ብዙ መረጋጋት አይታይበትም።

"ስለ ኢፌ ታሪክ የማውቀውን ያክል እነግርሃለሁ። ገና የሃያ አምስት ዓመት ወጣት ብትሆንም እኔ እሷን ያገኘኋት እመበለት ሆና ነው። በዚያን ጊዜ ሚስዝ ሑበርን እየተባለች ትጠራ ነበር። በወጣትነቷ ወደ ሰሜን አሜሪካ በመሄድ አትላንታ ውስጥ ትኖር ነበር። ሑበርን የሚባለውን ባሏን ያገባችውም እዚያ ነው። የታወቀ ጠበቃ ነበር። አንድ ልጅ ወልደዋል። ሆኖም በወቅቱ በአካባቢው በተፈጠረው የቢጫ ወባ ወረርሽኝ አባትና ልጅ የበሽታው ሰለባ ሆነዋል። ሁለቱም ሞተዋል። የሞት የምስክር ወረቀቱንም አይቼዋለሁ። በዚህም ምክንያት አሜሪካን ስለጠላችው ትዳር ከሌላት አክስቷ ጋር ሚድ ሰክስ ውስጥ፣ ፒነር በተባለ ቦታ ትኖር ነበር ። ባለቤቷ ብዙ ሃብት ትቶላት ማለፉንና አራት ሺህ አመስት መቶ ፖውንድ ካፒታል እንዳላት መግለጽ አስፈላጊ ይመስለኛል። ባለቤቷ ገንዘቡን ተገቢው ቦታ ላይ እንዲውል በማድረጉም ከዚሁ ገንዘብ የስባት በመቶ ትርፍ ታገኛለች። እኔና እሷ ስንገናኝ ፒነር ውስጥ መኖር ከጀመረች ገና ስድስት ወሯ ነበር። በጣም ስለተዋደድን ከጥቂት ሣምንታት በኋላ ተጋባን።

"የእኔ ሥራ ንግድ ነው። ከሰባት አስከ ስምንት መቶ ፖውንድ ገቢ አገኛለሁ። ኖርበሪ ውስጥ በዓመት ሰማንያ ፓውንድ የሚከፈልበት ቪላ ተከራይተን ኑሯችንን በጥሩ ሁኔታ መምራት ከጀመርን ቆይተናል። አካባቢው ለክተማ ቅርብ ነው። ከእኛ ቤት በላይ ሁለት መኖሪያ ቤቶችና አንድ ቡና ቤት አለ። ከፊት ለፊታችን ራቅ ብሎ ደግሞ አንድ ሌላ ቤት አለ። ወደ ባቡር ጣቢያ የሚወስደውን መንገድ



t.me/OLDBOOKSPDF

እስከምታጋምስ ሌላ ቤት አታይም። የጌሾ ንግድ ሥራየ ወቅታዊ ስለሆነ በተወሰኑ ወራት ውስጥ ወደ ከተማ እሄዳለሁ። በክረምት ግን ወደዚያ ለመሄድ የሚያበቃ ብዙ ሥራ የለኝም። እናም እኔና ባለቤቱ ባለን አቅም ደስተኞች ሆነን እንኖራለን። እውነቴን ነው የምልህ፣ ይሽ ሁኔታ እስከተከሰተበት ጊዜ በመካከላችን ምንም እንከን ተፈጥሮ አያውቅም።

"በነገራችን ላይ አንድ ሳልነግርህ ማለፍ የማልፈልገው ጉዳይ አለ። እንደተጋባን ባለቤቱ ሃብቷን ሁሉ ለእኔ አስተላልፋለች። ይሽ የሆነው ከእኔ ፍላጐት ውጭ ነው -- የንግድ ሥራዬ ቢስተጓጐል ችግር ሲፈጠር ይችላል የሚል ፍራቻ ነበረኝ። ያም ሆኖ እሷ እንዳለችው ሆነና ገንዘቡን እንድወስድ ተደረገ። ከዚያ የዛሬ ሁለት ወር ገደማ ወደ እኔ ጠጋ ብላ በዙም ነገር አነጋገረችኝ።

"ጃክ" አለችኝ። "ገንዘቡን ስሰጥህ በፈለግሁ ጊዜ ጠይቄ መውሰድ እንደምችል ነግሬሃለሁ አይደል!"

"ትክክል" አልኳት። "ሁሉም የራስሽ ነው።"

"መልካም" አለች "እንግዲያው መቶ ፓውንድ እፈልጋለሁ።"

አዲስ ቀሚስ ወይም ሌላ ነገር ለመግዛት ፈልጋ ሊሆን ይችላል ብየ ባስብም ትንሽ ግራ መጋባቴ አልቀረም።

"ለምን ፈለግሽው?" አልኳት።

"አይ የአንተ ነገር" አለች እንደመቀለድ እያለች።
"የእኔ የባንክ ደንበኛ አንተ ብቻ መሆንክን ነግረኽኛል። ባንክኛ ደግሞ የደምበኞቹን ገንዘብ አውጥቶ ሲሰጥ ለምን ብሎ እንደማይጠይቅ ታውቃለህ።"

"ከምርሽ ከሆነ ገንዘቡን እሰጥሻለሁ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ስለእውነት፣ ከምሬ ነው"

"እና...ለምን እንደፈለግሽው አልነግርህም ነው የምትይኝ?"

"ሻክ ምናልባት አንድ ቀን። አሁን መንገር ግን ውሸት!"

ለመጀመሪያ ጊዜ ከእኔ የተደበቀ አንዳች ምሥጢር መኖሩን ባውቅም ገንዘቡን ስለጣት አላመነታሁም። ቸክ ሰጠኋት። ከዚያም በኋላ ስለዚህ አስቤ አላውቅም። ይሽን ስል ግን ከዚያ ወዲህ ከተፈጠረው ጉዳይ ጋር ለማገናኘት ፈልጌ አይደለም። ምንም ግንኙነት ላይኖረው ይችላል።

"ከእኛ ቤት ትንሽ ራቅ ብሎ አንድ ቤት መኖሩን ነግሬሃለሁ። በመካከል ያለው ቦታ ሜዳ ነው። መንገዱን ተከትለህ ወደ መስኩ ስትዞር ቤቱን ታገኘዋለህ። ከዚያ አለፍ ብሎ ባሉት ሣፎች ውስጥ ለውስጥ የሽርሽር ገቢ ማድረግ ያስደስተኛል። ቤቱ ለስምንት መራት ያክል ሳይከራይ ባዶውን ቆይቷል። ያን የመሰለ ባለ ሁለት ፎቅና ቅንጅ በረንዳ ያለው ቤት ይህን ያክል ጊዜ ያለ ኪራይ መቆየቱ አሳዛኝ ነበር። በዚያ ባለፍኩ ቁጥር የቤቱም ሆነ የግቢው ንፅሕና ለመኖሪያ ምቹ እንደሚሆን አስባለሁ።"

"ባለፈው ሰኞ ምሽት ላይ ነበር። በዚያው መንገድ የሽርሽር ገቢ በማድረግ ላይ እያለሁ አንድ ባዶ የጭነት መኪና ሜዳውን አቋርጦ ሲመጣ አገኘሁት። በዚያው ቅጽበት የወለል ምንጣፎች አረንጓዴው ግቢ ላይ ተጠቅልለው ተቀምጠው አየሁ። ቢዘገይም ቤቱ መከራየቱ ግልጽ ነበር። አልፌ ከሄድኩ በኋላ እንደ ሥራ-ፈት ቆሜ መመልከት ጀመርኩ። ጉረቤቶቻችን እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ አሰብኩ። ወደዚያ በመመልከት ላይ እያለሁ ከፎቅ ላይ ሆኖ በመስኮት ወደ እኔ የሚመለከት ሰው አየሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከላይ ሆኖ ከሚመለከተኝ ሰው ገጽታ ላይ ምን እንዳለ አላውቅም ሚስተር ሆልምስ። በጀርባየ ላይ በረዶ የፈሰሰ ነው የመሰለኝ። ትንሽ ራቅ ብየ ነበርና ለይቼ ማወቅ አልቻልኩም ። ግን በዚያ ገጽታ ላይ ያልተለመደ ሁኔታ ይታይ ነበር። በውስጤ የተፈጠረው ስሜት ይህ ሆኖ እያለ፣ ፈጠን ብየ ወደፊት በመሄድ ያን የሚመለከተኝን ሰው ቀርቤ ለማየት ሞከርኩ። ግን ወዲያው ከእይታየ ተሰወረብኝ። ወደ ጨለማ ክፍል የገባ ይመስለኛል። ለአምስት ደቂቃ ያክል ባለሁበት ቆሜ ስለሁኔታው ማሰላሰሌ አልቀረም። ያየሁት ሰው ገጽታ የወንድ ወይም የሴት መሆኑን መለየት አልቻልኩም። የነበርኩበት ርቀት ያን ለማድረግ የሚያስችለኝ አልነበረም። ከሀሳም ያስገረመኝ ግን የፊቱ ቀለም ነው። ብዙ ያልተለመደ፣ ፍዝዝ ያለ ቢጫ ነው። በጣም የተረበሽኩት ደግሞ ቤቱ ውስጥ ማን እንዳለ ለማየት ከወሰንኩ በኋላ ነው። ወደ ቤት በመሄድ በሩን አንኳኳሁ። የሚያስፈራ ፊት ያላት ረጅም ቀጭን ሴት ቶሎ ብላ ከፈተችው።"

"ምን ፈለግ?" አለችኝ በሰሜን እንግሊዞች የአነጋገር ዘዩ።

"ጐረቤታችሁ ነኝ" አልኳት ወደ እኔ ቤት እየመለከትኩ። "በምትችሁን ስለሆናችሁ ምናልባት የምረዳችሁ ነገር ካለ ብየ ነው"

"ስንፈልግ እንጠይቅሃለን" አለችና ፊቴ ላይ ዘጋችብኝ። ሥነ-ምግባር የጐደለው አድራጐቷ ስላናደደኝ ቶሎ ብየ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። ምሽቱን በመሉ ስለ ሊሎች ጉዳዮች ለማሰብ ብሞክርም አዕምሮየ በመስኮቱ ስላየሁት ጣዕረ ሞት የሚመስል ገጽታና ስለ ሴትዮዋ ብልግና ከማውጠንጠን አልተቆጠበም። ቀደም ብዬ ስላየሁት ነገር ለባለቤቴ ለመንገር አልቸኮልሁም። ይህን ያደረግሁት ስለምትፈራና የተጐዳች ሰው ከመሆኗ አንፃር እኔ የተሰማኝ ዓይነት አስከፊ ስሜት በእሷ ላይ እንዲታይ ስላልፈለግሁ ነው። ከመተኛቴ በፊት ግን ቤቱ የተከራየ መሆኑን ስነግራት ምንም መልስ አልሰጠችኝም።



t.me/OLDBOOKSPDF

"በጣም እንትልፋም ከሚባሉት ሰዎች መካከል አንዱ ነኝ። 'ምንም ዓይነት ድምፅ ከእንትልፉ ሊያነቃው አይችልም' እያሉ ቤተሰቦቼ ይዘባበቱብኛል። ያን ዕለት ሴሊት ግን የረባ እንትልፍ አልወሰደኝም። በተፈጠረው ሁኔታ ምክንያት ይሁን ወይም አይሁን እኔም አላውቀውም። በመስማትና ባለመስማት መካከል ሆኜ በክፍሉ ውስጥ የሆነ ነገር እየተፈዘመ ይመስለኛል። ቀስ በቀስም ባለቤቱ ልብሷን ስትሰበስብ፣ ጫማዋን ስትጫማና ሻሿን ስታስር አየኋት። በእንትልፍ ልቤ የሆነ ነገር አጉረመርማለሁ። በሰመመን ውስጥ እንዳለሁ ዓይኔ በሻማ ብርሃን በሚታየው ፊቷ ላይ አረፈ። ገና በሴሊቱ ይደረግ የነበረው ዝግጅት በእንትልፍ ልቤም ቢሆን እያስገረመኝ ነበር። በገጽታዋ ላይ አይቼው የማላውቀው ስሜት ይነበባል፣ ፊቷ ፍዝዝ ብሏል። ትንሳሿ ቁርጥ፣ ቁርጥ ይላል። ሻሿን እያሠረች የቀሰቀሰችኝ መሆኗን ለማረጋገጥ ኮስተር ብላ ወደ አልጋው ትመለከት ነበር። የማልሰማ ስለመሰላት ድምጿን አጥፍታ ወጥታ ሄደች። በደቂቃ ውስጥ በሩ ሲጥጥ ሲል ተሰማኝ። አልጋየ ላይ ቁጭ ብየ የአልጋውን ብረት በእጄ ያገኩት። ከእንትልፌ መንቃቴን ለማረጋገጥ ያደረግሁት ነበር። ከዚያ ሰዓቱን ከትራሴ ውስጥ አውጥቼ ሳየው ከሴሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆኗል። ባለቤቱ ለምን ይሆን በዚህ ሰዓት ወጥታ የሄደችው?

"ለሃያ ደቂያ ያክል ተቀምጬ ምን ሊሆን እንደሚችል አሰብኩ። ብዙ ባሰላሰልኩ ቁጥር ግን የነገሩ መልክ እየተቀየረና ምሥጢሩ እየተዳፈነ መጣ። ከሁሉም እንቆቅልሽ የሆነብኝ በሩ ተከፍቶ በቀስታ ሲዘጋና ያን ተከትሶም ደረጃውን ስትወጣ ኰቴዋን መስማቱ ነበር።

"'ለመሆኑ የት ነበርሽ ኢፌ?'" ስል ገና ከመግባቷ ጠየቅኋት።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ንግግሯን በቁጣ ነው የጀመረችው። ጮክ ብላ ስትናገር ትንፋሿ ይቆራረጣል። ለመግለጽ አስቸጋሪ የሆነ የጥፋት ስሜት ከገጽታዋ ላይ ስለሚነበብ የበለጠ ተጨነቅሁ። ባለቤቴ ግልጽ ለው ናት። ባንዳሩ ሽክክ ብላ ወደ ቤት መግባቷን ብቻ ሳይሆን እኔ ባለቤቷ ሳናግራት የሰጠችኝ ሰቀቀን የተሞላበት ምላሽ አልተዋጠልኝም።

"'ተነስተሃል ጃክ?' እየተርበተበተች ጮክ ብላ ጠየቀችኝ። 'ለምን ተነሳህ' ከእንቅልፍህ ትነቃለህ ብየ በፍፁም አላብኩም።'

"ከየት ነው የምትመጭው?' አልካት ቁጣየ እየጨመረ።

"'ግራ ብትጋባ አልፈርድብህም' አለችና ያሠረችውን ሻሽ ስትፈታ የእጇ ጣቶች እንዴት ይንቀጠቀጡ እንደነበር አሁንም በዓይነ ሕሊናየ ይታየኛል። 'ለምን ብትለኝ በሕይወቴ እንደዚህ ዓይነት ደርሶብኝ አያውቅም። የሆነ ነገር አፍኖኝ ፣የምተነፍሰው አየር ፍለጋ በደመ-ነፍስ የሮጥሁ ነው የመሰለኝ። ባልወጣ ኖሮ እራሴን አስት ነበር። በሩ'ጋ ቆሜ ለጥቂት ጊዜ ከተናፈስኩ በኋላ ነው ነፍሴን ያወቅሁት።'

"ይሽን ሁሉ ታሪክ ትነግረኝ በነበረበት ሰዓት እንዴ እንካን ወደ እኔ አልተመለከተችም። ድምጿ የእሷ ድምጽ አይመስልም። የምትናገረው እውነት እንዳልሆነ ለእኔ ግልፅ ነበር። ምንም መልስ አልሰጠኋትም። ልቤ ስለተቀየመና አዕምሮየ በእያሌ ነገሮች ጥርጣሬ ስለተሞላ፣ ፊቴን ወደ ግድግዳው አዞርኩባት። ባለቤቴ ከእኔ የደበቀችው ነገር ምን ይሆን? ገና በሌለቱ የት ደርሳ ነው የመጣች? ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ እስካላገኘሁ የአዕምሮ ሰላም እንደማላገኝ ባውቅም፣ መጀመሪያ የሰጠችኝ መልስ ከእውነት የራቀ በመሆኑ ደግሜ ከመጠየቅ ተቆጠብኩ። ቀሪውን ሌሊት እንዲሁ የምይዝ የምጨብጠውን ሃሳብ አጥቼ እየተወራጨሁ ሳነሳና ስጥል አደርኩ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያን ዕለት ስሥራ ጉዳይ ወደ ኩዮማ መሄድ ነበረብኝ። ነገር ግን አዕምሮየ በጣም ተረብሾ ስለነበር ለሥራው ትኩረት መስጠት አልቻልኩም። ባለቤቴም እንደ እኔው የተረበሸች ትመስላለች። የተናገረችው ነገር እኔን እንዳላሳመነኝ ስታውቅ ግራ ግቧት እንዳላት ከሁኔታዋ ተረድቻለሁ። ያለምንም ንግግር ቁርሳችንን እንደበላን ስለ ጉዳዩ ለማሰላሰል ስል ገና በማለዳው ለሽርሽር ወጣሁ።

"ክሪስታል ፓላስ ድረስ በመሄድ ለአንድ ሰዓት ያክል ግቢው ውስጥ ከቆየሁ በኋላ በሰባት ሰዓት ወደ ኖርበሪ ተመለስክ። ስመለስ የመጣሁበት መንገድ ቀደም ሲል የጠቀስክት ቤት ባለበት በኩል የሚወስድ ነው። ከአንድ ቀን በፊት ያየሁትን ያልተለመደ የሰው ገጽታ በመስኮት ለመመልከት ለአንድ ደቂቃ ያክል ቆም አልክ። ሚስተር ሆልምስ፣ እንግዲህ እግዚአብሔር ያሳይህ! እኔ እዚያ ከመቆሜ በሩ ድንገት ተከፈተና ባለቤቱ ወጣች!

"ሳያት ከመደንገጤ የተነሳ እንደበቱ ተሳሰረ ። ዓይኖቿና ዓይኖቼ ተጋጩ ። በዚህ ጊዜ እሷ የተሰማት ስሜት ከእኔ ጋር ሲነጻጸር ግን የእኔ ምንም አልነበረም። ወደ ኋላ ተመልሳ ለመግባት ቃጣት። ድብብቆሹ ከንቱ መሆኑ ሲገባት የገረጣ ፊቷንና በፍርሃት የተዋጠ ዓይኖቿን በውሸት ፈገግታ ለመሸፈን መሞከሯ ከከንፈሯ ላይ እየተነበበ ወደ እኔ ገሰገሰች።

"'ኡ ጃክ!!' አለች 'እዲሶቹን ጉረቤቶቻችንን የምረዳቸው ነገር ካለ ለመጠየቅ መጥቼ ነው። ጃክ፣ ለምን እንደዚያ አድርገህ ታየኛለህ? ተቀየምከኝ?'

"'እናስ፣' አልካት። 'በሌሊት ተንሸራሽ የመጣሽው እዚህ ነበር?'

"'ምን ማለትህ ነው አለች?' ጮክ ብላ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያን ዕለት ሌሊት እዚህ እንደመጣሽ አልጠራጠርም። በበሌሊት የሚጠየቁ እነዚህ ሰዎች እንማን ናቸው።?'

"ከዚህ በፊት እንካን መጥቼ አላውቅም'

"ልብሽ አያወቀው ለምን ትዋሸኛለሽ?' ስል ጮኽባት። የድምጽሽ መቀያየር መዋሸትሽን ያሳብቃል። እኔ ከአንቺ የተደበቀ ነገር መቼ ኖሮኝ ያውቃል? ወደ ቤት ገብቼ ፍተሻ በማድረግ ጉዱን ሁሉ አጋልጣለሁ።'

"ጃክ፣እንደዚያማ መሆን የለበትም። ስለ እግዚአብሔር ብለህ!' አለች ስሜታን መቆጣጠር አቅቷት ትንፋሽዋ እየተቆራረጠ። ወደ በሩ እየተጠጋሁ ስሄድ በደመነፍስ የሽማቤን እጅጌ ይዛ ወደ ኋላ ሳበችኝ።

"ጃክ፣ ተማፅኖዬን ስማኝ! እንዳትገባ!' ስትል ጮኸች።'ከዕለታት አንድ ቀን እንደምነግርህ ቃል እገባልሃለሁ። አሁን ወደዚህ ቤት ብትገባ ግን አለቃቂ ሁኔታ ይፈጠራል።'

ልገፈትራት ስሞክር ተጠምጥማ ይዛ ትማፀነኝ ጀመር።

"እመነኝ ጃክ!' አለች ጮክ ብላ። 'የአሁኑን ብቻ እመነኝ። ለሀሁት የሚያበቃህ ምንም ምክንያት አይኖርም። ለአንተው ብየ ባላደረገው ኖሮ ከአንተ የሚደበቅ ምንም ምሥጢር ባልኖረኝ። ሕይወታችንም እንዲህ አደጋ ላይ ባልወደቀ ነበር። አብረኸኝ ወደ ቤታችን ከሄድን ሰላም ይወርዳል። ሃይል ተጠቅመህ ወደዚያ ቤት ከገባህ ግን የእኔና የአንተ ግንኙነት እዚህ ላይ ያከትማል።'

"ቅንነትና ተስፋ መቁረጥ ያልተለየው ንግግሯ እንደሰንሰለት አሥሮ አቆመኝ። ለመወሰን ስላቃተኝ በሩ ላይ ቆሜ ቀረሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"በመጨረሻም፣ 'በእንድ ቅድመ ሁኔታ የምትስማሚ ከሆነ እምንሻለሁ። እንድ ቅድመ-ሁኔታ ብቻ አልካት። 'ምሥጢሩ የሚያበቃውና ምሥጢርሽን የመጠበቅ ነፃነትሽ የሚከበረው ሊሊት ተነስተሽ ላለመሄድና ከእኔ ዕውቅና ውጭ ምንም ነገር ላለማድረግ ቃል ስትገቢ ነው። ወደፊት ይህ እንደማይደገም ዋስትና ከሰጠሽኝ ያለፈውን ለመተው ዝግጁ ነኝ።'

"እንደምታምነኝ እኔም አልጠራጠርም' አለች የልቧ እየደረሰ። 'ልክ አንተ እንዳልከኝ አደርጋለሁ። ና አባክህ ወደ ቤታችን እንሂድ!' አሁንም የልብሴን እጅጌ ይዛ ወደ ቤታችን በመሄድ ላይ እያለን ወደ ኋላ ስመለከት ያች ክስተር ያለ ቢጫ ፊት ያላት ሴት በላይኛው መስኮት ወደ እኛ ትመለከታለች። በዚች ፍጡርና በባለቤቱ መካከል ምን ግንኙነት ይኖር ይሆን? ወይም ያቺ ከእንድ ቀን በፊት ያየኋት ገስቋላ ሴት ከእሷ ጋር ምን አገናኛት? ያልተፈታ እንቅልሽ፣ ላወርደው ያልቻልኩት የአዕምሮ ሼክም ሆነብኝ።

"ከዘህ በኋላ ለሁለት ቀናት ከቤት አልወጣሁም። ባለቤቴም እኔ እስክማውቀው ድረስ ከቤት ስላልወጣች ቃል ከዳኋን ያከበረች መሰለች። ይሁን እንጂ በሦስተኛው ቀን የገባችው ቃል ከዳን ቤታንና ባለቤታን ጥላ ከመሄድ እንዳላገዳት ተረዳሁ። ያን ዕለት ወደ ከተማ የወጣሁ ቢሆንም ወደ ቤት የተመለስኩት ግን ሁል ጊዜ ወደ ቤት በምገባበት በ9:36 ሰዓት ሳይሆን በ8:40 ነበር። እቤት እንደገባሁ ሠራተኛዋ አየተርበተበተች ወደ ውስጥ ሮጣ ገባች።

"እመቤትሽ የታለች?' ስል ጠየቅኋት።

"ለሽርሽር የወጡ ይመስለኛል' የሚል መልስ ሰጠችኝ።

"በትጽበት ውስጥ ልቤ በጥርጣሬ ተሞላ። ቤት ውስጥ አለመኖሯን ለማረጋገጥ ወደ ፎቅ ወጣሁ። እዚያው እንዳለሁ በእንደኛው መስኮት ወደ ውጭ ስመለከት የደነገጥኩት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሠራተኞችን ሜዳውን አቋርጣ ወደዚያው ቤት አቅጣጫ ስትሮጥ አየኋት። ከዚህም ባለቤቱ እዚያ እንደሆነችና እኔ ወደ ቤት ስመለስ እንድትጠራት ትዕዛዝ ሰጥታ መሄዷን አረጋገጥሁ። እሳት ለብሼ እሳት ጉርሼ ሰንዳዩ ለአንዲና ለመጨረሻ ጊዜ አልባት መስጠት እንዳለብኝ ወሰኜ እኔም ወደዚያው ገሰገስኩ። ባለቤቱና ሠራተኛዋ ተመልሰው ሲመጡ መንገድ ላይ አገኘኋቸው፡ እነሱን ከማናገር ወደ ኋላ አላልኩም። በዚያ ቤት ውስጥ በእኔ ሕይወት ላይ የተሸረበ አንዳች ድብቅ ነገር አለ። የመጣው ቢመጣ ከእንግዲህ ምሥጢር ሆኖ እንደማይቆይ ቃል ለምድር ለሰማይ ብያለሁ። ከቤት ስደርስ በሩን እንኳ አላንኳኳሁም። በድንገት ከፍቼ ዘው ብየ ነው የገባሁት።

"ምድር ቤት ውስጥ ሁሉም ፀጥ ረጭ ያለ ነው። ኩሽና ውስጥ የተጣደ በራድ ሲፍሰቀሰቅ ይሰማል። ትልቅ ጥቁር ድመት ቅርጫት ውስጥ ተጠቅልላ ተኝታለች። ከዚህ በፊት ያየኋት ሴት ዳናዋ ጠፍቷል። ወደ ቀጣዩ ክፍል ስገባ ሰው አላገኘሁም። ከዚያ ወደ ፎቅ ወጣሁ። በሁለቱም ክፍሎች ሰው አልነበረም። ቤቱ በሙሉ ባዶ ነው።

የቤት ዕቃዎችና ፎቶግራፎች በብዛት ይታያሉ። በአንዱ ክፍል መስኮት አጠገብ ግን አዲስ ፎቶ ተመለከትኩ። በጣም ያምራል። በዚህም ጥርጣሬየ እየጨመረ መጣ። ባለቤቱ ከሦስት ወራት በፊት በእኔው ጉትጎችነት ቁማ የተነሳችውን ፎቶግራፍ ነበር ብፌ ላይ ተቀምጦ ያየሁት።

"ቤቱ ባዶ መሆኑንን ለማረጋገጥ ረጅም ጊዜ ቆየሁ። ከዚያ ሰውነቱን እንደከበደኝ ወጥቼ ሄድኩ። ቤቱ ስደርስ ባለቤቱ ሳሎን ውስጥ ነበረች። ውስጤ በጣም ስለተጨዳና ስለተናደድኩ ሳላናግራት አልፌ ሄጄ ወደ ጥናት ክፍሌ ገባሁ። ይሁን እንጂ በሩን ከመዘጋቱ በፊት ተከትላኝ ገባች።

"ጃክ፣ ቃል ከዳኔን በማፍረሴ በጣም አዝናለሁ' አለችኝ። 'ስለ ጉዳዩ ብታውቅ ግን ይቅርታ እንደምታደርግልኝ አልጠራጠርም።'



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይኸን ካልሽ ምንም ሳትደብቂ ንገሪኝ አልኳት።

"አልችልም ጃክ፤ በጭራሽ አልችልም !" አለች ጮክ ብላ።

"በዚያ ቤት ውስጥ ማን እንደሚኖርና ያን ፎቶግራፍ ለማን እንደሰጠሽው አስካልነገርሽኝ ድረስ በእኔና በአንቺ መካከል መተማመን ሊኖር አይችልም" አልኳትና ቤት ትቻት ወጣሁ። ይህ የሆነው ትናንት ነበር ሚስተር ሆልምስ። ከትናንት ወዲህ የሆነውን አላውቅም። አሷንም አላየኋትም። በመካከላችን እንክን ሲፈጠር ይህ የመጀመሪያችን ነው። በጣም ተረብሻለሁ። መላ-ቅጡ ጠፍቶብኛል። በአማካሪነት ሊረዳኝ የሚችል ሰው ሳስብ ድንገት አንተ ትዝ አልከኝ። እናም እየተጣደፍኩ ወዳንተ መጣሁ። እስክሄድ ከተናገርኩት ውስጥ ግልፅ ያላደረኩት ነገር ካለ ጥያቄዎችን ለመመለስ ዝግጁ ነኝ። ከሁሉም በላይ ግን ልቋቋመው ባልቻልኩት ችግር ውስጥ ስላለሁ አፋጣኝ መፍትሄ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ።"

ሆልምስ እና እኔ ይህን የመረበሽ ስሜት የተሞላበት ንግግር እጅግ ተመስጠን ነበር ያዳመጥነው። ጓደኛዬ አገጩን በእጁ አስደግፎ በዝምታ እንደተቀመጠ ሃሳብ ጭልጥ አድርጎ ወሰደው።

"እውነቱን ንገረኝ" አለ በመጨረሻ ። "በመስኮት ያየኸው ፊት የወንድ ስለመሆኑ ርግጠኛ ነህ?"

"ገጽታውን ባየሁበት አጋጣሚ ሁሉ ራት ያለ ቦታ ላይ ስለነበርኩ እርግጠኛ መሆን አልችልም"

"ባየኸው ነገር ግን ደስተኛ አልነበርክም"

"ያልተለመደ መልክ ነው። ምጥጥ ያለና ለዓይን እንግዳ የሆነ ገጽታ። ስቀርበው ፈጥኖ ይጠፋብኛል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ባለቤትህ መቶ ፓውንድ እንድትሰጣት ከጠየቀችህ ስንት ጊዜ ሆነው?"

"ሁለት ወር ገደማ"

"የመጀመሪያ ባሏን ፎቶግራፍ አይተኸው ታውቃለህ?"

"አላየሁትም። እሱ ከሞተ ጥቂት ቀናት በኋላ አትላንታ ውስጥ ትልቅ የእሳት ቃጠሎ ደርሶ ስለነበር ሰነዶቿ ሁሉ ነደዋል።"

"ያም ሆኖ እኮ የሞት የምሥክር ወረቀቱ አላት። ማየትህንም ነግረኸኛል።"

"እሞ፣ ከቃጠሎው በኋላ አንድ ኮፒ አውጥታለች።"

"አሜሪካ እያለች በደንብ የሚያውቃት ሰው አጋጥሞህ ያውቃል?

"አያውትም"

"አሜሪካ ደርሳ ለመምጣት ጥያቄ አቅርባልህ ታውቃለች?"

"አቅርባልኝ አታውትም"

"ወይም ከዚያ ደብዳቤ ደርሷት ያውቃል?"

"እኔ እስክማውቀው ድረስ አልደረሳትም።"

"አመሰግናለሁ። አሁን በጉዳዩ ላይ ትንሽ ላስብበት ። ቤቱ ተሰቆ ከሆነ ግን ትንሽ ሊያስቸግረን ይችላል። ያ ባይሆን እንኳን የአንተ መምጣት አስቀድሞ ስለሚነገራቸው ትናንትና በሄድክበት ሰዓት ቀድመው ሊወጡ ይችላሉ። አሁን መመለሳቸውን እናጣራለን። ቤቱ ውስጥ ሰው መኖሩን



t.me/OLDBOOKSPDF

ካወቅህ ሃይል ተጠቅመህ ለመግባት አትሞክር። ለእኔና ለጓደኛዬ ስልክ ደውልልን። መልዕክቱ በደረሰን በአንድ ሰዓት ውስጥ መጥተን የችግሩን ምንጭ እንደርስበታለን።"

"ቤቱ ባዶ ከሆነስ?"

"ያ ከሆነ ነገ መጥቼ ከአንተ ጋር እንነጋገራለን። ደህና ሁን። አደራ የምልህ ግን የነገሮችን መነሻ ሳታውቅ መበሳጨት የለብህም።"

ጓደኛዬ ሚስተር ግራንት መ·ንሮን ሸኝቶ እንደተመለሰ፣ "ዋትሰን ይሽ ጉዳይ የሚሳካ መሆኑ ያጠራጥረኛል" አለ ። "አንተስ ምን ይመስልሃል?"

"መጥፎ ስሜት ይሰማኛል" ስል መለስኩለት

"ተሳስቼ ካልሆነ የሆነ ማስፈራራት ያለበት ይመስለኛል"

"አስፈራራሪው ማነው?"

"መልካም፣ በዚህ በሚያምር ክፍል ውስጥ የሚኖረው ሰውየ መሆን አለበት ፎተግራፏን ከዕቃ መደርደሪያው ሳጥን ላይ ያስቀመጠው። ዋትሰን፣ በእኔ ይሁንብህ በዚያ መስኮት በታየው ጠየም ያለ ፊት ላይ አንዳች ምሥጢር አለ። ምንም ቢሆን አያመልጠኝም።"

"የምታውቀው ነገር አለ?"

"ለጊዜው አዎ። ትክክል ባይሆን ግን በጣም ይደንቀኛል። እዚያ ቤት ውስጥ ያለው የሴትዮዋ የመጀመሪያ ባል መሆን አለበት።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት እንደዚያ ልትል ቻልክ?"

"ሁለተኛው ባለቤቷ ወደዚያ ቤት እንዳይገባ ለማድረግ ስትል የምታሳየው መርበትበት የተሞላበት ድርጊት ነው። ከዚያ ሌላ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? እኔ እንደሚመስለኝ እውነታው ይኸው ነው። ይቺ ሴት አሜሪካ እያለች ባል አግብታለች። ባለቤቷ እየሞሰ እያደረ ደባል ፀባይ ማሳየት ይመጀመሩ፣ ወይም አስክፊ በሽታ ስለያዘው፣ ወይም የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ስለደረሰበት ሊሆን ይችላል ራቅ ወዳለ ቦታ ጥላው ከበልላለች። ወደ እንግሊዝ አገር ስትመለስ የተሻለ ሕይወት ለመኖር ስትል ስሚን ተየረች። የመጀመሪያው ባለቤቷ የሞተ መሆኑን ለማሳመን ስትል የሌላ ሟች፣ የሞት የምሥክር ወረቀት ለአሁኑ ባለቤቷ አሳየችው። የሰላም ኑሮ በመኖር ላይ እያሉ የተድሞው ባለቤቷ ወይም ከእሱ ጋር ግንኙነት ያላት አንዲ ተንከሎኛ ሴት ልትሆንም ትችላለች፣ አድራሻዋን ፈልገው ያገኛሉ። ከዚያም ካለችበት ድረስ በመሄድ ጉዷን በአደባባይ እንደሚያጋልጡ በመግለጽ ለሴትየዋ ዛቻ የተሞላበት ደብዳቤ ጽፈውላታል። ሆኖም እነሱን እንዳይመጡ ለማድረግ ስትል ከባለቤቷ ሙቱ ፖውንድ ወስዳ ለእነሱ ላክችላቸው። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች ባለቤቷ አዲስ ጎረቤት ማግኘታቸውንና ቤቱ መከራየቱን ሊነግራት እሷን የሚያሳድዱ ሰዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ተጠራጠረች። ከዚያ ባለቤቷ እንቅልፍ እስክሚወስደው ትጠብቅና የሰላም ሕይወቷን እንዳያሳጣት ለማሳመን ወደ እነሱ ገሰገሰች። በመጀመሪያው ስላልተሳካላት በሚቀጥለው ቀን ጧት ተመልሳ ሄደች። ባለቤቷ ራሱ እንደነገረንም ወደ ውጭ ልትወጣ ስትል ነው ድንገት ደጃፍ ላይ ያገኛት። ወደዚያ ቤት እንደማትመለስ ብትምልና ብትገዘትም፣ ከሁለት ቀናት በኋላ ከእነዚህ ሥጋት ከፈጠሩባት ጉረቤቶቿ ግንኙነት ማቋረጥ ቀላል አልነበረምና ሌላ መከራ አደረገች። በነገራችን ላይ ፎቶግራፏን የሰጠቻቸው እነሱ ስለጠየቋት ይመስለኛል። በዚህ አጋጣሚ ባል ከሄደበት ተመልሶ ሲመጣ ባለቤቱን ከቤት ያጣታል። ሠራተኛዋን በጥያቄ አጣደፋት። ሠራተኛዋ አባወራው መምጣቱን ለባለቤቱ ለመንገር ከቤት ወጥታ ትሮጣለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስት ባለቤታ እሷን ፍለጋ እንደሚመጣ ስላወቀች እንግዶችን በንሮ በር አዋክባ ታስወጣና ምናልባትም ከንሮ አትክልቱ ውስጥ እንዲደበቁ ታደርጋለች። እሱ እንደሚለው ከሆነም አጠገባቸው ነበር ማለት ነው። ሲሄድ ማንም አልነበረም። ዛሬ ምሽት ላይም የሚያጣቸው ከሆነ በጣም ይገርመኛል። መላ-ምቴን እንዴት ታየዋለህ።?"

"ሁሉም ምናባዊ ግምት ነው።"

"ግን ሁሉንም እውነታዎች ግምት ውስጥ ያስገባ ነው። በዚህ ውስጥ ያልተካተቱ አዲስ ነገሮች ሲመጡ እንደገና ለማጤን በቂ ጊዜ ይኖረናል። ወዳጃችን ከኖርበሪ አዲስ መልእክት እስካላስተላለፈልን በአሁኑ ሰዓት የተሰየ ነገር ማድረግ አንችልም።"

ብዙም ላንቆይ ግን መልእክቱ ደረሰን። "ቤቱ እንደተከራየ ነው" ይላል። "ከመስኮቱ አንጻር ያለውን ምስል አይቸዋለሁ። በእንድ ሰዓቱ ባቡር አጠቃችኋለሁ። ከመድረሳችሁ በፊት ምንም ዓይነት ርምጃ አልወስድም።"

ከባቡር ስንወርድ ደረጃው ላይ ሆኖ ይጠብቀናል።በባቡር ጣቢያው መብራት ወጋገን አሻግረን ስናየው ፊቱ ቀልጧል፤ መንፈሱ ተረብሿዋል።

" ሚስተር ሆልምስ፣ አሁንም እዚያው ናቸው" አለ እጁን ጓደኛየ ትከሻ ላይ ጣል አድርጎ። "እኔ ወደዚህ ስመጣ የቤቱ መብራት እየበራ ነበር። ለእንዲና ስመጨረሻ ጊዜ ችግሩ እልባት ያገኛል።"

"ታዲያ ምን አሰብክ?" ግራና ቀኝ በዛፎች የታጀበውን መንገድ ይዘን ስንጓዝ ሆልምስ ያነሳው ጥያቄ ነበር።

"በሃይልም ቢሆን ወደ ቤት ገብቼ ማን እንዳለ ለማወቅ መስኖለሁ። እናንተ ሰምስክርነት አብራችሁኝ እንድትሆኑ አፈልጋለሁ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ባለቤትህ ምስጢሩን ማወቅ እንደሌለብህ ብታስጠነቅቅህም ተቃራኒውን ለመፈጸም ቆርጠሃል ማለት ነው?"

" አዎ፤እንዲያ ለማድረግ ቆርጫለሁ።"

"ጥሩ! ትክክለኛ ውሳኔ ይመስለኛል። እውነትነቱ የተረጋገጠ ነገር ሁሉ ከመጠራጠር ያድናል።የዚህ ዓይነት አካሄድ ከህግ አንጻር ትክክለኛ ባይሆንም የተሻለ አማራጭ አይኖረንም።"

ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ነው። በዚህ ሳይ ዋናውን መንገድ ጨርሰን ቁጥቋጦና ሳር ወዳለበት ሰርጥ ስንገባ ዝናብ መዝነብ ጀመረ። ማስተር ግራንት ሙንሮ ትዕግስቱ አልቆ ወደፊት ሲገሰግስ እየወደቅንና እየተነሳንም ቢሆን መከተላችን አልቀረም።

"ያ መብራቱ የሚታየው የእኔ ቤት ነው" አሰ በዛፎች መሃል የሚታየውን የብርሃን ጭላንጭል ከሩቅ እያመለከተ። "እኔ እምገባበት ቤት ይኸውና።"

ንግግሩን እንደጨረሰ መታጠፊያ መንገዱን ይዘን ስንጓዝ አንድ ሀንጻ አጠገብ ደረስን። ከፊት ያለው በር በደንብ እንዳልተዘጋ ያስታውቃል። በሮቱ አንደኛው መስኮት ቦግ ያለ ብርሃን ይታያል። ወደ ውስጥ ስንመለከት መጋረጃው ሥር ደብዘዝ ያለ ጥቁር ነገር ይንቀሳቀሳል።

"ያ ነገር ያውና!" ግራንት ሙንሮ ጮክ ብሎ ተናገረ። "እዚህ ቤት ውስጥ የሆነ ሰው እንዳለ ማየት ትችላላችሁ። ተከተሉኝ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ነገር ይለይለታል።"

ወደበሩ እየተጠጋን ስንሄድ ድንገት ከጨለማው ክፍል የወጣች ሴት ቢጫ የሩፍስ መብራት ወዳለበት አካባቢ መጥታ ቆመች። በጨለማው መልኳን ማየት አልቻልኩም። ከንዶቿን



t.me/OLDBOOKSPDF

ስትዘረጋ ግን የምትማሪን ትመስላለች።

"ጃክ፣ ስለ እግዚአብሔር ብለህ እንዳትገባ!" ስትል ጮኸች። "ዛሬ ምሽት ላይ እንደምትመጣ ተጠራጥሬያለሁ። ከዚህ የተሻለ ነገር ይሆናል ብለህ አስብ የእኔ ፍቅር! አሁንም እመነኝ ። ምንም የሚያሳዝንህ ጉዳይ የለም።"

"ኢፌ፣ ብዙ ጊዜ አምኜሻለሁ" አለ ቁጣ በተመላበት ስሜት። "ልቀቂኝ፣ ልለፍበት! እኔና ጓደኞቼ ችግሩን ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት ቆርጠን ተነስተናል" አለና ወደ ጮን ገፍትሯት አለፈ። እኛ ከሥር ከሥሩ ተከትለነዋል። በሩን በርግዶ ሲገባ አንድ አሮጊት ሮጠው መጥተው ከፊቱ በመቆም ላለማሳለፍ ሞከሩ። ወደ ኋላ ገፈተራቸውና ቶሎ ብሎን ወደ ፎቅ ወጣን።ግራንት መንሮ ፅሀፊት ወዳለበት ክፍል ሮጠ ገባ። እኛም ተከትለነው ገባን።

አፓርትመንቱ በጣም ያምራል። በዕቃ የተሞላና በአራት ሻማዎች የደመቀ ነው። ሁለት ሻማዎች ጠረጴዛው ላይ፣ ሌሎች ሁለት ሻማዎች ከዕቃ መደርደሪያው ላይ ተቀምጠው ይንቀሰቀሳሉ። አንዲት ሴት ልጅ በክፍሉ ማዕዘን ካለው ጠረጴዛ ላይ አንገቷን ደፍታ ተቀምጣለች። ረጅም ቀይ ቀሚስ ለብሳ ረጃጅም ነጭ ጓንቶች አድርጋለች። ፊጥና በመዞር ከእኛ ስትቀላቀል የድንጋጤ ጩኸት አሰማሁ። ወደ እኛ የዞረችው ልጅ የፊቷ ገጽታ ሰተመልካች እንግዳና ሰማያዊ ቀለም ያለው ነው። ፍፁም ያልተለመደ ገጽታ። ብዙም ሳይቆይ ምሥጢሩ ተገለጠ። ሆልምስ እየሳቀ እጁን ወደ ሕዛኗ ጆሮ ግንድ አስጠግቶ ያደረገችውን ጭንበል ከፊቷ ላይ ላጠው። በጣም ጥቁር ሕዛን ልጅ እንደበረዶ የነጣ ጥርሷን በሚገርም ሁኔታ እያፍለቀለቀች ከፊታችን ገጭ አለች። ልጅቷ ስትቦርቅ እኔም በሳቅ ፈነዳሁ። መንሮ በመገረም ቆሞ ይመለከታል።

"ያንት ያለህ!" አለ ጮክ ብሎ። "ይሽን ምን ይሉታል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምንነቱን እኔ አነግርሃለሁ" አለች ወይዘሮዋ አሏም አንደአሉ ጮክ ብላ። ወደ ክፍሉ ስትገባ ኩራት ያልተለየውና የተረጋጋ ስሜት ፊቷ ላይ ይነበባል። "ከእኔ ፍላጐት ውጪ አንድነግርህ እያስገደድከኝ ነው። መሆኑ ካልቀረ ሁላችንም በበጐ መልኩ ልናየው ይገባል። ባለቤቱ አትላንታ ውስጥ ሞቷል። ልጅ ግን በሕይወት አለች።"

"የአንቺ ልጅ!?"

ከደረታ አካባቢ በአንገት ሃብል ላይ የተንጠለጠለ ክብር የተሠራ ጠፍጣፋ ነገር አወጣችና "ይህን ነገር ተከፍቶ አይተኸው አታውቅም" አለችው።

"አለመከፈቱን እያየሁት ነው"

ማስፈንጠሪያ ቁልፉን ስትጫነው ተከፈተ። በውስጡ አንድ በጣም የሚያምር ሰው ፎቶግራፍ ቁልጭ ብሎ ይታያል። አፍሪካዊ ዝርያ ያለው መሆኑ በግልጽ ይታያል።

"የአትላንታው ጆን ሔብሮን ማለት ይህ ነው" አለች ወይዘሮዋ። "ጥሩ ሰው ቢሆንም ጥሩ ዕድል አልገጠመውም። እሱን ለማግባት ስል ከዘር ማንዘሬ ተለይቻለሁ። በሕይወት ላለ እሱን በማግባቴ አንድም ቀን ተፀፅቼ አላውቅም። እንደዕድል ሆኖ ግን ብቼኛዋ ልጃችን የእኔን ሳይሆን የአባቷን ቀለም ይዛ ተወለደች። የዚህ ዓይነት አጋጣሚ ብዙ ጊዜ ይከሰታል። ትንሿ ሱሲ ከአባቷም በጣም ትጠቀራለች። ጥቁርም ትሁን ነጭ ልጄን እወዳታለሁ።" ሕሳኗ ልጅ የእናቷን ንግግር ስትሰማ ተመቻችታ ጭኗ ላይ ተጋደመች።

"አሜሪካን ስለት" በማለት ንግግሯን ቀጠለች። "ትንሽ አሟት ነበር። በዚያ ሁኔታ ላይ እያለች አገር መቀየሯ ሊጐዳት ይችላል ብየ አሰብኩ። በመሆኑም በጣም ታማኝ ለሆነችው ስኮትላንዳዊት ሞግዚታችን ትቻት መጣሁ። ልጄን ለመክድ



t.me/OLDBOOKSPDF

አስቤም ሆነ አልሜ አላውቅም። ጽክ፣ አህል ውሃ ከእኔ ጋር ሲያገናኘህ ግን እያፈቀርከህ መጣህ። ስለ ልጅ ለእንተ ለመንገርም ፈራሁ ። እግዜር ይትር ይበለኝ። ላግህ እችላለሁ የሚል ሥጋት አደረብኝ። እናም በዚህ ረገድ እንተን የመድፈር ወኔ አጣሁ። ከሁለት አንዳችሁን መምረጥ ነበረብኝ። በደካማነቴ ሕፃኗን ልጅን ችላ አልኳት። ለሦስት ዓመታት የእሷን መኖር ምሥጢር አድርጌ ያዝኩት። ያም ሆኖ ደህንነቷን አሰማ ነበር። ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከልጅ ጋር የመገናኘት ፍላጐቱ እየጨመረ መጣ። ብዙ ታገልኩ። አልቻልኩም። የሚደርሰውን አደጋ ባውቀውም ልጅቷን ለጥቂት ሣምንታትም ቢሆን ለማግኘት ወሰንኩ። ለአሳዳጊዋ መቶ ፖውንድ ላክሁላትና እዚሁ አጠገቤ ጉረቤቱ ሆና መቶየት እንድትችል መመሪያ በመስጠት በአካባቢያችን ስላለው ቤት ነገርኳት። የእኔ ፍላጐት ከጉርብትና ያለፈ ሌላ ግንኙነት እንደሌለኝ ለማስመሰል ነበር። ሕፃኗ ቀን ከቤት እንዳትወጣ፣ የአጅ ንክኪና የፊት ጭንበል እንዳይለያት ጥንቃቄ እንዲደረግ ጥብቅ መመሪያ ሰጠሁ። አላፊ አግዳሚው በዚያ ሲያልፍ ወደ መስኮቱም ቢሆን መመልከቱ ስለማይቀር እዚያ ቤት ጥቁር ልጅ አሰች አያሰ እንዲጠቋቆምባት አልፈለግሁም። ጥንቃቄ ባላበዛ ጥሩ ነበር። እኔ ግን አንተ ልታውቅ እንደምትችል ሳስብ የምይዘውና የምጨብጠው ይጠፋብኛል።

"ቤቱ መከራየቱን የነገርከኝ አንተ ራስህ ነህ። ልቤ በድንጋጤ ተሸበረ። እንቅልፍ በዓይኔ አልዞር አለ። እስክነጋ መቆየት እንዳለብኝና አንተን መቀስቀስ ራሱን የቻለ ችግር እንደሆነ ባውቅም ሹልክ ብየ ወጣሁ። አንተ ግን ስወጣ አይተኸኛል። የእኔ ችግር ከዚህ ይጀምራል። በሚቀጥለው ቀን ምሥጢሬን ብታውቀውም ጨዋነት በተሞላበት ሁኔታ የራስህን ጥቅም ብቻ ከማስጠበቅ ተቆጥበሃል። ይሁን እንጂ ከሦስት ቀናት በኋላ አንተ ሁኔታዎችን በድጋሜ ለማጣራት በፊት በር ስትገባ ሞግዚቷና ሕጻኗ በኋላ በር ወጥተው አምልጠዋል። እነሆ ዛሬ ምሽት ሁሉንም አወቅኸው። እናም የእኔና የሕፃኗ ልጅ እጣ ፋንታ ምን ሊሆን እንደሚችል



t.me/OLDBOOKSPDF

እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ።" እጆቿን አጣምራ መልስ እየጠበቀች ነበር።

ለሁለት ደቂቃዎች ያክል ዝምታ ሰፈነ። ግራንት መንሮ ዝምታውን ሰበረው። ምንጊዜም የማልረሳው ዓይነት ምላሽ ነበር የሰጠው። ሕፃኗን ልጅ ታቅፎ ሳማት። እሷን በግራ ጉኑ እንደታቀፈ ቀኝ እጁን ወደ ባለቤቱ እየዘረጋ ወደ በሩ ተመለሱ።

"ቤታችን ስንድርስ በጉዳዩ ላይ በሰፊው እንወያያለን" አለ። "ኢፌ፣ እኔ ጥሩ ሰው አይደለሁም። ይሁን እንጂ አንቺ ይሆናል ብለሽ ከምታስቢኝ የምሻል ይመስለኛል።"

እኔና ሆልምስ ወደ ቤታችን ተመለስን። ጓደኛዬ ያበራውን ሻማ ይዞ ወደ መኝታ ክፍሉ እስከገባበት ምሽት ድረስ ስለ ጉዳዩ ምንም ቃል አልተነፈሰም።

በኋላ ከእሱ እንደተረዳሁት ግን ለጉዳዩ ብዙም ትኩረት ሰጥቶት እንዳልነበር በሚገባ ተገንዝቧል። የሆነው ሁሉ እሱ ካሰበው ውጪ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

# የአዳኙ ውሻ እንቆቅልሽ

## ምዕራፍ አንድ

ከነአካቴውም ወደ መኝታ የማይሄድባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ቢሆኑም እያረፈደ መነሳት ያስለመደው ሚስተር ሼርሎክ ሆልምስ ቁርስ ወደሚበላበት ጠረጴዛ ቀርቦ ተቀምጧል። እኔ እሳቱ ዳር ቆሜ ትናንት ምሽት ላይ ቤታችን መጥቶ የነበረ እንግዳ ጥሎት የሄደውን ከዘራ አንስቼ አገልብጣለሁ። ወፈር ያለና በጣም ሚያምር ከዘራ ነው። አንጉቱ ላይ አንድ ኢንች ስፋት ያለው ከብር የተሠራ ጌጥ አለው።

"ለጀምስ ሞርቲመር፣ የሮያል ኮሌጅ ሐኪሞች አባል፣ ከቼሪንግ ክሮስ ሆስፒታል በ1884 ዓ.ም የተሰጠ" የሚል ተጽፎበታል። የቀድሞ ሐኪሞች ያዘወትሩት የነበረው ዓይነት ከዘራ ነው።

"እሽ ዋትሰን፣ ስለ እሱ ከዘራ ምን ታስባለህ? ባለቤቱ ደግሞ በር እያንኳኳ ነው። ሰጥሩም ይሁን ለመጥፎ በእንቱ መያ ለመጠቀም የሚፈልግ ሰው ሲመጣ የተገኘውን አጋጣሚ መጠቀም ጥሩ ነው ዶክተር ጀምስ ሞርቲመር ከሼርሎክ ሆልምስ ምን ይፈልጋል?- ግቡ!"

የሰውየው ቁመና ለየት ያለ ነው። በጣም ረዥምና ቀጭን፣ አፍንጫው ትልቅና አንደወፍ መንቆር ሾጥ ያለ ነው። ጉላ ጉላ ባሉት ግራጫ ዓይኖቹ ላይ መነጽር አድርጓል። ገና ወጣት ቢሆንም ጀርባው ጎባጣ ነው። ሲራመድ አንገቱን ወደ ፊት ሰገግ አድርጉና ረጋ ብሎ ነው። የደከመው ቢመስልም ፈገግታ አልተለየውም። እንደገባ ከዘራውን ሆልምስ እጅ ላይ አየው።



t.me/OLDBOOKSPDF

« በስጦታ የተገኘ ይመስላል» አለ ሆልምስ።

«አዎ ጌታዮ»

«ክቼሪንግ ክሮስ ሆስፒታል!»

«እዚያ ከሚገኙ ጓደኞቼ ጋብቻየን ምክንያት በማድረግ የተበረከተ ልዩ ስጦታ ነው። በነገራችን ላይ፣ ቁመናህ በጣም ደስ ይላል። ሚስተር ሆልምስ የራስ ቅልህ ትንሽነትና የአጥንትህ እድገት ከጠበቅሁት ውጭ ነው። በተለይ የራስህ ቅርጽ የተለየ ስሜት አሳድሮብኛል።»

«ትናንትና ማታም ሆነ ዛሬ የሰልክ ጥሪ ያደረግህልኝ የእኔን ራስ ለመመርመር ብቻ እንዳልሆነ አስባለሁ።»

«ያን የማድረግ አጋጣሚ በማግኘቴ ደስ ይለኛል። ሚስተር ሆልምስ፣ ወዳንተ የመጣሁት ግን በእኔ ሙያ ሊፈታ የማይችል ድንገተኛ ችግር ስለገጠመኝ በጉዳዩ ላይ እንድታማክረኝ ስለፈለግሁ ነው።»

## ምዕራፍ ሁለት

«ኪሴ ውስጥ ጥቂት ወረቀቶች አሉ» አለ ዶክተር ሞርቲመር። ከሦስት ወራት በፊት ከሞተው ከሰር ቻርልስ ባስከርቪል በአደራ የተሰጠኝ ናቸው። የባስከርቪል ሞት ዲቮንሻየር ውስጥ ከፍተኛ ድንጋጤ ፈጥሮ እንደነበር ይታወቃል። እነዚህን ወረቀቶች በጥንቃቄ ነበር የያዛቸው። ድንገተኛ ሞት እንደሚሞት አውቆ ራሱን ያዘጋጀ ይመስላል። »

ሆልምስ ወረቀቶችን ለመውሰድ እጆቹን ዘረጋ። በእሱ ትከሻ ላይ ተንጠራርቼ ቢጫው ን ወረቀትና ደብዛዛው ን ጽሑፍ ተመለከትኩት። ከላይ 'ባስከርቪል አዳራሽ' ይላል። ከታች ደግሞ ባለተስተካከለ ጽሑፍ *1742* የሚሉ ቁጥሮች ሰፍረዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

«የሆነ መልእክት ያለው ይመስላል»

«አም- በባስከርቪል ቤተሰብ በደንብ የሚታወቅ ታሪክ ነው። መልካም ፈቃድህ ከሆነ ለማንበብ ዝግጁ ነኝ ።»

ዶክተር ሞርቲመር ወረቀቶችን ወደ ብርሃኑ አድርገው ልብ የሚያንጠለጥለውን የቆየ ታሪክ አነበበው።

'«ስለ ባስከርቪል ቤተሰብ አዳኝ ውሻ ታሪካዊ አመጣጥ ብዙ መላ ምቶች አሉ። እኔ የሰር ሑጎ ባስከርቪል ልጅ ስለሆንኩና ታሪኩም ስለተነገረኝ፣ ለእሱም በበኩሉ አባቱ ስለነገረው ይኸን ታሪክ እንደወረደ ስጽፈው የተፈፀመት ነገሮች እውነት መሆናቸውን መሉ በመሉ በመተማመን ነው። ከዚህ ታሪክ የምንማረው ባለፈው የተፈጸመውን አያስታወስን አንድንፈራ ሳይሆን ለወደፊቱ እንድንጠነቀትና ቀደም ሲል መከራውን ያየው ቤተሰባችን ከድጋሚ ስቃይ እንዲገላገል ለማድረግ ነው።

"በ1650 ገደማ የባስከርቪል አዳራሽ ባለቤት ሑጎ ባስከርቪል የሚባል ጨካኝና አረመኔ ሰው ነበር። እሱም በአካባቢው አንድ ኮርማን መራት ብቻ ባለው የድሃ ገበሬ ልጅ ፍቅር ይነደፋል። ወጣቲ ግን ስሙ የሰይጣን ስም ነው ብላ ስለምታስብ ትጠላው ነበርና እምቢ ትሰዋለች።

"በዚህ የተናደደው ሑጎ ስድስት ያክል ጨካኝ ጓደኞቹን ይዞ አባቲና ወንድሞቿ በሌለበት ቀን አድቡኮ ይዜድና ወጣቲን ከነበረችበት ጉጆ አውጥቶ ይሄት ይጠፋል- ይጠልፋታል። ወደ ትልቁ አዳራሽ ይዘዋት በመምጣትም ፎቅ ላይ ባለ አንድ ክፍል ውስጥ አስገብተው ይዘጉባታል። ሑጎና ጓደኞቹ ምድር ቤት ሆነው ይጠጣሉ። ከላይ የተዘጋባት ምስኪኗ ልጃገረድ ከታች የሚሰማውን ዘፈን ሁካታና ፉከራ እየሰማች በፍርሃት ትርበተበታለች ። በዚህ አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ እያለች ከጠላፊዎች መካከል እጅግ ገበዝና ደፋር የተባለው ሰው የሚያስደነግጥ ድርጊት ትፈጽማለች። በማራው ሾልካ የቤቱን ግድግዳ ሸፍኖ ሽቅብ የተንሠራራውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሀረግ በመጠቀም ወደ መሬት ወርዳ ሦስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘው ቤታ ጥርግ ትላለች።

"ሐጉ ጥቂት ቆይቶ ሲሄድ ያጠመዳት ወፍ ማምለጫን፣ የነበረችበት ጉጅም ባዶ መሆኑን ይመለከታል። ከዚያማ የሰው ሰይጣን የክፋት ጉረኛ ሆኖ አረፈው። ደረጃውን ወርዶ ወደ ምንብ አዳራሹ እየሮጠ ሄደ። ትልቁ ጠረጴዛ ላይ በመውጣትም ፍንጃሉንም ሳህኑንም ይወረውር ጀመር። በዚህም አላበቃም። በዚያኑ ዕለት ማታ ወጣቷን ልጃገረድ ማግኘት ካልቻለ ሥጋውንም ሆነ ነፍሱን ለሰይጣን መንፈስ አሳልፎ እንደሚሰጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ አያሰተሰ ለጓደኞቹ ነገራቸው።

"ጠረኗን አሽትተው ይሰዩአት ዘንድ የልጅቷን መሃረብ ለአዳኝ ውሾቹ ሰጣቸው። ከዚያም ውሾቹን ተከትሎ በጨለማው ብርሃን እየታገዘ ሜዳና ሸንተረሩን እያቀራረጠ ሽምጥ ይጋልብ ጀመር። እየጠጠ የነበሩት ጓደኞቹ ለጥቂት ጊዜ መጠጡን ጋብ አድርገው ማሰብ ጀመሩ። መጠጥ በጉዳው አእምሯቸው በዚህ ጨለማ፣ ሰው አልባ በሆነው አምባ ምድር ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አወጡ አወረዱ። ሁሉም ግራ ገባቸው። አንዳንዶቹ ጠመንጃ አምጡ ይላሉ። ሌሎች ፈረስ ውሰዱ ይላሉ። ተራዎቹ የወይን መጠጥ ይፈልጋሉ። በመጨረሻ አሥራ ሦስቱም በየፈረሶቻቸው፤ ሐጉና አዳኝ ውሻዎቹን ተከትለው ጋለቡ። አንድ ሁለት ኪሎ ሜትር ያክል እንደተጓዙ መስክ ላይ በግ ከሚጠበቁ አረኞች መካከል በአንዱ አጠገብ ሲያልፉ አዳኝ ውሾቹን አይቶ እንደሆነ ጠርተው ጠየቁት። አረኛው በጣም ፈርቶ ስለነበር መናገር አልቻለም። በመጨረሻ ግን ያቺን ዕድሰብስ ልጃገረድ ሲያሳድዱ ማየቱን ነገራቸው። 'ሌላም አይቻለሁ' አሳቸው። 'ሐጉ ባስከርቪል በጥቁር ፈረስ እየጋለበ በዚህ ሲያልፍ ከኋላው የሰይጣን ውሻ ተከትሎት ነበር። እኔን ስመለከተው አግዚአብሔር እንደማይፈቅድለት ተስፋ አደርጋለሁ።' የሚንቀጠቀጡት ፈረሰኞች አረኛውን እየረገሙት ጉሚቸውን ተጠሉ። ብዙም ሳይቆዩ ግን ፍርሃት ስሜታቸውን አተበተበው። ከፊታቸው እየጋለበ የሚመጣ የፈረስ ኩቴ ይሰማል። ወዲያው የሐጉ ጥቁር ፈረስ ላቡ አስኪንቆረቆር ሽምጥ እየጋለበ



t.me/OLDBOOKSPDF

አልፎአቸው ሄደ። ኮርቻው ላይ ሰው የለም። ከዚያ በኋላ በጣም ስለፈሩ ፈረሶቻቸውን አጠጋግተው መጋለብን መረጡ። በመጨረሻ አዳኝ ውሾች ካሉበት ቦታ ደረሱ። እነዚህ ውሾች የሚታወቁት በአስፈሪነታቸውና በሃይለኝነታቸው ቢሆንም በአንድ ጉድጓዳ ሥፍራ እጅብ ብለው ተሰባስበው ቆመዋል። ከፈረሰኞቹ መካከል ደፋሮች ወይም ብዙ የጠጡት ወደፊት ፈጥነው ገሰገሱ። የጨረቃዋ ብርሃን ጨፍ ያለስትማል ። መከረኛዋ ልጃገረድ ከጎድጓዳው ሥፈራ ላይ ተዘርግታ ወድቃለች። በፍርሃትና በድካም ብዛት ሞታለች። አረመኔዎቹ ሰዎች ግን የእሷንም ሆነ አጠገቧ የወደቀውን የሉጉ ባስከርቪል ራሳ አይተው አልተደናገጡም። ሆኖም ግዙፍ አዳኝ ውሻ የሚመስል በሰው ልጅ ዓይን ታይቶ የማይታት ጥቁር አውሬ በሉጉ አስከሬን ላይ ቆሞ ጉሮሮውን ሲቦጫጭቀው ሲያዩ መሄጃው ጠፋባቸው። ቀጥሎም የእሳት ነበልባል የሚመስሉ ዓይኖቹንና በደም የተነከረ ጥርሱን ወደ እነሱ ሲያዞር በፍርሃት እንደተዋጡ ነፍሳቸውን ከሞት መንጋጋ ለማትረፍ ያን ኮረብታማ ምድረ-በዳ አቋርጠው ሸመጠጡ።

«ቤተሰቡን ሲያስጨንቀው የኖረው የአዳኙ ውሻ ታሪክ ይኸን ይመስላል እንግዲህ፣ ልጆቼ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የብዙ ቤተሰባችን አሟሟት በጣም አሳዛኝ ነው። ድንገተኛ ብቻም ሳይሆን ያልተለመደ አሟሟት። እናም በእግዚአብሔር እንድታምኑ እማፀናችኋለሁ። ያን አምባ ምድር /moor/ በጨለማ እንዳታቋርጡ አበክሬ አስጠነቅቃችኋለሁ። ሰይጣን በጨለማ ይነግሣል፤ ጉልበቱም ይበረታልና።»'

ዶክተር ሞርቲመር ይኸን አስገራሚ ታሪክ አንብቦ ሲጨርስ ወደ ሚስተር ሼርሎክ ሆልምስ አሻግሮ ተመለከተ።

"ሚስተር ሆልምስ፣ ከዘህ በመቀጠል የቅርብ ጊዜ ታሪክ አንብልሃለሁ። ከጋዜጣ የተወሰደ ነው። በያዝነው ዓመት የሰኔ 14 የዲቮን ክፍለ ግዛት ጋዜጣ ይሆት የወጣ ዜና ነው። ጋዜጣው ከጥቂት ቀናት በፊት ስለተከሰተው የሰር ቻርለስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ባስከርቨል አሚሚት አጭር ዘገባ አቅርቧል።»

ዓይኖዬ አንቱን ወደፊት ሰገግ አርጎ በጉጉት ያዳምጣል። እንግዳው ንግግሩን እንደገና ጀመረ።

«የሰር ቻርልስ ባስከርቨል ድንገተኛ አሟሟት በዲስከሪክቱ ኗሪ ላይ ከፍተኛ ሀዘን አስከትሏል። ሰር ቻርልስ ምንም እንኳን የባስከርቨል አዳራሽ በመባል በሚታወቀው አካባቢ ለአጭር ጊዜ የኖረ ቢሆንም ሰብዓዊነቱና ችርነቱ በብዙዎቹ ዘንድ ከበሬታን አትርፎለታል። እንደሚታወቀው ሰር ቻርልስ በንግድ ሥራ ተሠማርቶ ብዙ ሀብት ያፈራው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ነው። ልጆች የሉትም። በሕይወት እያለ እሱ የሚኖርበት አካባቢ በሙሉ የእሱ ሃብት ተጠቃሚ መሆን እንዳለበት በግልጽ ይናገር ነበር። ለበጎ ሥራ አገልግሎት እንዲውል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በዚህ ጋዜጣ ላይ ይዘገብ እንደነበር ይታወሳል። ከሰር ቻርልስ አሟሟት ጋር የተያያዙ የምርመራ ውጤቶች በግልጽ ተበራርተው ባይወጡም ጋዜጣው በአካባቢው የሚወራውን ወሬ ከመዘገብ አልቦዘነም። የተፈጥሮ ሞት መሞቱም ይነገራል።

«ሰር ቻርልስ ብቻውን ነበር የሚኖረው። ከማንኛውም ተራ ሰው ያልተለየ አኗኗር ። አሽከሮቹ ሁለት ብቻ ናቸው። ባልና ሚስቱ ሚስተርና ሚስዝ ባሪሞር ። እነሱ የሰጡት ታል ለኖቲት ጊዜም ቢሆን የቻርልስ የጤና ሁኔታ ጥሩ እንዳልነበር ያመለክታል። ምናልባት በልብ ሕመም ምክንያት ። በዚሁ ሳቢያ የፊቱ ቀለም ይለዋወጥና የመተንፈስ ችግርም ይታይበት እንደነበር ታውቋል። የግል ሐኪሙና ዓይኖው የነበረው ዶክተር ጀምስ ሞርቲመር በዚህ ይስማማል።

«ሰር ቻርልስ ባስከርቨል ወደ መኝታው ከመሄዱ በፊት በግቢው አካባቢ ባለውና ዛፎች በሚበዙበት መናፈሻ በምሽት መንሸራሸር ያዘወትር ነበር። ግራና ቀኝ በዛፎች የታጀበው የመናፈሻ መንገድ ከመኖሪያ አዳራሹ ግቢ ብዙም አይርትም። በተጣዩ ቀን ወደ ለንደን ለመሄድ ማቀዱን፣ በዋዜማው ስነ



t.me/OLDBOOKSPDF

አራት ተናግሯል። በተናገረበት ቀን ማታ ለአጭር ጊዜ ሽርሽር ወጥቶ ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ሲጋራ አጭሷል። ግን አልተመለሰም። እንደወጣ ነው የቀረ። አዙሰ ሊሊት ላይ ባሪሞር የፊት ለፊቱ በር ሳይዘጋ ሲያገኘው በጣም ተጨነቀ ። መዘራት ይህ ጊታውን ፍለጋ ጠላ። ቀኑ ርጥበታማ ስለነበር የሰር ቻርለስን ዱካ በመንገድ ላይ ማግኘት አልተቻገረም። ከመናፈሻው መንገድ አጋማሽ ላይ ወደ ኮረብታው የሚያስወጣ በር አለ። ሰር ቻርለስ ለጥቂት ጊዜ በሩ አካባቢ መቆመን የሚጠቁመው ምልክቶች ነበሩ። መንገዱን ተከትሎ ቁልቁል በሚወስደውና ከዚያ በጣም ርቶ በሚገኝ ቦታ ላይ ነው ሞቶ የተገኘ። ባሪሞር በሰጠው ቃል ውስጥ ያልተገለፀ አንድ ነገር አለ። ይኸውም የጌታው ዱካ ከግቢው ከወጣ በኋላ የተለወጠ መሆኑ ነው። የግቢውን በር አንዳለፈ በእግሮቹ ጣቶች አየተራመደ ሄዲል የሚል ጥርጣሬ ነው ያሳደረው። በሰውነቱ ላይ የነዳት ምልክት አይታይም። ይከተሩ የሚለው በፊቱ ላይ የመለዋወጥ ስሜት ይነበባል ነው። ሰውጡ በጣም አስክፊ ከመሆኑ የተነሳ ይከተር ሞርቲመር የጓደኛውን መልክ መለየት የማይችልበት ሁኔታ ገጥሞት እንደነበር ነው የሚናገረው። ነገር ግን በልብ ድካም በሚሞቱ ሰዎች ላይ ይህ ያልተለመደ ክስተት አይደለም። የምርመራው ውጤት በሰፊር አካባቢ ጉዳዩን አስመልክቶ ውስጥ ለውስጥ የሚብላሉትን አንገል አሉባልታዎች ወደ አደባባይ እንዳይወጡ አድርጓል።

«በሰር ቻርለስ ዕግር ተተኩዩ የሚሠራ ጠንካራ የሆነ የቤተሰቡ አባል ያለመገኘቱ ጉዳይ ደግሞ የተጠቀሰውን ታሪክ ውስብስበነት አያባባሰው መጥቷል። ወደ ባስከርቭል አዳራሽ ማን ይኖር ይሆን? አሁን ያለው የቅርብ የሥጋ ዘመድ ሚስተር ሔንሪ፣ የሰር ቻርለስ ባስከርቭል የታናሽ ወንድሙ ልጅ ነው። ወጣቱ ሔንሪ አስክቅርብ ጊዜ ድረስ አሜሪካ ውስጥ ይኖር እንደነበር ማወቅ ተችሏል። ስለሆነታው ለእሱ በመንገር የተፈጠረውን ጥሩ አጋጣሚ እንዲጠቀምበት ለማድረግ ሔንሪን የማፈላለጉ ሥራ ተጀምሯል።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ይህ ነው እንግዲህ ሚስተር ሆልምስ የሰር ቻርለስ ባስከርቪልን አሟሟት በተመለከተ ሕዝብ የሚያውቀው እውነታ።»

«ይህ ጋዜጣ ከሕዝብ የተገኙ መረጃዎችን ሁሉ ያጠቃልላል እያልከኝ ነው። ከግል ጋዜጦች የተገኙ መረጃዎችን ብታገኝልኝስ?»

«እስክ አሁን ለማንም ያልተናገርኩትን አሁን ላንተ እነግርሃለሁ። በኮረብታማው መልካ ምድር አካባቢ ሰፍረው የሚኖሩት ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው። በመሆኑም ጓደኛ ለመምረጥ የሚኖረው ዕድል በጣም ጠባብ ነው። ሰር ቻርለስ ባስከርቪልን ብዙ ጊዜ ነበር የማገኘው። ከተፈጥሮ ሳይንስ ባለሙያው ከሚስተር ስቴፕልተን በስተቀር ብዙ ርቀህ ብትሄድም የተማሩ ሰዎችን አታገኝም። ከእሱ ጋር ጓደኛ የሆንነው በሳይንሱ ዘርፍ የጋራ አመለካከት ስላለን ነው። ስለተለያዩ የአፍሪካ ጉዛምች አካላዊ አወቃቀር /አናቶሚ/ ጥናታዊ ውይይት ስናደርግ ብዙ ምሽቶች አብረን አሳልፈናል።

«ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ ሰር ቻርለስ በጣም ተጨናቂ ሰው እንደሆነ እየተገለፀልኝ መጣ። ያነበከላችሁ ታሪክ ያሳስበው እንደነበር ተረዳሁ። እናም በራሱ ግቢ ባለው መናፈሻ ውስጥ ቢንሸራሸርም በጨለማ ወደ ኮረብታማው አካባቢ ለመጡጣት የሚገፋፋው አንዳችም ነገር አልነበረም። ያም ሆኖ ሁሉም የቤተሰብ አባላት መጥፎ ዕድል እንደሚገጥማቸው በጣም ርግጠኛ ነበር። ስለአንዳንድ ርኩሳን መናፍስት አማሰብ ተቆጥቦ አያውቅም። ሰር ቻርለስ ወደለንደን እንዲሄድ ምክሬን ለገስኩት ። የልብ ድካም እንደነበረበት አውቅ ነበር። የነበረበት አላስፈላጊ የድንጋጤ ሁኔታም በጤናው ላይ አፍራሽ ተጽእኖ አላሳደረም አይባልም። በለንደን ከተማ ለጥቂት ወራት ሲዝናና ቆይቶ መንፈሱን አድሶ ይመለሳል ብየ ነበር ያሰብኩት። የሁለታችንም ጓደኛ የነበረው ሚስተር ስቴፕልተንም ከዚህ የተለየ ሃሳብ አልነበረውም። በመጨረሻ የተከሰተው ሁኔታ ግን እጅግ አሳዛኝ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሰር ቻርለስ በሞተበት ሌሊት አሽከሩ ባሪሞር መልዕክት ላከብኝ። በአንድ ሰዓት ውስጥ ባስከርቪል አዳራሽ ደረስኩ። በዛፍ በታጀበው መንገድ ላይ ኮቴውን ተከትየ ቁልቁል ወረድሁ። ቆሞ ቆይታ የተባለበትን የግቢ በርም አየሁት። ከዚህ በኋላ ከባሪሞር ዱካ በስተቀር ሌላ አለመኖሩን ተገነዘብኩ። በመቀጠል እኔ ከመድረሴ በፊት ማንም ያልነካውን አስከሬን በጥንቃቄ መረመርኩ።

«ሰር ቻርለስ ፊቱ ወደመሬት ተደፍቶ ተዘርሯል። ክንዶቹ ተዘርግተዋል። ጣቶቹ ወደ መሬት ገብተዋል። ፊቱ ከመቀየሩ የተነሳ ለመለየት ተቸግሬ ነበር። አሽከሩ ባሪሞር ከሰጠው ቃል ውስጥ ግን አንዱ ስህተት ነበር። በአስከሬኑ ዙሪያ ምንም ምልክት የለም ብሎ ነበር። መኖሩን አላስተዋለም። እኔ ግን ትንሽ ራቅ ብሎ በግልጽ የሚታይ ያልቀየ ምልክት አይቻለሁ።"

"የእግር ዱካ?»

"አዎ፣ የእግር ዱካ"

"የወንድ ወይስ የሴት?»

ዶክተር ሞርቲመር ባልተለመደ ሁኔታ ለአፍታ ያህል ወደ እኛ ተመልክቶ መልስ ሲሰጥ የማናገረው አይሰማም ነበር። ድምፁ መተት አለ።

"ሚስተር ሆልምስ፣ የግዙፍ አዳኝ ውሻ ዱካም ናቸው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሦስት

ዶክተሩ ሲናገር ይታይ የነበረው የድምጽ መንቀጥቀጥ ባየው ነገር ልቡ የተነካ መሆኑን ያመለክታል። ሆልምስ አንገቱን ወደፊት ሰግጎ፣ ዓይኑን አፍጥጦ በጉጉት ያዳምጣል።

«ለምንድነው ሴሎች ያላዩት»

«ምልክቶቹ ከወደቀው አስክሬን አሥር ሜትር ያክል ስለሚርቁ ትኩረት የሰጠ አልነበረም። እኔ ታሪኩን አውቅ ስለነበር...»

«የአየሩ ጠባይስ ምን ይመስል ነበር?»

«ርኃበታማና ቀዝቃዛ»

«መናፈሻውስ ምን ይመስላል?»

«ብመንገዱ ግራና ቀኝ ችፍግ ብለው የተተከሉ የጥድ ዛፎች አሉ። የመንገዱ ስፋት ስምንት ሜትር ይሆናል።»

"ግቢው በር አለው አይደል?»

"አዎ ወደ መናፈሻው የሚያስወጣ ትንሽ በር»

"ሌላ መውጫስ አለ?"

"የለም"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ወደመናፈሻው ለመድረስ ማንም ሰው ከቤት ተነስቶ ወደታች መውረድ ወይም ከኮረብታው በኩል ባለው በር ከፍቶ መግባት አለበት ማለት ነው?"

"በበጋ አልፍኑ በኩል ውስጥ ለውስጥ የሚያስወጣ መንገድም አለ»

"ሰር ቻርለስ ወደዚያ ሄዶ ነበር?"

"አልሄደም። ሃምሳ ሜትር ያክል ርቆ ነው የወደቀው»

"እሽ ዶክተር ሞርቲመር፤ ከግቢው በር ላይ ምን እንዳየህ አስቲ ንገረኝ?"

"ሰር ቻርለስ ለአምስት ወይም ለአሥር ደቂቃ እዚያ ቆሞ እንደነበር አርግጠኛ ከመሆን በስተቀር ምንም ምልክት አላየሁም።"

"እንዴት አወቅህ?"

"የሲጋራ አመድ ስለነበር"

"ግሩም! ይኸ ሊደነቅ የሚገባው አጋዥ መረጃ ነው፤ ዋትሰን። የዕግር ኩቱ አልነበረም?"

"በጣም ተምታቶባቸዋል።ሰር ቻርለስ በሄደበት መንገድ ሁሉ የራሱን ምልክት ትቷል። ሌላ ምልክት አላገኘሁም።"

ሼርሎክ ሆልምስ ተናደደና በአንድ እጁ የጣለ ጉልበቱን በሃይል መታው።

"ለምንድነው እዚያ ያልሄድኩት?" ሲል ድምፁን ከፍ አድርጐ ተናገረ። "ጉዳዩ በጣም የተለየና ሳይንሳዊ የሆነ ምርመራን የሚጠይቅ ነው። አ፤ ዶክተር ሞርቲመር



t.me/OLDBOOKSPDF

ለምንድነው ቀደም ብለህ ያልነገርከኝ?"

"እጅግ ገበገና ከፍተኛ ልምድ ላካበተ ሳይንቲስት እንኳን እንቆቅልሽ የሆኑ አንዳንድ ነገሮች አሉ። ሚስተር ሆልምስ፤ የሞት አደጋው ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ለጆሮየ እንግዳ የሆኑ ነገሮችን ሰምቻለሁ። ይኸ አሰቃቂ ሁኔታ ከመከሰቱ በፊት አያሌ ሰዎች በኮረብታማው ምድረ በዳ አካባቢ የባስከርቪል ቀሳፊ መንፈስ ነው ተብሎ የሚታመንበት አውሬ መሰል ፍጡር ማየታቸውን ይናገራሉ። ሳይንስ የማያውቀው እንስሳ መሆን አይችልም። በጣም ግዙፍና አሳት የሚተፋ አስፈሪ ፍጡር መሆኑን ሁሉም ያምናሉ። እነዚህን ሰዎች ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸዋለሁ። ሁሉም ስለዚህ እንስሳ የሚናገሩት ተመሳሳይ ነው። የግዙፉ አዳኝ ውሻ ታሪክ በአካባቢው ፍርሃትን አንግሷል። ጅግና ነኝ ያለ ብቻ ነው፤ የሰፈሙን መናፈሻ ሚዳና ሽንተረር በጨለማ ማቋረጥ የሚችል።"

"አንተ የሳይንስ ተማሪ እንደመሆንህ የተፈጥሮ ክስተት በመሆኑ አታምንም?"

" የመጀመሪያው አዳኝ ውሻ ተፈጥሮአዊ ነው። የሰውን ገረሮ ቆርጦ ለማጠጣትም ብቃት አለው፤ እንደዚያም ሆኖ አረመኔያዊ ባህሪም አለው።"

"በታሪክ የምታምን መሆንህን እያየሁ ነው። ነገር ግን በዚህ የምታምን ከሆነ ለምንድነው የእኔን አገዛ ፈልገህ ወደዚህ የመጣኸው ?"

ዶክተር ሞርቲመር ሰዓቱን ተመለከተ፤ "ሰር ሔንሪ ባስከርቪል በአንድ ሰዓት ተኩል ውስጥ ሸንደን ይደረሳል። ይህን መልካም ባህሪ የተላበሰ ወጣት አፈላልገን ካናዳ እየሠራ መሆኑን አረጋግጠናል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደሚመስለኝ ሴላ ያገባኛል ባይ ወራሽ የለም።"

"የለም። ከሦስቱ ወንድማማችነት ስለ ታናሹ ስለ ሮጀር ባስከርቪል በቂ መረጃ አለን። ሰር ቻርለስ የሁሉም ታላቅ ነው። ሁለተኛውና በወጣትነቱ የሞተው የወጣቱ ሔንሪ አባት ነው። ሮጀር የቤተሰቡ ማፊሪያ የሚል ቅጽል ስም የወጣለትና የትም ቀልጦ የቀረ ነው። እንደ አባቱ ጥበበኛና አያት ቅድመ አያቶቹን ይመስል እንደነበር ነግረውኛል። ሮጀር ወደ ማዕከላዊ አሜሪካ እንደተሰደደ በ.ጫ ወባ ይዞት በ1876 ሞተ። ስለዚህ የባስከርቪል ቤተሰብ የመጨረሻ ትውልድ የሆነውን ሔንሪን ዋተርሉ ባቡር ጣቢያ ሄጄ አቀበለዋለሁ። ሚስተር ሆልምስ፣ እሱን በተመለከተ ማድረግ ባለብኝ ጉዳይ ላይ ምን ትመክረኛለህ?"

"ለምን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት አይሄድም? በግለጽ ለማስቀመጥ ዳርትሙር ለባስከርቪሎች ደህንነት የሥጋት ምንጭ እንዲሆን የሚያደርግ ሃይለኛ የሰይጣን መንፈስ አለበት ብለህ እያሰብክ ነው?"

"ይመስለኛል"

"የአንተ ሃሳብ ትክክል ከሆነ በዳርትሙር በወጣቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሰው ርኩስ መንፈስ ለንደን ላይ ጥቃት የማያደርስበት ምክንያት አይኖርም። መቼም ሥልጣኑ በትውልድ መንደር ላይ ብቻ የሚወሰን ሰይጣን ይኖራል ብሎ ለማመን ያዳግታል። እኔ የምመክርህ በሰረገላ ወደ ዋተርሉ ጣቢያ በመሄድ ሰር ሄንሪ ባስከርቪልን እንድታገኘው ነው። እኔ ወስኜ እስከምነግርህ ምንም ነገር አታድርግ። ነገ አራት ሰዓት ላይ ሰር ሔንሪ ባስከርቪልን ይዘህ ትመጣለህ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዳልከኝ አደርጋለሁ ሚስተር ሆልምስ" አለና ወጥቶ እብስ አለ።

ሆልምስ ፍጹም ደስታ በተመላበት ስሜት ወደ መቀመጫው ተመለሰ።

"እየወጣህ ነው ዋትሰን? በደንበኛዬ በብራድሌይ ሱት ስታልፍ የአንድ ፖውንድ ሲጋራ እንዲልክልኝ ትነግርልኛለህ?"

ንደኛዬ ከባድ ሃሳብ ውስጥ ሲሆን ብቸኝነትን እንደሚመርጥ አውቃለሁ። በመሆኑም እስከ ምሽት ድረስ ወደ ቤከር ጎዳና ላልመለስ ከበብ ውስጥ ነው ጊዜየን ያሳለፍኩት። መጀመሪያ ላይ ክፍሉ በጪስ ሲታፈን ታጠሎ መስሎኝ ነበር ። የክባድ ሲጋራ ጭስ ጉረሮየን ዘግቶ ይዞ ያስለኝ ጀመር።

"ዋትሰን ቶሎ ብለህ መስኮቱን ክፈተው ። ቀኑን ሙሉ ከበብ ውስጥ እንደነበርክ ይገባኛል"

"ትክክል። ግን እንዴት አወቅህ?"

አነጋገሬ አስገርሞት ሳቀ።

"አንድ ሰው ዝናብ ሆኖ ጭቃ በበላበት ቀን ወደ ውጭ ወጥቶ ማታ ባርኔጣውም ሳይረጥበት፣ ጫማውም ሳይቆሽሽ ተመለሶ ከመጣ ምን ማለት ይቻላል? ቀኑን በሙሉ ሳይንቀሳቀስ በአንድ ቦታ ተቀምጦ ውሏል ማለት ነው። አባባሌ ግልጽ ነው?"

"አዎ አባባልህ ግልጽ ነው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ልብ የሚለው ባይኖርም ዓለም ግልፅ በሆኑ ነገሮች የተሞላች ናት። አንተ ከሄድክ በኋላ የዚህን የምታየውን አካባቢ ሜዳና ኮረብታ ግልፅ አድርጎ የሚያሳይ ካርታ አስመጥቻለሁ። እዚህ መሀከል ላይ የሚገኘው የባስከርቪል አዳራሽ በመባል የሚታወቀው ነው። እዚህ አጅብ ያሉ ሕንፃዎች ያሉበት ቦታ የግሪምነን መንደር ነው። ዶክተር ሞርቲመር የሚኖረው እዚህ ነው። እንደምታየው አልፎ አልፎ ቤቶች ይታያሉ። እዚህ ጋ ያለው ቤት የተፈጥሮ ሳይንስ ምሁሩ የስቴፕልተን ሊሆን ይችላል። እዚህ ደግሞ ሁለት ቤቶች አሉ። አሥር ኪሎሜትር ያክል ርቀት ታሳቱ የፕሪንስታውን አሥር ቤት ይገኛል። በዚህ አካባቢ ያለው በሙሉ አምባ ምድር እያሉ የሚጠሩት ባዶ ምድረ በዳ ነው።"

"በረሃ ነው ማለት ነው"

"አዎ፤ ሠይጣን በሰዎች ጉዳይ ጣልቃ የመግባት አትምና ፍላጐት ካለው—ማለት ዶክተር ሞርቲመር እንደሚለው ከተፈጥሮ ሕግ ውጪ ከሚንቀሳቀሱ ሃይላት ጋር እየተላተምን ከሆነ ክትትላችን እዚህ ላይ ያከትማል። ይሁን እንጂ የሚቻለውን ምርምር ሁሉ ከማድረግ መቆጠብ የለብንም። ለመሆኑ እንዳንድ ነገሮች ላይ ግንባቤ ወስደሀል። ለምሳሌ በፅሁፉ ኩቱ ላይ ስለታየው ለውጥ ምን ታስባለህ?"

"እንደባሪሞር አባባል ሰውየው ወደ መኖሪሻው የወረደው በፅገር ጣቶቹ ብቻ እየረገጠ ነው።"

"በመኖሪሻው ውስጥ በፅገር ጣት እየረገጡ የሚያስኬድ ምክንያት አለ? ይሮጥ ነበር ማለት ነው ዋትሰን? እግሬ አውጪኝ ብሎ ሕይወቱን ለማዳን ሮጦ እንደሆነስ- በዚሁ ሳቢያ ልቡ ፊንድታ በአፍ-ጢሙ አስክሚደፋ!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ችግሩ ያለው እዚህ ላይ ነው። ከመሮጡ በፊት ከፍተኛ ፍርሃት አድሮበት ራሱን ስቶ እንደነበር ግን ምልክቶች አሉ።"

"እንዴት ይህን ልትል ቻልክ?"

"እኔ እንደማስበው ለፍርሃቱ ምክንያት የሆነው ነገር ከወደ መናፈሻው የመጣ ነው። ያ ከሆነ ደግሞ ወደ ቤቱ መሮጥ ሲገባው ከቤቱ ወደጫካ የሚሮጥ አዕምሮውን መቆጣጠር የማይችል ዕብድ ብቻ ነው። ዕርዳታ ማግኘት ወደማይችልበት አቅጣጫ ነው የሮጠ። በጨለማ ማንን እየጠበቀ ነበር? ለምንድነው ቤቱ ሆኖ በመጠበቅ ፋንታ መናፈሻ ውስጥ ሆኖ መጠበቅ የፈለገው? ሰውየው ሽማግሌና የጤና ችግር የነበረበት ነው። የአየሩ ሁኔታ ርጥበታማና ቀዝቃዛ ነው። ዶክተር ሞርቲመር እንደሚለው የሲጋራ ኩስታሪው ሰውየው ለአምስት ወይም ለአሥር ደቂቃዎች ቆሞ ሲያጨስ እንደነበር ያመለክታል። ይኸም ግን አዲስ ነገር አይደለም።"

"ግን እኮ ሁልጊዜ ምሽት ላይ ለሽርሽር ይወጣ ነበር።"

"ወደ መናፈሻው በሄደ ቁጥር ሁልጊዜ ግቢው በር ላይ ይቆም ነበር ብየ አላስብም። እንዲያውም ወደዚያ መሄድ አቁሞ ነበር የማል መረጃ ነው ያለን። ያን ዕለት ማታ እዚያ ቆሞ ቆየ። ወደ ለንደን ሊሄድ ካቀደበት ቀን ዋዜማ ምሽት ላይ ማለት ነው። አሁን የነገሮችን ክዋኔ በቅደም ተከተል ማየት ጀመሬአለሁ።ዋትሰን! አባከህ ቫዮሊኔን አቀብለኝ? ነጣ ያሉ የሚመጡትን ዶክተር ሞርቲመርንና ሰር ሔንሪ ባስከርቪልን እስክምናገኝ ይኸን ጉዳይ ለጊዜው እናቆየው።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አራት

የቱርስ ጠረጴዛችን በጧቱ ጽድት ብሏል። ሆልምስ የሴሊት ገዋኑን እንደለበሰ እንግዶቹን ይጠብቃል። ዶክተር ሞርቲመር አንድ አጠር ያለ፣ ዓይኖቹ ጥቁር ሆነው ፊቱ ላይ የመጓጓት ስሜት የሚነበብበት ሰው ከጎላው አስከትሏል። በግምት ሰላሳ ዓመት ይሆነዋል። ሰውነቱ ፈርጠም ያለና ደልዳላ ነው። የዓይኖቹ ቅንድቦች ጉርችም ብለው የበቀሉ ናቸው። ፀሐይ ያቃጠለው ፊቱ ለረጅም ጊዜ በዝቅተኛ ቦታ የኖረ ያስመስለዋል። ቀላ ያለ ቡኒ መሉ ልብስ ለብሷል።

"ሰር ሔንሪ ባስከርቪል ይባላል" አለ ዶክተር ሞርቲመር። "እኔን የሚገርመኝ ሚስተር ሆልምስ፣ ኃይኛዩ ዛሬ ጧት ወደ አንተ ባይመጣ ነበር። እኔማ መቅረት አልችልም። አንዳንዶቹ እንቅትልሾች በኖልት አንዳሰበህ አውቃለሁ። ዛሬ ጧት ደግሞ የገጠመኝ ልፈታው የማልችለው ዓይነት ነው። እንኳ ይሽን ደብዳቤ ተመልከተው ። ደብዳቤ ልትለው ክቻልክ ማለቱ ነው። ዛሬ ጠዋት ነው የደረሰኝ።"

አንድ ኢንቨሎፕ ጠረጴዛው ላይ ሲያስቀምጥ ሁላችንም አድራሻውን ለማየት አተኮበስን፣ *ሰር ሔንሪ ባስከርቪል፣ ናርዝ አምበርላንድ ሆቴል* የሚል በትልት ፊደላት ተሞንጫጭሮ ተጽፎበታል። የፖስታው አርማ "ቼሪንግ ክሮስ" የሚል ሲሆን ፖስታ ቤት የገባው በትናንትናው ምሽት ነው።

"ወደ ናርዝ አምበርላንድ ሆቴል እንደምትሄድ ማን ያውቅ ነበር?" ሆልምስ ጠየቀ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ማንም አያውቅም። ከዶክተር ሞርቲመር ጋር ከተገናኘን በኋላ ነው የወሰንነው።"

"እውነትክን ነው! በእንተ እንትስታሴ ላይ ትኩረት አድርጉ እንዲሠራ የተመደበ ሰው አለ ማለት ነው።" ከኢንቨለሎፑ የሆነ መረቀት አወጣ። በታይፕ ተጽፈው የተበጣጠቱ ታላትን በመግጣጠም አንድ ዐረፍተ ነገር ተሠርታል፡ " If you value your life keep away from the moor- ለሕይወትህ ዋጋ የምትሰጥ ከሆነ ራስህን ከሩረቢታማው ጠፍ ምድር (ሙር) አርቅ እንደማለት። moor የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በእጅ፣ በተለም የተጻፈ ነው።

"ታዲያ ይኽ ምን ማለት ነው? በእኔ ጉዳይ ይህን ያክል ተጨንቆ ጣልቃ አየገባ ያለው ማነው?"

"ሰር ሔንሪ፣ ከዚህ ቤት ከመውጣትህ በፊት የምናውቀውን ሁሉ ለእንተ ለማካፈል ወደ ኋላ እንደማንል ቃል አግባልሃለሁ። የትናንቱ የታይምስ ጋዜጣ አለህ ዋትሰን? የውስጥ ገጹቹን አውጣና ስጠኝ። በተለይ የዋና ዋና መጣጥፎችን የውስጥ ገጾች ገልበጥ፣ ገልበጥ አደረገና፣ "እዚህ ጋ ጥሩ መጣጥፍ አለ። ነፃ ንግድን በሚመለከት የተጻፈውን በጥቂቱ እንዳነብላችሁ መልካም ፈቃዳችሁ ይሁን፣ "የአገር ውስጥ ንግድ ወይም ኢንዱስትሪ የሚበረታታው ከውጭ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ በሚጣል ታክስ ነው ብለህ ታስብ ይሆናል። እነዚህ ታክሶች ግን ከብዙ ጊዜ በኋላ የአገር ሃብትን መጥቶ አድርገው ይዘው ይጠፋሉ። ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎች የጠቃሚታ ዋጋም ይቀንሳል። እንዲህም አደለ በደሴቲቱ የሚኖረው አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ያሽቆለቁላል። አንተስ ምን ታስባለህ ዋትሰን?' " አለ ሆልምስ ድምፁን ከፍ አድርጉ የደስታና የእርካታ ስሜቱን ለመግለጽ እጁን እያሻሸ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምንም ግንኙነት አንደሌለው ነው የማስበው።"

"እንደዚያም ሆኖ ውድ ዋትሰን አንዱ ከሌላው የተወሰደ ስለሆነ በጣም የተቀራረበ ግንኙነት አላቸው። እነዚህ ቃላት ከየት እንደተወሰዱ ማየት አትችልም?" (በእንግሊዝኛው ጽሑፍ ላይ፤ *If you value your life keep away from the moor* የሚሉ ቃላት ስላሉ ማለት ነው።)

"ያንት ያለህ፤ትክክል ነህ!"

"እንዳትጠራጠር የሚያደርግህ *Keep away* የሚሉት ቃላት ለየብቻ ተቆራርጠው የወጡ ናቸው።"

"በእውነት ነው የምልህ ሚስተር ሆልምስ፤ ይህ ልገምተው ከምችለው ሁሉ በላይ ነው።" አለ ዶክተር ሞርቲመር ጓደኛዬን ሆልምስን በአግራሞት እየተመለከተ። "እንዴት መጣልህ"?"

"የአንድን ጭላ ራስ፤ ከሌላው ጭላ መለየት ትችላለህ ብየ እገምታለሁ ዶክተር"

"በእርግጠኝነት"

"ግን እንዴት?"

"እኔ የተለየ መ.ያየ ስለሆነ ነው። ልዩነቶቹም ግልጽ ናቸው።"

"ይኸ ደግሞ የእኔ የተለየ መ.ያ ነው። ልዩነቶችም እንዲሁ ግልጽ ናቸው። አንዱ አንዳልከው በሁለት ጭላዎች መካከል ልዩነት አንደሚኖር ሁሉ በታይምስ ጋዜጣና በሌሎች በርካሽ ዋጋ በሚታተሙ ጋዜጠች መካከል ያለው ልዩነት ቁልጭ ብሎ ነው የሚታየኝ። ስለ ወንጀል ለሚያጠና ሰው ስለ ሕትመት ጥበብ ማወቅ ከባድ ነገር አይደለም።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ስለዚህ መልእክቱን የሆነ ሰው በመቀስ ቆርጦ አውጥቶ ወረቀቱ ላይ ለጠፈው። አሁን ማወቅ የምፈልገው ግን መ-ር የሚለው ቃል ለምን እንደተጻፈ ነው።"

"ምክንያቱም ቃሉን ሕትመት ላይ ማግኘት አልቻለም። ሊሉት ግን ቀላል ናቸው። ከማንኛውም ጽሑፍ ላይ ሊገኙ ይችላሉ። 'moor' የሚለው ግን ተራ ቃል አይደለም።"

"እርግጥ ነው! ይህ አባባል ይገልጸዋል። በዚህ መልዕክት ውስጥ ግን ሌላ የተለየ ነገር ይታይሃል ሚስተር ሆልምስ?"

"የሆነ ፍንጮች አሉ። አድራሻው እንደምታየው በትላልቅ ፊደላት ተሞክሏቸው የተጻፈ ነው። የታይም ጋዜጣ የዘወትር ደንበኞች ግን የተማሩ ሰዎች ናቸው። ስለዚህም ምናልባት ፊደሎቹ የተደረደሩት በተማረ፣ ነገር ግን መሐይም የሠራው የማስመሰል ክህሎት ባለው ሰው ነው። ፊደሎቹ ቀጥታ መሥመር ይዘው እንዳልተቀመጡ ማስተዋል ይቻላል። ከፍና ዝቅ ብለው ነው የተደረደሩት። በችኮላ የተሠራም ይመስለኛል። ቁም ነገሩ ግን መጣደፍ ለምን አስፈለገ? ትናንትና ማታ በማንኛውም ሰዓት ቢሆን ለሰር ሔንሪ የተጻፈ ደብዳቤ ዛሬ ጧት ከሆቴሉ ከመውጣቱ በፊት ሊደርሰው የማይችልበት ምክንያት የለም። ወሐፊው የሆነ ሰው ያቋረጠኛል ብሎ ፈራ? ማንስ ያቋርጠዋል?"

"አሁን ግምታችንን እያስቀመጥን ነው" አለ ዶክተር ሞርቲመር

"ግምት አይደለም። ሊሆኑ የሚችሉትን አማራጮች በመተንተን የተሻለውን መምረጥ ነው። ግምትን በላይንሳዊ መንገድ የመጠቀም ጉዳይ ነው።" ቃላቱ የተለጠፉበትን ወረቀት ጠጋ ዓይኖቹ በማስጠጋት አገላበጠ አስተዋለና ወረወረው።

"ከዚህ ተልዕኮ ከሚስብ ደብዳቤ ማግኘት የምንችለውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ ያገኘን ይመስለኛል። ሰር ሔንሪ ለንደን ከመጣህ ጀምሮ የአንተን ትኩረት የሚስብ አዲስ ነገር ተፈጽሟል ትላለህ? በእንትስታሲህ ላይ ልዩ ትኩረት አድርጎ የሚከታተልህ ሰው ያለ ይምስልሃል?"

"ለምን ሲባል ይከታተለኛል ? በእኔስ ላይ ለምን የተለየ ትኩረት ይደረጋል?"

"እሱን በኋላ እንመጣበታለን። ሪፖርት የምታደርገው ነገርስ አለ?"

"ሪፖርት ሊቀርብበት ይገባል የምትሉት ጉዳይ ካለ ራሳችሁ ወስኑ ::"

"በዕለቱ ያልተለመደ ነገር ሲያጋጥም ሪፖርት ማድረግ የሚሻል ይመስለኛል።"

ሰር ሔንሪ እንደመሳቅ አለ። "ስለ አንግሊዛውያን አኗኗር ብዙ የማውቀው ነገር የለም። ሕይወቴን በሙሉ ያሳለፍኩት አሜሪካና ካናዳ ውስጥ ነው። እዚህ አገር ግን የአንድ ጫማ መጥፋት ያልተለመደ ይመስለኛል።"

"አንድ ጫማ ጠፍቶብሃል?"

"ጌታዮ!" አለ ዶክተር ሞርቲመር ድምፁን ከፍ አድርጉ። "ወዳረፍክበት ሆቴል ስትመለስ ታገኘዋለህ። ሚስተር ሆልምስ፣ በእንደዚህ ዓይነት ጥቃቅን ነገሮች ላይ መቸገር ለምን አስፈለገ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያልተለመደ ነገር ካለ እንድነግረው ስለጠየቀኝ እኩ ነው።"

"ተራ ነገር ሊመስል ይችላል። በእርግጥ ግን የአንድ እግርህ ጫማ ጠፍቶብሃል?"

"ለማንኛውም ፈልጌ ላገኘው አልቻልሁም። አሳዛኙ ነገር ደግሞ አንዱን ጥንድ ሬጫማ የገዛሁት ትናንትና ማታ ስለነበር ገና አልተጫማሁትም። ትናትና ለገበያ ወጥቼ ብዙ ዕቃዎች ገዝቻለሁ። እዚህ አገር የምኖር ከሆነ ለዚሁ የሚሆኑ ልብሶችን መግዛት ስለነበረብኝ ነው። ከዚሁ ጋር የገዛሁት ቡኒ ጫማ ነው ገና ሳላደርገው የተሰረቀ።

"ስርቆት ተራ ነገር ነው። እናም ጫማው በአጭር ጊዜ ውስጥ ይገኛል የሚለውን የዶክተር ሞርቲመርን እምነት አጋራለሁ።"

"እና ወንድሞቼ!" አለ ሰር ሔንሪ፣ "ታላችሁን ጠብቃችሁ እየሆነ ያለውን ነገር ሁሉ ለእኔ የምታስረዱበት ጊዜው አሁን ነው።"

በመሆኑም የሳይንስ ተማሪ የሆነው ጓደኞችን ዶክተር ሞርቲመር ወረቀቱን ከኪሱ አውጥቶ ጊት ለእኛ የነገረንን ታሪክ አንድም ሳይቀር ዝክዝክ አድርጎ ነገረው። ሰር ሔንሪ ባስከርቪል በጣም ተመስጦ አዳመጠውና አንድ ትኩረት የሚስብ አስደናቂ ነገር ተናገረ።

"መልካም" አሉና ጀመረ። "በእርግጥ ስለአዳኙ ውሻ ከልጅነቱ ጀምሮ እሰማ ነበር። ብዙም ትኩረት ባልሰጠውም በቤተሰቡ ውስጥ ትልቅ ቦታ የያዘ ታሪክ ነው። የአባቱን ሞት በሚመለከት ግን... አሁን ደግሞ ካለሁበት ሆቴል ድረስ የተላከልኝ ደብዳቤ ጉዳይ አለ፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

"በእኔ አስተያየት በአምባ ምድሩ አካባቢ እየተካሄደ ስላለው ነገር ከእኛ የበለጠ የሚያውቅ ሌላ አካል መኖሩን ለማሳየት እየተሞከረ ይመስለኛል" አለ ዶክተር ሞርቲመር። "ነገር ግን ቆራጥ ውሳኔ ላይ መድረስ ያለብን ወደ ባስከርቪል አዳራሽ ስለመሄድህ ጉዳይ ነው።"

"ወደ ቤተሰቦቼ ቤት ከመሄድ የሚያግደኝ ሰይጣን ወይም ሰብዓዊ ፍጡር አይኖርም።" ይህን እንደተናገረ ፊቱ ቀላ ። የባስከርቪል ቤተሰብ የቁጡነት ባህሪ፣ የመጨረሻው እንደራሴ በሆነው በአሰቃ ውስጥ እንዳለ በግልፅ ያስታወቃል።

"አሁን አንተ ስለነገርከኝ ሁሉ ለማሰብ በቂ ጊዜ የለኝም። ወደ አረፍተቤት ሾፑል እመለሳለሁ። አንተና ዶክተር ዋትሰን ወደዚያ አካባቢ ብቅ ብትሉና ምላ አብረን ብንበላስ?"

"ልንመጣ እንችላለን፤ ጋሪ ልናየራ?"

"አመሰግናለሁ፤ በእግሬ ብሄድ ነው የሚሻለኝ"

"ያው እንግዲህ ምሳ ላይ በድጋሚ እንገናኛለን ። ደህና አርፍድ።"

የእንግዶቻችን ኮቴ ደረጃውን ሲወርዱ ይሰማል። ወዲያው የፊት በሩ ተዘጋ። ሆልምስ በእንዴ ከሕልመኝነት ወጥቶ ወደ ተግባር ሰውነት ተሸጋገረ።

"ፍጠን ዋትሰን! አንድም ደቂቃ መባከን የለባትም።" ፒጃማውን እንደለበሰ ከነበረበት እየሮጠ ወጣና በሰከንዶች ውስጥ ኮት ለብሶ ተመለሰ። ደረጃውን ወርደን ወደ ቤከር ጐዳና አመራን። ሞርቲመርንና ባስከርቪልን በሁለት መቶ ሜትር ርቀት ያክል እያየናቸው ነበር። ከኋላ እየተከተልናቸው አክስፎርድ ጐዳና፣ ከዚያም ሪጀንት ጐዳና ደረስን። ጓደኞቻችን ወደ ሰቅ ጐራ ብለው ሲቆሙ ሆልምስ እንደ አነሱ ይቆማል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአፎይታ ድምጽ እያሰማ ዓይኖቹን ወደማፈልገው አቅጣጫ ሲወረውር፣ ተሳፋሪ የያዘ ጋሪ መንገድ ዳር ከቆመበት ሥፍራ ተነስቶ በዝግታ ሲንቀሳቀስ ከማየቱ፣ "ያን ሰው ተመልከተው ዋትሰን! ቶሎ በል! ሌላ ማድረግ እንኳን ባንችል በደንብ እናየዋለን" አለኝ።

በዚያ ቅጽበት አንድ ጸሙ ጥቅጥቅ ብሎ ያደገ ዓይነ ፈጣጣ ሰውየ ፊቱን ወደ እኛ መልሶ በጋሪው መስኮት ሲመለከት እያየሁት ሳለ የጨቨት ድምጽ ሰማሁ። ጋሪው በሪጀንት ጐዳና ቁልቁል እየወረደ ነበር። ሆልምስ አካባቢውን ታኒ፣ ማንም አልነበረም።

"እንደዚህ መጥፎ ዕድልና መጥፎ አመራር ገጥሞኝ አያውቅም። ባስከርቨል ሰንደን ከገባበት ጊዜ አንስቶ ክትትል እየተደረገበት መሆን አለበት። ያ ባይሆን ኖርዝ ሚበርላንድ ሆቴል ማረፉ እንዲህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ሊታወቅ ቻለ? በጣም መሠሪ ከሆነ ሰው ጋር ነው እየተፋጠጥን ያለነው ዋትሰን። በቀላሉ እያዘገመ ለመከተል ወይም ሳይታወቅ ቀድሞ ለማለፍ አመቺው መጓጓዣ ጋሪ ሊሆን እንደሚችል አስቀድሞ አውቋል። ከዚህም በተጨማሪ እነሱ በጋሪ ቢሄዱም እንኳ እንደማያመልጡት ተገንዝቧል። ለመሆኑ ጋሪ ውስጥ የነበረውን ሰው መልኩን ትለየዋለህ ?"

"ጥቁሩን ጸሙን ብቻ ነው መለየት የምችለው"

"እኔም እንዲሁ— ግን ፊቱን በከፊል ለመሸፈን ሲል የውሸት ጢም ተጠቅሞ ሊሆን እንደሚችልም እገምታለሁ። ለማንኛውም ዋትሰን ሰዓት አስኪደርስ በቦንድ ጐዳና አካባቢ ባሉት ሱቆች የተለያዩ አታሞችን እየየን እንቆያለን።"



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አምስት

"ሰር ሐንሪ ባስከርቪል ይፈልግሃል" አለ የሆቴሉ ሃላፊ የሆቴሉን ደረጃዎች ወጥተን እንደጨረስን። ሰር ሄንሪ ባስከርቪልን ራሱን አገኘነው። ፊቱ በንዴት በርበሬ እስኪመስል ቀልቷል። አንድ አሳራ የለበሰ አሮጌ ጫማ በእጁ ይዟል።

"እዚህ ሆቴል ውስጥ ያሉ ሰዎች ሊጫወቱብን እየሞከሩ ናቸው" ሲል ጮኸ። "ዓላማቸውን ስማሳነት ትክክለኛውን ሰው እንዳልመረጡ ያወቁታል! ከሠራተኞቹ አንዱ የጠፋውን ጫማዬን አግኝቶ ካላመጣው በስተቀር ችግር ይኖራል። እንደ ማንኛውም ሰው ቀልድና ጨዋታ ያስቀኛል፣ ሚስተር ሆልምስ። እነዚህ ግን በጣም አበዙት።"

"አሁንም ጫማህን እየፈለግህ ነው?"

"አዎ፣ እንደሚገኝም ተስፋ አደርጋለሁ።"

"ግን እኮ አዲስ ቡኒ ጫማ ጠፍቶብህ እንደነበር ስትናገር ሰምቻለሁ ልበል?"

"እርግጥ ነው። አሁን ደግሞ አሮጌውን ጥቁር ጫማዬን መስደውታል። "

"ምን እያልክኝ ነው?"

"ሦስት ጥንድ ጫማዎች ብቻ ናቸው ያሉኝ ። አዲስ ቡኒ፣ አሮጌ ጥቁርና አሁን ያደረግሁት ጫማ ማለት ነው። ትናንትና ማታ ከቡኒው አንድ ጫማ አንዱን፣ዛሬ ደግሞ አንዱን ጥቁር ጫማዬን ሰርቀውታል። በጣም የሚገርም ነው። በማንም ላይ ተፈጽሞ የማያውቅ የዕብዶች ሥራ ነው!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"በእርግጥም ተደርጉ የሚያውቅ አይመስልም አለ ሆልምስ በሃሳብ ባህር ውስጥ እየዋኜ።

"ለመሆኑ ምን ይመስልሃል?"

"እስካሁን ገብቶኛል የምለው ነገር የለም። ይህ የአንቱ ጉዳይ በጣም የተወሳሰበ ነው። ሰር ሔንሪ፣ ለማንኛውም አንድ ወይም ሁለት ፍንጮች አግኝተናል። ከሁለቱ አንዱ ወደ ትክክለኛው መንገድ ይመራናል።"

ምንም እንኳን ለአብሮነታችን ምክንያት ስለሆነው ጉዳይ ብዙ ባንነጋገርም ቭንጀ ምሳ ነበር የበላነው ። በመጨረሻ ማድረግ ስላሰበው ነገር ሆልምስ ባስከርቪልን ጠየቀው።

"በሳምንቱ መጨረሻ ወደ ባስከርቪል አዳራሽ መሄድ አለብኝ" አለ ሔንሪ።

"ጥሩ ውሳኔ ይመስለኛል። ዶክተር ሞርቲመር፣ ዛሬ ጧት ከእኔ ቤት ጀምሮ ሰዎች ይከታተሉህ እንደነበር አውቀሃል?"

"ክትትል? ማነው እሚከታተለኝ?"

"እሱን እንኳ መናገር አልችልም። ዳርትሙር ውስጥ ካሉት ጉረቤቶችህ ጥቅጥቅ ያለ ጥቁር ዒም ያለው ሰው አለ?"

"እንዲያውም ቆይ እስቲ ላስብ አም- ባሪሞር የሰር ቻርለስ አሽከር ጥቅጥቅ ያለ ጥቁር ጺም አለው።"

"ባሪሞር የት ነው የሚኖረው?"

"የአዳራሹ ኃላፊ ነው"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይኽ ባሪሞር የሚባለው ግን ምንድነው?" ሲል ባስከርቪል ጠየቀ።

"ባሪሞርና ባለቤቱ ለአያሌ ዓመታት በአሽከርነት ግቢው ውስጥ የኖሩ ታማኝ ባልና ሚስት ናቸው።"

"ባሪሞር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሰር ቻርለስ በመሞቱ የሚያገኘው ጥቅም ይኖራል?"

"እሱና ባለቤቱ እያንዳንዳቸው አምስት መቶ ፖውንድ ተሰጥቷቸዋል።"

"ሌላ ተጠቃሚስ ይኖራል?"

"በመጠኑም ቢሆን የተከፈላቸው አሉ። ቀሪው በመሉ የሰር ሔንሪ ነው።

"ስንት?"

"ሰባት መቶ አርባ ሺህ ፖውንድ"

ሆልምስ በመገረም ዓይኖቹን ገለጥ አደረገ። "ያን ያክል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ይኖራል ብየ አልገመትኩም። ሰደርስ የሚችለውን ጉዳት ቢያውቅም የመጣው ይምጣ በሚል ዘሎ ለመደንገር የወሰነ ሰው አለ! አያድርገውና ዶክተር ሞርቲመር፤ ወጣቱ ጓደኞችን ላይ አንድ የሆነ ነገር ቢደርስ የአዳራሹ ወራሽ የሚሆነው ማነው?"

"ማዕከላዊ አሜሪካ ውስጥ ይኖር የነበረ የሰር ቻርለስ ታናሽ ወንድም ሳያገባ ነው የሞተው። ስለዚህ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤትነት የሚተላለፈው ሰሜን እንግሊዝ ለሚኖረው ለሌላው የወንድም ልጅ ጀምስ ዴሞንድ ለሚባለው ቂስ ነው። በጣም ሽማግሌ ቢሆንም ጥሩ ኑሮ የሚኖር ደስተኛ ሰው ነው። ሰር



t.me/OLDBOOKSPDF

ቻርለስ ከመሞቱ በፊት የተወሰነ ገንዘብ ሊያወርሰው ሲፈለግ ስመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን አስታውሳለሁ። ደግ ጨዋ አረጋዊ ነው። በዚህ የሚጠረጠር ሰው አይደለም።"

"ሰር ሔንሪ፣ ለማንኛውም ወደ ዳርትመር ስትሄድ ብቻህን መሄድ የለብህም። ዶክተርሞርቲመር ሥራ ይበዛበታል። ከዚህም በተጨማሪ ቤቱ ያለው ከአንተ ራቅ ብሎ ግሪምፒን በሚባል ቦታ ነው። ከአንተ ጋር አብሮህ መሄድ ያለበት ለአንተ ባለው ታማኝነት የምትመርጠውና በማንኛውም ሰዓት ከአንተ ጋር የሚሰለፍ ሰው መሆን አለበት።"

"አንተ ራስህ መሄድ አትችልም ሚስተር ሆልምስ?"

"እንደዚያ እንኳን የሚሆን አይመስለኝም።"

"ታዲያ ማን ይሁን ትላለህ?"

"ጓደኛዬ ከአንተ ጋር ስመሄድ ፈቃደኛ ከሆነ ከጐንህ ለመቆም ከእሱ የተሻለ ሰው የለም።"

ሠልስ ለመስጠት ጊዜ ሳይሰጠኝ ባስከርቪል እጅን ጨብጦ አርገፈገፈኝ— በደስታ።

"በሳቅ አመሰግናለሁ፣ ዶክተር ዋትሰን!"

"ጆበዱ መሥራት ደስ ይለኛል" አልኩት። "እናም አብራህ ስመሄድ መሉ ፈቃደኛ ነኝ።"

"አደራህን በጥንቃቄ ሪፖርት አድርግልኝ" አለ ሆልምስ ። "ጊዜው ሲደርስ እንደት መሥራት እንዳለብህ መመሪያ አሰጥቻለሁ። እስከዚያ ሁላችሁም ቅዳሜ ጠዋት በ4:30 ከፖዲንግተን የሚነሳውን ባቡር ይዛችሁ መጓዝ ትችላለችሁ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመሄድ በተነሳበት ሰዓት ባስከርቪል የሆነ የጨኸት ድምጽ አሰማ። ወደ ክፍሉ ማዕዘን እየሮጠ ሄዶም ቡኒውን ጫማ ከጠረጴዛ ሥር አውጥቶ ይዞት መጣ።

"የጠፋው ጫማየ!" አለ ጮክ ብሎ።

"በጣም ይገርማል" አለ ዶክተር ሞርቲመር።

"ከምሳ በፊት ክፍሉን በመሉ አንድ ባንድ አስሸዋለሁ እኮ!"

"እኔም እንዲሁ" አለ ባስከርቪል። "ያልፈለግሁበት ቦታ የለም።"

"ያኔ በክፍሉ ውስጥ ምንም ጫማ አልነበረም።"

"በምርመራ ሊከሰት አልቻለም። ባለፉት ሁለት ቀናት ከተከሰቱት አያሌ ተያያዥነት ያላቸው ምሥጢራዊ ሁነቶች ሌላ ተጨማሪ ነገር ተገኘ። የታተመ ወረቀት፣ በጋሪ ውስጥ የነበረው ዒማም ሰውዬ፣ የአሮጌው ጥቁር ጫማ መጥፋት እና አሁን ደግሞ የአዲሱ ቡኒ ጫማ መገኘት።"

ወደ ቤከር ጉዳና በጋሪ ተመልሰን ስንሄድ ሆልምስ ወደ እኔ ዞር ብሎ "ዋትሰን፣ አሁን ልንዋጋው የሚገባን ጠላት አንዳለ ማወቅ አለብህ። ለንደን ላይ ተቸንፈያለሁ። ዳርትሙር ላይ መልካም ዕድል እንዲገጥምህ ብቻ ነው የምመኝልህ። አንተን በመላኬ ግን ደስተኛ አይደለሁም። መጥፎ ሥራ ነው ዋትሰን። በአደጋ የተሞላ ውስብስብ ሥራ። ባሰብኩት ቁጥር እየጠላሁት መጣሁ። እም፣ ወንድሜ አንተ ትስቃለህ። እኔ ግን ደስተኛ የምሆነው በሰላም ወደ ቤከር ጉዳና ተመልሰህ መምጣትህን ሳረጋግጥ ነው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ስድስት

ሼርሎክ ሆልምስ ፖዲንግተን ባቡር ጣቢያ ድረስ የሸኘኝ ቅዳሜ ቀን ነበር።

"በተቻለህ መጠን ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ስላለቸው ነገሮች ሁሉ ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖራቸውም እንካን የተሟላ ሪፖርት እንደምታስተላለፍልኝ እተማመናለሁ። ስለ ሰር ቻርለስ አሟሟት ወይም በሰር ሐንሪ ዙሪያ ስላሉት ሰዎች ዝርዝር መረጃዎችን ትልክልኛለህ። በአምባ ምድሩ አካባቢ ባሉ ቤቶች ሁለት ዓይነት ቤተሰብ ነው የሚኖረው። ታማኝነቱን እኔው ራሴ የምመለከርለት ጓደኞችን ዶክተር ሞርቲመር እና ስለማንኒ ምንም መረጃ የሌለን ባለቤቱ በአንድ በኩል፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ባለሙያ የሆነው ስቴፕልተን እና የውበት አመቤት ናት የምትባለው እህቱ በሌላ በኩል። ትጥቅህን እንዳትፈታ። መሣሪያህን ቀንም ይሁን ሌሊት ከእጅህ እንዳትለየው። ብቻህን አትሂድ።"

ጓደኞቻችን ባቡር ጣቢያ እየጠበቁን ነበር።

"ሌላውን ጫማህንስ አገኘኸው?"

"እንዲያውም፣ እሱ ሳይመለስ ሄዷል።"

"በጣም የሚያንት ነው። ልብ በል፣ ብቻህን እንዳትሂድ። ዶክተር ሞርቲሞር ካነበበልን አስገራሚ የቆየ ታሪክ ውስጥ አንዲን ዓረፍተ ነገር አስታውስ። *ምድረ በዳውን በጨለማ እንዲታጀርም– የሰይጣን ጉልበት በጨለማ ይበረታል።*"



t.me/OLDBOOKSPDF

ገዙው ፈጣንና ደስ የሚል ነበር። ባሁሩ ከአንድ አነስተኛ ጣቢያ ደርሶ ሲያቁም ሁላችንም ወረድን። አንድ በሁለት ፈረሶች የሚገሩት ሰረገላ እኛን እየጠበቀ ነበር። በአንድ ሰፊና ነጫቱ አውራ ጐዳና ላይ ፈጣን ገሢችንን ቀጠልን። ከጐናችን በአረንጓዴ ሳሮች የታጀበ ለጥ ያለ ሜዳ አለ። ከዚህ በኋላ ግን መንገዱ ጠመዝማዛ ፤ መልክአ ምድሩም አቀበታማ ነው። ወሐይዋ ለምሽቱ ቦታዋን እየለቀቀች ጨለማ እየነገሰ መጣ። ሰረገላው ዋናውን መንገድ አገባዶ ጠመዝማዛውን አቀበታማ መንገድ ተያይዞታል።

"ሐሌ!" አለ ዶክተር ሞርቲመር ድምፁን ከፍ አድርጐ። "ይኸ ምንድነው?"

"ቀጥ ያለ ዳገት፤ ወደ በረሃማው የተራራ ሰንሰለት እየገባን ነው።" ኮረብታው ጫፍ ላይ አንድ ወታደር በፈረስ ሆኖ ከሩቅ ሲመለከቱት ከድንጋይ የተሠራ ሃውልት መስሎ ይታያል። የእንቅስቃሴ ምልክት አይታይበትም። ጠመንጫውን አቀባበሉ ይህ እኛ የምንገዘበትን መንገድ በንቃት ይጠባበቃል።

ሰረገላ ነጂው ከመቀመጫው ላይ እንዳለ ፊቱን ዘወር አድርጎ፤ "አንድ ኢሥረኛ ከፕሪንስታውን ኢሥር ቤት አምልጧል። ሦስተኛ ቀኑ ነው። የኢሥር ቤቱ ጥበቃዎች በየበሩ ተሠማርተው ቢፈልጉትም አስክአሁን አላገኙትም። የዚህ አካባቢ ሰው ደግሞ ደስተኛ አይደለም። ተራ እስረኛ አይደለም ያመለጠው፤ የፈለገውን ለማድረግ የሚችል ሰው ነው። ሴልደን ማለት የኖርቲን ሐሌን የግድያ ወንጀል የፈፀመ ሰው ነው።"

እኔም በደንብ አስታውሰዋለሁ። ሰውየው በጨካኝነቱ የታወቀ ነፍሰ ገዳይ ነው። ከአረመኔነቱ የተነሳ ኡበድ ነው። አስከቀባል ደርሶ ነበር። ከፊታችን ሰፊው አምባ--ምድር መሰል ብሎ ይታያል። ነፋሱ ቁልቁል ይነፍሳል። ሠብሮ የወጣው ኢሥረኛ የት እንደሆነ ባይታወቅም በዚያ ጭው ባለ በረሃ ውስጥ እንደ ዱር አራዊት መሸንል። ጨለማው እየነገሠ ሲሄድ ባስከርቪል እንኳን ዝምታን መረጠ። ኩቱንም



t.me/OLDBOOKSPDF

አስተካክሎ ለበሰ። በጣም ደስ የሚለውን መልካ ምድር ከኋላ እየተውነው መጣን። ከፊታችን ያለው መንገድ ቀጥ ያለ አተበትና ጉምቱ ጉምቱ እድሜ ጠገብ ድንጋዮች የከተመበት ነው። አልፎ አልፎ ከድንጋይ የታነፁና ጣራዎቻቸውም በድንጋይ የተከደኑ ትናንሽ ቤቶች ተንጠባጥበው ይታያሉ። ከፊታችን ንፋስ ያገበጣቸውና ግራና ቀኝ ያጠማዘቸው ዛፎች ያሉበት ደልዳላ ቦታ ተመለከትን። ሁለት ረጃጅም ግንቦች ከዛፎች ከፍ ብለው ይታያሉ። ሰረገላ ነጂው በአሰንጋው እየጠቀመ፡-

"የባስከርቪል አዳራሽ" አለ

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የግቢውን በር አልፈን ሽቅብ በሚወስደው የውስጥ ለውስጥ መንገድ ገሠግሠንን ቀጠልን። ከሥር የረገፈው ቅጠል የሰረገላውን ጉማ ድምጽ ቀንሶታል። ከላያችን ንፋስ ያገበጣቸው የዛፍ ቅርንጫፎች ተገናኝተው ለሚያይ፣ ሆን ተብሎ መንገድ ላይ ቅስት የተሠራ ይመስል ነበር። ወጣቱ ባስከርቪል አካባቢውን ቃኜ።

"እገሌ በእንዲህ ዓይነት ቦታ እየኖረ ችግር ላይ እንደሚወድቅ ቢሰማው የሚያስደንቅ አየደለም። ማንም ቢሆን እዚህ እየኖረ ከፍርሃት ነፃ መሆን አይችልም።"

እየተጠጋን ስንሄድ መንገዱ አየገለጠ መጣና ጥቁሩ ሕንፃ ከፊታችን ገጭ አለ። ግንቡ ፊት ለፊቱ በሐረግ ተሸፍኗል። መካከል ላይ መንታ ሕንፃዎች ደረታቸውን ሰጥተው ቆመዋል። በአንዳንዶቹ መስኮቶች ደብዛዛ ብርሃን ይታያል። ከአንዱ ማዕድ ቤት ቀጭን ጭስ አመልማሎ እየመሰለ ሲወጣ ይታያል።

"እንካን ደህና መጣህ ሰር ሔንሪ! እንካን ወደ ባስከርቪል አዳራሽ በደህና ገባህ !"



t.me/OLDBOOKSPDF

ከበሩ አነባበቢ አንድ ረጅም ሰው ሲወጣ ይታያል። ዙኂላው አንዲት ሴት ከዚጫው መብራት ሥር ቆማለች። ፣ዣችንን ተጥበስው አስገቡት።

"እኔ ወደ ቤቱ መሄድ አለብኝ" አለ ዶክተር ሞርቲመር። "ምን አልባትም የሚጠብቁኝ ሥራዎች ይኖራሉ። ደህና ሁኑ። የእኔን እገዛ የሚጠይቅ ጉዳይ ካለ በማንኛውም ሰዓት መልእክተኛ ለመላክ ወደኋላ አትበሉ።"

የገባንበት ፎቅ ቤት በጣም ያምራል። ባሪሞር ከፊታችን ቆሟል። የሚያሳየው ሥነ ምግባር በደንብ የሠለጠነ የአልፍኝ አሽከር መሆኑን ይናገራል። ቱመቱ ሎጋ ነው። መልከ መልካም ሆኖ አጭርና ጥቅጥቅ ያለ ዒም አለው።

"ራት ቢቀርብ ምን ይመስላችኋል? በየመኝታ ቤታችሁ መታ ውሃ አለ።"

ራት ላይ ብዙ አላወራንም። መብራቱ ደብዘዝ ያለ፣ ምግብ ቤቱ ሰፊ ነው። ከላያችን ጥቁር ርብራብና ጢስ ያጠለሰው ጣራ ይታያል። የቀደምት የባስከርቭል ቤተሰብ አባላት ፎቶግራፎች ዙሪያውን ግድግዳ ላይ ተንጠልጥለው ወደ እኛ የሚመለከቱ ይመስላሉ። ዝምታው ግን ለእኛ ምቾት አልሰጠንም። ሚት የተሻለ ሁኔታ እንደሚገጥመን ተስፋችንን ሰንቀን በጊዜ ነው ወደየመኝታ ክፍላችን የገባን። በጣም ደክሞኛል፤ እንቅልፍ ግን ሊወስደኝ አልቻለም። ራት ብሎ በየአሥራ አምስት ደቂቃው የሚደውል ሰዓት ከመኖሩ በስተቀር እድሜ ጠገቡ ቤት ፀጥታ የሰፈነበት ነው። አከለ ሴሊት ላይ ድንገት የሆነ ድምጽ ሰማሁ። የአንዲት ሴት ጩኸት ። ከአልጋዬ ላይ ብድግ ብዬ ተነሳሁና ተቀምጬ ማዳመጥ ጀመርኩ። ለግማሽ ሰዓት ጠበቅሁ። ግን ከግድግዳው ሰዓትና ሕንፃው ላይ ካለው ሐረግ እንቅስቃሴ በስተቀር የተሰየ ድምጽ አልነበረም።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሰባት

የማለዳው ውበት የተላበሰ የአካባቢው ገጽታ ስለ ባስከርቪል አዳራሽ በውስጣችን የተፈጠረውን መጥፎ ስሜት በመቀነስ ረገድ የራሱ ድርሻ ነበረው። ባጋጣሚ ከቱርስ ቡኋላ ሚስዝ ባሪሞርን መተላለፊያው ላይ አገኘኋት። የዐሐይዋ ጨረር ፊቷ ላይ ያንዠባርቃል። ፊቷ የማይፊታ ትልቅ ሴት ናት። ዓይኖቿ ቀልተዋል። በቅጽበት ያበጡ ዓይኖቿን መርመር አድርጋ ተመለከተችኝ። ሴሊት የጨቨች እሷ ካልሆነች ማን ሊሆን ይችላል? እሷ ከሆነች ደግሞ ባለቤቷ ማወቅ አለበት። ያ መልክ ቀና ዒማም ሰው።

አካባቢው ገና ካሁኑ በዕንቶትልሽ የተሞላ ሆነ። ስለ ሰውየው የምናውቀው ከሰር ቻርልስ መሞት ቡኋላ ነው። በሪጀንት ጐዳና ላይ በጋሪ ሲሄድ ያየነው ራሱ ባሪሞር ሊሆን ይችል ይሆን? ዒመ. የእሱን ይመስላል። ባሪሞር ለንደን ድረስ መጥቶ ሊሆን ይችላል። እናስ? ለሴሎች ሰዎች ተመክሶ እየሠራ ነበር ማለት ነው? ወይንስ የራሱ የሆነ ዕቅድ ይኖረው ይሆን? ከታይምስ ጋዜጣ ተቀዶ ስለወጣው ማስጠንቀቂያ ማሰላሰል ጀመርኩ። እሱ ይሆን የሠራው? ወይስ የእሱን ዕቅድ ለማጨናገፍ ሌሎች አድርገውት ይሆን?

በዚያው አካባቢ ወደ ግሪምገን የሚወስደውን መንገድ ይገር በቀስታ እየተንዘዙ ነበር። ስሜን እየጠራ ወደ እኔ እየሮጠ የሚመጣ ሰው ድንገት ከሃሳቤ መለሰኝ። ዞር አልኩ። የሚገርመው ደግሞ ሰውየውን አላውቀውም። ዘንረ መልካም ሆኖ አጭር ነው። ከንፈሩ ሳሳ፣ ጥርሱ ሾል ያለ ነው። እድሜው በሰላሳና በአርባ ዓመት መካከል ይሆናል። ግራጫ መልክ ያለው መሉ ልብስ ለብሶ የሰሌን ባርኔጣ አድርጓል። በትከሻው የአትክልት መትከያ ሳጥን ተሸክሞ በእጁ የነፍሳት ማጥፊያ መረብ ይዟል።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይቅርታ ዶክተር ዋትሰን" አለኝ። "በዚህ አምባ ምድር አካባቢ የምንኖር ሰዎች ወግ አናጠብቅም። በሥርዓት እስክምንተዋወቅ ቆመን አንጠብቅም። ስለ እኔ ከሞርቲመር ስምህ ሊሆን ይችላል። ስቴፐልተን እባላለሁ። የሜሪፒት አዳራሽ ባለቤት ነኝ።"

"በመረብህና በሳጥንህ ላውቅህ ይገባ ነበር" አልኩት። "ምክንያቱም ሚስተር ስቴፐልተን እንስሳትና ዕፅዋት ሰብሳቢ መሆኑን አውቅ ስለነበር ነው። እኔን ግን እንዴት አወቅኸኝ?"

"ስታልፍ ሞርቲመር በጥቅማ አሳይቶኝ ስለነበር ነው። መንገዳችን አንድ ስለሆነ እንደምደርስብህና እንደምተዋወቅህ እርግጠኛ ነበርክ። ሰር ሔንሪስ በሰላም ገባ? ቤተሰቡን ስለሚያምሰው ስለ ሰይጣኑ ውሻ ታሪክ እንደምታውቅ አልጠራጠርም። የአካባቢው ማህበረሰብ እንዴት እንደሚያምንበት በጣም የሚገርም ነው። ሁሉም ያን የተለየ ፍጡር በዓይኔ አይቼዋለሁ እያለ ይምል ይገዘታል እኮ! ታሪኩ በሰር ቻርለስም ላይ ተጽእኖ አድርጓል። ለመሞት ያበታውም ይኸው ጉዳይ እንደሆነ አልጠራጥርም። ይመስለኛል፣ በዚያን ዕለት ምሽት ተመሳሳይ ነገር በመናፈሻው ውስጥ አይቷል። ሽማግሌውን በጣም እወደው ነበር። የልብ ችግር እንደነበረበትም አውቃለሁ።"

"እንዴት አወቅህ?"

"ጓደኛዬ ሞርቲመር ነግሮኛል"

"እና የሆነ ውሻ ሰር ቻርለስን ስላባረረው በዚያ ድንጋጤ ነው የሞተው ብለህ ታስባለህ?"

"አንተስ ከዚህ የተሻለ ትንታኔ ይኖርሃል?"

"እዚያ ድምዳሜ ላይ አልደረስክም"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሚስተር ሼርለክ ሆልምስስ?" ሲል አነጋገሩ አስደነገጠኝ። በእሱ ፊት ላይ ግን የተለየ ስሜት አይታይም።

"ይሽን ጥያቄ እንኳን መመለስ የምችል አይመስለኝም።"

"ትክክል ነህ፤ መጠንቀቅህ ተገቢ ነው።" ዋናውን መንገድ ትተን በቀጭኑ ጣራማ መንገድ በመጓዝ ወደ ኮረብታማው አቅጣጫ ተጠመዘዝን። "አሁን ወደ መሪጥ አዳራሽ የሚወስደውን አቅጣጫ ይዘናል። ምንአልባትም ከአሁቱ እንዳስተዋውቅህ የአንድ ሰዓት ጊዜ ከእኛ ጋር ታሳልፋለህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። አካባቢያችን በጣም ደስ የሚል ነው። በዙሪያችን ያሉትን አረንጓዴማ ደሴቶች ልብ ብለኻቸዋል? ያ እዚያ ጋ አምታየው የግሪምፖን ረግረጋማ ቦታ ነው። በዚህ ረግረግ ላይ በስህተት እንኳን የሚራመድ ካለ አውራም ይሁን ሰው ከዚያው ቀልጦ ቀረ ማለት ነው። በትንናትንናው ዕለት እንኳን አንድ ፈረስ እዚያ ውስጥ ገብቶ ሳይመለስ ነው የቀረው። ረግረጉ ውጦ አስቀረው ። ከመሸር ገናብ በኋላ ደግሞ በጣም የሚያስፈራ ነው። እኔ ግን መሀል ድረስ ብገባ እንኳ መውጫውን መንገድ ስለማውቀው ሕይወቱን ማትረፍ እችላለሁ። ያንት ያለህ ሲላ የፈረደበት ፈረስ ያውና!"

በአረንጓዴያማው ረግረግ መኻከል የሆነ ቡኒ ነገር ገብቶ ይዛትጣል። ለመውጣት ይፍረገረጋል። በተስፋ መቁረጥ ስሜት ረጅም አንገቱን ቀና ያደርግና ተመልሶ ይወድቃል። ወዲያዉ አስፈሪ ጩኸት አካባቢውን አደባለቀው።

"ሞቷል፤ ረግረጉ ውጦታል። ደረቅ ሲሆን ወደዚያ የመጓዝ ልምድ አለባቸው። ሲዘንብ ግን ማጡ ይስባቸዋል። ትልቁ የግሪምፖን ረግረግ አደገኛ ቦታ ነው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ግን ማቋረጥ እችላለሁ አያልህ ነው"

"አዎ ጉበዝ ለሆነ ሰው አቋርጦ መውጣት የሚቻልባቸው አንድ ወይም ሁለት መንገዶች አሉ። እነዚያን መንገዶች ለይቼ አውቃቸዋለሁ።"

"ግን እንደዚህ ዓይነት አደገኛ ማጥ ውስጥ መግባት ለምን አስፈለገ?"

"እነዚያን አጫጭር ኮረብታዎች ታያቸዋለህ? በረግረጉ ውስጥ ያሉ ደሴቶች ናቸው። የትም የሌሉ ዕፅዋትና ነፍሳት እነዚህ ደሴቶች ውስጥ ይገኛሉ። መድረስ ከቻልክ ማለት ነው።"

በዚህ ቅጽበት ከፍተኛ ባይሆንም ዘለግ ያለ ድምጽ በአካባቢው አስተጋባ። ድምጹ ከየት አትጣጫ እንደመጣ ማወቅ አይቻልም። ይኸው ድምፅ እንደገና ጉልቶ ይሰማና እየተስረቀረቀ ተመልሶ ይጠፋል። ስቲፕልተን ፊቱ ላይ የጥርጣሬ ስሜት እየተነበበ ወደ እኔ ተመለከተ።

"ምንድነው አሉ?" ስል ጠየቅሁት።

"የአካበቢው ኗሪዎች የባስከርቪል ቤተሰብ አዳኝ ውሻ ነው ይላሉ። ከዚህ በፊት አንዴ ወይም ሁለቴ ስሙቼው አውቃለሁ። ድምፁ ግን እንደዚህ ከፍተኛ አልነበረም።"

"አንተ የተማርክ ሰው ነህ፣ መቼም በእንዲህ ዓይነት አሉባልታ አታምንም!"

"ረግረጉ አንዳንዴ እንደዚህ ዓይነት የተለየ ድምጽ የሚያሰማው ጭቃው ወደታች ሲዘቅጥ ወይም ውሃው ወደላይ ሲወጣና በመላለሱት ምክንያቶች ነው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"በጥቁም ሕይወት ያለው ነገር ድምጽ አኮ ነው።"

"ምን አልባት ሊሆን ይችላል። ቢተርን በመባል የምትታወቀውን ወፍ ድምጽ ሰምተህ ታውቃለህ? ብዙ ጊዜ የማትታይ እንዲያውም እንግሊዝ አገር ውስጥ ዘሯ የጠፋ ወፍ ናት። ይኸ ቦታ ግን ድንግል ስለሆነ የማንኛውም ወፍ ዝርያ ሊኖርበት ይችላል። የሰማነው ድምፅ በመጥፋት ላይ ያሉት መሮች ጩኸት ቢሆን አይደንቀኝም።"

"ሀሕይወቱ ውስጥ ሰምቼ የማላውቀው ድምፅ ነው።"

"አዎ፣ ይኸ አካባቢ በአጠቃላይ ከሌላው የተለየ ነው። ወደዚያ ወደ ጋራው ሥር ተመልከት እንዚያ ምን ይመስሉሃል?"

ቀጥ ያለው ተራራ አቀቡቱ በመሉ ግራጫ በሆነ ቀለበታማ አለቶች የተሸፈነ ነው። ቢያንስ ሃያ ያክል ተመሳሳይ አለቶች ይኖራሉ።

"ምንድናቸው፣ የበግ ጉረኖዎች?"

"አይደሉም። የጥንታዊው ሰው መኖሪያ ቤቶች ናቸው። በዚህ ኮረብታማ አካባቢ በብዛት ይኖሩ እንደነበር አመላካች ነው። ከብቶቻቸውን በነዚህ ተራሮች አካባቢ ያሠማራሉ። የድንጋይ መሣሪያዎች በብረት መተካት ሲጀምሩ የቆርቆሮ ማዕድናት እየቆፈሩ ያወጡ ነበር። እና እንዳልከህ፣ ዶክተር ዋትሰን፣ በዚህ ድንግል በሆነ አምባ ምድር አካባቢ በጣም የተለዩ ነገሮችን ታገኛለህ። አ-አንዴ ይቅርታ-"

የሆነች ዝንብ በፊታችን አለፈች። ስቴፕልተን በሚያስገርም ፍጥነት ተከተላት። ዝንቢ በዚያ ረግረጋማ ቦታ ላይ ብትበርም ከመከተል ወደ ኋላ አላለም። መረቡን በአየር ላይ እየቀዘፈ ዝንቢን ተከትሎ ከቦታ ቦታ ይዘላል። ኩቱውን በሰማሁ ቁጥር ከአሁን አሁን አዳልጦት ከጭቃ ኩሬው ውስጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግባ እያልኩ በሥጋት ተውጥሬ ከቆምኩበት ቦታ ሳልነቃነቅ አጠብታለሁ። ዞር ስል አንዲት ሴት አጠገቤ ቆማለች።

ሚስ ስቲፐልተን ስለመሆኗ ቅንጣት ታክል አልተጠራጠርኩም። ምክንያቱም በዚህ አካባቢ ጥቂት ሴቶች መኖራቸውንና በተለይም ስለ እሷ ቁንጅና ጆሮ ጠገብ ስለሆንኩ ነው። እሱ ወርቃማ ፀጉርና ግራጫ ዓይኖች፣ እሷ ደግሞ ጥቁር ፀጉር፣ ደርበብ ያለ ቁመናና የሚያንጉ ጥቁቁር ዓይኖች አሏት። ከዚህ በስተቀር በሁለቱ መካከል የጉላ የመልክ ልዩነት አይታይም። ቀጠን ብሎ ዘለግ ባለው ቁመናዋ ላይ የለበሰችው ዘመናዊ ልብስ ባለችበት ቦታ ላይ ልዩ ሆና እንድትታይ አድርጓታል። ባርኔጣዋን አንስቼ የሆነ ነገር ልናገር ስል እሷ ቀድማኝ ተናገረች።

"ተመለስ! ቶሎ ብለህ በቀጥታ ወደ ሎንደን ተመለስ!" ስትለኝ ተገቢ ባልሆነ የአግራሞት ዓይን ተመለከትኋት።

"ለምንድነው የምመለሰው?"

"መግለጽ አልችልም" አለች ገዘት ባለ የሚያጓጓ ድምፅ። "ስለአግዚአብሔር ብለህ እኔ ያልኩህን አሽ በለኝ ተመለስና ሂድ፣ እንደገናም ፊትህን ወደዚህ እንዳታዞር።"

"መጥቼ እኮ አላውቅም-- የመጀመሪያየ ነው!"

"ማስጠንቀቂያው ለአንተ ደህንነት ሲባል የተሰጠህ መሆኑን ማወቅ ተሳነህ? ወደ ሎንደን ተመለስ! ቶሎ ብለህ ከዚህ ጥፋ! ወንድሜ እየመጣ ነው። ስለዚህ ምንም ነገር እንዳታወራው።"

ስቲፐልተን ዝንብ ማባረሩን አቁሟል። "ሔለ ቤሪል፣ እርስ በርሳችሁ ተዋውቃችኋል ብየ አገምታለሁ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እም፣ እውነተኛውን የዚህን አካባቢ የተፈጥሮ ውበት ለማየት ዘግይቶ መምጣቱን ሰሰር ሔንሪ እየነገርከት ነበር።"

"ለምን ለመሆኑ እሱ ማን ይመስልሻል?"

"እኔማ ሰር ሔንሪ ባስከርቪል ይሆናል ብዬ ስለገመትኩ ነው።"

"አይደለሁም" አልኳት። "እኔ ጓደኛው ነኝ። ስሜ ዶክተር ዋትሰን ይባላል።"

"አ–እንግዲያው ተራ ስህተት ፈጽሜአለሁ ማለት ነው። ለማንኛውም ትመጣለህ አይደል? የሚሪፒትን ሕንፃ ለማየት አትመጣም?"

ትንሽ ተጉዘን ከአንድ ባዶ የድንጋይ ቤት ደረስን። በቤቱ ዙሪያ ያሉት ዛፎች ትናንሽ ሆነው የተጠማዘዙ ናቸው። አካባቢው በመሉ ሐዘን ያጠላበት ይመስላል። ይህ ከፍተኛ ዕውቀት ያለው ሰውና ይቺን የመሰለች ቆንጆ እዚህ ምን ሊያደርጉ እንደመጡ ሳስብ በጣም ገረመኝ።

"ለመኖሪያነት የማመረጥ ቦታ አይመስልም አይደል?" አለ እኔ እየጠየቅሁ ያለውን ጥያቄ የሚመልስ ይመስል። እንደዚያም ሆኖ ግን እኛ ራሳችንን አስደስተን ለመኖር በትተናል፣ አይደል በሪል? በአንድ ወቅት በሰሜን እንግሊዝ ማዛት ትምህርት ቤት ነበረኝ። ይሁን እንጅ ዕደለኞች አልነበርንም። በትምህርት ቤቱ ውስጥ የወረርሽኝ በሽታ ተከሰቶ ሦስት ተማሪዎች ሞቱ። በዚህም ምክንያት ትልቅ ኪሣራ ደረሰብን። እዚህ መጥቼ ግን ብዙ ሥራ እየሠራሁ ነው። አህቴም እንዲሁ ለተፈጥሮ ሣይንስ ትልቅ ገንባሌ አላት። መጽሐፎች አሉን። የራሳችን የጥናት ውጤቶች አሉን። በዚህም ላይ ጥሩ ጐረቤቶች አሉን። ዶክተር ሞርቲመር በራሱ



t.me/OLDBOOKSPDF

የትምህርት ዘርፍ የጠሉቀ ዕውቀት ያለው ሰው ነው። ምስክነ ሰር ቻርለስም የሣራን እያድርገውና ጥሩ ባልንጀራችን ነበር። በጣም እንቀርበዋለን። በእሱ ሞት ትልቅ ሐዘን ነው የተሰማን።"

ወደ ሥራዬ የመመለስ ጉጉት አደረብኝ። በአካባቢው ያለው የሃዘን ድባብ፣ የፊረሱ አሟሟትና ከባስከርቪል ቤተሰብ ጋር የተያያዘ ነው የሚባለው ያልተለመደ የጨቨት ድምጽ፣ በእንድ ላይ ተደማምረው የጭንቀት ስሜት ፈጠሩብኝ። ማስ ስቴፕልተን በቅንነት የሰጠችኝ ማስጠንቀቂያም ሌላ ተጨማሪ ሥጋት ሆነብኝ። የሆነ አሳሳቢ ሁኔታ መኖሩን አመላካች ነገር አለ። እናም የምሳ ግብዣውን አልተቀበልኩትም። አዕምሮየ በፍርሃት እንደተወጠረ ወደ ባስከርቪል አዳራሽ አመራሁ።

## ምዕራፍ ስምንት

የግፍካቸው ደብዳቤዎች ከፊቱ ካለው ጠረጴዛ ላይ ተዘርግተዋል። በድርጊቶች ቅደም ተከተል መሠረት የራሴን ደብዳቤዎች ገልብጬ ለሼርሎክ ሆልምስ መላክ ይጠበቅብኛል። እኔ ከማስታውሰው የበለጠ ደብዳቤዎች በጊዜው የተሰማኝን ስሜት በትክክል ይገልፁልኛል።

*ባስከርቪል ሆል፣*
*ኦክቶበር 13*
*ውድ ሆልምስ፣*

ቀደም ብየ የላክኋቸው ደብዳቤዎችና መልዕክቶች በዚህ በጣም ርቀ በሚገኘው የእንግሊዝ የጠረፍ ግዛት ምን እየተደረገ እንደሆነ የትርብ ጊዜ መረጃ እንዲኖርህ ያደርጋሉ። ይሁን እንጂ ከዳርት ሙር አሥር ቤት ስላመለጠው አሥረኛ ብዙም አላልክም። ካመለጠ ሁለት ሳምንታት አልፈውታል። እስከአሁን የትም ቦታ አልታየም ወይም ስለ እሱ የተሰማ ነገር የለም።



t.me/OLDBOOKSPDF

በእርግጥ እነዚያ የፈራረሱ የድንጋይ ጉድጓች ለእሱ መደበቂያ ይሆናሉ።

ጓደኞችን ሰር ሐንሪ በቅንጅዋ ጉረቤቱ ስሚቱ ተነከቷል። ገና በመጀመሪያ ትውውቃቸው በውበቷ ተፈትኗል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወንድሟን ወይም እሷን ሳናይ አንድ ቀን እንኳ ያሳለፍንበት ጊዜ የለም ማለት እችላለሁ። ዛሬ እራት እዚህ ይበላሉ። በሚተኙለው ሳምንት ወደ አነሱ ስለምንሄድበት ሁኔታም ውይይት ይደረጋል። ስቲፐልተን ይህን ዓይነት ጋብቻ በደስታ ይቀበለዋል ብሎ የሚያስበው ሰው ተሳል አይደለም። እኔ ግን ከእንዲም ሁለቱ ሰር ሐንሪ ከእህቱ ጋር ሲነጋገር በገጽታው ላይ የቁጣ ስሜት አንብቤአለሁ። በነገራችን ላይ ሰር ሐንሪ ብቻውን እንዲሄድ መፍቀድ እንደሌለብኝ ነግረኸኛል። ባለት ችግሮች ላይ ፍትር ተጨምሮ ይህን ዓይነት ትዕዛዝ ማስፈፀም በጣም አዲጋች ነው የሚሆነው። መልካም ግንኙነታችንን እደጋ ላይ ይጥሰዋል!

አሁን ደግሞ ስለባሪሞር ቤተሰብ ተጨማሪ መረጃ ልስጥህ። ሰር ሐንሪ ብዙምቹን አርጌ ልብሶቹን ለባሪሞር የሰጠ መሆኑን ነግሮኛል። ከሰንደን የገዛቸው አዳዲስ ልብሶቹ መጥተውለታል። ሚስዝ ባሪሞር የሆነ ጥርጣሬ እያሳደረችብኝ ነው። ረጋ ብላ ፣ ሐይለኛና ልበ መሉ ሴት ናት። ያም ሆኖ በፊቷ ላይ የፅንባ ምልክት ደጋግሜ አይቻለሁ። ውስጧ ጥልት በሆነ ስሜት የተሞላ ይመስላል።አንዳንዴ የጥፋተኝነት ስሜት በውስጧ ተቀብሮ የሚያብለለስላት ይመስለኛል። አንዳንዴ ደግሞ ባሪሞር ራሱ ክፉ ስለሆነባት ነው ብየ አስባለሁ። ስለእሱ ሰውየ ሁልጊዜም የጥርጣሬ ስሜት አለኝ።

ጥሩ እንቅልፍ እንደሌለኝ ታውቃለህ። ይኸን ቤት መጠበቅ ከጀመርክበት ቀን ጀምሮ ደግሞ እንቅልፍ አልወስድህ ብሎኛል። ትናንትና ሌሊት ስምንት ሰዓት አካባቢ በመኝታ ክፍሌ አጠገብ ከውጭ ኮቴ ሰምቼ ለማዳመጥ ተነሳሁ። ወዲያው በመጠበት ተመለስ። ምንኑቴን ለመገመት ቢያስቸግርም በዚህ ቤት ውስዮ ምሥጢር የሆነ ጉዳይ



t.me/OLDBOOKSPDF

እየተፈፀመ ነው። ከሰር ሔንሪ ጋር ተነጋግሪን አንድ ዕቅድ አውጥተናል። አሁን ስለእሱ አልጽፍም። የሚቀጥለውን ሪፖርቱን ግን ጥሩ ያደርገዋል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ባስከርቪል ሆል፣
አክቶበር 15
ውድ ሆልምስ፣

ዛሬ ጧት ከቁርስ በኋላ ሰር ሔንሪ ባርኔጣውን አድርጎ ለመሄድ ተዘጋጅቷል። እኔም እንዲሁ።

"ለምንድነው እምትመጣው ዋትሰን?" ሲል ሄንሪ ጠየቀኝ።

"ሆልምስ በዚህ ምድረ በዳ አካባቢ ብቻችንን መሄድ እንደሌለብን ማስጠንቀቁን ታውቃለህ"

"የእኔ ወንድም!" አለ በደስታ ፈገግ እያለ።

"ሆልምስ እኔ እዚህ ከመጣሁ ጊዜ ጀምሮ የተፈጸሙት ድርጊቶች ሁሉ ይፈጸማሉ የሚል ግምት አልነበረውም። እየተረዳኸኝ ነው? ብቻየን ነው የምሄድ።"

አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ነበር የከተተኝ። እኔ ውሳኔ ላይ ሳልደርስ እሱ ዱላውን ይዞ ጥርግ ብሏል። ከዕይታዬ በመራቁ ግን ሕሊናዬ ዕረፍት አጣ። በመሆኑም በተቻለ ፍጥነት ወደ ሜሪፒት አዳራሽ የሚወስደውን መንገድ አቅጣጫ ይገር ተጓዝሁ። መንታ መንገድ ላይ ስደርስ የተሳሳተ አቅጣጫ እይዛለሁ በሚል ፍራቻ ጋራ ላይ ወጥቼ አካባቢውን ቃኘሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ ካለሁበት ትንሽ ራቅ ብሎም በአሻጋሪ አየሁት።

ከጐኑ አንድ ሴት ነበረች። ሚስዝ ስቴፐልተን መሆን አለባት። በትላልቅ አለቶች መካከል ቁሜ በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አወጣሁ አወረድሁ። ባጋጣሚ ሲወያዩ የምመለከታቸው እኔ ብቻ አለመሆኔን ተገነዘብኩ። አረንጓዴ ነገር ይታየኛል። የስቴፐልተን የነፍሳት ማጥመጃ መረብ ነው። ከእኔ ይልቅ እሱ ለጥንዶቹ በጣም ቅርብ በሆነ ቦታ ላይ ነበር። ወደ እነሱ የሚሄድ ይመስላል። በዚህ ጊዜ ሰር ሔንሪ ሚስ ስቴፐልተንን በትጽበታዊ እንቅስቃሴ ወደ እሱ አስጠጋት። በእጁ ተጠምጥሞባታል። እሷ ግን ፊቷን ሰማዞር ስትሞክር ያየኋት ይመስለኛል። ወዲያው ተነጣጥለው ዙሪያቸውን ተመለከቱ።

ስቴፐልተን ነፍሱን ስቶ ወደ እነሱ እየሮጠ ነበር። በብስጭት ከፍተረኛች ፊት ሲወራጭ ስተመለከተው የሚደንስ ይመስል ነበር። ምን እየተደረገ እንደነበር መገመት አልቻልኩም። ይሁን እንጂ ስቴፐልተን በሰር ሔንሪ ላይ የብልግና ቃላት የወረወረ ይመስለኛል። ሊያስረዳው ቢሞክርም ለመተበል ዝግጁ አልነበረም። በመሆኑም ሰር ሔንሪ ራሱ ተናደደ። በመጨረሻም ትኋቸው በመጣበት መንገድ አያዘገመ ተመለሰ። ጉዳዩ በትክክል ስላልገባኝ ከጋራው ላይ ተንደረድሬ በመውረድ ሰር ሔንሪን አገኘሁት። ከእሱ ተለይቼ ያልተረሁበትን ምክንያት አስረዳሁት። የተፈፀመውን ድርጊት በግልፅ በማየቱም የዓይን ምስክር መሆኔን አብራርቼ ነገርኩት። በመጨረሻ ግልጽ መሆኔን ሲረዳ ከት ብሎ ሳቀ። "ሁሉም ጉረቤት ያየ ይመስለኛል። ይኸ ወንድሟ ግን እብድ አይመስልህም? ከእኔ ጋር ያለው ችግር ምንድነው? የማፈቅራትን ሴት ከማግባት የሚያግደኝ ነገር አለ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"በእርግዮ አይኖርም።"

"ከተዋወቅን አጭር ጊዜ ነው። ካየኋት ጊዜ ጀምሮ ግን ለእኔ የተፈጠረች ነው የማመሰስለኝ። እውነቱን ነው የምልህ፣ እሷም ከእኔ ጋር ስትሆን በጣም ነው ደስ የሚላት። እሱ ግን ብቻችንን እንድንሆን በጭራሽ አይፈልግም። ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕድል ገጥሞኝ ብቻዋን አገኘኋት። ደጋግማ የነገረችኝ ነገር ቢኖር ይሽ ቦታ አደገኛ መሆኑንና እኔ ከዚህ ቦታ ለቅቂ እስካልሄድኩ ደስተኛ እንደማትሆን ነው። እሷን ካየሁ ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቦታ ለመልቀቅ እንደማልችል እና የምሄደውም እሷ ራሷ ከእኔ ጋር አብራኝ የምትሄድ ከሆነ ብቻ መሆኑን ነገርኳት። ለጋብቻም ጠየቅኋት። ገና መልስ ሳትሰጠኝ ወንድሟ አሳት ለብሶ፣ አሳት ጉርሶ አያበደ መጣ። ምን አደረግሃት? እንዴት ደፈርከኝ? በሥልጣንህ ተመክተህ ነወይ? ወዘተ... የሚሉ ዐያፍ አባባሎች የእኔንም ትዕግሥት አስጨረሱኝ። ምንአልባትም በክፍተኛ ብስጭት ውስጥ ሆኜ ስሜታዊ መልስ ሳልሰጠው አልቀረሁም። ያው እንዳየኸኝ፣ አሱም እሷን ይዞ እኔም ነገሩ እንቆቅልሽ እንደሆነብኝ ተለያየን አልሃለሁ። አስቲ የዚህ ፍቺ ምን ሊሆን እንደሚችል ንገረኝ ዋትሰን። ይሽን ካደረግህ አይከፍሉት ክፍያ አከፍልሃለሁ።"

እኔ ራሴ ፍፁም ግራ ተጋባሁ ። ጓደኞችን ወጣት ከመሆኑም በተጨማሪ በባህሪውም ሆነ በቁመናው እዚህ ቀርቶታል የሚባል አይደለም። በዚህ ረገድ ዕድል ለእሱ አድልታለች። በቤተሰቡ ላይ ካጠላው የጨለማ ድባብ በስተቀር። ያ ሁሉ ግምታችን ስቴፕልተን ከሰዓት በኋላ እኛ ጋ ሲመጣ አቆመ። ጧት ለፊፀመው ብልግና ይቅርታ ለመጠየቅ ነው የመጣው። እናም እርቅ የሚወርድ ይመስላል። ለዚህም ሲባል በሚቀጥለው ዓርብ በቤታቸው (Merripit House) ግብዣ ይኖረናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

"አሁንም እብድ አይደለም አልልም" አለ ሰር ሔንሪ። "ዛሬ ጧት ወደ እኔ ሲመጣ እንዴት ያየኝ እንደነበር አልረሳውም። እህቱ የሕይወቱ ሁሉ ሁለንተና መሆኗን ነው የሚናገረው። ተለያይተው አያውቁም። እንደእሱ አባባል እሷን አጣለሁ ብሎ ስለሚፈራ ከሌላ ጋር መወዳጀቷን በፍፁም አይፈልግም። ብቻውን ይኖራል። እኔ እሷን ስለማፍቀሬ ምንም ነገር እንደማያውቅና በዓይነ አይቶ ሲያረጋግጥ በጣም ከመደናገጡ የተነሳ ራሱን መቆጣጠር ተስኖት እንደነበር ይናገራል። ይሽውልህ ጉዳዩ እዚህ ሰይ ነው ያቆመው።"

አሁን ወደለላው የታሪክ አካል አልፋለሁ። ትናንት ማታ ከሰር ሔንሪ ጋር መኝታ ክፍሉ ውስጥ ቁጭ ብለናል። ሰዓቱ የመንፈቀቅ ያክል አያዘገመ ነበር። እንደዚያ አያለ ትልቁ ሰዓት፣ ሰባት ሰዓት፣ ከዚያም ስምንት ሰዓት... መሆኑን በደወሉ ያውጃል። በዚህ ሰዓት ላይ በመተላለፊያው በኩል የሆነ ኮቴ ተሰማ። ተስፋ ቆረጥን። ይሄዳል፣ ይራመዳል። ከዚያ ቀስ አድርገን በሩን ከፈትንና መከተል ጀመርን። አንድ ቁመቱ ዘለግ ያለ ጥቁር ዒም ያለው ሰው ባዶ ክፍል ውስጥ ሲገባ አየነው። ወደ ውስጥ ሰንመለከት በእጁ መብራት ይዞ በመስኮቱ ሥር ቁሟል። ፊቱን ወደ መስተዋቱ አስጠግቶ ወደ ጨለማው ይመለከታል።

"ምን እያደረግህ ነው ባሪሞር?"

በድንጋጤ ከመስኮቱ ስር ወደ ኋላ ተፈናጠረ። ፊቱ አመድ ሰበሰ። ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ። ዓይኖቹን ወደ ሰር ሔንሪና ወደ እኔ እያቅበዘበዘ ሲመለከት የመገረምና የፍርሃት ስሜት እያታየበት "ምንም አልሠራም ጌታዮ" ሲል መለሰ።

"ና ውጣ እንዳትዋሸኝ! እዚያ መስኮት ሥር ምን እያደረግህ ነበር?



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምልክት እየሰጠ መሆን አለበት"አልሁኝ። "እስቲ መልስ ካለው እናዳምጥ።" ወደ ጨለማው እየተመለከትሁ መብራቱን ወደ መስኮቱ አበራሁት። በጨለማው ውስጥ የወረቀት መርፌ የምታክል ቢጫ መብራት አየሁ። ትንቀሳቀሳለች። "ተመልከት! አሁንም የምልክት መስጫ ኮድ አይደለም ትላለህ? ተናገራ! ምን እየተሠራ ነው!"

"አልናገርም"

"ያ ከሆነ አሁኑኑ ከሥራ ትሰናበታለህ! ዘር ማንዝርህ ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ከእኔ ቤተሰብ ጋር በዚህ ቤት ኖሯል። አንተ ደግሞ በእኔ ላይ ተንኰል ስትሸርብ አገኘሁህ።"

"አይደለም፤ በጭራሽ አይደለም ጌታዬ። በአንተ ላይ አይደለም!" ሚስዝ ባሪሞር ፊቷ ቀልቶና ከባቢ ይበልጥ ተደናግጣ ከበሩ ሥር ቆማለች። "ምስክሩ ወንድሜ ጫካ ውስጥ ነው ያለው። በራሱን ላይ ሲሞት ገዝ ብሎን አናይም፤ ይኸ መብራት ምግብ የተዘጋጀለት መሆኑን ማሳያ ምልክት ነው። እሱ እዚያ የሚያሳየው መብራት ደግሞ ምግቡን የት እንደምናስቀምጥለት ለማመልከት ነው።"

"ማነው ወንድምህ?"

"ያመለጠው እሥረኛ ነው ጌታዬ ፤ ነፍስ-ገዳዩ ሲልደን ። አም ጌታዬ፤ የአኔ ስም ሲልደን ነበር ። እሱ ታናሽ ወንድሜ ነው። ከታሠረበት ሰብሮ ሲወጣ እሱን ለመርዳት እንደማላመነታ ያውቃል። አንድ ቀን ሌሊት ደክሞትና ርቦት እየተንገዳገደ ሲመጣ የእሥር ቤቱ ጥበቃዎች እሱን አያደነት ነበር። ምን እናድርግ አስገብተን ምግብ አበላነው። ጌታዬ በመካከሉ እናንተ ስትመጡ ወንድሜ ለደህንነቱ ጫካ ውስጥ መኖር እንደሚሻለው አሰበ። ሁልጊዜ ከዚህ ይሄዳል አያልን ተስፋ እናደርጋለን። ከጫካ እስካልወጣ ጊዜ ድረስ ግን እምቢ አንረዳህም ማለት ይከብዳል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እውነትክን ነው ባሪሞር?"

"እውነቱን ነው ሰር ሔንሪ። አንድም ውሸት የለበትም።"

"ጥሩ፣ ባለቤትህን ስላገዝክ ልወቅስህ አልችልም። እስከአሁን የተናገርከውን አርሳው። ስለዚህ ጉዳይ ሚት እንነጋገራለን።"

እነሱ ሲሄዱ እንደገና ወደ ውጭ ተመለከትን። ትንሽ በጫቄ መብራት በጨለማው ውስጥ ነቁጥ አክላ ትታያለች።

"ባሪሞር ምግቡን ከወሰደለት፣ ቦታው ብዙ ሩቅ አይደለም።"

"ነፍስ-ገዳዩ እዚያች ነቁጥ የምታክል ብርሃን ውስጥ ነው የሚጠበቅ። እውነቱን ነው የምልህ ዋትሰን ይሽን ሰውየ ልይዘው ነው።"

እኔም ተመሳሳይ ስሜት ነው ያለኝ። ሰውየው የሕብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ሥጋት ነው። ሊታዘንለት ወይም ይቅርታ ሊደረግለት የማይገባ ወንጀለኛ። ሥራችንን የምንሠራው ሰውየውን ጉዳት ሊያደረስ ወደማይችልበት ሁኔታ እንዲመለስ በማድረግ ነው። ወደ ኮረብታው ስንወጣ ካፊያ ማካፋት ጀመረ።

"እኔ የምልህ ዋትሰን፣ ሆልምስ በአሁኑ አድራጐታችን ምን ይላል ? የሰይጣን ሃይል በሚበረታበት በዚህ ጥቅጥቅ ጨለማ ገዢ---?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ለጥያቂው መልስ ለመስጠት ይመስል፣ ጨለማው በለፈነበት ጋራና ሸንተረር ውስጥ ከዚህ በፊት በግሪምነን ረግረግ ጠርዝ ላይ ቆሜ የሰማሁት ዓይነት ጨኸት አካባቢውን አናጋው። ነፋሱን ተከትሎ አስፈሪ የሆነ ኩሬተኛ ድምፅ ተስተጋባና መልሶ አረጭ አለ።

"ያንት ያለህ! ምንድነው ዋትሰን?"

"ምን እንደሆነ አላውቅም፣ በዚህ ኮረብታማ ምድረ በዳ አካባቢ የማለማ ድምጽ ነው። ከዚህ በፊት አንዴ ሰምቸዋለሁ።"

"ዋትሰን የአዳኝ ውሻ ድምጽ ነው! ድምፁ አንዳች ነገር ይዞት በድንጋጤ የሚጮህ የሚመስል መልዕክት ያስተላልፋል። የአገሬው ሰዎች ይሸን ድምጽ ምን ይሉታል፡?"

ትንሽ አቅማማሁ። በገዘምታ ላልፈው ግን አልቻልኩም። "እነሱማ የባስከርቪል ቤተሰብ የአዳኝ ውሻ ጨኸት ነው ይሉታል።"

"ከግሪምነን ረግረጋማ ቦታ አቅጣጫ የማመጣ አይመስልም? አንተስ የአዳኝ ውሻ ድምፅ መሆኑን ትጠራጠራለህ? እኔ ሕሣን አይደለሁም። እውነቱን ንገረኝ!"

"ከዚህ በፊት ይህን ድምጽ የሰማሁት ከስቲፐልተን ጋር ሆኜ ነበር። የተለየ ዝርያ ያላቸው ወፎች ድምጽ ሊሆን እንደሚችል ነግሮኝ ነበር።"

"በጭራሽ የአዳኝ ውሻ ድምጽ ነው። አምላኬ- ከዚህ ከሚወራው ታሪክ ሁሉ ጥቂት እውነት ይኖር ይሆን? እውነትም በአደጋ ቀጠናው ውስጥ ገብቼ ይሆን? ለንደን ውስጥ ሆኖ መሳቅና ጭው ባለ ምድረ በዳ ውስጥ በድቅድቅ ጨለማ ቁም ልብ የሚያብረከርክ ድምፅ መስማት የተለየዩ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሮች ናቸው። እኔ ፊሪ አይደለሁም። ዋትሰን ያ ድምፅ ግን ልቤን ቀጥ ሊያደርጋት ምንም ያክል አልቀረውም።"

በድቅድቁ ጨለማ ተስ እያልን ጉዟችንን ወደፊት ቀጠልን። ዙሪያችን በተራሮች የተከበበ ነው። ያች ቢጫ የብርሃን ነቁጥ ነዲድ ከፊታችን ትታያለች። ቢያንስ የት እንዳለች ማወቅ ችለናል። ግራና ቀኝ ጋሻ በሆኗት ስንጥቅ አለቶች ውስጥ ተጣብቃለች። ከባስከርቪል አዳራሽ አቅጣጫ ብቻ እንድትታይ ሆና ነው የተቀመጠች።

ከዚያ እሱንም አየነው። የሚያስፈራ ቢጫ ፊት ያለው ሰው አለቱ ላይ ቁሞ ይታያል። ሰው ነው ለማለት ያስቸግራል። ዓመሙ ጭቃ የተቀባ፣ ሀገሩ የአውሬ ይመስላል። በድንጋይ ዋሻ ውስጥ ይኖር የነበረው ጥንታዊው ሰው ከየት መጣ ያሰኛል። ወደፊት ገሰገስን። በዚህ ጊዜ ተናዶ የሆነ ነገር እየተናገረ ሰመሮኖ አከበከበ። አጋጣሚ ሆኖ ጨረቃዋም ከደመናው ግርዶሽ ተላቃ ወጥታለች። እኛ ተራራው ጫፍ ላይ ስንወጣ በፍጥነት እየተንደረደረ መርዶ ሄደ። እሱን የመያዝ ዕድላችንን የተመናመነ መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብንም። ቆም ብለን ትንሽ ተንፈስ ካልን በኋላ ፊታችንን ወደ ቤት አዞርን። በዚህ ጊዜ አንድ ያልታሰበና አንግዳ የሆነ ነገር ተፈጠረ። ጨረቃዋ በስተቀኛችን በኩል እያሽቆለቆለች ነበር። ከአሷ ትይዩ የአለት ቁልል ግንብ መስሎ ተገትሯል። መቼ በዚህ በቃና! በጨረቃዋ ማሽቆልቆል ከአለቱ ሥር በተፈጠረው የጥላ ግርዶሽ ውስጥ ጥቁር የሆነ የሰው ምስል ይታያል። በሕይወቱ እንደዚህ ቁልጭ ብሎ የታየኝ ነገር አላውቅም። አሥረኛው አይደለም። ይህ ሰው አስረኛው ከነበረበት በጣም ርቆ ነው የሚታየው። በዚህም ላይ በጣም ረጅም ነው። የባልንጀራዎን ክንድ ለመጨበጥ ዞር ስል ያ ያየሁት ሰው ቁመና የለም።



t.me/OLDBOOKSPDF

የአካባቢውን ሰው በመጠየቅ ጥናት ለማካሄድ ፈልጌ ነበር። ሰር ሐንሪ ግን ከዚህ የተለየ አዲስ ነገር እንዲሠራ ፍላጐት የለውም። አሁንም በዚያ ባልታወቀ ድምፅ ውስጡ እንደተረበሸ ነው። ስለ ድምፁ ሲያስብ የቤተሰቡ የጨለማ ገዛ ትውስ ይለዋል።

"እሥረኛ ጠባቂ መሆኑ አያጠራጥርም" አለ። "እሱ ካመለጠበት ጊዜ ጀምሮ ይኸ አካባቢ በእነሱ ተጥለቅልቋል።" አባባሉ ልክ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ተጨማሪ ማረጋገጫ እንዲኖረኝ አፈልጋለሁ። ይቺ አካባቢ ሕዝቧንና ምሥጢሯን እንጻዘለች ከምንጊዜውም በላይ ብርቅየ ሆና ትኖራለች። ለማንኛውም ያንተ ወደ እኛ መምጣት ወሳኝ አማራጭ ነው...።

## ምዕራፍ አሥር

በአውደ ዕለት የተደገፈ የማስታወስ ችሎታዮን እተማመንበታለሁ። ከጧት ጀምሬ በዱር በገደሉ የነበረንን በጀብደኝነት የተሞላ ገዛ ዘንቢሁ።

አክቶበር 16፣ ክብድ ያለ ዝናባማ ቀን ነበር። ቤቱ በደመና ተጋርዷል። በየዕለቱ አደጋ አደጋ ይሸተኛል። አሰቃቂ አደጋ። አሰቃቂ የምለው ልገልፀው ስላልቻልኩ ነው።

የቅርብ ጊዜ ክስተቶችን እንመልከት። የአዳራሹ የመጨረሻው ወራሽ አሚሚት ጉዳይ፣ በአካባቢው አስ የሚባለው ልዩ ፍጡር ወይም አውሬ ነገር፣ ከሚታወቀው የተፈጥሮ ሕግ ውጭ ናቸው ብሎ ለመውሰድ አይቻልም። አየሩን በጩኸት የሚሞላና የእግሩ ኩቴ መሬት ላይ የሚታይ የአዳኝ ውሻ መንፈስ! ከተሞከሮ ያገኘሁት ዕውቀት በዚህ ጉዳይ ላይ እንዳምን አያደርገኝም። በዚህ ማመን የአገሬው ሰዎች በአፋና በዓይኑ እሳት የሚተፋ የሰይጣን ውሻ አስ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚባለውን አባባል አምኖ መቀበል ማለት ነው። ሆልምስ ለእንዲህ ዓይነቱ ተልድ ጆሮውን አይሠጥም። በእርግጥ እኔው ራሴ ይህን ያልታወቀ የጨዅት ድምፅ ከእንዴም ሁለቱ ሰምቼዋለሁ። ዋናው ጥያቄ ግን ትላልት አዳኝ ውሾች ወደ ጋራው ተለቀዋል ቢባል እንኳን የት ነው የተደበቱት? ከየት ነው ምግብ የሚያገኙት? ከየት ተለቀቱ? ለምንድነው በቀን የማይታዩት? የሚል ይሆናል። ተፈጥሮን ተከትለን ትንተና እንስጥ ብንል የዚያኑ ያክል ብዙ ችግር ውስጥ እንገባለን። ከቋጥኙ ሥር ያየሁት የሰው ምስልስ? ይህ ያልታወቀ ሰው ከስቴፕልተን ዘለግ ያለ ነው። ባሪሞር ይሆናል እንዳንል ቤት ትተነው ነው የመጣን። ተከትሎን እንደማይመጣ እርገጠኛ ነኝ። ለንደን ውስጥ እንደተደረገው ሁሉ አሁንም የሚከታተለን ሰው አለ። ያንን ሰው ከያገኙት ችግሮቻችን ሁሉ እዚህ ላይ ያበቃሉ።

ዛሬ ጧት ባሪሞር ሰር ሔንሪን መጻሕፍት ቤት ውስጥ በግል አነጋግሮታል። ሰር ሔንሪ በሩን ከፍቶ ወደ ቤተ መጻሕፍቱ እንድገባ ጠየቀኝ።

"ባሪሞር የሚናገረው ጉዳይ አለ" አለኝ

"ሰር ሔንሪ እኛን በጥሩ ሁኔታ ተቀብለህ አስተናግደሀል። በመሆኑም የሆነ ነገር በማድረግ ውለታህን መክፈል አለብኝ። ስለምስኪኑ ሰር ቻርለስ አሟሟት ጥቂት የማውቀው ነገር አለ። ይህን ያወቅሁት ግን ከምርመራ በኋላ ነው። በዚያ ሰዓት በመናፈሻው የግቢ በር ላይ ለምን ቆሞ ሲጠብቅ እንደነበረ አውቃለሁ። በእንዲት ሴት ጋር ለመገናኘት ነው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

" እሱ ሴት ለመገናኘት?"

"እም ጌታዬ"

"ስሟ ማን ይባላል?"

"ስሟን አላውቀውም ጌታዬ። የስሟ የመጀመሪያ ፊደላት ግን 'ኤል ኤል' የሚል ነው።"

"እንዴት አወቅህ ባሪሞር?"

"አጐትህ ያን ዕለት ጠዋት ደብዳቤ ይደርሰዋል። ከምቢ ትሬሲ ከሚባል ቦታ የተላከ ነበር። ከዚያ በላይ አላውቅም። ከጥቂት ጊዜ በፊት ባለቤቱ የሰር ቻርለስን ክፍል ሰታሀዳ የተቃጠለ ደብዳቤ አመድ ከአላት ዳር ታገኛለች። ከመሉ ገጹ በስተመጨረሻ ያለው ቱራጭ እንዲህ የሚል ነው። አሁንም ማንበብ ይቻላል። 'እባክህ፣ አባክህ አንተ የተከበርክ ሰው ስለሆንክ ይህን ደብዳቤ አቃጥለው። ግን በአራት ሰዓት በሩ ላይ ጠብቀኝ።' ከዚህ በታች 'ኤል ኤል' የሚሉ የእንግሊዝኛ ፊደላት ተጽፈዋል።"

"ኤል ኤል ስለሚለው የምታውቀው ነገር አለ?"

"እኔ አንተ ከምታውቀው በላይ አላውቅም ጌታዬ" የቤተሰቡ አንጋፋ የሆነው አሽከር ትዩን ሲወጣ ሰር ሔንሪ ወደ እኔ በመዞር፣ "እሺ ዋትሰን፣ ምን ይመስልሃል?" ሲል ጠየቀኝ።

"ኤል ኤል ምን እንደሆነ ተከታትለን ከደረስንበት ነገሩ ግልጽ ይሆናል። ለሆልምስ ቱሉ ብዬ አላውቀዋለሁ። ከለንደን ወደዚህ ካልመጣ ስህተቱ የእኔ ነው ማለት ነው"

ዛሬ ኦክቶበር 17 ነው። ቀኑን መሉ ገናብ ሲዘንብ ነው የዋለ። በሐረጉ ላይ የሚወርደውን ዝናብ እያየሁ ከወህኒ



t.me/OLDBOOKSPDF

አምባው አምልጦ በጫካ ውስጥ ስለሚኖረው አሥረኛ አሰላስልክ። ጋሪ ውስጥ ስላየነው ሰው፤ በጨረቃዋ ትይዩ ቋጥኝ ሥር ቆሞ ስለተመለከትክ‌ት ሰው፤ አወጣሁ አወረድሁ። ይህ ጨለማን ተገን አድርገ‌ው የቆመ ሰው ዝናብ እየመታው ይሆን?" ስል ራሴን ጠየቅሁ።

ዶክተር ሞርቲመር እኛን ሳይጠይቅ አንድ ቀን እንኳ የቀረበትን ጊዜ አላስታወስም።

"በነገራችን ላይ ሞርቲመር" አልሁት በሣሬው ዕለት። "አንተ የማታውቃቸው ጥቂት ሰዎች በዚህ ኮረብታማ ምድር አካባቢ የሚኖሩ ይመስለኛል። ስሚ በኤል ኤል የሚጀምር ሴት ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"ሳውራ ሊዮንስ የመጀመሪያ ስሞቿ በኤል ኤል የሚጀምሩ ናቸው። እሷ ግን ኮምቢ ትራስ በሚባል አካባቢ ነው የምትኖረው። የዚህን አካባቢ መልካ ምድር ለመሥራት የመጣ የሥዕል ባለሙያ አግብታ ነበር። ባለቤቷ ከዚህ ለቋል። እሷንም ትታት ነው የሄደ። አባቷ ያለ እሳቸው ፈቃድ ስላገባች ምንም ሳያደርጉላት ነው የቀሩት። በዚህም ልጅቷ መልካም ስም አልነበራትም። ቡኋላ ታሪኳ እየታወቀ ሲመጣ ግን በአካባቢዋ የሚኖሩ አያሌ ሰዎች ሕይወቷን የተቃና ለማድረግ እገዛ አድርገውላታል። ስቱፐል‌ተንና ሰር ቻርለስ የየበኩላቸውን ድጋፍ አድርገውላታል። እኔም ራሴ ጥቂት ረድቻታለሁ። ዓላማው የጽሕፈት ሥራ አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ድርጅት እንድታቋቁም ለማገዝ ነው።"

ሞርቲመር እስከ አራት ሰዓት ቆየ። ከዚያም እሱና ሰር ሔንሪ ካርታ ሲጫወቱ ቆዩ። የእልፍኝ አሽከሩ ቡናየን ላይብራሪ ውስጥ አመጣልኝ፡

"እሺ ባሪሞር" አልኩት። "ያ ዘመድህ ለቆ ሄደ? ወይስ እስከ አሁን ጫካ ውስጥ እንደሸፈተ ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"አላወቅሁም ጌታዬ። ከሦስት ቀናት በፊት ምግብ ካስቀመጥኩለት ቀን ጀምሮ አይቼው አላውቅም። ያስቀመጥኩለትን ምግብ ወስዶታል ብዬ አስባለሁ። በዚያ በኩል ሳልፍ አላገኘሁትምና።"

"ስለዚህ እዚያው ነው ማለት ነው?"

"ምግቡን የወሰደው ሌላ ሰው ካልሆነ በስተቀር እንደዚያ ነው።"

የቡና ስኒየን ይገር ወደ ከንፈራ እያስጠጋሁ ባሪሞርን በአግራሞት ተመለከትኩት።

"አዎ ጌታዬ፣ በአካባቢው ሌላ ሰው አለ። ሴልደን ከሳምንት በፊት ስለእሱ ነግሮኛል። እሱም እዚያው ሸፍኗል። እሱ ግን እንዳጣራሁት ከመሀኒ አምባ ያመለጠ አይደለም። ነገሩ አላማረኝም፣ ዶክተር ዋትሰን። ይህ ሰው ማንን እያደባ፣ማንንስ እየጠበቀ ነው? ይኸ ደፈጣ ለምድረ ባስከርቪልም ሆነ ለኗሪዎች ስም አይበጅም።"

"ሴልደን ስለዚህ ሰው ምን ይላል? ምን እያደረገ እንደሆነስ አውቋል?"

"መጀመሪያ ፖሊስ መስሎት ነበር። ቢኋላ ግን የራሱ የሆነ ዓላማ እንዳለው ተረዳ።"

"ሴልደን ሰውየው የት እንደሚኖር ነግሮሃል?"

"በጋራው ላይ፣ ጥንታዊው ሰው ይኖር በነበረበት የድንጋይ ጉጅ ውስጥ ::"



t.me/OLDBOOKSPDF

የእልፍኝ አሽከሩ ሲወጣ ወደ ጥቁሩ መስኮት ተጠግቼ በፍጥነት ወደሚጓዙት ደመናዎችና ወደሚወነጨፉት ቅርንጫፎች ተመለከትኩ። ውስጥ ሆኖ ሲያዩት ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ነው። በጋራው ባሉ የፊራሪሱ የድንጋይ ጉጆዎች ውስጥ ሆነው ለሚያዩትስ እንዴት ይሆን? ምን ዓይነት ጥላቻና ምሬት ቢሰማው ነው አንድ ሰው በዚህ ወቅት ወደዚህ ቦታ መጥቶ እንዲኖር የሚገደደው? እጅግ እያስጨነቀኝ ያለው የችግር ሐረግ ሥሩ የሚመዘዘው ከዚያ ጋራ ላይ ካለ ድንጋይ ጉጆ ውስጥ መሆን አለበት። ያ ሰውየ የምሥጢሩን ቁልፍ ለማግኘት ያደረገውን ሁሉ ለማድረግ ከአሁኗ ሰዓት ጀምሬ ቃል ገብቻለሁ።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

የግል ማስታወሻዬን የመጨረሻ ገጾች የሞላው የመስክ ስምሪት ሪፖርቱ እስከ ኦክቶበር 18 ያዘልቃል። የቅርብ ጊዜ ሁነቶች ግና ከአእምሮዬ ያልጠፉ ትኩስ ዜናዎች ናቸው።

ኩምቢ ትራሲ ከተባለው ቦታ እንደደረስኩ የሚስገ ሊዮንስን ቤት ለማግኘት ብዙ አልተቸገርኩም። የቤቱን ደጃፍ አልፌ ከቆንጆዋ ሴትዮ ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጥን፤ ለምን እንደመጣሁ ጠየቀችኝ። እስክምትጠይቀኝ ድረስ ያለሁበት ሁኔታ አስቸጋሪ መሆኑ አልገባኝም ነበር።

"ስለሚቹ ስለቻርለስ ባስከርቪል አሟሟት ለማወቅ ነው የመጣሁት።"

"ስለ እሱ ምን ልልህ እችላለሁ?" ስትል መልሳ ጠየቀችኝ። የእጇ ጣቶች ከመጻፊያ መኪናው ቁልፎች ጋር ይጫወታሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"በቀጠሮ እንድትገናኙ ደብዳቤ ለሰር ቻርለስ ጽፈሽ ነበር?"

ሚስዝ ሊዮንስ በንዴት ፊቷ ቀላና፣ "ኧረ እኔ በጭራሽ አልጻፍኩም!"

"ራስን ማታለል ካልሆነ የፃፍሽውን ደብዳቤ እኔ እንኳን በከፊል አስታውሳለሁ። እባክህ፣ እባክህ አንተ የተከበርክ ሰው ስለሆንክ ይህን ደብዳቤ አታጥለው- በአራት ሰዓት ግን በሩ ላይ ጠብቀኝ"

"አዎ እኔ ነኝ የፃፍኩት" ስትል ጮኸች ። "እኔ ነኝ የፃፍኩት፣ ለምን አስመስላለሁ? ሊያሳፍረኝ የሚችል አንዳችም ምክንያት የለም። ካገኘሁት እንደሚረዳኝ ስላመንኩ መናፈሻው ውስጥ እንድንገናኝ ጠየቅሁት።"

"በዚህ ሰዓት ቀጠሮ ለምን ?"

"ምክንያቱም በቀጣዩ ቀን ወደ ለንደን እንደሚሄድ ስለሰማሁና ከሄደ ደግሞ ለወራት ይቆያል ብየ ስለተጠራጠርኩ ነው።"

"እዚያ ስትሄጅ ምን ሆነ?"

"ሌላ ጉዳይ ስላጋጠመኝ አልሄድኩም።"

"ሰር ቻርለስን የቀጠርሽው አሁን በሞተበት ቦታና ሰዓት ቢሆንም በቀጠሮው አልተገኘሁም እያልሽ ነው?"

"ትክክል"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጥፋተኛ ካልሆንሽ፣ መጀመሪያ ስጠይቅሽ ለሰር ቻርለስ አልዓፍክም ያልሽ ለምንድ ነው?"

"የተሳሳተ ትርጉም ይሰጠዋል ብየ ስለፈራሁና ስሜ ሊጠፋ ይችላል የሚል ሥጋት ስለነበረኝ ነው።"

"ሰር ቻርለስ ደብዳቤውን እንዲያቃጥለው የፈለግሽው ለምንድው?"

"ከጠላሁት ባለቤቱ ጋር ማቆሚያ በሌለው መጣት ውስጥ ነበርሁ። ሕጉ እሱን ይደግፈው ስለነበር ከእሱ ጋር እንድኖር ሊያስገድደኝ የሚችልበት ሁኔታ ተፈጠረ። ለሰር ቻርለስ የዓፍክለት የተወሰነ ገንዘብ ብክፍል ነፃነቴን እንደማገኝ ስለተረሁ ነው። ያ ከሆነ ደግሞ ለእኔ የአዕምሮ ሰላም፣ ደስታ ክብር-- ሁሉም ነገር ማለት ነው። እናም ሰር ቻርለስ ደግ ሰው መሆኑን ስለማውቅና ታሪኬን እኔው ራሴ ባስረዳው ይገባዋል ብዬ አሰብክ።"

"ለምን ታዲያ በቀጠሮው ላይ አልተገኘሽም?"

"በመሀሉ ከሌላ ሰው እርዳታ ስላገኘሁ ነው።"

"ታዲያ ለሰር ቻርለስ ይሽንኑ ገልፀሽ ለምን አልዓፍሽለትም?"

"በቀጣዩ ቀን ጧት በወጡት ጋዜጦች ላይ ስለመሞቱ ባላንብ ኖሮ እንደዚያ አደርግ ነበር።"



t.me/OLDBOOKSPDF

የሴትዮዋ ንግግር ምክንያታዊ ስለነበር የእኔ ጥያቄ የሰጠችውን ምላሽ አላዛባውም። ምናልባትም የተናገረችው በሙሉ ያለዚያም ደግሞ በከፊል እውነት ሊሆን ይችላል። እንደገና ወደ ታሪካዊው አዳራሽ እየተመለስኩ ነው። ምርመራ ባካሄድኩ ቁጥር በሃሳቤ እየመጣ የሚጋረጥብኝ እሱ ነው። የመልስ ጉዞዬን ስጀምር ተስፋ ቆርጬ ነበር።

መንገዱን ይዤ ወደ ጋራው ወጣሁ። ከአንድ ኮረብታ ጫፍ ላይ ስደርስ ፀሐይዋ እየጠለቀች ነበር። ከታች የሚታየው ረጅም የተራራው ሸንተረር በአንድ በኩል አረንጓዴ ወርቅ በሌላ በኩል ግራጫ ሆኖ ይታያል። ከእኔ ሥር ካለው ጉድጓዳ ቦታ የጭስ ድንጋይ ቤቶች ክብ ሆነው ይታዩኛል። አንደኛው ቤት አሁንም ሰመጠለያ የሚሆን በቂ ጣሪያ አለው። በአለቶች መካከል ያለው ጠባብ መንገድ ወደ አንድ በሩ የፊረሰ ዋሻ ያመራል። ሁሉም ነገር ወና ያለ ነው። ያልታወቀው ሰው እዚህ ተደብቆ ወይም በአምባው አካባቢ እየተንቀሳቀሰ ነው። ሰውነቱ በፍርሐት ተንቀጠቀጠ። ከዚያም የያዝኩትን ሲጋራ ወርውሬ ጠመንጃዬን አጥብቄ በመያዝ ወደ ዋሻው መግቢያ ገሰገስኩ። ወደ ውስጥ ስመለከት ምንም ነገር አላገኘሁም።

ሰውየው እዚህ እንደሚኖር ግን አረጋግጫለሁ። እሳት በነደደበት ቦታ ላይ አመድ ተቆልሎ ይታያል። የወዳደቁ ቅርቅሮዎች ሰው እንደነበረበት ያመለክታሉ። የዚህን ሰው ማንነት አስከማውቅ ከዚህ የድንጋይ ጉጅ /ዋሻ / ለቅቄ ላለመሄድ ወሰንኩ። ፀሐይዋ እየጠለቀች ነው። የምዕራብ የሰማይ አድማስ በሐምራዊ የተፈጥሮ ቀለም ተጨፍልቋል። በጨለማ ዋሻው ሥር ተቀምጬ መጠበቅ ጀመርኩ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያ ሲመጣ ሰማሁት። ጫማው ከድንጋይ ጋር ሲላጋ ከሩቅ ይሰማል። የኸው ድምፅ እየቀረበ መጣ። ጠመንጃዬን አቀባብዬ ይዤ ከማልታይበት ጨለማ ቦታ ተደበቅሁ። የሆነ ነገር ላላይ ላለመውጣት መስኖለሁ። ሰዋቲት ጊዜ ኩቱው ጸጥ አለ። ከዚያ እየቀረበ ሲመጣ ዋሻው ላይ ጥላ መታየት ጀመረ ።

አንድ በጣም የማውቀው ድምጽ "በጣም ደስ የሚል ምሽት ነው ዋትሰን" ሲል ይሰማኛል። "ከውስጡ ይልቅ ውጪ በጣም አንደሚመች አልጠራጠርም።"

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ለአንድ ደቂቃ ያክል አልተነፈስኩም። ጆሮዬን ማመን ተሳነኝ። ከዚያ ነፍስ ዘራሁ አና መናገር ጀምርኩ።

"ሆልምስ!" አልሁና ጨኽቱን አቀለጥሁት።

"ና ውጣ!" አለኝ፣ " ጠመንጃህን ተጠንቅቀህ ያዝ።" ከአለቱ ላይ ተተምጦ በእኒያ ግራጫ ዓይኖቹ ፊቴን ያስተውለኛል። በሁለታችንም ገጽታ ላይ የመደመም ስሜት ቁልጭ ብሎ ይነበባል።

"በሕይወቱ አንተን እዚህ ከማግኘት የበለጠ ያስደስተኝ ምንም ነገር የለም" አልሁት እጁን እየጨበጥኩት።

"ወይም በጣም ያስገረመህ - አይደል? መገረም እንኳን ሁላችንም ተገርመናል። እውነቱን ልንገርህ! በሩ ጋ ለመድረስ ሃያ ሜትር እስኪቀረኝ ወደ ተደበቅሁበት ሥፍራ ትገባለህ የሚል ሃሳብ አልነበረኝም። ታገኘዋለህ ብዬ እንኳን አልገመትኩም።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዱካየን ስላገኘህ መሆን አለበት"

"አይደለም ዋትሰን :: የአንተን ዱካ ከሌሎች ሰዎች ለይቼ ለማወቂ እርግጠኛ አይደለሁም:: እኔን ማታለል ከፈለግህ ሲጋራህን መለወጥ አለብህ፣ ያለዚያ ሲጋራህ ጫፍ ላይ ያለውን BOS የሚል ጽሑፍ ሳይ ጓደኛዬ ዋትሰን በእካባቢው መኖሩን ማወቂ የማይቀር ነው:: ወደ ዋሻው ስትገባ ሲጋራህን እንደወረወርከው አልጠራጠርም! በአንተ ቤት እኔ ወንጀለኛው ሽፍታ መሆኔ ነው አይደል?"

"ማንነትክን እንኳን አላወቅሁም :: ማወቅ አንዴስብኝ ግን ቆራጥ አቂም ወስጂ ነበር::"

"ግሩም ዋትሰን! ምን አልባትም ወንጀለኛውን እያደናችሁ በነበረበት ሌሊት ሳታየኝ የቀረህ አይመስለኝም:: ጀርባየን ለጨረታዋ ብርሃን ሰጥቼ ነበር የቆምክት :: የሞኝ አቂቂም ነው አይደል::"

"አንተ ነበርክ እንዴ! ግን በምን ተአምር እዚህ ትመጣለህ ብየ ላስብ? ከሎንደን የወጣህ አልመሰለኝም::"

"የእኔም ምኞት እንደዚያ እንድታስብ ነበር:: ከሰር ሔንሪና ከአንተ ጋር ብሆን ኖሮ ጠላቶቻችን ይነቁብን ነበር:: እንደልቤ መንቀሳቀስም አልችልም ነበር::"

" ስለዚህ ሪፖርቶቹ ሁሉ ከንቱ ሆነዋላ!"

ሆልምስ ጥቅል ወረቀት ከኪሱ አወጣና:- "ውድ ባልደረባየ እነዚህ ያንተ ሪፖርቶች ናቸው:: ዋጋ አላጡም :: አንዲያውም በጥንቃቂ ተመርምረዋል ተጠንተዋል:: አሁን ከማስ ላውራ ሊዮንስ ጋር ያደረግኸው ውይይት እንዴት እንደነበር አስቲ ንገረኝ:: እሷን ለማነጋገር ኩምቢ ትሬሲ ድረስ ሄደህ እንደነበር መገመት አያዳግትም::"



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሴትዮዋ ጋር ስላደርግሁት ውይይት ለሆልመስ ነገርኩት።

"ይህ ጠቃሚ መረጃ ነው" አለኝና በመቀጠልም "ጉዳዩን በተመለከተ የተፈጠረውን ክፍተት ለመመላት ያስችለናል። ምን አልባትም በዚች ሴትዮና ስቴፐልተን በተባለው ሰው መካከል የጠበቀ ግንኙነት መኖሩን ታውቅ ይሆን? ይህ በእጃችን ላይ ያለ ትልቅ የመረጃ መሣሪያ ነው። እሱን ከሚስቱ ለመነጠል የምንጠቀምበት ከሆነ--"

"ሚስቱ?"

"ብዙ መረጃዎች ሰጥተኸኛል። እኔ ደግሞ ጥቂት መረጃ ልስጥህ። ያች ወይዘሪት ስቴፐልተን እያለ የሚጠራት ሴት ሚስቱ ናት።"

"ያንተ ያለህ! እርግጠኛ ነህ ሆልምስ? ሰር ሔንሪ በፍቅሯ ወደቅሁ ብሎ እንደዚያ ሲሆን ግን እንዴት አስቻለው?"

"ያ ከሰር ሔንሪ በስተቀር ማንንም አይጐዳም። አንተም እንዳስተዋልከው ሰር ሔንሪ ከእሷ ጋር እንዳይፋቀር ስቴፐልተን ልዩ ጥንቃቄ አድርጓል። አሁንም ደግሜ የምነግርህ ሴትዮዋ ሚስቱ እንጂ እህቱ አይደለችም።"

"ለምን ያጭበረብራል ታዲያ?"

"ለእሱ ዓላማ ተፈፃሚነት ተፈላጊና ጠቃሚ የምትሆነው ያላገባች ሴት መሆኗ ሲታወቅ ነው።"

በልቤ የያዝኳቸው ያልተነገሩ ጥርጣሬዎች ሁሉ መልክ እየያዙ ሲመጡ ትኩረቱ በተፈጥሮ ላይንስ ተመራማሪው ላይ ሆነ። ያ የሰሌን ባርኔጣ አድርጐ የነፍሳት



t.me/OLDBOOKSPDF

ማጥመጃ መረብ የያዘ ሰው ወሰን የሌለው ትዕግሥትና ፈገግታ ያለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን መሠሪነቱና አረመኔነቱ ቁልጭ ብሎው ታየኝ።

"ማን አርግጠኛ ነህ ሆልምስ? ሴትዮዋ ባለቤቱ መሆንዋን እንዴት አወቅህ?"

"ከአንተ ጋር መጀመሪያ በተገናኛችሁ ጊዜ አውነተኛ ነገር ስለነገረህ ነዋ ! ሳይፀፀት የቀረ አይመስለኝም። ስለ አንድ ትምህርት ቤት ሃላፊ ለማወቅ ልዩ ጥረት አይጠይቅም። በሥራ ላይ ያሉትን ሁሉ መዝግበው የሚይዙ ቀጣሪ ድርጅቶች አሉ። ባደረግሁት መጠነኛ ክትትል፡- ትምህርት ቤቱ መዘጋቱን፣ ባለቤቱ ማን እንደነበረ- ስሙ ሌላ ነው፣ ሚስቱን ይዞ መጥፋቱን አውቁያለሁ። መረጃው እነሱን በትክክል የሚገልጽ ነው። የጠፋው ሰው የተፈጥሮ ሳይንስ ልሂት መሆኑን ስረዳ ስቲፕልተን ስለመሆኑ አልተጠራጠርኩም።"

"ይቺ ሴት ባለቤቱ ከሆነች ሚስዝ ላውራ ሊዮንስ ምን ጥልቅ አደረጋት?" ብየ ጠቅሁት።

"የአንተ የምርመራ ሪፖርት ፍንጭ ከሰጠቻቸው አንዱ ነጥብ ይሽ ነው። ለመፋታት ያቀደች መሆኗን አላወቅህም ነበር። እንደዚያ ከሆነ ስቲፕልተን ያላገባ መስሏት እሱን ለማግባት ተስፋ አድርጋ ነበር ማለት ነው።"

"እውነቱ ሲወጣስ?

"ቁም ነገሩ እሱ ላይ አይደል! ያኔ ነው እሷ የበለጠ የምትጠቅመን።"

"ሆልምስ አንድ የመጨረሻ ጥያቄ! ይሽ ሁሉ ድካም ለምንድ ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆልምስ በሽክሽክታ መለሰ፡ "የነፍስ ግድያ መንጀል ነው ዋትሰን። ጭካኔ የተሞላበት አረመኔያዊ ግድያ! መጠንቀቅ ያለብን አንድ ነገር ላይ ብቻ ነው። እኛ ከመዘጋጀታችን በፊት ስቲፐልተን ቀድሞ ሊያጠቃን ይችላል። በነገው ዕለት ዝግጁነን አጠናቅቃለሁ። እስከዚያ ግን ለሰር ሔንሪ ከፍተኛ ጥበቃ አድርግለት። ልብ ብለህ እዳምጠኝ!"

ሀዮታ ሰፍናበት ከነበረው አምባ ምድር የወጣ ከፍተኛ ጩኸት አካባቢውን አናጋው። ልቤ ቀጥ ያለች ነው የመሰለኝ። ሆልምስ ዘሎ በመቆም "የት ነው?" አለ በለሆሳስ ድምፁ እየተቆራረጠ። ያ ደፋርና የብረት መዝጊያ ነው የምለው ባልደረባዬ ልቡ በፍርሃት ሲርድ አየሁት።

አሰቃቂው ጩኸት አሁንም በመደጋገም የፀዮታ ድባብ የነገሰበትን ጨለማ ድብልቅልቁን አወጣው። ድምፁ እየጨመረና እየተረበ መጣ። ከዚሁ ጋር ተቀላቅሎ ሌላ አንደ መዚታ ከፍና ዝቅ እያለ ግን ለስሜት የማይሰጥ አስፈሪ ድምጽ ተሰማ። ከፍና ዝቅ አባባሉ የባሕር ሞገድ ይመስላል።

"የአዳኝ ውሻ ጩኸት!" አለ ሆልምስ ጮክ ብሎ። "ዋትሰን ቶሎ ፍጠን! ያንት ያለህ! ከዘገየን..."

ከኮረብታው ላይ በፍጥነት በመንደርደር ላይ እያለን ከፊታችን ራቅ ብሎ ከሚገኘው ጠጣ ገባ መስክ አካባቢ አንድ ተስፋ አስቆራጭ ሊባል የሚችል የመጨረሻ ጩኸት ተሰማ። በዚያ ጨለማ ሌላ ድምፅ አይሰማም።

"በጣም በመዘግየታችን አሸንፎናል ዋትሰን"

"በጭራሽ እያሸንፈንም!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ተቀድሜያለሁ። መዘግየት አልነበረብኝም። ግን እውነቱን ልንገርህ የክፋ ነገር ቢመጣ እንኳን እንበቀላለን!"

ያ አስፈሪ ድምፅ የመጣበትን አቅጣጫ ይዘን የጨለማ ሩጫችንን ቀጠልን። ከእለት እየተላጋን፣ ቁዮቋጦና ጢሻ እየጣስን አቀበትና ቁልቁለቱን እየወጣንና እየወረድን፣ እየወደቅን እየተነሳን ወደፊት ገሰገስን። በስተግራችን ከፍተኛ የድንጋይ ቋጥኝ አለ። ከሥሩ ያለው አቀበት ድንጋያማ ነው። በዚያ ላይ አንድ ለየት ያለ ጥቁር ነገር ይታየኛል። እየተረበሽው ስንሄድ አንድ ሰው በፊቱ ተደፍቶ መሬት ላይ ተዘርሯል። አንጉቱ እንዳልሆነ ሆኖ ተጠምዝዟል። ሆልምስ በሰውየው ራስ ላይ እጁን ጣል አድርጉ ቆየና ቀና አደረገው። የጫረው ክብሪት በደም በተነከረው የእጁ ጣት ላይ ብልጭ ድርግም ይላል። መላ ሰውነቱ በደመ አበላ ተነክሯል። ሬላ ነው፣ የሰር ሐንሪ ባስከርቪል ሬሳ!

ሁለታችንም ባስክሬት ላይ ያለው ቀላ ያለ ቡኒ መሉ ልብስ የእሱ ስለመሆኑ አልተጠራጠርንም፣ ስመጀመሪያ ጊዜ ለንደን ስንገናኝ ለብሶት የነበረው ልብስ ነው።

"የሰይጣን ሥራ ነው! የሰይጣን ሥራ! አ- በእሱ ሞት እኔ ራሴ ተጠያቂ ነኝ። የራሴን ገዳይ ሳሳድድ የእሱን ሕይወት አስቀጠፍኩት። ግን እንዴት እንደዚያ አያስጠነቀቅሁ እዚህ ጭር ካለ ምድረ በዳ ውስጥ መጥቶ ሕይወቱን አሳልፎ እንደሚሰጥ ማወቅ እችላለሁ? አጮኅና የወንድም ልጅ ሁለቱም ተገደሉ። አንዱ አስፈሪውን አውሬ ሲያይ በደረሰበት ድንጋጤ፣ ሌላው ከአውሬው ሰማምለጥ ሲሽሽ በደረሰበት አደጋ። አሁን በትክክል ማወቅ ያለብን በስቲፐልተን እና በአውሬው መካከል ያለውን ግንኙነት ነው። ስለአውሬው መኖር እንኳ አርግጠኛ መሆን አንችልም። ምክንያቱም ሰር ሐንሪ ለሞት የተዳረገው ድንጋይ ላይ ስለወደቀ ነው። ሰውየው ግን መሠሪ ስለሆነ ተድሞኝ ርምጃ ሊጠነድ ይችላል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

የወደቀውን ራሳ ደግሜ ተመለከትሁት። እንደዚያ የተጠማዘዘትን የሰውነቱ አካላት ሳይ ዕምባየ ችርፍፍ አለ። "ሆልምስ፣ እርዳታ እንዲመጣልን ካልጠየቅን በስተቀር ብቻችንን ወደ ቤት ለመውሰድ የማይሞከር ጉዳይ ነው" አልሁት።

ሆልምስ አስከሬኑ ላይ አንዳጐነበሰ ነበር። ወዲያው እየዘለለ፣ እየደነሰና በሳቅ እየተፍነከነከ መጣና እጀን እየጨመቀኝ "ጂም! ጂም! ሰውየው ጂም አለው! ሰር ሔንሪ አይደለም፣ ይህ ሰው---"

"በምን እንደሞተ ባይታወቅም ከአሥር ቤት ያመለጠው ሰውየ ነው!"

እየተጣደፍን በፊቱ ተደፊቶ የነበረውን አስከሬን ገልበጠን በጀርባው እንጋለልነው። ደም የረጨው የጺሙ ፀጉር በጨረቃዋ ብርሃን በደንብ ይታያል። ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። ያ በብርሃን ጭላንጭል አይኑን የሸሸው ሰው ትክክለኛ መልክ ነው። የወንጀለኛው የሴልደን ገጽታ። በትጽበት ውስጥ ሁሉም ነገር ግልፅ እየሆነልኝ መጣ። ሰር ሔንሪ ለባሪሞር አሮጌ ልብስ ሰጥቼዋለሁ ማለቱን አስታወስኩ። ባሪሞር ልብሱን ሰብሶ ለመሰወር እንዲረዳው ሰወንድመ ሰጥቶታል። ጫማው፣ ኮፍያው ገርጐርጐር ያለ ቡኒ ልብስ ሁሉም የሰር ሔንሪ ናቸው።

ለዚያ ምስኪን ሰው ሞት ምክንያት የሆነውም ይኸው ነው! ውሻው የሰር ሔንሪን ጠረን አነፍንፎ እንዲያድን ነው የተደረገው፣ ምንአልባትም ለዚህ ሁሉ ያበቃው ከሆቴሉ የተሰረቀው ጫማ ሊሆን ይችላል። ውሻው የጫማውን ጠረን አነፍንፎ በሰውየው ደረሰበት።

"ውሻው በዛሬው ሌሊት እንዴት ሊለቀቅ ቻለ? ስቲፕልተን ሰር ሔንሪ መኖሩን ሳያረጋግጥ ውሻውን አይለቀውም።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሐሰ ዋትሰን! ምንድነው እሚታየኝ? በጣም የሚገርም ነው!--"

በጋራው ላይ የሆነ ሰው ወደ እኛ እየመጣ ነው። ይብሰዘ ያለ የሲጋራ ፍም ቀይ ሆኖ ይታየኛል። በጨረታ ብርሃን የሚታየው ሰውየ የተፈጥሮ ሳይንስ ተመራማሪው መሆኑን ለይቼዋለሁ። እኛን ሲያየን ቆመ፣ ከዚያ ወደፊት ቀጠለ። "ዶክተር ዋትሰን! ነህ- አይደለህም? በዚህ ሌሊት እንዲህ ዓይነት ቦታ ላይ ትገኛለህ ብየ መገመት ያዳግተኛል። ምንድነው እሱ የተገዳ ሰው አለ ? ኳደኞችን ሰር ሐንሪ ላይ ገዳት ደርሷል እንዳትለኝ!"

ፊጠን ብሎ አልፎኝ ሄደና የተጋደመውን አስከሬን ጉንበስ ብሎ አስተዋለው። ቶሎ ቶሎ ሲተነፍስ ይሰማኛል። የያዘው ሲጋራ አምልጦት ወደቀ። "ማ ማ ማነው?" አለ በለሆሳስ።

"ሴልደን ነው። ከፕሪንስታውን ያመለጠው አስረኛ።"

ስቲፕልተን አመድ የለበሰ የማመስለውን ፊቱን ወደ እኛ መለሰ። እንደምንም ብሎ ትንፋሹን ዋጥ አደረገና የተሰማውን የብስጭት ስሜት ለመሸፈን ሞከረ። ከዚያ አንዴ ወደ ሆልምስ ከዚያም ወደ እኔ ተመለከተና፣ "ምን ዓይነት መጥፎ አጋጣሚ ነው! ጨዝት ሰምቼ ነው የወጣሁት። ስለ ሰር ሐንሪ ጥሩ ስሜት አልነበረኝም።"

"ለምን ስለ ሐንሪ ብቻ ታስባለህ?" ብየ ከመጠየቅ ወደ ኋላ አላልኩም።

"እኛን ለመጠየቅ ይመጣል ብየ ስላሰብክ ነው። አለመምጣቱ ግን ገርሞኛል። በጋራው ላይ ያን የመሰለ ጨዝት ስለማ ስለ አሱ ደህንነት ማሰቢ ያልተለመደ አይደለም ተፈጥሮአዊ ስሜት ነው። የዚህ ምስኪን ሰው አሟሟት እንዴት ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ፍርሃት፣ ቅዝቃዜና ረሃብ ተፈራርቀው ለእብደት እንደዳረጉት አልጠራጠርም። አቅሉን አጥቶ በዚህ ጋራ ላይ ሲሽከረከር የመጨረሻ እጣው ይኸ ሆነ። በጨለማ ሲካ,ትን በቋጥኝ ድንጋይ ላይ ወድቆ አንገቱ ተሠብሮ ፈጣሞት ።"

"አንተስ ምን ይመስልሃል ሚስተር ሸርሎክ ሆልምስ?"

ጓደኛዬ በትህትና ከአንገቱ ጐንበስ ብሎ "እኔነቱን ለመለየት ጊዜ አልወሰዱብህምሳ!"

"ዶክተር ዋትሰን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ሁላችንም እዚህ አካባቢ ያለን ሰዎች እንደምትመጣ እንገምት ነበር። አሰቃቂ ሞት ላይ ነው የደረስከው።"

"አም ጓደኛዬ የተናገረው ሁሉ እውነት ነው። የሚያሳዝነው መጥፎ ትዝታ ይገር ነገ ወደ ለንደን መመለሴ ነው።"

"አ፣ ነገ ትመለሳለህ? እርግጠኛ ነኝ የአንተ ጉብኝት እዚህ አካባቢ ለተፈጠሩት ችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ያግዛል።"

"የምንቋምጥለትን ስኬት ሁል ጊዜ አናገኘውም። በምርመራ ሂደት ትክክለኛ ማስረጃ የማግኘት ጉዳይ ወሳኝ ነው። ያለዚያ ተራ ወሬ ወይም አሰ ሰጡኝ ነው የሚሆነው። እናም ለምርመራ የሚያበቃ ጉዳይ አይደለም።

ጓደኛዬ ለጉዳዩ ደንታ እንደሌለው አድርጐ ነው የተናገረው። ስቲፐልተን ግን አሁንም ኩስተር ብሎ ነበር የሚመለከተው። ከዚያ ወደ እኔ ዞር አለ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይኸን ምስኪን ሰው ወደ ራሴ ቤት መውሰድ ነበር ፍላጐቱ፤ ግን እሁቱ ስለምትፈራ ወደ እዚያ መውሰድ ያስቸግራል። ለማንኛውም እስኪነጋ መጠበቅ ይሻላል።"

ሆልምስና እኔ ወደ ባስከርቪል አዳራሽ ጉዟችንን ቀጠልን። ወደ ኋላ ስንመለከት የሚችን ጥቁር አስከሬን በጨረቃዋ ብርሃን አሻቅበን አየነው። ስቲፕል-ሁንም አቀበትና ቁልቁሉቱን እያቋረጠ ሲሄድ ከሩቅ ይታይ ነበር።

"ስውየው እንዴት ቀፎታል?" አለ ሆልምስ፤ "እሱ ባጠመደው ወጥመድ ሌላ ሰው እንደገባበት ሲያውቅ እንዴት ፈጥኖ ስሜቱን እንዳስተካከለ አየኸው አይደል! ለንዶን እያለን ነግሬሃለሁ ዋትሰን፤ አሁንም ደግሜ ልነግርህ የምፈልገው ከእሱ የከፋ ጠላት የሌለን መሆኑን ነው።"

"ለምን ፉሉ ብለን በቴጥጥር ሥር አናውለውም?"

"ውድ ዋትሰን፤ አንተ ስተግባር የተፈጠርክ ሰው ነህ። ሁልጊዜም ወሳኝ ርምጃ እንዲወሰድ ትፈልጋለህ። ይኸን ብናደርግ ግን ምንም ሕጋዊ ማስረጃ አይኖረንም። አንረታውም። ያ ማለት ለክርክር የሚያበቃ ጉዳይ ሳይሆን አሉባልታ ይዘን ቀረብን ማለት ነው።"

"የሰር ቻርለስ ሞት ማስረጃ አይሆንም?"

"ሞቱ ከመገኘቱ በስተቀር ምንም ምልክት አልተገኘም። በፍርሃት መሞቱን የምናውቅ እኔና አንተ ብቻ ነን። ምን እንዳስፈራውም እናውቃለን። ፍርድ ቤቱን ግን እንዴት ማሳመን እንችላለን? አዳኝ ውሻ ምን ምልክቶች አሉት? ጥርሶቹ ላይ ያሉት ምልክቶች በየት በኩል ናቸው? እርግጥ ነው አዳኝ ውሻ የሞተ አካል እንደማይበላና ሰር ቻርለስ የሞተውም ተናካሽ አውሬው እሱ ጋ ከመድረሱ በፊት መሆኑን እናውቃለን። ይኸ ሁሉ በማስረጃ መረጋገጥ አለበት። እኛ ግን ማስረጃ የለንም።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሽ፣ የዛሬው ሴሲት ክለተትስ ለመረሻነት አደበቃምን"

"እሱም ቢሆን አይመረጥም። አነፍናፊውን ውሻ አላየነውም። በእርግጥ ሰምተነዋል። ግን ሰውየውን አያሳያደ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለንም። እንደዚያ አይደለም ወዳጄ። በአሁኑ ሰዓት ለክርክር የሚያበቃ ጉዳይ የሌለን ስለመሆኑ እንተማመን። ከዚህ በኋላ በማስረጃ የተደገፈ የመከራከሪያ ነጥብ ለመፍጠር ድፍረቱ ይኑረን። ሚስ ላውራ ትተባበረናለች ብየ ተስፋ አደርጋለሁ። አንድ የመጨረሻ ቃል ዋትሰን። ስለአዳኙ ውሻ ስለሌንሪ ምንም እንዳትነግረው። ሴልደን የሞተው አንተ ተደም ሲል እንዳልከው በተለያዩ እንግልቶች ላቢያ አዕምሮውን ስቶ ከገደል ጫፍ ላይ በመውደቱ መሆኑን አሳምነው። የአንተን ሪፖርት በትክክል አስታውሺ ከሆነ ሌንሪ ከእነዚህ ሰዎች ቤት ራት ለመብላት ነገ ማታ ቀጠሮ ይዛል።"

"እም፣ እኔም አለሁበት።"

"ስለዚህ አንተ ይቅርታ ጠይቅና እሱ ብቻውን ይሂድ።"

## ምዕራፍ አሥራ ምስት

ሰር ሌንሪ ሼርለክ ሆልምስን ሲያገኘው መገረም ብቻ ሳይሆን በጣም ደስ አሰኘው። በቅርብ ጊዜ የተፈፀመት አንዳንድ ድርጊቶች ከለንደን እንዲመጣ ያደርጉታል የሚል ግምት ነበረው።

ቀኑን መሉ ሥራ ፈትቼ እቤት ነው የዋልኩት። ብቻዬን አንዳልሄድ ባልታዘዝ ኖሮ ስቱፐልተን ቤት ጥሪ ስለነበረኝ ከእሱ ጋር ምሽት አሳልፍ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

"በጣም ጥሩ ምሽት ታሳልፍ እንደነበር አልጠራጠርም" አለ ሆልምስ ድርቅ ባለ አነጋገር።

"ስለዚያ ጉዳይስ የደረስክበት ጉዳይ አለ?"

"አለ...፤" ድንገት ንግግሩን በማቆም ረጋ ብሎ ሥዕሉን አትኩሮ ይመለከታል። የፋኖሱ መብራት ፊቱ ላይ ያብረቀርቃል። በጣም ተመስጦ ስለነበር ከዓይኖቹ በስተቀር ፊቱ የማይንቀሳቀስ ግዑዝ አካል ይመስላል። "ደስ የሚሉ ፎቶግራፎች ናቸው" አለ ፊት ለፊት ወዳለው ግድግዳ በእጁ እያመለከተ። "ሁሉም የአንተው ቤተሰብ አባላት ናቸው ልበል ?"

"አዎ፤ ሁሉም"

"ይኸ ከፊት ለፊት ያለው የአሥራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሰው ማነው?"

"እሱማ የዚህ ሁሉ ችግር ሰበብ የሆነው ሰው ነው። የባስከርቪሎች የአዳኝ ውሻ ታሪክ በእሱ ነው የሚጀምረው።"

"እንዲያ ነው?" አለ ሆልምስ። ገጽታው ላይ ርኃታና ሰላማዊነት ይነበባል። "በጣም ጨካኝና ሃይለኛ ይመስለኛል።"

"ለዚያ ምንም ጥርጥር የለውም። ስሙ እና 1647 የሚል በሥዕሉ ጀርባ ላይ ተጽፏል።"

ሆልምስ አንዳንድ ነገሮችን የተናገረ ቢሆንም የሥዕሉን ያክል ትኩረቱን የሳበው ነገር አልነበረም። ዓይኑን ከሥዕሎቱ ላይ አልነቅል አለ። በመጨረሻ ሰር ሔንሪ ወደ ክፍሉ ሲሄድ እኔን ወደ ምግብ አዳራሽ እንድሄድ መራኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"እዚያ ጋ ያለው ነገር ይታይኻል?"

ትልቅ ባለ ላባ ባርኔጣ፣ የተጠቀለለ ፀጉር፣ ነጭ ሸሚዝና ኮስተር ያለ የፊት ገጽታ ተመለከትሁ። ሰውነቱ ፊርጠም፣ ከንፈሩ ሳሳ ያለና ዓይኖቹ ፍዝዝ ያሉ ናቸው።

"ቆይ እስቲ" አሰና ወንበሩ ላይ ወጥቶ ቆመ። መብራቱን በግራ እጁ ይዞ፣ ቀኝ እጁን በማጠፍ በረጅም ፀጉር ላይ ባርኔጣ አድርጐ የሚታየውን ሥዕል ለመከለል ይሞክራል።

"ኧረ በተሰቀለው!" አልሁና ጮክ ብዬ ተናገርሁ። የስቲፕልተን ፊት ሥዕሉ ላይ ቁልጭ ብሎ ታየኝ።

"አየህ አይደል! ዓይኖቹ የሰለጠኑት የፊት ገጽታን አይቶ ለመመርመር እንጂ በዚያ አካባቢ ያሉትን ነገሮች ለማጥናት አይደለም። ሰውየው የባስከርቪል ቤተሰብ አባል ነው። ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። ይህ ውሉ የጠፋውን የግንኙነት መስመር ይቀጥለዋል። ዋትሰን፣ አሁን በአስተማማኝ ሁኔታ ደርሰንበታል።"

ከመኝታዬ በጧት ነበር የተነሳሁት። ሆልምስ ደግሞ ከእኔም ይቀድማል። ልብሴን እየለበስኩ ሳለ መንገድ ላይ አይቼዋለሁ። "ወደ ጋራው ብት ብለህ ነበር?"

"የሴልደንን ሞት በሚመለከት ከግሪምፐን ወደ ፕሪንስታውን ሪፖርት ልኬለሁ። የሚቀጥለው ሥራችን ሰር ሔንሪን ማግኘት ይሆናል። እንዲያውም ይኸውና!"

"እንደምን አደርክ ሆልምስ? ከኤታማጆር ሹመ ጋር ለመዋጋት ያቀደ ጀኔራል ትመስላለህ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያለንበት ትክክለኛ ሁኔታ የሚገልፀው ይሽንኑ ነው። ትዕዛዝ እየሰጠሁ ነው። ጓደኞችን ስቴፐልተን ቤት የዕራት ግብዣ ፕሮግራም እንዳለብህ አውቃለሁ።"

"አንተም ትመጣለህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ብትገኝላቸው ደስታውን አይችሉትም።"

"ዋትሰንና እኔ ወደ ለንደን መሄድ አለብን።"

"ወደ ለንደን? በዚህ ጉዳይ ላይ ልታግዙኝ የመጣችሁ ነበር የመሰለኝ። አዳራሽና በአካባቢው ያለው ምድረ በዳ እንካን ብቻን ሆኖ አብረን እያለንም በጣም ያስፈራል።"

"የእኔ ወንድም እመነኝ። አንድታደርግ የምጠይቅህን ነገር ደግሞ በአግባቡ ፈጽም። ለአስቸኳይ ሥራ ወደ ለንደን ባንሄድ ኖሮ ከአንተ ጋር ለመምጣት ደስተኞች እንደነበርን ነገራቸው። ዋትሰን ደግሞ እራት ላይ ለመገኘት የማትችል መሆንህን ገልጸህ ለስቴፐልተን የይቅርታ ማስታወሻ ብትጽፍለት ምን ይመስልሀል?"

"ከእናንተ ጋር ወደ ለንደን መሄድ ነው የምፈልገው" አለ ሰር ሔንሪ። "እዚህ ብቻዬን ምን አደርጋለሁ?"

"እዚህ የመሆን ሃላፊነት ስላለብህ ነው። ትዕዛዜን ለመቀበልም ቃል ስለገባህልኝ እዛህ እንድትቆይ ወስኛለሁ።"

"እንዲያ ከሆነማ - እሺ- እቆ ነለሁ"

"ሌላው ተጨማሪ ነገር ወደ ሜሪፒት ስትሄድ ሰረገላ ተጠቀም። ሰረገላውን ግን መጓለህ ላከው። በእግርህ እንደምትመለስ ገልፀህ ንገራቸው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያንን ምድረ በዳ በፅሞር? ግን እኮ ደጋግመህ ያስጠነቀቅኸኝ ይህን እንዳላደርግ ነበር።"

"በእንተ ደፋርነት ባልተማመን ኖሮ እንደዚህ ባላልከህ ነበር። ደግሞም በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ማድረግ አለብህ።"

"እሺ፤ እንዳልከኝ አደርጋለሁ"

"ለሕይወትህ ዋጋ የምትሰጥ ከሆንክ ከሜሪፒት አዳራሽ እስክ ግሪምፑን ጉዳና የሚወስድውን አውራ መንገድ ይዘህ ካልሆነ በስተቀር በእቋራጭ ለመምጣት እንዳይቃጣህ። ወደ ቤትህ ለመመለስ ትክክለኛው መንገድ እሱ ብቻ ነው።"

"በእውነት እንዳልከኝ አደርጋለሁ።"

በዚህ ፕሮግራም ላልገረም አልቀረሁም። ሆልምስ በሃፊው ዕለት ወደ ለንደን እንደሚመለስ ለስቲፐልተን ቢነገረውም እኔ ከእሱ ጋር ስለመሄዴ የማውቀው ነገር አልነበረም።

እሱ ራሱ በጣም አስጊ ሁኔታ ውስጥ መሆናችንን እየነገረን ሁለታችንም ከአካባቢው ለምን እንደምንጠፋ አልገባኝም። ለማንኛውም ትዕዛዙን መቀበል አለብኝ። ከሁለት ሰዓት በኋላ ኩምቢ ትሬሲ ጣቢያ ስንደርስ የመጣንበትን ሰረገላ እንዲመለስ አደረግነው።

ሆልምስ በጣቢያው በኩል መልእክት ተልኮለት እንደሆነ ሲያጣራ የቴሌግራፍ መልእክት አምጥተው ሰጡት።

"መልእክትህ ለአሥራ ሁለት ሩብ ጉዳይ ደርሷል። ሊስትሬድ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዛሬ ጧት ለላክሁት መልእክት የተሰጠ ምላሽ ነው። ሊስትሬድ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ፖሊስ ነው። የእሱ እገዛ የሚያስፈልገን ይመስለኛል። ዋትሰን፣ ጊዜያችንን ለመጠቀም ሚስዝ ላውራ ሊዮንስን ሄደን ማነጋገር ይኖርብናል።"

የነደፈው የድርጊት መርሐ ግብር ግልፅ እየሆነ መጣ። ሰር ሔንሪን የፊለገው ቀደም ብሎ ሄዶ ሆልምስ ወደ ለንደን መሄዱን ለስቱፐልተን ቤተሰብ ነግሮ እንዲያሳምንለት ነው። እኛ በምንፈልግበት ቅፅበት እዚያ ለመድረስ ቶሎ መመለስ ይኖርብናል።

ሚስዝ ላውራ ሊዮንስን ቤታ ውስጥ ያገኙት ሼርሎክ ሆልምስ እንደደረሰ ንግግሩን ከመጀመር ወደ ኋላ አላለም። በሁኔታው እሷም ተገርማለች።

" ስለ ሰር ቻርለስ ባስከርቪል አሟሟት ጉዳይ ምርመራ እያካሄድኩ ነው። ሰር ቻርለስ ከመናፈሻው በር ላይ ቁሞ እንዲጠብቅሽ ቀጠሮ ሰጥተሽው እንደነበር ቀደም ሲል ታል ሰጥተሻል። ቀጠሮአችሁ በአራት ሰዓት ላይ እንደነበረም አረጋግጠሻል። በዚህ ቦታና ጊዜ መሞቱን አውቀናል። የእነዚህ ድርጊቶችን ግንኙነት ግን ማመን አልፈለግሽም።"

"ምንም ግንኙነት የለውም"

"በጣም የሚገርም ነው። ግለጽ ሆኜ ነው የማናግርሽ ሚስዝ ሊዮንስ። ይኸ ጉዳይ ከነፍስ ግድያ ጋር የተያያዘ ነው። እናም ጓደኛሽን ሚስተር ስቱፐልተንን ብቻ ሳይሆን ባለቤቱንም ጭምር ከመንጀሉ ነፃ ሊያደርግ ይችላል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ወይዘሮዋ ከወንበሯ ላይ ነጥራ ተነሳችና "ባለቤቱ!" ስትል ጮኸች።

"ከአሁን በኋላ ምሥጢርነቱ አብቅቷል። እህት ተብየዋ ባለቤቱ መሆኗ ተረጋግጧል።"

"ባለቤቱ!" አለች ደገመችና። "ባለቤቱ! እሱ እኮ አላገባም። አግብቷል ካልክ ማረጋገጫ ስጠኝ። ይኸን ማድረግ ከቻልክ" የሚያስፈራራው ዓይኗ ከምንም በላይ ስሜቷን ይገልፃል።

"ለዚሁ ጉዳይ ተዘጋጅቼ ነው የመጣሁ" አለ ሆልምስ የተሰያዩ ወረቀቶችን ከኪሱ እያወጣ። "ከአራት ዓመት በፊት ሁለቱም በአንድ ላይ ሆነው ዮርክ ውስጥ የተነሱት ፎቶግራፍ ይኸው።"

ከፎቶግራፉ በስተጀርባ 'ሚስተርና ሚስዝ ቫንድለር ይላል። "ባይፃፍበትም ግን እሱን ሰመለየት አትቸገሪም። የምታውቂያት ከሆነ እሷም ብትሆን አትጠፋሽም። እነዚህ ሦስት የጽሑፍ ማስረጃዎች የባልና ሚስቱ ንብረት በነበረው በቅዱስ አሪቨር የግል ትምህርት ቤት ጠባቂዎች የተፃፉ ናቸው። አንበቢያቸውና ሃሳብሽን ትነግሪኛለሽ።"

ወረቀቶቹን ለማንበብ ጊዜ አልፈጀባትም። ፊቷ ላይ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ይነበባል። "ሚስተር ሆልምስ፤ ይህ ሰው ከባለቤቴ የተፋታሁ መሆኔን አውቆ ጋብቻ ጠይቆኛል። ዋሽቶኛል። አሁን የእሱ የግል ጉዳይ ማስፈፀሚያ እያደረገኝ መሆኑ እየገባኝ ነው። እሱ ታማኝ ላይሆንልኝ እኔ ለእሱ እንዴት ታማኝ ልሆንለት እችላለሁ? እንደዚህ ዓይነት ሥራ


t.me/OLDBOOKSPDF

እየሠራ እንዴት የእሱን ጉድ አሸፍናለሁ? የፈለግኸውን ጠይቀኝ። ሁሉንም እነግርሃለሁ። እውነቱን ነው የምልህ፣ ለሸማግሌው ደብዳቤ ስጽፍለት፣ በእሱ በደጉ አሳውንት ወጻጅ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ያደርሳል ብየ በጭራሽ አላሰብኩም።"

"የምትይኝን ሁሉ አምናለሁ። ይህን ደብዳቤ እንድትልኪለት ሃሳቡን ያመነጨልሽ ራሱ ስቲፐልቲን ነው?"

"አዎ፤ ምን ብየ መዋፍ እንዳለብኝም ነግሮኛል።"

"ከመፋታችሽ ጋር በተያየዘ የሚያስፈልግሽን ገንዘብ ከሰር ቻርለስ ልታገኚ እንደምትችይ ነግሮሻል?"

"ትክክል"

"ደብዳቤውን ከላክሽ በኋላስ በቀጠሮው ሰዓት እንዳትገኚ ያደረገሽ እሱ ነው?"

"አዎ፣ ለዚህ ዓላማ ከሌላ ሰው ገንዘብ ብቀበል የእሱን ክብር መቀነስ እንደሚሆን አስጠንቅቆኛል።"

"ከዚያስ በኋላ፣ ከሰር ቻርለስ ጋር ቀጠሮ ስለመያዝሽ ለማንም እንዳትነግሪ ቃል አላስገባሽም?"

"አስገብቶኛል። ቀጠሮ ያለኝ መሆኔን ከተናገርኩ በእሱ ሞት ጉዳይ ተጠርጣሪ እንደምሆን ነግሮኛል። በመሆኑም ምንም ትንፍሽ እንዳልል አስፈራርቶኛል።"

"ዕድለኛ በመሆንሽ ይመስለኛል አምልጠሻል--። ይኸው አስከአሁን በሕይወት መኖር ችለሻል። ደህና አርፍጅ ሚስዝ ሲዮንስ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጉዳያችን እዚህ ላይ ያበቃል። ከባድ ሽክም ሆኖብን የነበረው ችግር ተቃሏል" አለ ሆልመስ ከኩምቢ ትሬሲ ባቡር ጣቢያ ቆመን ከሱንደን የሚመጣውን ፈጥኖ ደራሽ ባቡር በመጠባበቅ ላይ እያለን። ባቡሩ ከጣቢያው ድርሶ እንደቆመ አንድ አጠር ያለ ፈጣን ሰው ከአንደኛ ማዕረግ ፉርኖ ወጣ። ሦስታችንንም የእጅ ሠላምታ ተለዋወጥን።

"ተልዕኳችንን ለመጀመር ሁለት ሰዓት ብቻ ይቀረናል" አለ ሆልምስ ። "የእራት መብያ ጊዜ ላንሰጣቸው እንችል ይሆናል። ከዚያም ሌስትሬድ፣ በሱንደን ጭስ የተበከለውን ሳምባህን በዳርትሙር የንፁህ አየር ትንፋሽ እናድስልሃለን። መኖተህ አታውቅም አይደል? ትሰማኛለህ? ይህን የዳርትሙር የመጀመሪያ ጉብኝትህን ምንግዜም የምትረሳው አይመስለኝም።"

## ምዕራፍ አሥራ አራት

ስህተት መሆን ያለመሆኑ ባይታወቅም ሸርሎክ ሆልምስ ሥራውን ሠርቶ ከማጠናቀቁ በፊት የዕቅዱን ዝርዝር መረጃ ለማንም ሰው ለመግለጽ አይፈልግም። እንደገና ወደ ኮረብታው እየተጠጋን ስንሄድ ውይይታችን በተከራየነው ሰረገላ አሽከርካሪ ላይ ብቻ የተወሰነ ነበር። ወደ አዳራሹ ከዚያም ወደ ትርኢቱ እየቀረብን መሄዳችን ለእኔ ግልግል ነበር። ከግቢው በር ላይ ስንድርስ ወረድን። ሰረገላው ወደ ኩምቢ ትሬሲ ሲመለስ እኛ ሜሪፒት ወደሚገኘው የስቴፐልተን የመኖሪያ አዳራሽ በዕግር ጉዟችንን ጀመርን።

"የሚቀጥለው ቦታ ነው" አለ ሌስትሬድ ዙሪያውን የከበበውን ኮረብታና ጉም የሸፈነውን የግሪምፒን ረግረጋማ ቦታ እየተመለከተ። "ከፊታችን ካለው ቤት ውስጥ መብራት ይታየኛል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ ወደ ቤቱ የሚያመራውን መንገድ ይዘን ተጓዝን። ቤት ለመድረስ ሁለት መቶ ሜትር ገደማ ሲቀረን ሆልምስ አቆመን።

"ከዚህ አናልፍም" አለ። እነዚህ አሉቶች ጥሩ ከለላ ይሆኑንናል። ሴስትሬድ እዚህ ጉድጓዳ ቦታ ውስጥ ታደፍጣለህ። ዋትሰን፣ እዚህ ቤት ገብተህ ስለምታውቅ የክፍሎቹን አቀማመጥ ታስታወሳለህ። በደረትህ እየተሳብህ ሂድና ምን እንደሚያደርጉ እያቸው። አደራ የምልህ ግን ከትኩል እየተደረገባቸው ስለመሆኑ ምንም እንዳይነቁ—"

እየተሳበክ ሄደ አጠር ካለው ግድግዳ ሥር አገንብስክ። በግድግዳው ጥላ ተከልየ መጋረጃው ባልተጋረደበት መስኮት በኩል በቀጥታ ወደ ምግብ ቤት ማየት የምችልበት አጋጣሚ ተፈጥሮልኛል። ቤት ውስጥ ያሉት ሰር ሐንሪና ስቴፐልተን ብቻ ናቸው።

"ሴትዮዋ የለችም እያልከኝ ነው ዋትሰን?" አለ ሆልምስ ሪፖርት ሳቀርብለት። "ሌላ ክፍል ውስጥ መብራት የለም። ታዲያ የት ልትሆን ትችላለች?"

ታሳቱ የግሪምፐን ረግረግ ባዙቶ በመሰለ ነጭ ጉም መሸፈኑን ቀደም ሲል ገልጫለሁ። ጉሙ በነፋስ ሃይል ወደ እኛ እየመጣ ነበረና ካጠገባችን ሲደርስ እንደ ግንብ ተቆለለ።

"ወደ እኛ እየመጣ ነው ዋትሰን—ብቻ ይህ ነገር ዕቅዴን አንዳያከሽፈው። የእኛ ዕቅድ መሳካት ብቻ አይደለም። የእሱም ሕይወት ጉሙ መንገዱን ከመሸፈኑ በፊት ወደዚህ ከመምጣቱ ጋር የሚወሰን ነው።"

ከላያችን ያለው ሰማይ በዚያ ጨለማ ጥርት ብሎ ይታያል። ከዋክብቱ ባይሞቁም ብልጭ ድርግም እያሉ ማብረቅረቃቸውን አላቋረጡም። ጨረቃዋ ከአድማስ እስከ አድማስ ወገግ ብላ ለስለስ ያለ ብርሃኗን እንካችሁ ብላለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

የኮረብታውን አካባቢ ግማሽ በግማሽ የሸፈነው እንደ ጥጥ ባዙቶ የነጣ ጉም በየደቂቃው ወደ ቤቱ እየተቃረበ ነው። የግቢው አጥር በጉሙ ተከልሏል። ከጉሙ ዘልቀው የሚታዩት ረጃጅሞቹ ዛፎች ብቻ ናቸው። ሆልምስ ተናደ ከፊታችን ያለውን አለት በእጁ መታው። በእግሩም ረገጠው። "በሩብ ሰዓት ውስጥ ካልወጣ መንገዱ በሙሉ ይሸፈናል። ግማሽ ሰዓት ከቆየን እንኳንስ ሌላ ሰው የራሳችንን እጅ ማየት አንችልም።"

"ወደ ኋላ አፈግፍገን ከፍተኛ ቦታ ላይ እንሁን?"

"አዎ ጥሩ ሃሳብ ነው።"

የጉም ባዙቶ ወደ እኛ ሲጥመለመል እኛ ከኋላ ወደ ተለቀቀው ቦታ በመመለስ ከቤቱ ግማሽ ኪሎ ሜትር ያክል ርቀን አደፈጥን።

"በጣም መራቅ የለብንም" አለ ሆልምስ። "እኛ ከመድረሱ በፊት ለመያዝ አይቃጣንም፣ አ--እግዚአብሔር ይመስገን እየመጣ ነው መሰለኝ።"

የፊጣን አርምጃ ኩቴ የኮረብታውን አካባቢ ገምታ ሰበረው። በአለቶች መካከል ተደብቀን ከፊታችን ያለውን የጉም ቁልል እናስተውላለን። ርምጃው ድምፁ እየጨመረ መጣ። የምንፈልገው ሰውም በጉሙ ተከልሎ ሲመጣ ከመጋረጃ የወጣ ይመስላል። የጨረቃዋ ብርሃን ከደመቀበት ቦታ ላይ ሲደርስ ግራና ቀኝ ተመለከተ። ከዚያ በፊጣን ርምጃ እኛ ያለንበትን ቦታ አልፎ ከጀርባችን ያለውን ረጅም አቀበት መውጣት ጀመረ። በተራመደ ቁጥር ወደኋላው እየዞረ ያያል— እንደቀፈፈው ሰው።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይኸውና!" አለ ሆልምስ ድምፁን ከፍ አድርጉ። ጠመንጃውን አቀባበሉ ይሏል። "እየመጣ ነው!"

ከእኛ ሃምሳ ሜትር ያክል ርቆ ከሚገኘው ጉም አካባቢ የሩጫ ድምፅ ይሰማል። እየመጣ ያለው አስፈሪ ነገር ምን እንደሆነ ባናውቅም ዓይናችን ከዚያው አልተነቀለም። ከሆልምስ ጉን ስለነበርኩ ለአፍታ ፊቱን ተመለከትኩት ። ፊቱ ቀልቷል። ዓይኖቹ በጨረቃዋ ብርሃን ያበራሉ። ድንገት ወደፊት ተንቀሳቀሰ። ሌስትሬድ በድንጋጤ ጮኸና በራሱ ሃይል ተወርውሮ መሬት ላይ ሄዶ ተዘረጋ። እኔ ተነስቼ ቆምኩ። ጠመንጃዬን ይዣለሁ። ከጉሙ ተስፈንጥሮ የወጣውን አስፈሪ አካል ላይ በጣም ተገረምኩ። አዳኝ ውሻ ነው—ግዙፍ የሆነ ጥቁር አዳኝ ውሻ። እንደዚህ ዓይነት ውሻ ግን በሰብአዊ ፍጡር ዓይን ታይቶ ይታወቅም። አፉ እሳት ይተፋል፣ ዓይኖቹ ያቃጥላሉ። ጥርሱ የእሳት ነበልባል ይመስላል። ዘግናኝ የሆነ መጥፎ ሕልም ታየ ቢባል እንኳን ከዚያ የጉም ደመና ውስጥ ተውዘግዝጎ ከወጣው አውሬ የከፋ አስፈሪ ሊሆን አይችልም። አስፈሪው ፍጡር በከፍተኛ ዝላይ እኛን አልፎ ሄደ። እኔና ሆልምስ በአንድ ላይ ተኮሰን። ያ አስፈሪ ፍጡር የስቃይ ጩኸት አሰማ። ከሁለት አንዳችን ሳንመታው አልቀረንም። ይሁን እንጂ ወዲያው ተነስቶ ሮጠ። ሰር ሔንሪን መንገድ ላይ ከሩቅ አየነው። ፊቱ በጨረቃዋ ብርሃን ፊክቶ ይታያል። በድንጋጤ እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቷቸዋል። በተስፋ መቁረጥ ስሜት ከኋላው የሚያባርረውን አስፈሪ ነገር እየዞረ ይመለከታል።

ነገር ግን ከአዳኝ ውሻው የሚጠጣው የስቃይ ጩኸት ፍርሃታችንን አቅመው። ማቁለል ከተቻለ መግደል ይቻላል። ከፊታችን ያለውን መንገድ ይዘን ስንበር የሰር ሔንሪን ተከታታይ ጩኸትና የአዳኙን ውሻ የማንጉር ድምፅ ሰማን። አውሬው ዘሎ ሰር ሔንሪን በመጣል ጉሮሮውን ሊይዘው ሲታገል እና እኔ ስደርስ አኩል ሆነ። ወዲያው ሆልምስ በአውሬው ላይ አነጣጥሮ አምስት ጥይቶች አከታትሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተኩሰ። በመጨረሻ የጣዕር ጩኸት አያሰማ በጀርባው ሄዶ ተዘረረ። ከዚያም በጉን ተጋደመ። አጉንብሼ የዕፎይታ ትንፋሽ ከተነፈስኩ በኋላ የጠመንጃዬን አፈሙዝ ከወደቀው አውሬ ላይ ብደትንም መተኩስ ጥቅም እንደሌለው አወቅሁ። ያ አስፈሪ ግዙፍ አውሬ ሞቷል።

ሰር ሔንሪ ራሱን ስቶ እንደወደቀ ነው። ልብሱን አወለቅንለት። ሆልምስ በሔንሪ ሰውነት ላይ ምንም ቁስል ያለመኖሩንና በጊዜው ደርሰን ከአደጋው ያተረፍነው መሆኑን ሲረዳ የምሥጋና ፀሎት አደረሰ። ጓደኛችን ዓይኖቹን እያርገበገበ እንደመንቀሳቀስ አለ። ከዚያ ሁሉቱንም ዓይኖቹን እኛ ላይ ተክሎ፡ "ያንተ ያለህ!" አለ በለሆሳስ። "ምን ነበር? ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ንገሩኝ፤ ምን ነበር የሆንኩት?"

"ምንም ይሁን፤ አዚህ ላይ ያበቃል!" አለ ሆልምስ። "ቤተሰቡን ሲያሸብር የነበረው ርኩስ መንፈስ ጉዳይ ታሪክ ሆኖ ይቀራል። ላይመለስ ተሰናብቷል።"

ያ እጅግ አስፈሪ የሆነ ፍጡር ከፊታችን ተዘርግቷል-ወድቋል። አስፈሪነቱ፤ ሃይለኛነቱና ግዙፍነቱ ከሴት አምበሳ ይወዳደራል። እንዲህ ሞቶም የመንጋጋ ጥርሶቹ ሰማያዊ የእሳት ነበልባል ይመስላሉ። በእሳት የታጠሩ የሚመስሉት ዓይኖቹ አሁንም ያስፈራሉ። እጅን አፋ ላይ አደረግሁት። ከዚያ ያነሳሁትን እጅን ጣቶች ስመለከታቸው በጨለማው ያብረቀርቃሉ።

"ፎስፎረስ!" አልኩኝ። "እንደዚህ የማበለጭለጭ ባሕሪ ያለው ንጥረ ነገር እሱ ነው።"

"እም፤ ብልህ ያዘጋጀው ፎስፎረስ" አለ ሆልምስ። "በእንስሳው ጠረን ላይ ምንም ዓይነት ተፅእኖ አይኖረውም። ሰር ሔንሪ ትልቅ ይቅርታ እንጠይቃለን። እኔ አዳኝ ውሻ ነው አልሁ እንጂ እንደዚህ ዓይነት አውሬ ይሆናል ብየ አልገመትኩም። በዚህ ላይ ጉመ. ደግሞ ፋታ ሊሰጠን



t.me/OLDBOOKSPDF

አልቻለም። እዚህ ጠብቀንና አንዳችን ወደ ቤት እናደርስሃለን።" ወደ ድንጋዩ አስጠግተን አስተመጥነው።

"ሰውየአችንን ቤቱ የምናገኘው አይመስለኝም አለ ሆልምስ። እየተጣደፍን ቀልቁሰቱን በመውረድ ወደዚያው በመጓዝ ላይ እያለን "እነዚያ የተከሱ ድምፆች በጨዋታው የመሸነፋን መርዶ ነግረውት መሆን አለበት። ለማንኛውም ርግጠኛ ለመሆን ቤቱን እንፈትሻለን።"

የፊት ለፊቱ በር ክፍት ስለነበር ዘው ብለን ገባን። ሆልምስ ፋኖስ ይዞ በየክፍሉ እየገባ ፈለገ። የሰው ዳና አላገኘንም። ወደ ፎቅ ስንወጣ አንዱ መኝታ ክፍል ጥርቅም ብሎ ተዘግቷል።

"እዚህ ክፍል ውስጥ የሆነ ሰው አለ!" አለና ሌስትራድ ተጣራ። "እንትስታሲ ይሰማኛል። በሩን ከፈተው!"

ከውስጥ ድክም ያለ ድምፅ ይሰማል። ሌስትራድ ክቱልፉ በላይ ያለውን የበሩን አካል በሃይል ሲመታው በሩ ተገንጠለና ቦግ ብሎ ተከፈተ። ሦስታችንም የጦር መሣሪያችንን በተጠንቀቅ እንደያዝን በአንድ ላይ ዘው ብለን ገባን። ያልጠበቅነውን ነገር አየን። በክፍሉ መካከል ላይ ጣሪያውን ወጥሮ የያዘ ምሰሶ አለ። ወንድ ወይም ሴት መሆኑ የማይታወቅ ሰው ከምሰሶው ጋር ዙሪያውን በተጠመጠመ አንሶላ ታስሯል። አንድ ፎጣ ደግሞ ጉሮሮው ላይ ተጠምጥሞ ከምሰሶው ገር ተቋጥሯል። ከላይ ቢሐዘንና በሐፍረት የተሞሉ ጥቂቱር ዓይኖች ወደ እኛ አፍጥጠው ይመለከታሉ። በደቂቃ ውስጥ ሁሉንም ፈትተን እንደጨረስን ሚስዝ ስቱፐልተን ነፍሷን ስታ ከሥራችን ካለው መለል ላይ ዘፍ አለች። ፊት ለፊት ወድቃ ስለነበር አንገቷ ላይ ያለውን ቀይ የግርፋት ሰንበር አየሁት።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሰይጣን!" አለ ሆልምስ። "ወንበር ላይ አስቀምጣት። ራሷን በደንብ አታውቅም።"

ዓይኖቿን እንደገና ገለጠችና "አምልጧል?" ስትል ጠየቀች።

"ሊያመልጠን አይችልም"

"አይደለም፤ባለቤቴን አይደለም። ሰር ሔንሪ ተርፏል ወይ?"

"አዎ"

"አዳኙ ውሻስ "

"ተገድሏል"

"እግዚአብሔር ይመስገን! ያ አረመኔ እንዴት እንዳደረገኝ ተመልከቱ!" ክንዶቿን አውጥታ ገላዋ ላይ የቀሩትን ጠባሳዎች አሳየችን። "ግን ይኸ ሁሉ ምንም አይደለም! ተቋቁሜዋለሁ። ሁሉንም፡- በደሉን፤ ብቸኝነቱን ሲታሰሉ መኖሩንና ሌላውንም ሁሉ ፍቅሩ እስካለኝ ድረስ ችየዋለሁ። አሁንም ግን እንዳታለለኝና እንደተጠቀመብኝ አውቃለሁ።"

"የት እንደምናገኘው ንገሪና?"

"በረግረጉ መካከል ካለው ደሴት ውስጥ አንድ የጥንት የቆርቆሮ ማዕድን ማውጫ ጉድጓድ አለ። አዳኝ ውሻውን ያስቀመጠው እዚያ ነበር። እሱም እዚያ ተደብቆ ይሆናል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ጉሙ አስካልገለጠ ድረስ ወደዚያ መሄዱ ዋጋ አለነበረውም። ሌስትራድን እዚያው ሜሪፒት አዳራሽ ውስጥ ተውነው። ሰር ሔንሪን ወደባስከርቪል አዳረሽ ወሰድነው። ሌሊት በተፈፀመው የማጥቃት እንቅስቃሴ በድንጋጤ ከደረሰበት ህመም እንዲያገግም በዶክተር ሞርቲመር ሕክምና እየተደረገለት ነው። ከሕመሙ ተፈውሶ የባስከርቪልን አዳራሽ በባለቤትነት ተረክቦ ለማስተዳደር ሰላማዊ የሆነ የደስታ ሕይወት ለመምራት ወራት ሊፈጅበት ይችላል።

አሁን ወደ ታሪኩ መጠናቀቂያ በፍጥነት እየተንገዘገዘ ነው። አዳኝ ውሻው በሞተበት ዕለት ጧት በአካባቢው የነበረው ጉም ጠፍቷል። እኛም በሚስጢ ስቲፓልተን መሪነት ወደረግረጉ የሚወስደውን ቀጭን መንገድ ይዘን መንገዝ ጀምረናል። አልፎ አልፎ የተተከሉት ሽመል መሰል ችካሎች አረንጓዴ በለበሰው አረንቋ የሚያቋርጠውን መንገድ አትጣሒ ይጠቁማሉ። ግማት ግማት ይሸታል። አረንቋው ያረገርጋል። ተሳስተን ያልሆነ ቦታ ላይ ከረገጥን እግራችን አልም ካለ የጭቃ ኩሬ ውስጥ ጥልት ማሉቱ ነው። ስንራመድ የሚውጠውን ያክል ግን እግራችንን ወደላይም ይገፋዋል። አንድ ጊዜ ብቻ ከእኛ በፊት የሆነ ሰው ማለፉን የሚጠቁም ምልክት አገኘን። ጉርብጥብጥ ካለ ሣራማ ቦታ ላይ የሆነ ጥቁር ነገር ተጋድሟል። ሆልምስ ጥቁሩን ነገር ለመያዝ መንገዱን ስቶ በመርገጡ አስከወገቡ ድረስ ሰጠመ። እኔና ሌስትራድ ጉትቱን ባናወጣው ኖሮ ተልጦ መትረቱ ነበር። አንድ አሮጌ ጫማ የያዘበትን እጁን ወደ ላይ አድርጉ አሳየን። በጫማው የውስጥ ቆዳ ላይ "Meyers Toronto" የሚል ታትሞበታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

"የጓደኞችን የሰር ሔንሪ የጠፋው ጫማ ነው። ስቲፕልተን አዳኝ ውሻው በዚህ ጠረን አነፍንፎ እንዲያጠምድለት የተጠቀመበት ስልት ነው። በመጨረሻ እዚህ ወርውሮታል። ቢያንስ እስከዚህ ድረስ መጥቷል ማለት ነው።"

በረግረጉ ላይ ዱካ አልተገኘም። ከረግረጉ ወጥተን መሬት ከረገጥን በኋላ እንኳን የእሱን ዱካ ለማግኘት ነበር የጓጓነው። ያ ክፉ ጨካኝ፣ አረመኔ ሰው በዚያ አረንቋ ውስጥ ተቀብሮ ቀርቷል። በግሪምፐን የጭቃ ባሕር ሆድ ውስጥ ተቀብሯል። በደሴቲቱ ላይ አያሌ የእሱን ምልክቶች አይተናል። የፊራረሰውን የማዕድን ማውጫ ቦታ አግኝተናል። የማዕድን አውጭዎችን የመኖሪያ ቤት ፍርስራሽ ተመልክተናል። በእንዱ ቤት ውስጥ የተቆለለው የአጥንት ክምር አዳኝ ውሻው የት እንደነበር ያመለክታል።

"መልካም" አለ ሆልምስ ። "በዚህ ቦታ ከዚህ የተለየ ተጨማሪ ምሥጢር ይኖራል የሚል ግምት የለኝም። እንስሳውን መደበቅ ይቻላል። ድምፁን ግን ማፈን አይችልም። እነዚያ አሰቃቂ ድምፆች እንኳንስ በሌሊት በቀን ተሰምተዋል። በዚህ ጣሳ ውስጥ ያለው ቀለም ፎስፎረስ ይዘጋጅበት የነበረ ነው። ጥሩ ፊጠራ ነው። እንኳንስ ሳይታይ አይተውት እንኳን ለማመን ስለሚማያስቸገረው አውሬ ማን ደፍሮ ይጠይቃል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

ታኅሣሥ ወር መጀመሪያ ላይ ነው። የሌሊቱ አየር ርጥበታማና ደመናማ ነው። ሆልምስና እኔ ቤከር ጐዳና በሚገኘው ቤታችን በተንገለጠጠው እሳት ዳር ግራና ቀኝ ተቀምጠን እንሞቃለን።

"ከሚስዝ ስቴፕልተን ጋር ሁለት ውይይቶች አድርጌያለሁ" አለ ሆልምስ ።"ጉዳዩ አሁን ግልጽ እየሆነ መጥቷል። ፎቶግራፉ አላበለም። ስቴፕልተን የባስከርቪል ቤተሰብ አባል መሆኑ እውነት ነው። ይህ ሰው አሳፋሪ ተግባር ፈጽሞ ወደ ማዕከላዊ አሜሪካ አምልጦ የገባው፣ የሰር ቻርለስ ታናሽ ወንድም የሮጀር ባስከርቪል ልጅ ነው። ሳያገባ ነው የሞተው ይባል እንደነበር አስታወሳለሁ። ግን አግብቷል። ልጁ የአካባቢው ተወላጅ የሆነች በሪል ጋሪሽያ የምትባል ቆንጆ ኮስታሪካዊት ያገባል። ባል ሆየ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ገንዘብ ይዘርፍና ስሙን ወደ ቫንዳለዩር ለውጦ እንግሊዝ አገር ይገባል። ከዚያም ዮርክሻየር ውስጥ ትምህርት ቤት ይከፍታል። ትምህርት ቤቱ ግን ዕውቅና የነበራቸውን የአካባቢውን የትምህርት ባለሙያ በሞት ካጣ በኋላ ገዘናው እየወረደ ይመጣል። በመጨረሻም ይዘጋል። የቫንዳሊዩር ቤተሰብ ስምም ወደ ስቴፕልተን ይቀየራል። በዚህም ብቻ ሳይወሰን ባልና ሚስት ወንድምና እህት ነን ይላሉ። ያስመስላሉ። ስቴፕልተን ቀሪውን ሃብቱንና የተፈጥሮ ሳይንስ ክህሎቱን ይዞ ወደ ደቡባዊው የእንግሊዝ ክፍለ ሀገር ይጓዛል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የመጀመሪያው ዕቅዱ በቤተሰቦቹ ቤት አካባቢ ለመስፈር ሲሆን፣ ሁለተኛው ከሰር ቻርለስ ባስከርቪል ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ነበር። ሽማግሌው አጐቱ የልብ ድካም እንዳለበት ስቴፐልተን ከዶክተር ሞርቲመር ለመረዳት ችሏል። በቀላል ድንጋጤ ሊሞት እንደሚችልም አውቋል። ሰር ቻርለስ ስለ አዳኙ ውሻ ለሚወራው ታሪክ ክብደት እንደሚሰጥም ተገንዝቧል። በመሆኑም ወንጀሉ በማይታወቅበት ሁኔታ ግድያ ለመፈፀም አሴረ። ለዚህም ለንደን ውስጥ በአስፈሪነቱና በሃይለኛነቱ ወደር የለውም የሚለውን ውሻ ገዛ። ነፍሳት ሲያድን በነበረበት አጋጣሚ ረግረጉን እንዴት እንደሚያቋርጥ ትምህርት ወስዷል። እናም ውሻውን ደብቆ የሚያኖርበት ቦታ አግኝቷል። ሽማግሌውን በጨለማ ለማግኘት ግን ቀላል አልነበረም። በጨለማ ከግቢው ርቆ አይሄድም። ስቴፐልተን ሚስቱ እንደምትተባበረው ተስፋ አድርጐ ነበር። እሷ ግን በዚህ ጉዳይ ለመተባበር ፈቃደኛ አልሆነችም። ጥላቻም ሆነ ዱላ ሊበግሯት አልቻሉም።

ከዚያ ሰር ቻርለስ ሚስዝ ላውራ ሊዮንስን በማገዝ ረገድ እንዲተባበረው ስቴፐልተንን ይጠይቀዋል። አላገባሁም የሚለው ሚስተር ስቴፐልተንም ስምምነቱን ይገልፃል። ከእሷ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም ነበርና እንደተፋታች የሚያገባት መሆኑን ቃል ይገባላታል። ሳይታሰብ ሰር ቻርለስ ወደ ለንደን የሚሄድ መሆኑን ይሰማል። ፈጣን ርምጃ ለመውሰድም ይጠስናል። በመሆኑም ወደ ለንደን ከመሄዱ በፊት ልታገኘው እንደምትፈልግ ገልጻ ደብዳቤ እንድትጽፍለት ሚስዝ ሊዮንስን ያሳምንና በተጠሮው ቀን እንዳትገኝ ያግባባታል። ይህም ያሰበውን ለማሳካት መልካም አጋጣሚ ፈጠረለት።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከለንደን የገዛውን ውሻ ከፎስፎረስ በተቀመመ ኬሚካል አትልሞታል። ይህ አስፈሪና ግዙፍ ውሻ መናፈሻው በር ላይ ቆሞ ሚስዝ ሲዮንስን ይጠብቅ በነበረው ሰር ቻርለስ ላይ እንዲዘምት ነው የተደረገ። በዚያ አረንጓዴ መናፈሻ ጥቁር ግዙፍ አውሬ አሳት ለብሶ አሳት ጉርሶ ሲመጣ ማየት እጅግ ያስቅቃል። ሰር ቻርለስ የሚያደርገውን ቢያጣ ወደ ግቢው ላይሆን ወደ መናፈሻው ጫፍ እየሮጠ ሄዶ በአፍጢሙ ተደፋ። ድንጋጤ ባናወጠው የልብ ድካም ሕይወቱ አለፈ። አዳኙ ውሻ በአፋጣኝ ወደ ረግረጉ እንዲመለስ ነው የተደረገው። በመሆኑም የጉዳዩን ምንነት አጣርቶ በማወቅ ክስ ለመመሥረት አልተቻለም። ማስረጃ የለም። ሁለቱም ሴቶች ስቴፐልተን ስለመሆኑ ተጠራጥረዋል። ሁለቱም ግን በእሱ ቁጥጥር ስር ስለነበሩ ምንም የሚያስፈራው ነገር አልነበረም። ከዚህ ሁሉ በኋላ ሰር ሔንሪ ከውጭ አገር የማመጣ ስለመሆኑ ዶክተር ሞርቲመር ለስቴፐልተን በገዘርገር ይነግረዋል። የስቴፐልተን የመጀመሪያ ዕቅድ ሰር ሔንሪ ወደ ዳርትሙር ከመምጣቱ በፊት እዚያው ለንደን ውስጥ ለመግደል ነበር። ሰር ቻርለስን በማጥመድ ሥራ እንድትተባበረው ጠይቂት እምቢ ካለችው ወዲህ ባለቤቱን በዓይነ ቁራኛ ነበር የሚጠብቃት። እናም ወደ ለንደን ከእሱ ጋር ይሂት ሄዶ ባረፈችበት ሆቴል ክፍል ውስጥ ቆለፈባት። እሱ ግን የውሸት ዒም አድርጎ ዶክተር ሞርቲመር በሄደበት ሁሉ ይከታተለው ነበር። መጀመሪያ ቤከር ጉዳና፣ ቀጥሎም ዋተርሉ ባቡር ጣቢያ፣ ከዚያም ናርዝ አምበርላንድ ሆቴል የክትትሉ ቀጠናዎች ነበሩ። ባለቤቱ በአደጋ ቀለበት ውስጥ የገባውን ሰው ቀድማ ለማስጠንቀቅ አልደፈረችም። በመጨረሻ ግን መልእክት ማስተላለፍ የሚችሉ ቃላት ከወረቀት ላይ ቆርጣ በማውጣት ለሰር ሔንሪ ላከችለት።



t.me/OLDBOOKSPDF

ስቴፐልተን አዳኙ ውሻ የሰር ሔንሪን ጠረን አነፍንፎ መከታተል እንዲችል የራሱ የሆነ ዕቃ ማግኘት ነበረበት። አዲሱ ጫማ ገና ስላልተደረገና ለዚህ ዓላማ እንደማይውል ስለታወቀ ከስርቆት ተመለሰ። በእሱ ፋንታ የሔንሪ ጠረን ያለበት አሮጌው ጫማ ተሰረቀ። ይህም በትክክል ከአዳኙ ውሻ ጋር እየተፋጠጥን ስለመሆኑ አመላካች ነበር። እንደዚህ ያልተለመዱና ምንም ስሜት የሚሰጡ የማይመስሉ ነገሮች የቅርብ ክትትል ያስፈልጋቸዋል ዋትሰን። እንድን ጉዳይ ለማወሳሰብ የተተበተበን ነገር በሳይንሰዊ ምርመራ ድሩን በጣጥሶ ደባውን ማጋለጥ ይቻላል።

ከዚያ በቀጣዩ ቀን ማለዳ ጓደኞቻችን እኛን ለመገብኘት ሲመጡ ስቴፐልተን ተከትሏቸው ነበር። ጉዳዩን ለፖሊስ ያመለክትክ መሆኔን ሲረዳና እንዳልተሳካለት ሲያውቅ ወደ ዳርትሙር ተመለሰ።

የታተመ ታሳት የተለጠፉበትን ወረቀት ስመረምር በቀላሉ አይቼ ለየሁት። ጠረኑን አሽተቼ የሴት እጅ እንዳረፈበት ገመትሁኝ። አሁን ሃሳቤ ሁሉ ወደ ስቴፐልተን ቤተሰብ መንገዘ ጀመረ። ስለ አዳኙ ውሻ መኖርም እርግጠኛ ስለነበርኩ ገና ወደ ዳርትሙር ከመሄዳችን በፊት ወንደለኛው ማን ሊሆን እንደሚችል ጠርጥሬአለሁ።

ስቴፐልተንን በትርብ መከታተል ነበረብኝ። ከእናንተ ጋር ብሆን ኖሮ ይህንን ማድረግ አልችልም ነበር። ምክንያቱም እሱ ሊጠራጠር ይችላል የሚል ፍራቻ ስለነበር ነው። በመሆኑም አንተን ጨምሮ ሁላችሁንም ማታለልና የህቡዕ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሥራ መሥራት ነበረብኝ። ሎንዶን መሆኔ እየተወራ በምሥጢር ወደዚህ መጣሁ። ኩምቢ ትራሲ አርፌ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ነበር ጋራው ላይ እየወጣሁ በጉጉው ውስጥ የምጠለለው። ሪፖርቶችህ ፈጥነው ነበር የሚደርሱኝ። ከቤከር ጉዳና እኔ ወዳለሁበት ወደ ኩምቢ ትራሲ ነበር የሚላኩልኝ። በጣም ነው የጠቀመኝ። በተሰይ ስለ ስቴፐልተን ቀደምት ሕይወት የተጻፈው። አሁን ስለእነሱ ማንነት አውቂያለሁ። ያመለጠው አሥረኛና ከባሪሞር ቤተሰብ ጋር ያለው ግንኙነት ጉዳዩን አወሳስቦት ነበር። ግን ነገሩን በተሳካ ሁኔታ ግልፅ አድርገኸዋል።

አንተና እኔ አምባው ላይ በተገናኘንበት ጊዜ ስለ ሁሉም ነገር አውቅ ነበር። ያም ሆኖ ወደ ፍርድ ቤት ሊተርብ የሚችል የከሰ ማስረጃ አልነበረኝም። ያን ዕለት ሴሲት ምስኪኑን ያመለጠ አሥረኛ ለሞት ያበቃውና በሰር ሔንሪ ላይ የተቃጣው የግድያ መከራ እንኳን እምብዛም ለማስረጃነት አይበቃም። ስቴፐልተንን እጅ ከፍንጅ መያዝ ነበረብን። ሚስዝ ስቴፐልተን ባለቤቷን አሳልፋ ሳትሰጥ ለሰር ሔንሪ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ሞክራለች። ስቴፓልተን የቅናት ስሜት ያደረበት ይመስላል። ያም ሆኖ ግን ሰር ሔንሪ ሜሪ ፒት ወዳለው ቤታቸው አዘውትሮ እየሄደ እንዲጠይቃቸው ለማድረግ ሲል ወዳጅነቱን እንዲያጠናክር ነበር የሚገፋፋው። ከዕለታት አንድ ቀን ምሯቱ እንደሚሳካ ያውቃል። ባለቤቱ ግን ስለ አሥረኛው ሞት የሰማችው ነገር አለ። አሁንም ሌላ መንጀል ለመሥራት ስለማቀዱ ከሳዋለች። ይህም ቁጣን አስከትሏል። ከዚህም የተነሳ ለመጀመሪያ ጊዜ ሌላ ፍትረኛ እንዳለው ፍንጭ አሳይቷል። የባለቤቱ የሚስዝ ስቴፐልተን ፍትር እና ታማኝነት ወደ መራር ጥላቻ ስለተቀየረ አሳልፋ እንደምትሰጠው ተረዳ። እናም ለሰር ሔንሪ ማስጠንቀቂያ እንዳትሰጠው ለመከላከል ሲል እሷን ከምሰሶ ጋር ጠፍሮ አሠራት።



t.me/OLDBOOKSPDF

የሰር ሔንሪ ሞት የቤተሰቡ ርግማን ውጤት መሆኑን የአካባቢው ሕብረተሰብ መቀበሉን ስትረዳ የምታውቀውን ምሥጢር ደብቃ አርፋ ትቀመጣለች ብሎ ነበር ያሰበው። የተሳሳተ ይመስለኛል። የስፖኝ ደም ያላት ሴት ቂሚን በቀላሉ አትረሳም።

ውድ ዋትሰን፤ የአሁኑን ምሽት ትኩረታችንን ወደ መዝናናቱ ብንመልሰው ሳይሻል አይቀርም። የትያትር ትኬት ገዝቻለሁ። ስለዚህ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ተዘጋጅና ዕግረ መንገዳችንን ማርጂኒ ሪስቶራንት ራት በልተን ወደ ትያትር ቤት አንድንገባ መልካም ፈቃድህን እጠይቃለሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# የወጣቷ ቢስክሌተኛ ፈተና

ከ1894 እስከ 1901 ያሉት ዓመታት ሼርሎክ ሆልምስ በሥራ ብዛት በጣም ተወጥሮ የነበረባቸው ነበሩ። በእነዚህ ስምንት ዓመታት በአማካሪነት ያልሠራባቸው ማሕበራዊ ጉዳዮች አልነበሩም። ብዙ የተለያየ ባሕሪ ያላቸው ውስብስብ ችግሮችን በመፍታት ትልቅ ሚና ተጫውታል። በዚህ ተከታታይ በሆነ የሥራ ውጣ ውረድ ውስጥ አያሌ ስኬቶችንና ጥቂት የሚባሉ ሽንፈቶችን አስተናግዷል። ሥራውን የማውቀው ቢሆንም የተለያዩ ጉዳዮችን ሪፖርት ማጠናቀርና ለየትኛው ጉዳይ ቅድሚያ መሠጠት እንዳለበት መለየት ቀላል አልነበረም። ነባሩን መመሪያ በመከተል ከመንጀሉ ክበደት ይልቅ ችግሩን ለመፍታት ለሚጠይቀው ብልሀትና ተውኔታዊ ፈጠራ ቅድሚያ እንዲሰጥ አሻለሁ። በዚህም መሠረት ወይዘሪት ቫዮሌት ስሚዝን የሚመለከተውን ጉዳይ ለእንባቢያን አቅርቤያለሁ። የቻሊንግተኟ ቢስክሌተኛ ወይዘሪት ቫዮሌት ስሚዝ የታሪኩ ምስሶ ናት።

የ1895 ማስታወሻዬን ስመለከት ስለ ወይዘሪት ቫዮሌት ስሚዝ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማነው ኤፕሪል 23 ቀን፣ በዕለተ ቅዳሜ ነበር። ሆልምስ ለእሷ የነበረው አቀባበል ጥሩ እንዳልነበረ አስታውሳለሁ። ለዚህም ዋናው ምክንያት ጆን ቪንሰንት ሐርደን የተባለ ሐብታም የሲጋራ ነጋዴ ግድያ ጋር ቡተያያዘ እጅግ አስቸጋሪና ውስብስብ በሆነ የምርመራ ሥራ ተጠምዶ ስለነበር ነው። ተጨባጭ መረጃ ማጠናቀርን ከሁሉም አብልጦ የሚወደው ጓደኛዬ የጀመረውን ሥራ የሚያቋርጥና ሃሳቡን የሚበትን ነገር ጣልቃ ሲገባበት አይወድም። ለቆንጆዋ ወጣት ያላየው ትሕትና ግን ከእሱ ተፈጥሮ ውጭ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘለግ ብላ፣ ንግሥታዊ ግርማ ሞገስ የተላበሰችው ወጣት በሌሊት ቤከር ጉዳና ድረስ መጥታ ዕርዳታ እንዲያደረግላትና ምክር እንዲለግሳት ስትማህነው ልቡ እንቢ ሊላት አልፈቀደም። የመጣችበትን ጉዳይ ሳታስረዳ ላለመውጣት ቆርጣ የመጣችን ወጣት ሥራ በዛ ብሎ መመለስ የማይቻል ነበር። ለሥራው ፋታ ሰጥቶ እየጨነቀውም ቢሆን ፊገግ አለና ቁንጅየዋን ወጣት ችግሯን ተቀምጣ እንድታስረዳው ጠየቃት።

"የጤና ጉዳይ እንዳልሆነ እገምታለሁ" አላት ዓይኖቹን ከእሷ ላይ ሳያነሳ። "እንደ አንቺ ዓይነት ቢስክሌተኛ ለመሆን ጥንካሬን ይጠይቃል።"

በመገረም ጉንበስ ብላ ዕግሮቿን ተመለከተች። እኔም ከቢስክሌቱ መረገጫ ጋር በተፈጠረው ስብቀት በመጠኑም ቢሆን የሻከረውን የውስጥ ዕግሯን ዳርና ዳር አስተዋልኩት።

"ሚስተር ሆልምስ፣ ጥሩ ቢስክሌት ጋላቢ ነኝ። ዛሬ ወዳንተ የመጣሁትም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ነው።"

ጓደኛዬ ጓንት ያልሸፈነውን የልጅቷን እጅ ትኩር አድርጎ እያየ መረመረው---።

"ሥራዬ ስለሆነ ይቅርታ እንደምታደርጊልኝ አልጠራጠርም" አላት እጇን ከእጁ ውስጥ እያወጣ። "ጽሕፈት መኪና ላይ ትሠሪያለሽ በሚል ግምት ስህተት ላይ ልወድቅ ነበር። በእርግጠኛነት ግን የመዚቃ መሣሪያ እንደምትጫወቺ ተረዳሁ። በሁለቱም ባለመያዎች ላይ የሚታየውን የጣት ላይ ምልክት ተለየዋለህ ዋትሰን? ፊት ላይ መንፈላዊነት ይነበባል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ረጋ ብሎ ወደ ብረሃኑ እንድትዞር አደረጋት---። "ጽሕፈት መኪና ላይ የምትሠራ ሴት የመንፈሳዊነት ገጽታ አይታይባትም---ይቺ ልጅ መዘቀኛ ናት።"

"አም፣ ሚስተር ሆልምስ። መዚቃ አስተምራለሁ።"

"ከሁኔታሽ ከከተማ ውጭ የምትሠሪ ይመስለኛል።"

"ትክክል ነው። በሱሪይ ጠረፍ ፋርንሐም አጠገብ።"

"---ታስታውሳለህ ዋትሰን? ስነድ አጭበርብሮ (ፎርጅድ) በመሥራት የሚታወቀውን አርቺ ስተምፎርድን ካመጣንበት አካባቢ ነው። አሁን ደግሞ ወደዘረተ ባህሉት መጣች። በሱሪይ ጠረፍ፣ ፋርንሐም አካባቢ ሣን ላይ የተፈፀመው ነገር ምንድነው?"

ወጣቷ ከሩዳ ግልጽ በሆነና ስሜት በሚስብ የአነጋገር ለዛ የሚከተለውን ተናገረች።

"አባቴ ሞጂል ሚስተር ሆልምስ። ጀምስ ስሚዝ ይባላል። የቀድሞው የቤተ መንግሥት ትያትር ቤት አር ኬስትራ ሃላፊ ነበር። እኔና እናቴ ከአንድ ራልፍ ስሚዝ ከሚባል አገር በስተቀር ምንም ዘመድ የለንም። ከእሱም ጋር ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት ወደ አፍሪካ ከሄደበት ጊዜ ጀምሮ ተገናኝተን አናውቅም። አባቴ ሲሞት ድህነታችንን ይዘን ቀረን። ነገር ግን በታይም ጋዜጣ ላይ የእኛን አድራሻ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚጠይቅ ማስታወቂያ መውጣቱን ሰማን። ይህን ስንሰማ እንዴት እንደተደሰትን መገመት አያቅትህም። የሆነ ሰው ሃብት አውርሶናል የሚል ተስፋ በውስጣችን ስላደረ ነው። ቶሎ ብለን ስመ ጌጋዜጣው ላይ ወደ ተጠቀሰው ጠበቃ አመራን። እዘያም ሁለት ሰዎች አገኘን። ሚስተር ካሩተርስና ሚስተር ውድሌይ ይባላሉ። ከደቡብ አፍሪካ ወደዚህ ለጉብኝት የመጡ ናቸው። አጐቴ ጓደኞቸው እንደነበረና ከጥቂት ወራት በፊት አጥቶ ነጥቶ እንደሞተ ነው የሚናገሩት። በመቀጠልም በሞት አፋፍ ላይ በነበረበት ሰዓት ዘመዶቹን እንዲፈልጉለትና ምንም የማይፈልጉ ስለመሆናቸው እንዲያጣሩ የጠየቃቸው መሆኑን ገልጸውልኛል። በሕይወት እያለ ያላስታወሰን አጐታችን፣ ሚስተር ራልፍ ሲሞት እንዴት ሊያስብልን እንደቻለ ለእኛም ግራ ገብቶናል። ሚስተር ካሩተርስ ደግሞ የሚለው የወንድሙን መሞት የሰማው በቅርብ ጊዜ ስለነበር እኛን የመንከባከብ ሃላፊነቱ በእሱ ላይ እንደሚወድቅ ስለተገነዘበ ነው።"

"ይቅርታ" አለ ሆልምስ "ጥያቄና መልሱ የተካሄደው መቼ ነበር?"

"ባለፈው ታኅሣሥ፣ ከአራት ወራት በፊት"

"እሺ- ቀጥይ"

"ሚስተር ውድሌይ በጣም አስጠሊታ ሰው ነው። ዓይኑን ከእኔ ላይ ጥሏል። ፂመ ቀይ፣ መልኩ አስቀያሚ ነው። ከእንደ እሱ ዓይነት ሰው ጋር እንድተዋወቅ ሳይሪል እንደማይፈቅድልኝ በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እ፣ሳይራል ነው ስመ፲" አለ ሆልምስ እንደመሳቅ እያለ። ልጅቷ ፊቷ በሐፍረት እየቀላ ሳቀች።

"እም፣ሚስተር ሆልምስ። ሳይራል ሞርተን ይባላል። የኤሌክትሪክ መሐንዲስ ነው። በያዝነው ዓመት መገባደጃ ላይ ለመጋባት አስበናል። ግን ስለ እሱ ይኸን ሁሉ ምን አናገረኝ? ስለ ሚስተር ውድ ሌይ አስቀያሚነት ነበር መናገር የፈለግሁት። ከእሱ ይልቅ በእድሜው ጠና ያለው ሚስተር ካሩተርስ ይሻላል። ጠየም ያለ፣ ጸ.ሙን በደንብ የተላጨና ትዕግሥተኛ ሰው ነው። ትሁትና ፈገግታው ማራኪ ነው። የቤተሰባችንን ታሪክ ስለተረዳና ድህነታችንን ስላወቀ የአሥር ዓመት ብቸኛ ልጅን መዚቃ እንዳስተምርለት ጠየቀኝ። ከእናቱ ተለይቼ መሄድ እንደማልፈልግ ነገርኩት። እሱ ግን በየሳምንቱ እየመጣሁ መጠየቅ እንደምችልና አንድ መቶ ፖውንድ በዓመት እንደሚከፍለኝ ገልፆ ነገረኝ። ክፍያው ቀንጅ ሆኖ ስላገኘሁት ስምምነቱን ገልጨ ከሩርንሐም ስድስት ማይል ያክል ርቆ ወደሚኘው ወደ ቺልተርን ግራንጌ አመራሁ። ሚስተር ካሩተርስ ሚስቱ ሞታበታለች። ግን ቤቱን፣ ሐብቱንና ንብረቱን የምታስተዳድርለት ሚስዝ ዲክሰን የምትባል ጠና ያለች ሠራተኛ ቀጥሯል። ሕዛኒ በጣም ደስ የምትልና በትምህርቷም ንበዝ ናት። ሚስተር ካሩተርስ እጅግ ደግና ተጫዋች ሰው ነው። ጥሩ ምሽቶችን አብረን አሳልፈናል። በየሳምንቱ መጨረሻ እናቱን ለመጠየቅ ወደ ከተማ እመጣለሁ።

"ባለቀይ ዓ.መ. ሰውየ፣ ስተር ውድሌይ ሲመጣ የነበረኝ የደስታ ስሜት በሃዘን ተበረዘ። ለአንድ ሣምንት ንብኚት ነበር የመጣው። ለእኔ ግን ሦስት ወር ነው የሆነብኝ። ለማንም ሰው አስቸጋሪና አስፈሪ ቢሆንም ለእኔ ግን ከሁሉም የከፋ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከእኔ ፍቅር እንደያዘው በመግለጽ ግግም አለብኝ ። በሃብቱ ጉራውን ይነሩል። እሱን ካገባሁ ሎንዶን ውስጥ ተወዳዳሪ በማይገኝለት የአልማዝ ጌጣጌጥ እንደሚያንቆጠቁጠኝ ይናገራል። በመጨረሻ ከእኔ ምንም ምላሽ ሲያጣ አንድ ቀን ከእራት በኋላ፣ በዚያ ፈርጣማ እጁ እጅን ጨምድዶ ይዞ ካልሳምኩት በስተቀር እንደማይለቀኝ መሃላውን ይደረድር ጀመር። ሚስተር ካሩተርስ ደርሶ እጁን መንጭቆ አስለቀቀኝ። በዚህም ተናዶ ሚስተር ካሩተርስን ፊቱ ላይ በቡጢ ነርቶ ጣለው። ዳግም ለጥየቃ አልተመለሰም። ሥራውን ያውቃልና። በሚቀጥለው ቀን ሚስተር ካሩተርስ ይቅርታ ጠየቀኝ። መደፈትም ለእንደዚህ ዓይነት አሳፋሪ ሁኔታ እንደማልጋለጥ አረጋገጠልኝ። ከዚያን ቀን ጀምሮ ሚስተር ውድሌይን አይቼው አላውቅም።

"ሚስተር ሆልምስ፣ አሁን ወዳንተ የመጣሁት የአንተን ምክር የሚጠይቅ የተለየ ጉዳይ ስላጋጠመኝ ነው። እንደነገርከህ በየሳምንቱ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ሩርነሐም ባቡር ጣቢያ ድረስ በቢስክሌት እየተንገዘብ በ6፡22 የሚነሳውን ባቡር ይዤ ወደ ከተማ እመጣለሁ። ከቺልተርን ግራንጌ ወደ ጣቢያው የሚመስደው መንገድ በጣም ጭር ያለ ነው። በተለይ ደግሞ የቻርሲንግተን ሜዳ በአንድ በኩል፣ ጥቅጥቅ ያለው ቁጥቋጦ ደን በሌላ በኩል ያለበትን የአንድ ማይል ርቀት መንገድ ይዘህ ስትንገዘ አካባቢው ሆኖ ረጭ ያለ ነው። በዕግርም ሆነ በጋሪ የሰው ዘር ዝር ሲል አይታይም። ወደ ክሩስበሪ ዳገት እስክምትጠጋ የተሻለ ሁኔታ አታይም። የሰው ያለህ ያሰኛል። ከሁለት ሳምንታት በፊት በዚሁ መንገድ ላይ በመንዘ ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

እያለሁ ወደ ኋላየ ዞር ብየ ተመለከትኩ። ከኋላየ አንድ መቶ ሜትር ርቀት ላይ አንድ ሰው በቢስኪሌት ሆኖ ሲመጣ አየሁት። የሚመ· ጠንር አጠር ብሎ ጥቁር ሲሆን እድሜው መካከለኛ ይመስላል። ፋርንሐም ከመድረሴ በፊት ዞር ብየ ስመለከት ሰውየው አልነበረም። እኔም ስለ እሱ ማሰቤን ተውኩት። የሚገርመው ግን ሚስተር ሆልምስ፣ ሰኞ ተመልሼ ስመጣ ያንኑ ሰው እዚያው መንገድ ላይ አየሁት። በቀጣዩ ቅዳሜና ሰኞም ተመሳሳይ ሁኔታ ገጠመኝ። ሁልጊዜም ርቀቱን ጠብቆ ነው የሚነዳው። በእርግጥ አላስቸገረኝም። ሁኔታው ግን ያልተለመደ ስለሆነ ያሳስባል። ስለ ጉዳዩ ለሚስተር ካሩተርስ ነገርኩት ። እሱም የጉዳዩን አሳሳቢነት ተረድቶ ይመስለኛል ወደፊት በዚህ ሰው አልባ መንገድ ላይ ብቻየን መሄድ እንደሌለብኝና ሁኔታውን የሚከታተል ሰው እስክንጋራው እንዲመደብ ትዕዛዝ መስጠቱን ነገረኝ።

"እጃቢው ባለጋሪ በዚህ ሣምንት ይመጣል ተብሎ ነበር የሚጠበቀው። ይሁን እንጂ አልመጣም። ሰምን እንዳልመጣም አይታወቅም። እኔም ያው እንደተሰመደው በቢስክሌት ወደ ባቡር ጣቢያ መሄድ ነበረብኝ። ዛሬ ጧት ቢስኪሌቱን እየነዳሁ ቻርለንግቱን ሜዳ ስደርስ፣ ከሁለት ሳምንታት በፊት ይከተሰኝ የነበረው ሰውየ አሁንም ተከትሎኛል። መልኩን አይቼ ማንነቱን እንዳለየው ከእኔ አንድ ኪሎ ሜትር ያክል ርቆ ነው የሚያሽከረክረው። ፊቱ ላይ የሚታየኝ ነገር ቢኖር ጥቁር ፂመ· ነው። በእርግጥ እኔ የማውቀው ሰው አይደለም። ጥቁር መሉ ልብስ ለብሶ የጨርቅ ክዳያ አድርጓል። ዛሬ ብዙም አልደነገጥሁም እንዲያውም የሰውየውን ማንነትና ምን እንደሚፈልግ ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አደረብኝ። የቢስኪሌቴን ፍጥነት ስቀንስ እሱም ቀነሰ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከነጭራሹም አቆምኩት። እሱም መንዳቱን አቆመ። ከዚያ አድፍጬ ልጠብቀው አሰብኩ። ከባድ የመጠምዘግዘግ መንገድ ላይ ስደርስ በፍጥነት ነዳሁና ኩርባውን እንደጨረስኩ አቆምኩ። እኔ እንዳደረግሁት በፍጥነት ነድቶ በቆምኩበት አልፎኝ ሊሄድ ይችላል ብየ ነበር ያሰብኩት። እሱ ጭራሽ አልመጣም። ወደ ኋላ ተመልሼ የመጠምዘግዘግ ማዕዘኑን አካባቢ ስቃኝ በአካባቢው ማንም የለም። ድራሹ ጠፍቷል። የሚገርመው ደግሞ በአካባቢው ከዋናው መንገድ የሚገነጠል መጋቢ መንገድ የለም። በዚህ ወይም በዚያ መንገድ ሄደ ለማለት የሚያስችል ሁኔታም አልነበረም።"

ሆልምስ እንደመሳቅ አለና መዳፎቹን አፋተገ። "ይኸ ጉዳይ መቼም ራሱን የቻለ አንድ ተልዕኮ ይኖረዋል" አለ። "ለመሆኑ ማዕዘኑን ሀረሽ ምንም ሰው ያለመኖሩን ለማረጋገጥ ስንት ጊዜ ፈጀብሽ?"

"ሁለት ወይም ሦስት ደቂቃ"

"ስለዚህ በአንዱ ወይም በሌላው በኩል በአግር መንገድ ሄዶ ሊሆን ይችላል።"

"በሚዳው ሊሆን አይችልም። በዚያ ቢሄድ አየው ነበር"

"ከዚህ የምንረዳው ሰውየው የቻርሊንግተን ሕንፃ ያለበትን አቅጣጫ ተከትሎ ሄዲል ማለት ነው። ሕንፃው ከመንገዱ በአንደኛው ጉን በኩል ነው። ሌላስ የምትይው ነገር አለ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያንተን ምክር ካላገኘሁ በስተቀር የልቤ አይደርስም ከማለት በስተቀር ሌላ የምለው የለኝም::"

ሆልምስ ለጥቂት ደቂቃዎች ዞር ብሎ ከቆየ በኋላ፡- "ሎፍሽ የት ነው የሚኖረው?" ሲል ጠየቃት::

"ክቬንትሪ በሚባል ቦታ ሚድላንድ የኤሌክትሪክ ኩባንያ ውስጥ ይሠራል"

"ድንገተኛ ጉብኝት ሊያደርግ አይችልም ትያለሽ?"

"አይ ሚስተር ሆልምስ! አዲስ እኮ አይደለንም!"

"ሌሎች አድናቂዎችስ አሉሽ?"

"ሳይሪልን ከማውቁ በፊት አያሌ ነበሩ::"

"ከዚያ ወዲህስ?"

"አድናቂ ነው ኩባለ፣ ያ አስቀያሚ ፣ ውድሌይም አለ::"

"ሌላስ የለም?"

አስተዋይዋ ደንበኛችን ትንሽ ግራ እንደመጋባት አለች::

"ማነው?" ሲል ሆልምስ ጠየቃት

"የራሴ ግምት ቢሆንም አሠሪየ ሚስተር ካሩተርስ ለእኔ ከፍተኛ ጉጉት ያለው ይመስላል:: ሁለታችንም ግን በሥራ ተወጥረናል:: ማታ ማታ ጓደኞቹን አስተናግድለታለሁ:: አንድም ነገር ብሎኝ አያውቅም :: ፍፁም ጨዋ ሰው ነው:: ግን ሴት ልጅ ሁልጊዜም የወንድን ስሜት ታውቃለች::"



t.me/OLDBOOKSPDF

"አሃ!" አለ ሆልምስ ኮስተር ብሎ። "በምንድነው የሚተዳደር?"

"ሃብታም ነው"

"ሠረገላ ወይም ፈረስ የለውም?"

"ቢሆንም መካከለኛ ቱጃር የሚባል ነው። በሳምንት ሁለቴ ወይም ሦስቴ ግን ወደ ከተማ ይሄዳል። ለደበብ አፍሪካ የወርቅ ማዕድናት አክስዮኖች ትልቅ ግምት ይሠጣል።"

"ሚስ ስሚዝ አዲስ ነገር ሲናር ትነግሪኛለሽ። አሁን በጣም ሥራ በዝቶብኛል። በአንቺ ጉዳይ ላይ ምርመራ ለማድረግ አመቺ ጊዜ አፈልጋለሁ። እስከዚያው እኔን ሳታሳውቂ ምንም ርምጃ እንዳትወስጂ። ደህና ሁኚ። ከአንቺ ጥሩ ነገር እንደምናገኝ አተማመናለሁ።"

"የተፈጥሮ ጉዳይ ነው። ይቺን የመሰለች ወጣት ተክታዮች ቢኖሯት የሚያስደንቅ አይደለም" አለ ሆልምስ ፒፓውን እያወጣ። "ጭር ላለ የገጠር መንገድ የሚመረጠው ግን ብሲኪሌት አይደለም። የሆነ ምሥጢረኛ አፍቃሪ ሊሆን እንደሚችል አያጠራጥርም። ስለዚህ ጉዳይ አያሌ ግምቶች ይኖራሉ-ዋትሰን።"

"ስንደርስበት ብቻ ብንነጋገር አይሻልም?"

"ትክክል። የመጀመሪያው ሥራችን የቻርሊንግተን ሕንፃ ተከራዮች እነማን እንደሆኑ ማወቅ ነው። ከዚያ በካሩተርስና በውድሌይ መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር ። የተሰያዩ



t.me/OLDBOOKSPDF.

ለዎች ስለመሆናቸውስ እርግጠኛ መሆን ይቻላል? ሁለቱም ለዎች ከራልፍ ስሚዝ ቤተሰብ ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት እንዴት ትልቅ ግምት ሊሰጡ ቻሉ? ለአንዲት የመዘቃ አስተማሪ ከገበያው ዋጋ እጥፍ አድርገው እየከፈለ፣ ከባቡር ጣቢያው ስድስት ኪሎ ሜትር ብቻ በርቅ እንኳን ልጅታን የሚሸኝ ሰው የማይመድብ ምን ዓይነት ቤተሰብ ነው? በጣም ያልተለመደ ነገር ነው ዋትሰን!"

"እሄዳለሁ እየልነ ነው?"

"ውድ ጓደ፣ እኔ ሳልሆን አንተ መሄድ አለብህ። እዚህ ግባ እማይባል ተራ ተንኰል ሊሆን ይችላል። በጣም ትልቁን የምርመራ ሥራዬን ለዚህ ብየ ማቋረጥ የለብኝም። ለኛ ዕለት ጧት ወደ ፋርንሐም ተጉዘህ ቻርሊንግተን ሜዳ አካባቢ አድፍጠህ ጠብቅ። እውነቱን ፈልፍለህ በማውጣትም የራስህን ሚዛናዊ ርምጃ ውሰድ። ከዚያ በሕንፃው ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ቃል ተቀብለህ ወደ እኔ ተመልሰህ ሪፖርት አቅርብ። ዋትሰን፣ ወደ መፍትሔው የሚያሻግረን ተጨባጭ ነገር እስክምናገኝ ስለ ጉዳዩ የተለየ ወሬ ማውራት አያስፈልግም።"

ልጅታ ለኛ 3፡50 ከዋተርሉ በሚነሳው ባቡር እንደምትሄድ አረጋግጠናል። በመሆኑም እኔ ጧት በ3፡13 የሚነሳውን ባቡር ነበር የያገኩት። ፋርንሐም ባቡር ጣቢያ ስደርስ ወደ ቻርሊንግተን ሜዳ ለመሄድ ብዙ አልተቸገርኩም። በቁጥቋጦ ደን በተከበበው መናፈሻና በሜዳው መካከል ያለውን



t.me/OLDBOOKSPDF

መንገድ በማየት ልጅቷ የተጋፈጠችውን ችግር ለመገመት አያዳግትም። ግራና ቀኝ በቆሙ የዋና በር አምዶች ላይ አርማዎች ተቀርፀዋል። ሽበት ቢወርሳቸውም ከጥርብ ድንጋይ የተሠሩ ናቸው። ከዋናው መንገድ በተጨማሪ ወደ ጫካው የሚያስገቡ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች መኖራቸውን ተገንዝቤያለሁ። የቻርሊንግተኑን ሕንፃ መንገዱ ላይ ሆኖ ማየት አይቻልም። አካባቢው ቅፍፍ የሚልና ብስባሽ የበዛበት ነው። በወርቃማ አበቦች የተሸፈነው መስክ በፀደይ የማለዳ ፀሐይ ደምቋል። ከብዙ የአበባ ስብስቦች መካከል አንዱን ከላላ አድርጌ ነበር ያደፈጥሁት ። እዚያ ሆኜ ዋናውን የግቢ በርና የመንገዱን ግራና ቀኝ መቆጣጠር እችል ነበር። እኔ ከመጣሁበት ተቃራኒ አቅጣጫ አንድ ቢስክሌተኛ እየነዳ ሲመጣ አየሁ። ጥቁር መሉ ልብስ ለብሷል። ዒመም ጥቁር ነው። ጥቂት እንደተጓዘ ከቢስክሌቱ ወርዶ ወደ ቁጥቋጦው በሚወስደው ጠባብ መንገድ ገብቶ ከእይታየ ተሰወረ።

ከሩብ ሰዓት በኋላ ሌላ ቢስክሌተኛ ተመለከትሁ ። ወጣቷ ልጅ ነበረች። ቻርሊንግተን ከሚገኘው ቁጥቋጣማ ደን አካባቢ ስትደርስ በንዴት ዙሪያዋን በዓይኗ ስታማትር አየኋት ። ወዲያው ሰውየው ከተደበቀበት ወጥቶ ሳይክሉን እየጋለበ ተከተላት። በዚያ አውራ መንገድ ላይ ከእነሱ በስተቀር ሌላ መንገደኛ አልነበረም። ቢስክሌቷ ላይ ቀጥ ብላ ተቀምጣ የምትነዳ ግርማ ሞገስ ያላት ልጃገረድና ከቢስክሌቱ መሪ ላይ አቀርቅሮ የሚያሽከረክር ወንድ። ፍጥነቷን ቀንሳ ወደ ኋላ ተመለከተች። እሱም ፍጥነቱን ቀነሰ። እሷ ስታቆም እሱም ከእሷ መቶ ሜትር ያክል ርቆ አቆመ። ቀጣዩ ጉዞዋ ያልተጠበቀ ነበር። ሳይታሰብ ብስክሌቷን ወደ ኋላ አዙራ ቀጥታ ወደ እሱ ነዳች። እሱም በተመሳሳይ ፍጥነት አዞረና



t.me/OLDBOOKSPDF

ሽምጥ ጋለበ። እሷም ኩራት ባልተለየው ስሜት ተመለሰች። ሌላ ተመልካች ስለመኖሩ እንደማታውቅ ከሁኔታዋ መገመት ይቻል ነበር። እሱም ያው እንደተለመደው ተመልሶ ይከተላት ጀመር። ጠመዝማዛውን መንገድ እንደዞሩ ከአይታ ተሠወሩብኝ።

እኔ እዚያው ካደፈጥሁበት ቦታ ላይ ቆየሁ። መቆየቴ ጥሩ ነበር። ሰውየው ተመልሶ ሲመጣ አየሁት። ከግቢው በር አካባቢ ሲደርስ ዞሮ ከቢስክሌቱ ወረደ። ለጥቂት ደቂቃዎች ዛፎች ሥር ቆሞ ቆይታ። የእጁን እንቅስቃሴ ሳየው ክራቫቱን የሚያስተካክል ይመስላል። ከዚያ በቢስክሌቱ እየጋለበ ወደ አዳራሹ በሚወስደው መንገድ ቁልቁል ወረደ። ከእኔ ርቋል። ከመስኩ ተነስቼ በመሮጥ ወደ ጫካው ገባሁ። አሮጌው ግራጫ ሕንፃና የጭስ መውጫዎቹ ከሩቅ ይታዩኝ ነበር። እሱን ግን ላየው አልቻልኩም።

ያም ሆኖ በእኔ ግምት የጣት ሥራየን በጥሩ ሁኔታ ያጠናቀቅሁ ስለመሰለኝ ወደ ፋርንሐም ጣቢያ ስለመሰስ የርካታ መንፈስ እየተሰማኝ ነበር። የአካባቢው የቤቶች ጉዳይ ኃላፊ ስለ ቻርሊንግተን የመኖሪያ ሕንፃ ምንም መረጃ አልሰጠኝም። ፖልሞል አካባቢ የሚገኘውን የታወቀ ድርጅት መጠየቅ እንደሚሻል ነበር የነገረኝ። ወደ ቤቴ ስሄድ እግረ መንገዴን ሃላፊውን አገኘሁት። በዚያው ወቅት በቻርሊንግተን ሕንፃ ውስጥ የሚከራይ ባዶ ክፍል ማግኘት አልቻልኩም። በጣም የዘገየሁ መሆኔና ከወር በፊት ተከራይቶ ያለቀ መሆኑ ነበር የተነገረኝ። ተከራዩ ሚስተር ዊሊያምሰን ይባላል። በጣም የተከበረ አላውንት ነው። ትዳሩ ወኪል ይሆን ከመንገር ባለፈ ስለደንበኞቹ የግል ጉዳይ ዝርዝር ውስጥ መግባት እንደሌበት ያውቃል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስተር ሸርሎክ ሆልምስ በዚያን ምሽት ያቀረብኩለትን ሪፖርት በጥሞና አዳመጠኝ። እኔ ያሰብኩትን ያክል ውዳሴ የተቸረው ግን አልነበረም። እንዲያውም የፈፀምኳቸውንና ያልፈፀምኳቸውን ጉዳዮች ሲገመግም ፊቱ ላይ ይታይ የነበረው ስሜት ጥሩ አልነበረም።

"ውድ ዋትሰን፣ ያደፈጥክበት ቦታ ትክክል አልነበረም። መስኩ ውስጥ ሳይሆን ከጫካው በኩል ካለው ቁጥቋጦ ሥር ነበር መደበቅ የነበረብህ። ያ ቢሆን ኖሮ በቅርብ የማየት ዕድል ይኖርህ ነበር። ከሰውየው መፉ ሜትር ያክል ርቀት ስለነበረህ፣ የወይዘሪት ስሚዝን ያክል እንኳን መረጃ ልትሠጠኝ አልቻልክም። እሷ ሰውየውን አላውቀውም ብላ ታስባለች። በእኔ እምነት ግን የምታውቀው ይመስለኛል። ካላወቀችው ከፊቷ ለመሰወር ይህን ያክል ራሱን የሚያሸሽበት ምክንያት ምንድነው? እንዳልከውም ብስክሌቱ መሪ ላይ አቀርቅሮ ነበር--ራሱን ለመደበቅ ። በእውነት ጥሩ ሥራ አልሠራህም። እሱ ወደ ቤቱ ተመልሶ ሳለ ማንነቱን ለማወቅ ትፈልጋለህ። ለዚህም ስትል የሉንዶንን የቤቶች ጉዳይ ተጠሪ ፍለጋ መጣህ።"

"ምን ማድረግ ነበረብኝ?" ስል በቁጣ ጮኽበት።

"በአካባቢው ካሉ የሕዝብ መናኸሪያ ቤቶች ወደ አንዱ ገራ ብለህ ብትጠይቅ አገሬው ምን እንደሚያወራ በትክክል ትረዳ ነበር። ማን፣ የት እንደሚኖር ከአባወራው እስከ ቤት አሽከር ያሉትን ስሞች ዘርዝረው ይነግሩህ ነበር። ሞሊያምሰን! ለእኔ ምንም ትርጉም አይሰጠኝም። የዚህ ሰው አላውንትነት



t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅቷን ከሚከታተሉት ሰው ጋር ምን ግንኙነት አለው? ከእነሱ የመስክ ጉብኝት ምን አገኘን? ልጅቷ የነገረችኝ እውነት ስለመሆኑ አልጠራጠርም። በቢስክሌተኛውና በሕንፃው መካከል ግንኙነት ስለመኖሩም ቢሆን አልተጠራጠርኩም። አዳራሹ በዊሊያምሰን ስለመከራየቱም እንዲሁ። ሰያዝነው ጉዳይ በጣም ተፈላጊው ማነው? ወንድሜ ዋትሰን አይክፋህ። እስከሚቀጥለው ቅዳሜ አንዳንድ ነገሮች ማድረግ እንችላለን። እስከዚያው አንድ ወይም ሁለት ነገሮችን እኔው ራሴ ለማጣራት እሞክራለሁ።"

በቀጣዩ ቀን ጧት ከወይዘሪት ስሚዝ አንድ ማስታወሻ ደረሰን። እጥር ምጥን አድርጋ የደረስኩባቸውን ነገሮች በግልጽ አስቀምጣቸዋለች። የደብዳቤው ፍሬ ነገር ያለው ግን ከግርጌው ነው።

*"ሚስተር ሆልምስ፣ አሠሪየ ለጋብቻ ስለጠየቀኝ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያለሁ መሆኔን ስገልጽልህ ምሥጢሬን እንደምትጠብቅልኝ እምነቴ የሀና ነው። ትንንት ያልተለየው ብርቱ የፍቅር ስሜት እንዳለው ተገንዝቤአለሁ። ቀደም ሲል የገባሁት ቃል ኪዳን መኖሩን ነግሬሃለሁ። ጥያቄውን ባለመቀበሌ በጣም የተሰማው ቢሆንም ጨዋነቱ አልተለየውም። ሁኔታው ትንሽ ጫና እንደሚፈጥር መገመት ትችላለህ።"*

"ወጣቷ ጓደኞችን ከፍተኛ ችግር ውስጥ የተዘፈቀች ትመስላለች" አሉ ሆልምስ ደብዳቤውን እንበቦ ሲጨስ በልቡ እያሰላሰለ። "ጉዳዩ በጣም አሳሳቢና ቀደም ብየ ከገመትኩት በላይ ሞጋች እየሆነ ነው። የሰላም ቀን ያርገውና ከዚህ ወጥቼ አንድ ወይም ሁለት የራሴን መከራዎች ማድረግ አፈልጋለሁ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆልምስ ቀኑን ከከተማ ውጭ በተለየ ሁኔታ ነው ያሳለፈው። ምሽት ላይ ቤከር ጐዳና አካባቢ ካለው ቤቱ ሲደርስ ከንፈሩ ተሰንጥቋል። ግንባሩ ማበጥ ብቻ ላይሆን የተፈጥሮ ቀለሙን ቀይሯል። የሠራው ጀብዱ በጣም አስገርሞት ባስታወሰው ቁጥር ከልቡ ክት ብሎ ይስቃል።

"ጥቂት የአካል እንቅስቃሴ ማድረጌ በጅ" አለ። "እንደምታውቀው ድሮ ትልቅ የቡጢ ችሎታ ነበረኝ። አንዳንዴ ይጠቅማል። ያ ባይሆን ኖሮ ዛሬ አሳፋሪ ሁኔታ ውስጥ ወድቄ ነበር።"

ምን ተፈጥሮ እንደነበር እንዲነግረኝ ተማፀንኩት። "ያን ለእንተ የነገርከህን የገጠር መሸታ ቤት አገኘሁት። ባደረግሁት ጥንቃቄ የተሞላበት ምርመራ ጠቃሚ ነገሮችን አግኝቻለሁ። በና ቤቱ ውስጥ ገብቼ ከአንድ ተናጋሪ ባለሀብት የፊለግሁትን ሁሉ መረጃ አግኝቻለሁ። ዊሊያምሰን ማለት ሺበታም ዒም ያለውና ከጥቂት አሽከሮቹ ጋር ብቻውን የሚኖር ሰው ነው። ሰውየው ካህን እንደነበር የሚጠቁሙ አንዳንድ ጭምጭምታዎች አሉ። አሁን ባለበት ቤት ውስጥ ባደረገው አጭር ቆይታ የሠራቸው አንዳንድ ሥራዎች ግን ከሃይማኖታዊ ሥነ-ምግባር ያፈነገጡ ናቸው። ከአንድ የሃይማኖት ድርጅት ጋር የተወሰነ ቆይታ አድርጌ ነበር። እንዲህ የሚባል ስም ያለው ሰው መኖሩንና ስለ ሥራው ግን ማንም እንደማያውቅ ነው የነገሩኝ። ባለ ሃብቱ ቀደም ሲል ከነገረኝ በተጨማሪ 'በየሳምንቱ መጨረሻ አያሌ ሰዎች የመኖሪያ አዳራሹን ይጐበኛሉ። በተለይ ባለ ቀይ ዒመ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስተር ውድሌይ ሁልጊዜም ከዚህ ተለይቶ አያውቅም አለኝና በእሱ መሪነት ቢራ ወደ ሚቀዳበት ቀጣይ ክፍል ገባን። ለካስ ይኸን ሁሉ ስናወራ ሰውየው በዚህ ክፍል ውስጥ ሆኖ ቢራ እየጠጣ ያዳምጠን ኖሯል። የእኔን ማንነት፣ ምን እንደምፈልግና ለምን እንደምጠይቅ ሁሉ አውቋል። ሲናገር አንደበተ ርቱዕ ነው። በመጨረሻ በሌላ ሰው እያስመሰለ የአግቦ ስድብ ጀመረ። ልታገሰው አልቻልኩም። ስድቡ ቀጥታ እኔ ላይ አነጣጠረ። በጥባጭ፣ ወሮበላ እያለ መቀባጠሩን ቀጠለበት። ያው እንደምታየኝ ትዕግሥቴ አለቀ። ሚስተር ውድሌይ በጋሪ ሂደ። ይኸውልህ የመስክ ጉዞየ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ተደመደመ አልሃለሁ። ቀኑ ለእኔ የከፋ ነበር ባልልም ከተልዕኮየ አንፃር ግን ወደ ሱሪይ ጠረፍ ያደረግሁት ጉዞ የተሳካ ነበር ማለት አልችልም። ከአንተ የተሻለ ነገር አላደረግሁም።

ሐሙስ ዕለት ከደንበኞችን ሌላ ደብዳቤ ደረሰን።

"ሚስተር ሆልምስ፣ ከሚስተር ካሩተርስ ጋር የነበረኝን ውል አቋርጬ ሥራዬን ለቅቄያለሁ ስልህ ብዙ እንደማትደነቅ ተስፋ አደርጋለሁ። የማገኘው ከፍተኛ ደሞዝ ከገጠመኝ ችግር ገላግሎ ሰላሜን ሊገዛልኝ አልቻለም። ቅዳሜ ወደ ከተማ መጥቼ፣ ሳልመለስ ወስኛለሁ። ሚስተር ካሩተርስ ጋሪ አስመጥቷል። ስለዚ ብቻየን ስለማልሄድ በእኔ ላይ ሊፈጠር የሚችል አደጋ አይኖርም።

"የእኔ ሥራ መልቀቅ ከሚስተር ካሩተርስ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ከዚያ አስቸጋሪ ፍጡር ከሚስተር



t.me/OLDBOOKSPDF

ውድሌይ ተመልሶ መምጣት ጋር የተያያዘ እንጅ። በጣም የሚያስጠላ ሰው ነው። አሁን ደግሞ አደጋ ላይደርስበት አይቀርም። የበለጠ አስጠልቷል። በመስኮት ከማየት ባለፈ በአካል ባለማግኘቱ ደስ ብሎኛል። ከሚስተር ካሩተርስ ጋር ረጅም ውይይት ሲያካሂዱ ነበር። ሚስተር ካሩተርስ የተደናገጠ ይመስላል። ውድሌይ ካሩተርስ ቤት አላደረም። ጉረቤት ጋ ነው ያረፈው። ዛሬ ጠዋት ሽክክ ብሎ ወደ ጫካው ሲገባ አይቼዋለሁ። ስአርዊ ምድር ቢዳርገው ምኞቱ ነበር። ልናገር ከምችለው በላይ አፈራዋለሁ። እጠላዋለሁም። ሚስተር ካሩተርስ እንደዚህ ዓይነቱን ፍጡር ለደቂቃስ ቢሆን እንዴት ይታገሰዋል?... ለማንኛውም በመጪው ቅዳሜ ከችግሬ ሁሉ እላቀቃለሁ።"

"የእኔ እምነት ዋትሰን" አለ ሆልምስ ኮስተር ብሎ፣ በዚያች ወጣት ዙሪያ አንድ ትልቅ ሠናመድ ተዘርግቷል። በዚህ በመጨረሻ ጉዞዋ ማንም ችግር ላይ እንዳይጥላት ማረጋገጥ የእኛ ተግባር ነው። በመሆኑም ዋትሰን፣ ቅዳሜ ጠዋት እኔና አንተ አብረን በመሄድ ይህን ልብ አንጠልጣይና ማለቂያ የሌለው ሥራ መቋጫ ልናበጅለት ይገባል።"

እስከአሁን ለጉዳዩ ክብደት አልሰጠሁትም ነበር። እንደቀላል ነገር ስለወሰድኩት ወደ አደጋ ሊያመራ የሚችል አልመሰለኝም። አንድ ወንድ፣ ቆንጆ ልጃገረድ አይቶ ተከታተላት መባሉ የሚያስደንቅ አይደለም። ቀርቦ ለማነጋገር ድፍረት በማጣቱ በሩቅ እያያት ስለሄደ በእሷ ላይ ጥቃት ያደርሳል ለማለትም አያስችልም። የውድሌይ ሁኔታ ግን የተለየ ነው። እሱም ቢሆን ግን ከአንዴ በስተቀር አላስቸገራትም። አሁን ደግሞ እሷ በሌለችበት ነው የካሩተርስን ቤተሰብ የጉበኘው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ባለቢስክሌቱ ሰውየ ያለምንም ጥርጥር በየሳምንቱ መጨረሻ ወደ አዳራሽ ከሚመጡት ታዳሚዎች መካከል አንዱ መሆን አለበት። ባለቡና ቤቱ ይናገር የነበረውም ስለ እሱ ነው። ግን ማንነቱንና ምን እንደሚፈልግ የሚታወቅ ነገር የለም። ሆልምስ አምርሯል። ማምረሩንም ያወቅሁት ከቤት ከመውጣታችን በፊት ሽጉጡን ወደ ኪሱ ሲያስገባ ስላየሁት ነው። ይህም ከዚህ ጉዳይ በስተጀርባ አደጋ ሊፈጠር ይችላል የሚል ሥጋት አሳድሮብኛል።

ሌሊቱ ዝናባማ ቢሆንም ማለዳው የተፈጥሮ ብርሃንን ፀጋ የተላበሰ ነበር። ከስተማ ውጭ ያለው መስክ የተለያዩ ቀለማት ባላቸው አበቦች ተውቦ ዓይንን ይማርካል። ሆልምስ እና እኔ በወፎች ዝማሬና በማለዳው የሀደይ አየር እስትንፋስ እየተዝናናን በሰፊው አሸዋማ ሜዳ ላይ ጉዟችንን ቀጥለናል። መንገዱን ተከትለን ወደ ክሩስበሪ ዳገት እያቀናን ስንሄድ ከቁመቱ ዘለግ ብሎ በዋርካ ዛፎች የተከበበውን ዕድሜ ጠገብ ሕንፃ /አዳራሽ/ ቁልቁል ተመለከትነው። ዛፎቹ ረጅም እድሜ ያላቸው ቢመስሉም የቤቱን ያክል አላረጁም ። ሆልምስ ከሩቅ የሆነ ነገር ተመለከተ። አንድ ጋሪ ወደ እኛ እየመጣ ነበር። ሆልምስ ትዕግሥቱ ሊያልቅ እየተቃረበ መሆኑ ይታወቅበታል።

"የግማሽ ሰዓት ገደብ ሰጥቻለሁ" አለ። "እሷን የሚያጠምድ ከሆነ ቀዳሚውን ባቡር ይዛለች ማለት ነው። ዋትሰን፣ ሳናገኛት ቻርሊንግተንን አልፋ ሄዳለች የሚል ፍራቻም አለኝ። አቀበቱን እንደጨረስን ያ ከሩቅ ያየነው ተሽከርካሪ



t.me/OLDBOOKSPDF

በቅጽበት ውስጥ ከዓይናችን ተሠወረብን። ፍጥነታችንን ስንጨምር የዕግር መንገድ ያልለመደው ዕግሬ ወደ ኋላ እያስቀረ አጋለጠኝ። የሰውነት ማጠንከሪያ ልምምድ የሚያዘወትረው ሆልምስ እኔን ወደ ኋላ ትቶኝ ገሠገሠ። ከእኔ ፊት ሰፊት አንድ መቶ ሜትር ያክል ርቆ ቆሞ ሃዘን በተሞላበት የተስፋ መቁረጥ ስሜት በአንድ እጁ አየሩን ሲቀዝፍ አየሁት። በዚያው ቅጽበት አንድ ባዶ ጋሪ በሰጋር ፊረስ አየተሳበ ኩርባውን መንገድ ዞሮ ከፊታችን ከች አለ።

"በጣም ዘገየን ዋትሰን፤ በጣም!" አለ እያለከለከሁም ቢሆን የደረስኩበት መሆኔን ያወቀው ሆልምስ። "ቀድሞ የሄደውን ባቡር ማሳለፍ አልነበረብኝም! ጠለፋ ነው ዋትሰን! ጠለፋ! ግድያ! ምን እንደሆነ እግዚአብሔር ይወቀው! ፊረሱን አስቁመው! አም ዘለህ ውጣ! እስካሁን የሠራሁት ጥፋት በዚህ የሚካስ ከሆነ እናያለን።"

ጋሪው ላይ ወጥተናል። ሆልምስ ጋሪውን ካዞረ በኋላ ፊረሱን ደህና አድርጉ በአሰንጋ ሲገርፈው ወደ መጣንበት አቅጣጫ ተመለስን። እንደወፍ በረርን ማለት ይቻላል። ኩርባውን መንገድ ስንጨርስ በአዳራሽና በመስኩ መካከል የተዘረጋው መንገድ ወለል ብሎ ይታያል። የሆልምስን ክንድ ነካ አደረግሁት።

"ሰውየው ያውና" አልኩት እያቃሰትኩ

አንድ ብስክሌተኛ ወደ እኛ እየገሰገሰ ነበር። ከእንቱ ደፋ፤ ከጀርባው ጉብጥ ብሎ ያለ የሌለውን ሃይሉን የብስክሌቱን ፔዳል ለመርገጥ አውሎታል። ውድድር ላይ ያለ እንጂ ብቻውን



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚጓዝ አይመስልም። እንደ ጉድ ይበራል። ያንን ሚማም ፊቱን ቀና ሲያደርግ አጠገቡ መሆናችንን ተመለከተና ከበስኪሌቱ ወረደ። የሚመ ጥቁረት የፊቱን ቅላት አድምቆታል። የዓይኑ ቅላት ትኩሳት ያለበት በሽተኛ አስመስሎታል። መጀመሪያ ወደ እኛ ቀጥሎ ወደ ጋሪው ተመለከተ። በገጽታው ላይ የመገረም ሁኔታ ይነበባል።

"ስማ! ስማ! አቁም!" ሲል ጮኸ በያዘው ብስክሌት መንገዱን ለመገጋት እየሞከረ። "እሱን ጋሪ የት ነው ያገኛችሁት? ውረዱ!" አለ በቁጣ ከጉን ኪሱ ሽጉጥ እያወጣ። "ውረዱ ብያለሁ፤ ያለዚያ ጊዮርጊስ አይለመነኝ ፊረሱን በጥይት እመታዋለሁ።"

ሆልምስ ልጓሙን ለእኔ ወረወረና ከጋሪው ላይ ዘሎ ወረደ። "እኛ እምንፈልግህ አንተን ነው። ወይዘሪት ቫዮሌት ስሚዝ የታለች?" አለና እትጩን ነገረው።

"እኔ እምጠይቀውን ጥያቄ ነው የጠየቅኸኝ። የእሷን ጋሪ የያዛችሁት እናንተ ናችሁ። የት እንዳለች ማወቅ ያለባችሁም እናንተ ራሳችሁ ናችሁ።"

"ጋሪውን መንገድ ላይ ነው ያገኘነው። ማንም አልነበረበትም። ወደ ኋላ የተመለስነው ወጣቷን ለመርዳት ስንል ነው።"

"ያንተ ያለህ! የመድኃኒያለም ያለህ! ምን ይሻለኛል?" ሲል ብስኪሌተኛው በቀጠሀ ተስፋ ጮኸ። "ያ የሲኦል ውሻ፣ ውድሌይ እና ያ ርከስ ደብተራ አግኝተዋታል ማለት ነው። በእውነት ጓደኞቿ ከሆናችሁ ኑ ተከተሉኝ። አብረን ተባብረን ልጅቷን ከጉድ እናውጣት።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሽጉጡን በእጁ እንደያዘ ውስጡ እየተረበሸ ወደ ቁጥቋጦው ደን በሚያስገባው መንገድ ሩጫውን ቀጠለ። ሆልምስ ተከትሎታል። እኔም ፈረሱን መንገድ ዳር ትቼው ሆልምስን ተከተልኩት።

"በዚህ ውስጥ ነው የመጡት" አለ የብዙ ዕግሮች ዱካ ወዳለበት ጭቃማ መንገድ እያመለከተ። "ሐሎ! እስቲ ቆም በሉ። ቁጥቋጦው ውስጥ ማን አለ?"

ዕድሜው አሥራ ሰባት ዓመት ገደማ የሚሆን ወጣት በጠፍር የታሠረ ገምባሌ አድርጎ ዝልፍልፍ ብሎ በጀርባው ተንጋሏል። ራሱ በአሰቃቂ ሁኔታ ተፈንክቷል። ነፍሱን ቢስትም ሕይወቱ አላለፈም። ቁስሉን ስመለከት አጥንቱ እንዳልተጐዳ ተገነዘብኩ።

"ፈረስ አጣቢው ፒተር ነው" ሲል እንግዳው ሰውየ ጮኸ። "እሱ ነው በጋሪ የሸኘት። እነዚያ አረመኔዎች ከጋሪው አስወርደው ደብድበው ጥለውት ሄደዋል። ምንም ልናደርግለት ስለማንችል እሱን ተውትና እሷን ሊደርስባት ከሚችል የከፋ አደጋ እናውጣት።"

የቁልቁሉቱን መንገድ ይዘን፣ ዱር ለዱር ቁጥቋጦ ለቁጥቋጦ የችኮላ ሩጫችንን ቀጠልን። ከዚያ በቤቱ አካባቢ ባለው የቁጥቋጦ አጥር ሥር ደረስን። ሆልምስ ቀድሞን ደርሷል።

"ወደ ቤት አልገቡም። ዱካቸው ወደ ግራ መሄዳቸውን ነው የሚያሳየው በዚህኛው ቁጥቋጦ! አዎ አውቄዋለሁ!"



t.me/OLDBOOKSPDF

ልክ ይኸን እንደተናገረ ጆሮ የሚበሳ ቀጭንና አሰቃቂ የሆነ የሴት ልጅ ጩኸት ከፊታችን ካለው ጥቅጥቅ ካለ ቁጥቋጣማ ደን ውስጥ አስተጋባ። ወዲያው ያ ከፍተኛ ጩኸት ወደ ወፍራም የማንቋረር ድምፅ ተቀየረ። ከታነቀ ጉረሮ የሚወጣ የድምፅ ዓይነት።

"ወደዚህ! ወደዚህ! ጉድጓዳው ውስጥ ናቸው" አለ እንግዳው ሰውየ ዱር ለዱር እየጣሰ በመግስገስ። "አህ-ፊሪ ውሾች! ተከተሉኝ ወንድሞቼ! ተቀድመናል! በዘረኞች ተቀድመናል!"

እየተሹለከለኩን ሄደን በአገር በቀል ዛፎች ከተከበበና በጣም ከሚያምር አረንጓዴ የመናፈሻ ደሴት ደረስን። ራቅ ብሎ ከሚገኝ ትልቅ የዋርካ ዛፍ ጥላ ሥር ሦስት ሰዎች ፈንጠር፣ ፈንጠር ብለው ቆመዋል። አንዲ ሴት ናት-የእኛዋ ደንበኛ። አፏ በመሐረም ታሥሯል። ጥውልግልግ ብላ ደክማለች። ከአሷ ፊት ለፊት ጨካኝነቱ ፊቱ ላይ የሚነበብ፣ ቀይ ሪዝ ያሰው ገንባሌ ያደረገ ወጣት ዕግሮቹን ግራና ቀኝ ወድሮ ቆሟል። በአንድ እጁ መገቡን በሌላው አሰንጋ ይዞ ሲያወናጭፍ ለሚያየው ሰው ድል አድራጊ አርበኛ ይመስላል። በመካከላቸው ካባ መሰል ነገር በረጅም ልብስ ላይ የደረቡ፣ ግራጫ ዒም ያላቸው አዛውንት የፀሎት መጽሐፋቸውን ወደ ኪሳቸው ከተው በጣም የሚያስፈራውን መሽሬ ትከሻውን መታ፣ መታ ሲያደርጉት ደረስን። እንኳን ደስ ያለህ ለማለት። የጋበቻው ሥነ-ሥዓት ተፈጽሟል።

"ተጋብተዋል!" አልኩ እየቃተትኩ

"ቶሎ በሉ!" አለ እንግዳው መሪያችን ጮክ ብሎ። ቶሎ በሉ!" እያለ በደን የተከበበችዋን ጠባቧን ደሴት አቋርጦ ሲሄድ ሆልምስና እኔ ከሥር ከሥሩ ተከትለነዋል። እየተጠጋን ስንሄድ ልጅቷ እየተንገዳገደች ሄዳ የዋርካውን ግንድ ተደግፋ ቆመች። የቀድሞው ቄስ ዊሊያምስን ጉንበስ ብሎ የፈዝ ሠላምታ ሰጠን። ጥቃት ፈፃሚው ውድሌይ እንደ አንበሳ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግልገል እየፈነጠዘ ድምፁን ከፍ አድርጐ ይስቃል። በጭካኔው የልቡ ደርሷል።

"ዒምህን ማውለቅ ትችላለህ ቦብ!" አለ። በመቀጠልም "እኔ እንኳን በደንብ አውቅሀለሁ። ለማንኛውም አንተና ጓደኞችህን ከሚስዝ ውድሴይ ጋር ላስተዋውቃችሁ በምችልበት ሰዓት ላይ ደርሳችኋል።"

መንገድ መሪያችን ቁርጥ ያለ መልስ ነበር የሰጠው። ለማላላቻ ፊቱ ላይ ያደረገውን ሰው ሠራሽ ፀጉር ከፊቱ ልጦ መሬት ላይ ወረወረው። በደንብ የተላጨና የገረጣ ፊቱ ቁልጭ ብሎ ይታያል። ሽጉጡን አውጥቶ አሰንጋ ይዞ በአደገኛ ሁኔታ ወደ እሱ ይገሰግስ ወደነበረው ጨካኝ ወጣት ላይ አነጣጠረው።

"አም" አለ ተባባሪያችን "ቦብ ካሩተርስ ነኝ። ይቺ ሴት ሕጋዊ መብታ ሲከበር ማየት አሻለሁ። የአዕምሮ ሠላም የማገኘውም ያኔ ነው። ካበሳጨኸት በአንተ ላይ ምን ዓይነት አርምጃ እንደምወስድ ነግሬሃለሁ። አግዚአብሔር ምሥክሬ ነው፤ ቃሌን አላጥፈውም!"

"ተቀድመሃል! ባለቤቱ ናት!"

"በጭራሽ። ባለቤቷን በሞት ያጣች ብትል ይሻልሃል።"

ሽጉጡ ተተኮሰ። በውድሴይ ሰደርያ ላይ ደም ሲንፎለፎል ይታየኛል። እየጮኸ ሲሽከረከር ቆየና በጀርባው ሄዶ ተዘረጋ። በረጅም የካህን ልብሳቸው ላይ ካባ የደረቡት አዛውንት ሽጉጣቸውን ቢያወጡም ከማነጣጠራቸው በፊት የሆልምስን ሽጉጥ አፈሙዝ ቁልቁል ተመለከቱ።

"በቃ!" አለ ጓደኛየ በተረጋጋ መንፈስ። "ሽጉጡን አስቀምጥ! ዋትሰን፣ ሽጉጡን አንስተህ በጭንቅላቱ ላይ አነጣጥረው! አመሰግናለሁ። ካሩተርስ ሽጉጥህን ስጠኝ። ከእንግዲህ ምንም ረብሻ አይኖርም። አምጣና አስረክብ!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመሆኑ አንተ ማነህ?"

"ሼርሎክ ሆልምስ እባላለሁ"

"የመድኃኔዓለም ያለህ!"

"ስለ እኔ ታውቃለህ ብየ እገምታለሁ። ፖሊስ እስክሚመጣ ራሴ ፖሊስ እሆናለሁ። ስማ...ስማ!" አለና ራቅ ብሎ ቆሞ በፍርሃት ሲንቀጠቀጥ የነበረውን ፊረስ አጣቢ ጮኸበት። "ና ወደ እኔ ተጠጋ። እንካ፣ በፍጥነት እየጋለብክ ሂድና ይሆን ማስታወሻ ለፋርንሐም ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ስጠው። እሱ እስክሚመጣ ሁላችሁም በእኔ ቁጥጥር ሥር ናችሁ።"

ጠንካራው ሆልምስ የሐዘን ድባብ የዋጠውን አካባቢ በቁጥጥሩ ሥር አዋለው። ሁሉም የእሱ ታዛዦች ሆኑ። ዊሊያምሰንና ካሩተርስ ቁስለኛውን ውድሌይን ተሸክመው ወደ ቤት እንዲወስዱት ተደረገ። በፍርሐት የምትንቀጠቀጠው ልጃገረድ የእኔን ክንድ ይዛ መሄድ ጀመረች። ቁስለኛውን በራሱ አልጋ ላይ አስተኝተን በሆልምስ ጥያቄ መሠረት የሐኪም ምርመራ አደረግሁለት። ሪፖርቴን ይገዜ በሣጠራ በተከፋፈለችው ምግብ ቤት ውስጥ ሁለቱን እሥረኞች ከፊት ለፊቱ አድርጎ ወደ ተቀመጠው ሆልምስ ሄድኩ።

"አይሞትም" አልኳቸው

"ምን!?" ሲል ካሩተርስ ከመቀመጫው እየተነሳ ጮክ ብሎ ጠየቀ። "ከተኛበት ክፍል ሄጀ አጨርሰዋለሁ። ያቺ ምስኪን ልጃገረድ፣ ያቺ ንግሥት ከሮሪንግ ጃክ ውድሌይ ተቆራኝታ ትኖራለች እያልከኝ ነው?!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያ እንተን የሚመስክት ጉዳይ አይደለምᵐአለ ሆልምስ ::
"እሷ በምንም ዓይነት የእሱ ሚስት ልትሆን የማትችልበት ሁለት ቁቲ ምክንያቶች አሉ:: በመጀመሪያ ሚስተር ዊሊያምሰን የጋብቻ ቡራኬ ለመስጠት ያለው ሥልጣን እስከምን ድረስ እንደሆነ የመጠየቅ መብት አለን::"

"ሥልጣነ ክህነት ተሰጥቶኛል" አለ ወስላታው አረጋዊ

"መሰጠቱ ብቻ ሳይሆን መነጠቁም ይታወቃል::"

"አንዴ ከቀሰስክ ሁልጊዜም ቂስ ነህ"

"አይመስለኝም:: የሥራ ፈቃድስ አለህ?"

"የጋብቻ ፈቃድ አለኝ:: ኪሴ ውስጥ ነው::"

"እሱን አጭበርብረህ ያገኘኸው ነው:: ምንም ቢሆን ግን አስገድዶ ማግባት ሕጋዊ ሳይሆን በጣም ከባድ ወንጀል ነው:: ወደፊት ይገለጽልሃል:: ካልተሳሳትኩ በማረሚያ ቤት የአሥር ዓመታት ትምህርት ትወስዳለህ:: ካሩተርስ ደግሞ ሽንጥህን ከኪስህ ባታወጣው ጥሩ ነበር::

"እኔም እንደዚያ እያሰብኩ ነበር ሚስተር ሆልምስ :: ነገር ግን ይቺን ልጅ ከአደጋ ለመከላከል የምችለውን ሁሉ በጥንቃቄ አድርጌያለሁ:: ስለምወዳት ነው ሚስተር ሆልምስ:: ፍቅር ምን እንደሆነ ሳውቅም የመጀመሪያ ጊዜየ ነው:: በዚህ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ በታወቀ አረመኔ ወሮ-በላ እጅ መውደቋን ሳስብ ቀውሼ ነበር ማለት ይቻላል:: ብታምንም ባታምንም ሚስተር



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆልምስ፣ ይቺን ልጅ ከቀጠርክበት ጊዜ ጀምሮ ከቤት ስትወጣ ብቻዋን ሄዳ አታውቅም። እነዚህ ቀጣፊዎች አድፍጠው እንደሚጠብቷት ባውቅም ሊደርስባት ከሚችል ጉዳት ለመታደግ እሷ ሳታውቅ በብስክሌት ርቀቴን ጠብቄ ሳጅባትና ስጠብቃት ኖሬያለሁ። እኔነቴን እንዳታውቀኝ በሚል በፊቴ ላይ ሰው ሠራሽ ዒም አድርጌያለሁ። ይሽን ሁሉ ያደረግሁት ልጅቷ ቆንጆና መንፈሰ-ጠንካራ ስለሆነች ነው። ያን ያክል ጊዜ የተከታተልኳት እኔ መሆኔን ብታውቅ ኖሮ ከእኔ ጋር ለረጅም ጊዜ ባልቆየች ነበር።"

"ሊደርስባት ስለሚችለው አደጋ ለምን አስቀድመህ አልነገርካትም?"

"ያን ባደርግ ጥላኝ ትሄዳለች። ይሽ ደግሞ ልሸከመው የማልችለው ታላቅ ሰቆቃ ነው። ባትወደኝ እንኳ ለእኔ ያን የሚያምር ዳሌዋንና ግርማ ሞገሷን ማየት ትልቅ ክብር ነው። ድምጿ ለእኔ ጣፋጭ መዐዛዋ ነው።"

"እሺ፣ ሚስተር ካሩተርስ! አንተ ይህን ፍቅር ትለዋለህ። እኔ ግን ራስ ወዳድነት ነው የምለው።"

"ምን አልባት ሁለቱ ነገሮች አብረው ሊሄዱ ይችሉ ይሆናል። ለማንኛውም እንድትሄድ አልፈለግሁም። በተጨማሪም ብዙ ሰው ዓይኑን ለጣለባት ቆንጆየ ልጃገረድ ከዚህ ሁሉ ሊከላከልላት የሚችል ጠባቂ መኖሩ ተገቢ ነበር። ቴሌግራሙ ሊመጣ የሆነ ርምጃ ለመውሰድ እንደሚሞክሩ አውቅ ነበር።"

"የምን ቴሌግራም ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ካሩተርስ የቴሌግራም መልዕክት ከኪሱ አወጣና፣ "ይኸውና" አለው

"ራልፍ ስሚዝ ሞተዋል።" አጥር ምጥን ያለ መልዕክት።

"ይገርማል!" አለ ሆልምስ። "አንዳልከውም ይኸ መልዕክት ሊመጣ ሊገናኙ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም። ለማንኛውም እየቆየን ስንሄድ የምታውቀውን ሁሉ ትነግረኛለህ።"

ባለካባው ሽማግሌ የብልግና ስድቡን ማውረድ ጀመረ።

"እግዚአብሔር አይለመነኝ። ካሩተርስ ይኸን ልፍለፋህን ካላቆምክ ጃክ ውድሌይ የተጉነጨውን ጽዋ ለአንተም አስጉነጭሀለሁ። ስለ ልጅነ አፍህን ብትከፍት የራስህ ጉዳይ ነው። ስለ እኛ ስለ ጓደኞችህ ለዚህ ሲቪል ፖሊስ ብትቀባጥር ግን በሕይወትህ ውስጥ በጣም አስከፊ ነገር እንደሠራህ ይቆጠራል።"

"ክቡር አባታችን መደናገጥ የለብዎትም" አለ ሆልምስ ሲጋራውን እያቀጣጠለ። "የቀረበባችሁ ክስ ግልፅ ነው። እማያሻማ አይደለም። ለራሴ ጥንቃቄ ግን ዘርዘር አድርጋችሁ ብትነግሩኝ መልካም ነው። ለእኔ መንገር ችግር ያመጣል ብላችሁ ካሰባችሁ ደግሞ እኔ ራሴ ልነግራችሁ እችላለሁ። ምሥጢራችሁ ምን ያክል እንደተጠበቀ የማወቅ አጋጣሚም ታገኛላችሁ።በመጀመሪያ ደረጃ ሦስታችሁም ዊሊያምሰን፣ ካሩተርስና ውድሌይ ከደቡብ አፍሪካ ነው የመጣችሁ።"

"ቱጥር አንድ ውሸት" አሉ ሽማግሌው።



t.me/OLDBOOKSPDF

"እስከዛሬ ሁለት ወር ሁለቱንም አይቻቸው አላውቅም። በሕይወቱ የአፍሪካን ምድር የረገጥሁበት ጊዜም የለም። ስለዚህ ይሽን አለ-ባልታህን በፒፓህ ውስጥ ጨምርና አጭሰው። ለማህ ሚስተር ሆልምስ! ሚስተር ጥልቅ ብየ!"

"እውነቱን ነው" አለ ሚስተር ካሩተርስ።

"አዎ፤ ሁለታችሁ ከዚያ መጣችሁ። ቂስ ተብየው ግን እዚሁ እኛው አገር የተሠራ ሽቀጥ ነው። ራልፍ ስሚዝን ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ታውቂቸዋላችሁ። በሕይወት የመኖር ዕድላቸው እጭር እንደሆነም በቂ መረጃ አላችሁ። ከዚያም አልፎ የሀብታቸው ሕጋዊ ወራሽ የወንድማቸው ልጅ እንደምትሆን ደርሳችሁበታል። ልክ ነኝ አይደል-!?"

ካሩተርስ ራሱን ነቀነቀ። ዊሊያምሰን መሃላውን ደረደረ።

"ቀጣይዋ የሥጋ ዘመድ እሷ መሆኗ አጠራጣሪ ባይሆንም ሽማግሌው ምንም ነገዚ እንደማይተው እውቃችኋል። "

"ማንበብና መፃፍ አይችሉም" አለ ካሩተርስ

"በመሆነም እናንተ ሁለታችሁ ወደዚህ መጥታችሁ ልጅቷን ማደን ጀመራችሁ። ዓላማችሁ ከሁለት አንዳችሁ እሷን በማግባት ሌላው ደግሞ የውርሱ ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ነበር። በሆነ ምክንያት ውድሌይ ልጅቷን እንዲያገባ ተመረጠ ለምን?"

"በመርከብ ስንመጣ ካርታ ተጫወትን። ያሸነፈ እንዲወስዱት ተስማማንና ገጠምን። እሱ አሸነፈ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ገባኝ አንተ ልጅቷን ቀጥረህ ስታሠራት ውድሌይ ደግሞ እሷን የማለማመድና የማሽኮርመም የሥራ ድርሻ ወሰደ። ሰካራምነቱንና ወሮ በላነቱን ስላወቀች ጠላችው። በዚህ ሂደት ውስጥ አንተ ራስህ በልጅቷ ፍቅር ስለወደቅህ ዕቅዳችሁ ሁሉ እንዳልነበር ሆነ። ፈራረሰ። የዚህ ጨካኝ መሮ በላ እሷን በአጁ ሥር የማስገባት ጉዳይ ለአንተ የማይታሰብ ሆነብህ ። ቅናት አደረብህ።"

"ጊዮርጊስ ምስክሬ ነው። ላስበው አልችልም"

"በመካከላችሁ ጠብ ተፈጠረ። አንተን ብስጭት ውስጥ ከቶ ጥሎህ ሂደና የራሱን ዕቅድ ብቻውን መንደፍ ጀመረ።"

"ዊሊያምሰን የዚህ ሰው ንግግር ልቤን እየነካው ነው። ከዚህ የበለጠ እኛ ለእሱ የምንናገረው ያለ አይመስለኝም።"
በማለት ካሩተርስ ድምፁን ከፍ አድርጉ እየተናገረ የምሬት ሳቅ ሳቀ። "እም ተጣልተን ደብድቦኛል። ለማንኛውም በዚያ ምንም ቲም አልያዝክብትም። እሱ ግን ከዓይኔ ተሠወረብኝ። ከዚህ ውዳቂ ደብተራ ጋር ተገናኙ ማለት ነው። ከቤት ወጥታ ባቡር ጣቢያ እስክምትደርስ ይከታተላት እንደነበር አወቅሁ። ከዚያ በኋላ ዓይኔን ከእሷ ላይ አላነሳሁም። ሠይጣናዊ ሥራ ሊሠራ እንደሚችል ጥርጣሬ ነበረኝ። ምን ለማድረግ እንደሚችሉ ለማወቅ በቅርብ እከታተላቸው ስለነበር በየጊዜው አያቸዋለሁ። ከሁለት ቀናት በፊት ውድሌይ ይኸን ቴሌግራም ይዞ ቤቱ መጣ። ቴሌግራሙ ራልፍ ስሚዝ መሞታቸውን የሚገልጽ መርዶ ነበር። ስምምነቱን እንዳከበር ጠየቀኝ። እምቢ አልኩት። ልጅቷን እንዳገባትና የውርሱ ተካፋይ እንዳደርገው ጠየቀኝ። በራሴ በኩል ፈቃደኛ እንደሆንኩና እሷ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግን ለማግባት ፈቃደኛ እንዳማትሆን ነገርኩት። ከሁለት እንዳችን እናግባትና ከአንድ ወይም ከሁለት ሚሥጥ በኋላ ነገሮች ሁሉ ካለፈው የተሻሉ መሆናቸውን ትረዳለች አለኝ። ጠብ ወይም ረብሻ ለማንሳት እንደማልፈልግ ገለጽኩለት። ከዚያ በቱጥጥሩ ሥር እንደሚያደርጋት እየዛተ የርግማንና የስድብ ናዳ አወረደብኝ። በዚህ ሳምንት መጨረሻ ላይ ከእኔ ለመለየት ወስና ነበር። ባቡር ጣዚያ የሚያደርሳት ጋሪ ብመድብላትም አላስችለኝ ስላለ ዘግየት ብየ በብስክሌት ተከተልኳት። እሷ ቀድማኝ ሄዳ ስለነበር ቱሉ ልደርስባት አልቻልኩም። በዚህ አጋጣሚ በተፈጠረው ክፍተት በተንኮል መረባቸው ውስጥ አስገቢት። ችግር እንደተፈጠረ ያወቅሁት አንተና ጓደኛህ በእሷ ጋሪ ተሳፍራችሁ ስትመለሱ ላይ ነው።"

ሆልምስ ከመተመጫው ተነስቶ የሲጋራውን አላቂ መክስተሪያው ላይ ጣለው። "በጣም ዘገምተኛ ሆኖለሁ ዋትሰን" አለ። "በሪፖርትህ ላይ በቱጥቂጦው ሥር ተደብቆ የነበረው ቢስክሌተኛ እጅን ሲያንቀሳቅስ ክራባቱን የሚያስተካክል ይመስላል ስትለኝ እንዳሁኑ ግልጽ ሊሆንልኝ ይገባ ነበር። ያም ሆኖ በዚህ ቀልብን በሚስብና ልዩ በሆነ ጉዳይ የተሳካ ሥራ በመሥራታችን ልንኮራ ይገባል። ሚት በተፈጠረው ግርግር በማንም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አለመድረሱን በመስማቱ ደስ ብሎኛል። የሕክምና ባለመ.ያ ከመሆንህ አንፃር ሚስ ስሚዝ በደንብ ማገገሚን ብታረጋግጥና በደንብ ከተሻላት ወደ አናቷ ቤት ብትሸኛት ደስ ይለኛል። በደንብ ካልተሻላት ሚድላንድ ስሚገኘው ወጣት ኤሌክትሪሽያን ቴሌግራም እንደምንልክ ፍንጭ ብንሰጣት ከበሽታዋ ትፈወሳለች። ሚስተር ካሩተርስ ሴራውን ለማክሸፍ የምትችለውን ሁሉ በማድረግ ድርሻህን ተወጥተሃል። እንካ ካርዴን ጌታየ። በፍርዱ ሂደት የእኔን እገዛ የምትሻ ከሆነ የምችለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ታሪኩ ማጠቃለያ ስንመጣ ሚስ ቫዮሌት ስሚዝ በውርስ ብዙ ሃብት አግኝታለች። በአሁኑ ሰዓት የሞርተን እና ኬኔዲ ከፍተኛ የአክስዮን ባለድርሻ የሆነው የሳሪል ሞርተን ሚስት ሆናለች። ይህ ኩባንያ ዝነኛ የዌስት ሚኒስትር የኤሌክትሪክ ባለሙያዎች የተሰባሰቡበት ነው። ዊሊያምሰንና ውድሌይ በጠለፋና በያታ ጥቃት ወንጀል ተከሰው ዊሊያምሰን የሰባት ዓመት፣ ውድሌይ የአሥር ዓመት እሥራት ተፈርዶባቸዋል።

ስለ ካሩተርስ የደረሰኝ መረጃ ባይኖርም፣ የእሱን ጥፋት ፍርድ ቤቱ ቀለል አድርጐ እንደሚያየው አልጠራጠርም። ውድሌይ ተደጋጋሚ ጥፋት የፈፀመ አደገኛ ወንጀለኛ ስለሆነ ነው። ለማንኛውም በጥቂት ወራት ውስጥ በተደረገ ብርቱ እንቅስቃሴ የፍትሕን ጥማት ማርካት ተችሏል ብየ አስባለሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሞገደኛው መርማሪ

ወይዘሮ ሐድሰን የሼርሎክ ሆልምስ ቤት አከራይ ናት። ለአያሌ ዓመታት በተከራዮች ስትሰቃይ ኖራለች። የአፓርትመንቱ የመጀመሪያ ፎቅ ደባል ፀባይ በተጠናወታቸው ሰዎች የተሞላ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በተለይ በአንዱ ተከራይ ላይ የሚታየው ከሰዎች ያፈነገጠ ባሕሪና የኑሮ ዘይቤ የቤቱን ባለቤት የሐድሰንን ትዕግሥት የሚፈታተኑ ነበር። የማይታመነው የንፅህና ጉድለቱ፣ ያለጊዜው መዚቃ እየከፈተ የማስጮህ ልማዱ፣ አልፎ አልፎም በር ላይ ሽጉጥ እየተኮሰ ዒላማ መለማመዱ፣ መኖሪያ ቤቱን የሳይንስ ቤተ መከራ በማስመሰል ከባቢውን አየር በሚከረፋ ሽታ መበከሉ እና ሁለንተናው በረብሻና በእደጋ የተሞላ መሆኑ በሱንዶን ከተማ የተጠላና በጥባጭ ጭሰኛ አስከመባል አድርሶታል። በሌላ በኩል የሚከፍለው ከራይ ብዙ ነው። ሆልምስ ከእኔ ጋር አብሮ በኖረባቸው ዓመታት የከፈለው ገንዘብ ቤቱን ራሱን ሊገዛው ይችል እንደነበር አልጠራጠርም።

የቤቱ ባለቤት ለእሱ ፍርሃት ያልተሰየው አክብሮት አላት። ነገረ ሥራው ሁሉ የሚሰሞኘጥ ቢሆንም እሱን ለመናገር ድፍረቱ አልነበራትም። ከዚህም ባሻገር ሴቶችን ሰመርዳት በሚያሳየው ጨዋነት ያልተሰየው ጥረቱ በጣም ትወደዋለች። እሱ ሴቶችን አለመውደድ ብቻ ሳይሆን አያምናቸውም። ያም ሆኖ ለእነሱ ቅን አመለካከት አለው። ወይዘሮ ሐድሰን ለእሱ ያላትን ልባዊ የሆነ በጐ አመለካከት ስለማውቅ ከገባሁ ሁለተኛ ዓመቴን በያዝኩበት መኖሪያ ክፍሌ መጥታ ስታናግረኝ በጥሞና አዳመጥኋት። ምስኪኑ ጓደኛየ ስለሚገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ ነበር የነገረችኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"እየሞተ እኮ ነው ዶክተር ዋትሰን" አለችኝ። "ሦስት ቀናት ሙሉ መናገር አይችልም። የዛሬዋን ዕለት በሕይወት ማሳለፉም ያጠራጥረኛል። ምግብ እንድወስድለት ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም። ዛሬ ጧት አፈንግጠው የወጡ የሚመስሉ የፊት አጥንቶቹንና ፍጥጥ ብለው የሚመለከቱኝን ጎድጓዳ ዓይኖቹን ሳይ ስሜቱን መቆጣጠር አልቻልኩም። 'ሚስተር ሆልምስ ፈቀድክም አልፈቀድክም በዚች ቅጽበት ዶክተር ለማምጣት መሄዴ ነው' አልኩት። 'እሽ፣ ግን ዶክተር ዋትሰንን' አለኝ። 'እሱን ለማምጣት አንድ ሰዓት አይፈጅብኝም ጌታየ፣ ያለዚያ ሞት ይቀድምህና እሱንም ላታየው ትችላለህ' ብየው መጣሁ።"

ስለመታመሙ የሰማሁት አንዳችም ነገር አልነበረምና ደነገጥሁ። ቶሎ ብየ ኮትና ባርኔጣዬን አነሳሁና እየተጓዝን እያለን ዝርዝር ሁኔታውን እንድታጫውተኝ ጠየቅኋት።

"ጌታዬ፣ አንድ ነገር ልንገርህ። በቱምስ ወንዝ አካባቢ በሚገኙ የኢንዱስትሪ መንደሮች የሆነ ሥራ ይሠራ እንደነበር ታውቃለህ። በሽታውን ያመጣው ከዚያ ነው። ከሮብ ዕለት ጀምሮ ከአልጋው ንቅንቅ አላለም። ላለፉት ሦስት ቀናት ምግብ የሚባል ነገር በአፉ አልዞረም።"

"ያንተ ያለህ! ለምን ዶክተር አልጠራሽለትም።"

"ፈቃደኛ አልሆነም። እንደምታውቀው እሱ አዋቂ ሰው ነው። ትዕዛዙን ልጥስ አልደፈርኩም። ነገር ግን ሕልፈተ ሕይወቱ እየተቃረበ መምጣቱን ዓይኑን አይተህ ትፈርዳለህ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

እውነትም በጣም አሳዛኝ ፍጡር ነው። ጭጋጋማው የወርሐ ሕዳር የፀሐይ ብርሃን ደብዝዟል። የበሽተኛው ክፍል ገና ከሩቅ ይቀፋል። ፊቱ ክስትብሏል። ዓይኖቹ አትኩረው ሲመለከቱኝ ልቤን ተስፋ አስቆረጡት። የእሳት ነበልባል የሚረጩ ይመስላሉ። ግራና ቀኝ ጉንጮቹ ቀልተዋል። ከንፈሮቹ ደርቀዋል። አልጋ ልብሱ ላይ ያሉትን ቀጫጭን እጆቹን ያነሳ-ይጥላቸዋል። ይቁነጠነጣል። አልፎ አልፎ ጉረሮው ላይ የማንቋረር ድምጽ ይሰማል። ወደ ክፍሉ ስገባ ፀጥ ብሎ ተኝቷል። ማንነቱን እንዳወቀ ከዓይኖቹ ላይ ማንበብ ይቻላል።

"እሺ ዋትሰን፣ መጥፎ ሁኔታ ውስጥ እየወደቅን መሰለኝ" አለ በደከመ ድምፅ። ቀደም ሲል ይታይበት የነበረው የልቡ-መሉነት ስሜት የተለየው አይመስልም።

"ወይኔ ወንድሜን!" አልኩና እየቀረብኩት ስሄድ፡-

"ተመለስ! አሁኑኑ ወደ ኋላ ተመለስ!" አለኝ ኮስተር ባለና ባልተለመደ የአነጋገር ቃና። "ዋትሰን ብትጠጋኝ ከዚህ ቤት አስወጣሀለሁ።"

"ግን ለምን ?"

"ያ የራሴ ጉዳይ ነው። አይበቃም?"

ሚስዝ ሐድሰን እውነቷን ነው። ዋትሰን አዋቂ ሰው ነው። ያን የመሰለ ጥበበኛ ሰው ደግሞ እንደዚህ ድክም ብሎ ሲታይ በጣም ያሳዝናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

"የሕክምና ዕርዳታ ላደርግልህ እፈልጋለሁ" አልኩት

"ትክክል፡ ዕርዳታህ የተሻለ የሚሆነው ግን የተባልከውን በአግባቡ ስትፈጽም ነው::"

"በዚያ አልጠራጠርም ሆልምስ::" ሻከር ያለውን ሥነ-ምግባሩን ለማለሳለስ ሞከረ::

"አትቆጣም?" ሲል ትንፋሹ እያቃተተ ጠየቀኝ::
"እንደዚህ ስትሰቃይ እያየሁህ እንዴት ልቆጣ እችላለሁ?"

"ለራስህ ጥቅም ነው ዋትሰን" አለ እንደ እንቁራሪት እያንቋረረ::

"ያውም ለራሴ!"

"የበሽታዬን ምንነት አውቄዋለሁ:: የኩሲ በሽታ በመባል ይታወቃል:: ከእኛ የበለጠ ደግሞ ደኾች ያውቁታል:: ስለበሽታው ብዙ ባይመራመሩም እስከአሁን ርግጠኛ መሆን የተቻላው ገዳይ በሽታ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከአንዱ ወደ ሌላው በቀላሉ የሚተላለፍ መሆኑም ጭምር ነው::"

በስሜት መናገር ጀመረ:: እጆቹ እየተንቀጠቀጡ ከእሱ እንድርቅ በምልክት ያሳየኛል::

"በንክኪ ይተላለፋል ዋትሰን -አዎ በንክኪ :: ራቅ ብለህ ቁም፤ ራቅ ካልህ ችግር አይኖርም::"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ስለ እግዚአብሔር ብለህ ሆልምስ! እንደዚህ ሆነህ እንዴት ስለ እኔ ታስባለህ? ምንም አያደርገኝም። ለረጂም ጊዜ ጓደኛዬ ማድረግ የምችለው እርዳታ በዚህ ይደናቀፋል ብለህ ታስባለህ?"

ልቀጥል ስል በቁጣ አስቆመኝ። "እዚያው ከቆምክ እናገራለሁ። ያለዚያ ግን ከፍሉን ለቀህ ውጣልኝ።"

የአስተሳሰብ ልዩነት ቢኖረንም ለሆልምስ ልዩ ችሎታዎች ልባዊ አክብሮት አለኝ። አሁን ግን መ.ያዊ ስሜቱ ተቀስቅሷል። ታሞ በተኛበት ክፍል ውስጥ ያለ እኔ ሌላ የለውም። በማንኛውም ቦታ ሊያገዘኝ ይችላል። ቢያንስ በበሽተኞች ክፍል ግን አልትናው የእኔ መሆን እንዳለበት አሰብኩ።

"ሆልምስ" አልኩት። "ራስህን አታውቅም። በሽተኛ ሰው እንደ ሕፃን ነው። እንከባከብሃለሁ፣ አስታምምሃለሁ። ወደድህም ጠላህም የሕመመ.ን ምልክቶችን መርምሬ በማወቅ የሕክምና ዕርዳታ እንዳደርግልህ መ.ያዊ ሥነ-ምግባሩ ያስገድደኛል።"

የተቆጡ ዓይኖቹን ፍጥጥ አድርጎ ተመለከተኝ።

"ሐኪም የሚያስፈልገኝ ከሆነ ቢያንስ እኔ የምተማመንበት ቢሆን የተሻለ ነው" አለ ሆልምስ

"በእኔ መ.ያዊ ችሎታ አትተማመንም ?"

"በጓደኝነትህ አዎ! ያለዚያ እውነቱን እንነጋገር ዋትሰን።አንተ አጠቃላይ ሐኪም ነህ ። ዕውቀትህም ከዚህ ያልዘለለ ተራ ዕውቀት እንጅ የተለየ አይደለም። ይሆን ስል ስሜትህ ሊነካ እንደሚችል ሳላውቅ ቀርቼ አይደለም። ግን ምንም አማራጭ አልሰጠኸኝም" ሲለኝ በጣም ነበር ስሜቱ የተጎዳው።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይህ ዓይነት አነጋገር ለአንተ አይበጅህም ሆልምስ። ይህ በግልፅ የሚያሳየኝ ነገር ቢኖር ነርቭህ ትክክል ያለመሆኑን ነው። ሆኖም በእኔ መያ እምነት ከሌለህ ምንም ዓይነት ዕርዳታ አላደርግልህም። መልካም ፈቃድህ ከሆነ ሰር ዳስፐርማኪን ወይም ፔንሮስፊሸርን ወይም ሌሎች የሎንደን ዕውቅ ሐኪሞችን ላመጣልህ እችላለሁ። ያም ሆነ ይህ፣ ሰው ያስፈልግሃል። ይህ የመጨረሻ ነው። ያለምንም እገዛ እዚህ ገዘም ብየ ቆሜ ያንተን መሞት እንድመለከት የምትጠብቅ ከሆነ ተሳስተሃል።"

"ጥሩ ብለሃል ዋትሰን" አለ ሕመምተኛው እያቃሰተ። "ደንቆሮ መሆንህን ላረጋግጥልህ? ስለ ታፖኑሊ ትኩሳት ወይም ስለ ብላክ ፎርሞሳ ኮራፕሽን ምን ታወቃለህ?"

"ስለ ሁለቱም ሰምቼ አላውቅም።"

"በሽታው ብዙ ውስብስብ ችግሮች አሉት ዋትሰን። ምሥራቃውያን ስለ ልዩ ልዩ በሽታዎች አያሌ ምርምሮች አድርገዋል።" የመናገር አቅሙን ለማሰባሰብ በዝምታ ተውጦ ቆየ። "በትርብ ጊዜ ከሕክምና ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን በተመለከተ ካደረግናቸው ጥናቶች ብዙ ትምህርት ወስጃለሁ። በሽታውን የሸመትኩትም በዚሁ እንቅስቃሴ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ነው። ምን ታደርገዋለህ።"

"ላይሆንም ይችላል። ለማንኛውም ዶክተር አይንስትሪ የሚባል የትሮፒካል በሽታዎች ከፍተኛ ተመራማሪ ሎንደን ውስጥ እንደሚገኝ አውቂያለሁ። መወቃቀሱ ዋጋ የለውም ሆልምስ ። ብዙ ጊዜ ሳልፈጅ ላመጣው መሄዴ ነው" አልኩትና ወደ በሩ አመራሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደዚህ ደንግጨ አላውቅም። በሽተኛው በሚያስገርም ፍጥነት እንደ ነብር ዘሎ መንገዱን ዘጋብኝ። የበሩ ቁልፍ ጥርቅም ተደርጎ ሲዘጋ ይሰማኛል። እሱም በቅጽበት እየተንገዳገደ ተመለሰ። ከድካም የተነሳ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል።

"ዋትሰን፣ መቼም በግድ ነጥተህ ቁልፉን አትወስድብኝም። አንተን ጓደኛዬን አግኝቻለሁ። እኔ እስከሚሻለኝ እዚሁ ትቆያለህ። አይዞህ አጫውትሃለሁ፣ አዝናናሃለሁ።" ሲናገር አሁንም ትንፋሹ ይቆራረጣል። "አንተ ከልብህ ለእኔ ደህንነት የምታስብ ሰው እንደሆንክ በደንብ አውቃለሁ። ሬጋ በል፣ ትሄዳለህ። ሰውነቱ በረድ እስኪል ግን ትንሽ ጊዜ ስጠኝ። አሁን አሥር ሰዓት ነው። አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ መሄድ ትችላለህ።"

"ይህ እኮ እብደት ነው ሆልምስ"

"ሁለት ሰዓት ብቻ ታገሰኝ ዋትሰን። በአሥራ ሁለት ሰዓት እንደምትሄድ ቃል እገባልሃለሁ። ትቆያለህ አይደል?"

"እንዲያውስ ምን አማራጭ አለኝ?"

"ምንም አማራጭ የለህም ዋትሰን። በጣም አመሰግናለሁ። ልብሴን ስማስተካከል ምንም እገዛ አያስፈልገኝም። ዋትሰን፣ አሁን ሌላ ተጨማሪ ግዴይ ልሰጥህ ነው። እገዛ የሚያስፈልግህ ከእኔ ሳይሆን ቅድም ከጠቀስኳቸው ሰዎች አንዱ ነው። ምርጫውን ለእኔ ተወው።"

"ያለውን አማራጭ ሁሉ እጠቀማለሁ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዋትሰን፣ እዚህ ክፍል ከገባህ ጊዜ ጀምሮ ሦስት ስሜትን የሚነኩ ታላላት ተናግረሃል...። እዚያ ጋ ጥቂት መጽሓፎች ታገኛለህ። ...በጣም ድክም ብሎኛል። ድንጋዩ ያለቀ ባትሪ ሆኛለሁ። ዋትሰን፣ ውይይታችንን በአሥራ ሁለት ሰዓት እንቀጥላለን።"

ውይይቱ ግን ከተባለው ሰዓት ቀደም በሉ እንዲቀጥል ነበር የተወሰነው። ያን አልጋው ላይ ፀጥ ብሎ የተኛውን ሰው ቀጥ ብየ ቆሜ ለደቂቃዎች አትኩሬ ተመለከትሁት። በከፊል ፊቱን ሸፍኖ ስለነበር እንትልፍ የወሰደው ይመስላል። አዕምሮየን አነባበቤ ወደ ንባብ ላመጣው አልቻለኩም። ስለዚህ በክፍለ ውስጥ በዝግታ ወዲያና ወዲህ እየተንጎራድኩ ግድግዳው ላይ የተደረደረውን የታወቁ ሰዎች ፎግራፍ አንድ በአንድ ተመለከትሁት። ፎቶግራፎቹ የግድግዳ ጌጥ ሆነዋል። ዓላማ ቢስ የሆነ የቤት ውስጥ ሽርሽር በማድረግ ላይ እያለሁ አሳት ማንደጃው ዳር ካለ የዕቃ መደርደሪያ ቁም ሳጥን ሥር ደረስኩ።

ቁርጥራጭ ቢንቢዎች፣ የሲጋራ ጋኮ፣ ሲሪንጆች፣ የሽንጥ ቀለሆች ወዘተ... ዝርክርክ ብለው ተቀምጠዋል። በእነዚህ በተልከሰከሱ አልባሌ ቁሳቁስ መካከል ጥቁርና ነጭ ቀለም ያላት ባለ ተንሸራታች ክዳን ትንሽ የገረጣ ጥርስ ሳጥን ተቀምጣለች። ምን እንደሆነች መርምሬ ለማወቅ ጠጋ ብየ እጅን ስዘረጋ፣ በጣም አስፈሪ የሆነ ጩኸት አሰማ። ከቤት አልፎ እስከ መኪና መንገዱ ድረስ የሚሰማ አስደንጋጭ ጩኸት። ሀኑራ ቆመ ሰውነቴም ቀዘቀዘ። ዘወር ስል በንዴት የጋለ ፊት፣ በቁጣ ተንልጉሎ ሊወጣ የደረሰ ዓይን ገጠመኝ። ትንሿን ሳጥን በእጁ እንደያዝኩ እዚያው ደርቄ ቀረሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"አስቀምጠው! አሁኑኑ አስቀምጠው! ዋትሰን። አስቀምጠው ብየሃለሁ!" ሳጥኑን ወደ ነበረበት ስመልስ ራሱን ትራሱ ውስጥ ቀብሮ የእፎይታ ትንፋሽ አሰማ። "ያስቀመጥክ-ት ዕቃ ሲነካብኝ አልወድም· ዋትሰን። አንተም ታውቃለህ። ትዕግሥቴን አስጨረስከኝ። አንተ ሐኪም ነህ። ሥራህ ደግሞ በሽተኞችን መንከባከብ ነው። በል አንተም ተቀመጥ እኔም ልረፍበት።"

አጋጣሚው በአዕምሮየ ውስጥ መጥፎ ስሜት ፈጠረብኝ። ረብሻና ምክንያት አልባ ብስጭቱን ተከትሎ ያወረደው ድፍረት የተሞላበት ንግግሩ የውስጡ ያለመረጋጋት ነፀብራቅ እንደሆነ አሳይቶኛል። ከጉዳቱ ሁሉ ልዩ ችሎታ ባለው ሰው ላይ የሚደርስ ጉዳት በጣም አሳዛኝ ነው። የተጠቀሰው ጊዜ እስኪያልፍ መከፋቱን በገዘምታ አጅየ ተቀመጥሁ። ወደ ሰዓቱ ብቻ ሳይሆን ወደ እኔም የሚመለከት ይመስላል። ምክንያቱም ከቅድመ· ተመሳሳይ በሆነ የጋለ ስሜት መናገር ሲጀምር አሥራ ሁለት ሰዓት እንኳን አልሞላም።

"እሺ፣ ዋትሰን" አለ ሆልምስ ። "በኪስህ ውስጥ ዝርዝር ገንዘብ ይኖርሃል?"

"አዎ"

"ብርስ?"

"በመጠን·"

"ስንት·"

"አምስት·" አለኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

"እህ፣በጣም ትንሽ ነው። እንዴት አለመታደል ነው ዋትሰን? ለማንኛውም እነሱን በምሥጢር ኪስህ ታስቀምጣቸዋለህ። ቀሪውን ፕንዘብህን ደግሞ በሱሪህ የግራ ኪስ። አመሰግናለሁ። እንዲያ ሲሆን ሚዛኑን ይጠብቅልሃል።"

የለየለት ዕብደት ነበር። ይንተባተባል። ከዚያም የሳል አይሉት የለቅሶ ድምፅ አሰማ።

"አሁን ጋዙን አብራው ዋትሰን። ግን ከግማሽ በላይ እንዳይበራ ጥንቃቄ አድርግ። በጣም ጥሩ። አመሰግናለሁ። አይሆንም መጋረጃውን መግለጥ አይኖርብህም። አሁን ጥቂት ደብዳቤዎችና መረቀቆች ወደ እኔ ጠጋ አድርገህ እዚህ ጠረጴዛ ላይ እንድታስቀምጥልኝ መልካም ፈቃድህን አጠይቃለሁ። አመሰግናለሁ። አሁን ደግሞ ከዕቃ መያርያሪያ ሳጥኑ ላይ ካሉት ቁርጥራጭ ነገሮች ጥቂቱን አምጣልኝ። ግሩም ዋትሰን! እዚህ ጋ መቆንጠጫ አለልህ። ያችን የገዘሃን ጥርስ ሳጥን አምጣና ከወረቀቆቹ መካከል አስቀምጣት።መልካም! አሁን በታችኛው በርክ፣ 13ኛው ጉዳና የሚኖረውን ሚስተር ክልቨርተንን ሄደህ ማምጣት ትችላለህ።"

እውነቱን ለመናገር ዶክተር ለማምጣት የነበረኝ ፍላጐት ተዳክሟል። ምስኪኑ ሆልምስን እንደዚያ እያቃሰተና እየተወራጨ ባዶ ቤት ጥሎ መሄድ አደጋ ሊያስከትል ይችላል የሚል ፍራቻ አደረብኝ። ይሁን እንጂ የተባለውን ዶክተር ለማግኘት በጣም ነጐድ ስለነበር ብቻህን ትቼህ አልሄድም ብለው ቺክ እንደሚል ስላወቅሁ... "እንደዚህ የሚባል ሰው ሰምቼ አላውቅም" አልኩት።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ወንድሜ ዋትሰን፣ ላታውቀው ትችላለህ። ሆኖም ስለ በሽታው ጠንቅ የሚያውቅ በዓለም ላይ ብቸኛው ሰው ዶክተር ላይሆን ገበሬ ነው ቢባል ሊያስገርምህ ይችል ይሆናል። ሚስተር ክልቨርተን ስሚዝ የታወቀ የሰማተራ ኗሪ ነው። አሁን ሎንደንን በመገብኘት ላይ ይገኛል። በሽታው ሕክምና በማይገኝበት የአርሻ ልማት ሠራተኞቹ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። በዚህም ስለበሽታው ሰፊ ጥናት እንዲያደርግ አጋጣሚ ተፈጠረለት። ጥናቱ ከታሰበው በላይ ውጤታማ ሆነ። በጣም ብልህ ሰው ነው። ከዚህ ባለፈ ግን ከአሥራ ሁለት ሰዓት በፊት እንድትሄድ አልፈልግም። ምክንያቱም በጥናት ክፍሉ ውስጥ እንደምታገኘው ስለማውቅ ነው። ስለበሽታው ያለውን ልምድ ወይም ገጠመኝ መኖሩ ለእኛ እንዲያካፍለን የምታሳምነው ከሆነ ትልቅ እገዛ ሊያደርግልኝ እንደሚችል አልጠራጠርም።"

ሆልምስ ሲናገር ትንፋሹ ይቆራረጣል። እጁንም ያወራጫል። ድርጊቱ ሁሉ ስቃይ የበዛበት መሆኑን ያሳብቃል። አብሬው በቆየሁባቸው ጥቂት ሰዓታት የከፋ እንጅ የተሻለ ነገር አላየሁም። ዓይኑ ሲፈጥ፣ ፊቱ ሲጨማደድ፣ ላቡ በግንባሩ ላይ ሲንቸረፈፍ ይታያል። ያም ሆኖ ግን ተንፋሹን አሰባስቦ ከመናገር ወደኋላ አላለም። እንደዚያ አያጣጣረ ሽንፈቱን መቀበል አይሻም—ሆልምስ እጁን አልሰጠም።

"በምን ሁኔታ ላይ እያለሁ ትተኸኝ እንደሄድክ አውነቱን ንገረው" አለኝ። "አንተ ራስህ የተሰማህን ስሜት በትክክል ገልፀህ አስረዳው---በጣዕረ ሞት ላይ ያለ የሚያደርገውን ያጣ ሰው መሳው የውቲያኖስ መደብ በዕልፍ አዕላፍ ዓሣ ለምን እንዳልተሸፈነ ማሰብ አልቻልክም። አቤት መላክር! አንጐልን አንጐል ሲቆጣጠር! ታምር ነው !---ለመሆኑ ምን እያልክ ነበር ዋትሰን?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ስለሚስተር ኩልቨርተን።"

"እም፣ አስታወስክ። ለሕይወቱ ወሳኝ ነገር ነው። በመካከላችን ጥሩ ስሜት ባይኖርም እንደምንም ብለህ ተማፀነው። በእህቱ ልጅ- ዋትሰን ትሰማኛለህ? በነፍስ ማጥፋት ወንጀል አጠረጥረዋለሁ። ጉዳዩን በጥሞና እንዲያስብበት ነግሬው ነበር። ወጣቱ በሚያሰቅቅ ሁኔታ ነው የተገደለው። እናም በእኔ ላይ ቂም ይዟል። ዋትሰን፣ ስሜቱን ለማለስለስ ሞክር። በእጅ በእግሩ ንብተህ፣ ለምነህና ተለማምጠህ ወደዚህ እንዲመጣ አድርገው። ሊያድነኝ የሚችል እሱ ነው። እሱ ብቻ!"

"ማምጣት ካለብኝ በጋሪ ይገፍው አመጣለሁ።"

"እንደዚያማ ብለሙ ነገር የለም። አሳማኝ ምክንያት ሰጥተኸው ብቻህን መመለስ ነው ያለብህ። የፊለግኸውን ሰበብ ፍጠር እንጅ አብረኸው አትመለስ። ልብ በል ዋትሰን ። እንዳታዋርደኝ። አዋርደኸኝም አታውቅም።"

ያ የበሩህ አዕምሮ ባለቤት የሆነ ታላቅ ሰው እንደ ሕፃን ልጅ እየተንተባተበ ትቼው ወጣሁ። ቁልፉንም ሲሰጠኝ በደስታ ነው የተቀበልኩት። ከውስጥ ይቆልፈዋል የሚል ሥጋት ነበረብኝ። ሚስዝ ሐድሰን ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠና እያስቀሰች መተላለፊያው ላይ ሆና ትጠብቃለች። ከፎቁ እየወረድሁ እያለሁ የሆልምስን ቁጭን ሆኖ የሚሰቀጥጥ የማቃሰት ድምጽ ከኋላየ ሰማሁ። ከታች መርጀ ጋሪ ለማስቆም ሳፋጭ ጉም ነበር። ወዲያው አንድ ሰው ወደ እኔ መጣና፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያ ሚስተር ሆልምስ እንዴት ነው ጌታየ?" ሲል ጠየቀኝ።

የስኮትላንዱ ኢንስፔክተር ሞርተን የቀድሞ ወዳጄ ነው። ግሪንርገር ልብስ ለብሷል።

"በጣም ታሚል" አልኩት።

ሲያየኝ አስተያየቱ በጣም ለየት ያለና ዘና ያለ ነበር። በፊቱ ላይ ደስታ ይነበባል።

"አንዳንድ ጭምጭምታ ሰምቻለሁ" አለ

እኔ በጋሪ ስሄድ እሱ እዚያው ነበር። የታችኛው በርክ ጐዳና በዳርና በዳሩ በታነፁት ጥሩ ጥሩ ቤቶች የሚታወቅ ሲሆን በኖቲንግ ሂልና በኪንግስተን መካከል ይገኛል። በተለይ በጋሪ የምንሄድበት ቤት ያለበት ሰፈር መንገዱ፣ አጥሩም ሆነ በሩ በጥንት ሞዴል የተሠራ ቢሆንም አነባቢው ውበት አልተለየውም። የቤቱ ግቢ የተከበረ ነው። ብዙ ታጣፊ በሮች ከመዳብ የተሠሩ ብልጭልጭ ነገሮች ይታያሉ። ትለዩቱ የአልፍኝ አሽከር የለበሰው ልብስ ኮኒላው በሚበራው የኤሌትሪክ ብርሃን ፀዳል ሲያዩት ሐምራዊ ቀለሙ ደምቆ ይታያል።

"ሚስተር ኩልቨርተን ስሚገኝ ፊልጌ ነበር። ዶክተር ዋትሰን አባላለሁ።"

"ሚስተር ኩልቨርተን ስሚገ አሉ። ዶክተር ዋትሰን! እሺ ጌታየ፣ ካርድዎን አሰጣቸዋለሁ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

የመጠሪያም ሆነ የማዕረግ ስሜ የሚስተር ኩልቨርተን ስሚዝን ልብ ያስደነገጠ አይመስልም። ገርበብ ብሎ በተዘጋው በር በኩል ንጭንጭ ያለ ጆሮ አደንቋሪ ድምፅ ይሰማኛል።

"ማነው እሱ? ምንድነው የሚፈልገው? ለመሆኑ ስንት ጊዜ ነው የነገርኩህ ስቲፕልስ? በጥናት ላይ እያለሁ ማንም እንዳይረብሸኝ አላልኩህም?"

የእልፍኝ አሽከሩ ጨዋነት በተመላበት ያነጋገር ለዛ ለማረጋጋት ሞከረ።

"ቢሆንም አላነጋግረውም ስቲፕልስ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሥራ እንዳቋርጥ አልፈልግም። ቤት ውስጥ አለመኖሬን ንገረው። ማናገር ከፈለገ ጧት እንዲመጣ አድርገው" አለ እንደማጉረምረም እያለ።

"በቃ፤ በቃ ይቅርብኝ ንገረው። ጧት መምጣት ይችላል። ካልቻለም ይቅር።ለእሱ ሲባል የእኔ ሥራ መደናቀፍ የለበትም።"

ሆልምስ በታመመ ጐኑ ከተኛበት አልጋ ላይ እየተገላበጠ ከአሁን አሁን 'ዕርዳታ' ደረሰልኝ እያለ ደቂቃዎችን ሲቆጥር በዓይነ -ሕሊናዬ ታየኝ። ቆሜ የማይበት ጊዜ አይደለም። የእሱ በሕይወት መኖር በእኔ ፍጥነት ይወሰናል። በመሆኑም ትሑቱ የእልፍኝ አሽከር መልስ ከማምጣቱ በፊት እሱን አልፌ ወደ ክፍሉ ዘው ብየ ገባሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከእሳት ዳር ከተቀመጠ ተለማጭ የመደገፊያ ወንበር ላይ የተነሳ ሰው በቀጭን ድምፁ የቴጣ ጨዋነት ያሰማል። ወደ ቢጫነት የማዘነደው የትልት ሰው ፊት ይታየኛል። ፊቱ ሽክራ፣ የሚያብለጨልጭና አገጩ ትልት ነው። ቺፍግ ብሎ ከበቀለው ትንድቡ ሥር አትከረው የሚያዩኝ ሰማያዊ ዓይኖቹ የጣቻ መልዕክት የሚያስተላልፉ ይመስላሉ። መላጣው ሰውየ ወደ አንድ ጉን ጋደል ያለች ትንሽ ክሩይ ኮፍያ አድርጓል። ጭንቅላቱ ትልት ነው። ትክክለኛው የሰውየው ቁመና ግን በሚያስገርም ሁኔታ ትንሽና ቀጭን ነው። የማሠበር ይመስላል። ትከሻው ጠማማ ጀርባውም ጉባጣ ነው። በሕዛንኑ የአጥንት ልምሻ እንዳለታየው መገመት ይቻላል።

"ምን እየተደረገ ነው!" ቴጣ የተመላበት ከፍተኛ የጨቨት ድምጽ አሰማ። የምን ሥራ ማስፈታት ነው? ነገ ጧት እንገናኛለን ብየ መልዕክት አልተውክም?"

"በጣም አዝናለሁ። አልኩት" ጉዳዩ ጊዜ የማሰጠው አይደለም። ሚስተር ሼርሎክ ሆልምስ ---"

የጓደኛዬን ስም መጥራቱ በትንሹ ሰውየው ላይ የተለየ ስሜት ፈጥሯል። በፊቱ ላይ ይታይ የነበረው የቴጣ መንፈስ ወዲያውኑ ከላዩ ላይ ተገፈፈ። በጥንታቱና በንታት ማዳመጥ ጀመረ።

"ከሆልምስ ጋ ነው የመጣኸው?" ሲል ጠየቀኝ።

"አዎ፣ ቤቱ ትቼው ነው ወደዚህ በችኮላ የመጣሁት"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሚስተር ሆልምስ ደህና ነው?"

"በጣም አሞታል- በሚያሰጋ ሁኔታ ላይ ነው! ለዚህም ነው ተጣድፌ ወደዚህ የመጣሁት።"

ሰውየው እኔን እንድቀመጥ ጋበዘኝና ወደራሱ ሥራ ተመለሰ።ወዲያው በብራው ላይ ባለው መስታወት የሰውየውን ፊት ስመለከት የተንከል ፈገግታ በገጽታው ላይ አነበብኩ። ያም ሆኖ ,የነርቭ መኮማተር ይሆናል ብየ ራሴን ጥርጣሬ ውስጥ ከተትኩት። በሚያስገርም ሁኔታ በትጽበት ውስጥ ፊቱን ወደ እኔ አዙሮ እውነኛው ስሜቱን አሳየኝ።

"በጣም አዝናለሁ" አለኝ። "እኔ ሚስተር ሆልምስን የማውቀው ባለን አንዳንድ የሥራ ግንኙነት ነው። በጠባዩም ሆነ በችሎታው በጣም የማደንቀው ሰው ነው። እሱ የልምድ ወንጀል መምርማሪ እንደሆነ ሁሉ እኔም የልምድ ደዝተር (ሐኪም) ነኝ። እሱ ወንጀለኛን ለማጥፋት ሲታገል እኔ ደግሞ ረቂቅ ሕዋሳትን ለመዋጋት እያክማለሁ። እነዚህ የምታያቸው ለእኔ እሥር ቤቶቼ ናቸው" አለ ጠረጴዛ ላይ ወደ ተደረደሩት ጠርሙሶች፣ ቢልቃጦች፣ ማሠሮዎችና ሌሎችም ነገሮች እየተመለከተ...

"ያለህን ልዩ ችሎታ በመገንዘብ ነው ሚስተር ሆልምስ አንተን ለማግኘት የፈለገ። ለአንተ ከፍተኛ ግምት አለው። በመሆኑም ለንደን ውስጥ ካሉት ባለመያዎች ሁሉ ልትረዳው የምትችል አንተ ብቻ መሆንህን ይናገራል።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰውየው መናገር ሲጀምር ራሱ ላይ የነበረችው ትንሽ ኩፍያ ወለል ላይ ወደቀች። በፊትም በቅጡ አልተደረገችም ነበር።

"ለምን?" ሲል ጠየቀ። ሚስተር ሆልምስ እኔን ለችግሩ ይያደርስልኛል ብሎ እንዴት አሰበ?"

"ከምሥራቅ ስለመጡ ተላላፊ በሽታዎች ባለህ ዕውቀትና ክህሎት።"

"የያዘው በሽታ ከምሥራቅ የመጣ መሆኑን እንዴት አወቀ?"

"የራሱን የምርምር ሥራ ሲያካሂድ ከቻይና መርከበኞች ጋር ይሠራ ስለነበር..."

ሚስተር ኩልቨርተን ስሚዝ ደስ በሚል ፈገግታ ትንሿን ኩፍያ ከወደቀችበት አነሳ።

"አዎ ሊሆን ይችላል" አለ። "አንተ የምታስበውን ያክል አደጋ እንደማይከሰት ተስፋ አደርጋለሁ። ለመሆኑ ሕመሙ ከጀመረው ስንት ቀን ሆነው?"

"ሦስት ቀናት ገደማ"

"ይቃጣል?"

"አንዳንዴ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ፓ!ፓ! በጠና ታሟል ማለት ነው። ለዚህ ፈጣን ምላሽ አለመስጠት ኢ-ሰብአዊት ነው። ሚስተር ዋትሰን፣ እኔ የጀመርኩትን ሥራ ማቋረጥ አልወድም። ይኸ ግን የተለየ ሁኔታ ስለሆነ አሁኑኑ አብረን እንሄዳለን።

የሆልምስን የፍርድ ቤት የማዘግየ ወረቀት አስታወስኩ።

"እኔ ሌላ ቀጠሮ ስላለኝ አብሬ አልሄድም" አልኩት።

"በጣም ጥሩ። ብቻዬን እሄዳለሁ። የሚስተር ሆልምስ አድሪሻ ማስታወሻዬ ላይ አለ። ብዘገይ እንኳን በግማሽ ሰዓት ውስጥ እዚያ እንደምገኝ እርግጠኛ ነኝ።

እንደዚያ እያጣጣረ ብቻውን ትቼው ሄጄ ስለነበር ሕይወቱ ልታልፍ ትችላለች በሚል ፍራቻ ልቤ ታምቡር ይመታል። ወደ ሆልምስ መኝታ ክፍል ገባሁ። እንዲያውም ከነበረበት ሁኔታ አገግሞ ነው ያገኘሁት። ሰውነቱ በጣም የተጉዳ መሆኑ ቢታወቅም ከድካሙ በስተቀር ቀደም ሲል የነበረው መታገቱ ምልክት አይታይበትም። በጉጉት ነበር የሚጠብቀኝ።

"አገኘኸው ዋትሰን?"

"አዎ፣ እየመጣ ነው።"

"ግሩም ዋትሰን፣ ግሩም መልእክተኛ!"

"አብሬው እንድመለስ ፊልጌ ነበር።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያማ ሊሆን አይችልም ዋትሰን! ለመሆኑ ምን በሽታ እንዳመመኝ ጠየቀህ ?"

"አዎ፣ እኔ ግን በምሥራቅ ሱንደን ስላሉት ቻይናውያን የመርከብ ኩባንያ ሠራተኞች ነገርኩት።"

"ትክክል! ዋትሰን ከአንድ ጥሩ ጓደኛ የሚጠበቀውን አደራ ሁሉ በትክክል ተወጥተሃል። አሁን ኩቲህን ከዚህ አጥፋ።"

"እዚህ ቆይቼ የሚሰውን መስማት አፈልጋለሁ።"

"አባባልህ ትክክል ነው። ነገር ግን ዘና ብሎ የሚናገረው ብቻችንን ስንሆን ነው። ካልጋየ ሥር በራስጌ በኩል ተደብቀህ ማዳመጥ ትችላለህ።"

"እንዴት ሆኖ ሆልምስ?!"

"ዋትሰን፣ ምንም አማራጭ የለንም። ይኸ እዚህ ክፍል ምንም ነገር ለመደበቅ አያመችም። እሱም ጥርጣሬ እንዲሰማው አንፈልግም። ግባ ዋትሰን! የተለየ አማራጭ የለንም።"

ድንገት ተነስቶ ቁጭ ሲል በለውጡ ላይ ድካም ይታየበት ነበር።

"ከውጭ የተሸከርካሪ ድምፅ ይሰማል ዋትሰን! ቶሎ በል! የምትወደኝ ከሆነ ቶሎ በል ምንም ይሁን ምን ጊዜ አታጥፋ። ትሰማኛለህ! እንዳትናገር! እንዳትንቀሳቀስ! ጀሮህን ቀስረህ ብቻ በጥሞና አዳምጥ" ከማለቱ ያ በድንገት ታይቶ የበረው ብርታቱ በተመሳሳይ ቅጽበት ጥሎት ጠፋ። እንደቡቱ ታሠረ፣ ሁለንተናው ተገለፈለፈ። አልፎ አልፎም ቢሆን ማጉረምረምና መቃተት ጀመረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደዚያ ተጣድፌ በተሸሸግሁበት ቦታ ውስጥ እያለሁ በደረጃው ላይ የዕግር ኩቴ፣ ቀጥሎም የመኝታ ክፍሉ በር ሲከፈትና ሲዘጋ ይሰማኛል። ከዚያ በኋላ ሰፍኖ የነበረው የፀጥታ ድባብ በበሽተኛው ሃይለኛ የማቃሰት ትንፋሽ ተሰበረ። እንግዳው ከአልጋው ገን ቆሞ የበሽተኛውን ሥቃይ እየተመለከተ እንደሆነ ገምቻለሁ። በመጨረሻ ራሱ መናገር ጀመረ።

"ሆልምስ!" አለና ድምፁን ከፍ አድርጉ ተጣራ። "ሆልምስ!" አለ ደገመና የተኛን ለመቀስቀስ በሚመስል የድምጽ ቃና። "ሆልምስ አትሰማም!" አለና ትከሻውን ይዞ ነቀነቀው።

"ሚስተር ስሚዝ ነህ?" አለ ሆልምስ በለሆሳስ ። "ትመጣለህ የሚለው ተስፋዬ የመነመነ ነበር።"

ሚስተር ስሚዝ ሳቀ።

"መምጣት ባይኖርብኝም ይኸው መጥቻለሁ" አለና በመቀጠል "የእሳት ፍም ሆልምስ የእሳት ፍም!" አለው። (ጠላትህ በራብ አበላው ፣ቢጠማም አጠጣው ይህን ባታደርግ የእሳት ፍህም በራስ ላይ ትከምራለህ እንዲል ታላቁ መጽሐፍ)

"ደግ ሰውነህ-በጣም የተከበርኽ ሰው ችሎታህን በጣም አደንቃለሁ።"

ስሚዝ የሺመጥ ፈገግታ ፈገገ።

"...ለመሆኑ ምን እንደሆንክ አውቀኽል

"ያው እንደሰማኽው ነው"

"እህ! ምልክቶቹን ታውቃቸዋለህ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"በማ!"

"አያስደንቀኝም ሆልምስ። መሆኑ አያስደንቀኝም። ያ ምስኪን ቪክቶር በአራተኛው ቀን ነው የሞተ። ጠንካራና የደስ ደስ ያለው ለግላጋ ወጣት ነበር። በእርግጥ አንተም እንዳልከው በሚገርምና ባልታሰበ ሁኔታ ይህን ከአስያ የመጣ በሽታ ሸምቶ መሆን አለበት--መኻል ሰንደን ላይ በዚህ በሽታ ላይ ልዩ ጥናት አድርጌአለሁ። ያንተ ደግሞ የተለየ አጋጣሚ ነው። ሆልምስ። ማስታወስህ፣ ንብዝናህን ያመለክታል። ከዚህ ውጭ ማለቡ ግን ቅንነት አይመስለኝም።"

"የገደልከው አንተ መሆንህን አውቃለሁ"

"እርግጠኛ ነህ? ታውቃለህ? ምንም ማስረጃ የለህም። ኧረ ለመሆኑ ያን ዓይነት- ሪፖርት በእኔ ላይ አያሠራጨህ ሲቸግርህ ከእኔ ሥር ተንበርክከህ ዕርዳታ ስትፈልግ ምን ይለማሃል? ምን የሚለት ጨዋታ ነው እስቲ...?"

የበሽተኛው ንርናና ድምጽና የደከመ ትንፋሹ ይሰማኛል። "ውሃ ስጠኝ!?" አለ እያቃሰተ።

"ሞትህ እየተቃረበች ናት። የእኔ ወንድም። ሆኖም አንድ ቃል ላልነግርህ እንድትሰናበት አልፈልግም። ውሃ የምሰጥህም ለዚህ ነው... እየሰማኸኝ ነው?"

ሆልምስ በሃይል አቃሰተ።

"እባክህ የምትችለውን ሁሉ አድርግልኝ። ውሾን ያነሳ ... ይሁን " አለ በለሆሳስ። "ከውስጤ ያለውን ሁሉ አወጣዋለሁ--ቃል ነው አተወዋለሁ --ብቻ አድነኝ--ሁሉንም ረሳዋለሁ።"

"ምኑን ነው የምትረሳው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"የቪክቶር ሳቬጅን ሞት-- አንተ መግደልህን እዚሁ አምነሃል ብየ ነው--ምንም አይደል አተወዋለሁ።"

"ተውከውም አልተውከውም የራስህ ጉዳይ ነው። እንደፈለግህ። ከእንግዲህ በእኔ ላይ ለመመስከር ምሥክሮች በሚቆመብት ሳጥን ውስጥ ስትቆም አላይህም። በእርግጠኝነት ፍፁም ከዚህ በተለየ ሳጥን ውስጥ ነው የማይህ። የእህቴ ልጅ እንዴት እንደሞተ አንተ አወቅህ አላወቅህ ደንታ የለኝም። እያወራን ያለነው ስለአንተ እንጅ ስለ እሱ አይደለም።"

"እውነት ነው እውነት"

"እኔን ለመውሰድ የመጣውን ሰው ስሙን ዘነጋሁት በሽታውን የሸመትከው ከምሥራት ሱንዶን ከመርከበኞች መሆኑን ነግሮኛል።"

"ለዚያ ተጠያቂው እኔ ብቻ ነኝ"

"በጭንቅላትህ ትመካለህ አይደል ሆልምስ? ንበዝ ነኝ ብለህ ትንጠራራለህ!? አሁን ግን ከአንተ ከሚበልጥ ጀግና ጋር ተጋጥመሃል። አሁን ወደ ኋላ ተመልሰህ አስብ ሆልምስ። በበሽታው ልትለክፍ የምትችልበትን ሌላ ምክንያት ማሰብ ትችላለህ?"

"ላስብ አልችልም። ናላየ ዞሯል። ስለ እግዚአብሔር ብለህ እርዳኝ!?"

"እሺ፣ አግዝሃለሁ። የት እንዳለህና እንዴት እንደሄድህ እንዲገባህ ረዳሃለሁ። ከመሞትህ በፊት የኸን እንድታውቅ እፈልጋለሁ።"

"ለሕመሜ ማስታገሻ የሚሆን ነገር ስጠኝ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"በጣም አመመህ አይደል? አዎ፣ ክሊዎች በመጨረሻዋ ሰዓት ጫጫታ ያበዛሉ። እንደ ሽባ ይቆጥሩሃል--እየተለድክ ነው።"

"እውነትም ሽባ!"

"ለማንኛውም የምልህን ስማ! በደንብ አዳምጥ!"

"የዚህ በሽታ ምልክት ከመታየቱ ጥቂት ቀደም ብሎ በሕይወትህ ያጋጠመህ አንዳች እንግዳ ነገር እንደነበር ታስውሳለህ?"

"ምንም የማስታውሰው ገጠመኝ የለም"

"እሰቲ መለስ ብለህ አስታውስ"

"በጣም ስለታመምኩ ማስታወስ አልችልም።"

"እሺ ላግዝህ። በፖስታ የመጣ ነገር አለ?"

"በፖስታ?"

"ሳጥን ምን አልባት?"

"ነፍሴን ስቻለሁ የለሁም"

"አዳምጥ፣ ሆልምስ!" በሽተኛውን እያወዛወዘ የሚቀሰቅሰው ቢመስለኝም፣ በተደበቅሁበት ክፍል ውስጥ አድፍጬ አርፎ ከመቀመጥ የተሻለ አማራጭ አልነበረኝም።



t.me/OLDBOOKSPDF

"አዳምጠኝ። በደንብ አዳምጠኝ። ስለ ሳጥኗ ታስታውሳለህ? የገዛሁን ጥርስ ሳጥን? ሮብ ቀን በፖስታ ቤት የመጣውን። ከፍተኸው ነበር- አስታወስክ?"

"አም፣ አም ከፍቼልሁ። በውስጡ ተስፈንጣሪ ብረት (ስፕሪንግ) አለ።" ትንሽ ቀልድ...

"ቀልድ አይደለም። ዋጋህን ታገኛለህ። አያገኘህም ነው። የእኔን ቀይ መሥመር አልፈህ እንድትመጣ ማን ፈቀደልህ? ባትደርስብኝ አልደርስብህም ነበር።"

"አስታወሳለሁ" አሰና ከልቡ አቃሰተ። "ስፕሪንግ!" ደም ይመጣል። ትንሿ የገዛሁን ጥርስ ሳጥን--ጠረጴዛው ላይ ያለችው"

በትክክል፣ ከአሁን በኋላ ያለህ የመጨረሻ ማስረጃ ስለሚሆን በክሴ አይዘዋለሁ። ስማኝ ሆልምስ፣ እኔ እንደምገድልህ አውቀህ እንድትሞት አፈልጋለሁ። ቨክተር ሳቨጅ ስለደረሰበት አደጋ ከሚገባው በላይ ታውቃለህ። እናም የችግሩ ተካፋይ ትሆን ዘንድ ወደ አሱ አልክሃለሁ። ወደ የሕይወትህ ማክተሚያ ጊዜ እየተቃረበ ነው ሆልምስ። እዚህ ቁጭ ብሎ ስትሞት ማየት አፈልጋለሁ።"

የሆልምስ ድምፅ መውጣት አለ። ሊሰማ ወደማይችል ደካማ ስትንፋስ ተለወጠ።

"ምንድነው?" አለ ስሚዝ "ጋዙን አብራው። ኧህ፣ እየመሸ ነው አይደል? አም፣ እንቲን ለማየት እንዲመቸኝ፣ አኔው አበራዋለሁ" አሰና ሄዶ መብራቱን ሲያበራው ወገግ ብሎ መታየት ጀመረ። "ሌላ ልሰጥህ የምችለው አገልግሎት አለ የእኔ ወንድም?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ክብሪትና ሲጋራ አፈልጋለሁ"

ይህን ስሰማ ከመደሰቴና ከመገረሜ ብዛት ልጣራ ምንም ያክል አልቀረኝም። ድምፁ ወደነበረበት የተፈጥሮ ቃናው ተመልሷል። ደክም ከማለቱ በስተቀር በፊት የማውቀው ድምጽ ነው። በመሃል ፀጥታ ሰፈነ። በውስጤ ሚስተር ኩልቨርትን ስሚዝ በሁኔታው ተገርሞ ሆልምስን ትክ ብሎ በገረምታ የሚመለከተው ይመስለኛል።

"ምን ማለት ነው?" ሲል ሰማሁት በመጨረሻ ድርቅ ባለ ሻካራ ድምፅ።

"የአንድን ገፀ ባሕሪ ድርሻ በትክክል ተውነክው የሚባለው ራሱን ሆነህ ስትሠራው ነው" አለ በለሆሳስ ። "እውነቱን ነው የምልህ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ምግብም ሆነ መጠጥ የሚባል ነገር በአፌ አልሠረም። አንተ አገዘህልኝ ያን የብርጭቆ ውሃ ከመስጠትህ በስተቀር ማለቱ ነው። ክሲጋራ መለየቱ ነበር ከሁሉም አስጨናቂ የሆነብኝ። ኧህ፤ ጥቂት ሲጋራ እዚህ አለ ለካ።" ኩበሪት ሲጫር ሰማሁ። "ከሁሉም የሚሻለው ይህ ነው። አሎሄ! አሎሄ! የጓደኞቼን ኩቱ ከውጭ እየሰማሁ ይመስለኛል።"

ይሽን ከማለቱ በሩ ተከፈተና ኢንስፔክተር ሞርተን ከተፍ አለ።

"ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል። ሰውያችሁን ተረክበኝ!" አለ ሆልምስ።



t.me/OLDBOOKSPDF

መኮንኑ ተገቢውን ዝግጅት አድርጓል።

"በሚስተር ቪክተር ሞት በቀረበብህ ክስ ምክንያት በቁጥጥር ሥር ውለሃል" አለው።

"ሼርሎክ ሆልምስን ለመግደል የተደረገው መከራ አንድ ተጨማሪ ክስ ነው" አለ ጓደኛዬ ፊገግ እያለ። " በነገራችን ላይ አሥረኛው በኩቱ የቀኝ ኪስ አንድ ትንሽ ሳጥን ስለያዘ አንዲያስረክብ ቢደረግ።"

"አመሰግናለሁ። እዚህ አስቀምጠውና በፍርድ አሰጣጡ ሃደት የራሱ ሚና ይኖረዋል።"

በድንገት የተከሰተውን ሩጫና ግብ ግብ ተከትሎ የበረታ ሳቅና ጩኸት ይሰማል።

"ራስህን ብቻ ነው የምትገዳው" ይላል ኢንስፔክተሩ። "አርፈህ ቁም፣ አትቆምም?" ሲለው ትንሽ ቡጢ ነገር ይሰማ ነበር።

"ጥሩ ወጥመድ" የሚል ክፍተኛ የቁጣ ድምጽ ይሰማል።

"ሆልምስ፣ እኔ ሳልሆን ለፍርድ መቅረብ ያለብህ አንተ ነህ። -ክሕመመ- እንድፈውሰው አስቸኳይ መልዕክት የላከብኝ እሱ ነው። አሳዝኖኝ መጣሁለት። አሁን ባልሠራሁት ወንጀል ፣ በውሸት ማስረጃ ሊከሰኝ ይፈልጋል። እንደፈለገህ መዋሸት ትችላለህ ሆልምስ፣ እኔ ግን..."



t.me/OLDBOOKSPDF

"የመድኃኒዓለም ያለህ!" አለና ሆልምስ ጮክ ብሎ ተናገረ። "ጭራሽ ረስቼዋለሁ። ወንደሜ ዋትሰን፣ በጣም ይቅርታ! ከሚስተር ኩልቨርተን ስሚዝ ጋር ጠዋት ስለተገናኛችሁ ማስተዋወቅ አይኖርብኝም። ታክሲዋ እስካሁን ትቆያለች? ለብሼ እከተልሃለሁ። ምን አልባት ፖሊስ ጣቢያ ከእኔ የሚፈልጉት መረጃ ካለ"

"ከእንግዲህ በቃ" አለ ሆልምስ ተጣጥቦ እንድ ብርጭቆ ወይን እየጠጣና ጥቂት ብስኩት እየበላ ራሱን ሊያዝናና እየሞከረ። ስለ ሠራው ጀብዱ ነበር የሚናገረው። "ይሁን እንጅ እንደምታውቀው ቋሚ ልማድ የለኝም። የዚህ ዓይነት ስኬት ለሌሎች ቢገዘፍም ለእኔ ግን አምነት ነው። ሚስ ሐድሰን የነበርከብትን ሁኔታ አይታ እንድታምን ማድረግ ነበረብኝ። እሷ አንተን ካላመነች አንተ ደግሞ እሱን ማላመን ትችላለህ በሚል የተነደፈ ዕቅድ ነው። ዋትሰን አትናደድም ብየ ተስፋ አደርጋለሁ። ከብዙምች ልዩ የሆነ ችሎታምችህ ሁሉ ምሥጢር መደበቅ የሚባል ነገር አንተ ጋ ቦታ እንደሌለው ትገነዘባለህ። ምሥጢሬን ባካፍልህ ኖሮ ስሚዝን እንደዚያ አሳምነህ ልታመጣው አትችልም ነበር። ቂመኛ ተፈጥሮውን ስለማውቅ የእጅ ሥራውን ሰመመልክት እንደሚመጣ ርግጠኛ ነበርክ።"

"ያ አስቀያሚ -ሞትን የሚጠራ ፊትህስ ሆልምስ?"

" ሦስት ቀን ጠንክሮ መያም ሰውነት አያባባም አይባልም ዋትሰን። ስለሌላው ፣ ስፖንጅ የማያፀዳው ነገር አልተቀባሁም። ግንባርህን ቫስሊን ትቀባለህ፣ ዓይንህን በጭንበል ታሰራለህ። አገጭህን ቀለም፣ከንፈሮችህን ሰም ትቀባለህ። ከዚያ ልዩ የሆነ ገጸታ ትፈጥራለህ።በዚህም



t.me/OLDBOOKSPDF

የመሞቻ ጊዜህ መቃረቡን ሰምች እንዲያምኑ ታደርጋለህ። አለመረጋጋትህን ቅጌትህን እውን ለማስመሰል ዓሣ፣ ሽልንግ ምናምን እያልክ የባጥ የቆጡን ትተባጥራለህ። ታሪክ ይኸው ነው።

"ግን ምንም በሽታ እንደሌለብህ አያወቅህ እንዴልጠጋህ የከለከልኸኝ ሰምንድ ነው?"

"ይኸን ልትጠይቀኝ ባልተገባ ነበር ዋትሰን። በሕክምና ሙያ ያለህን ችሎታ ጥያቄ ውስጥ የማስገባና በእንተ ሙያዊ ክህሎት የምሳለቅ ይመስልሃል? ከአራት ሜትር ርቀት አንተን ማታለል እችላለሁ። ያን ማድረግ ባልችል ስሚዝን ማን አምጥቶ እጅ ውስጥ ያስገባልኝ ነበር? በጭራሽ አይሳካም ነበር። ያች ሳጥን በበሽታው የተበከለ ተስፈንጣሪ ብረት ይዛለች። አቤት ሲያስፈራ ሳጥኑ ሲከፈት ስለቱ የአፋንት አፍ መስሎ ይወጣል። በእንዲህ ዓይነት ተንኮል ነው ያ ምስኪን ሳዘጅ በዚህ ጭራቅ መጥመድ ውስጥ ገብቶ ስለባ የሆነው። ራሴን በመከላከል ማድረግ የፈለግሁትን አድርጌአለሁ። በችሎታው የተጣመሰ መስሎት ሲከራከር በዘዴ ጥፋቱን አናዝገርዋለሁ። እኔ ታሽገው በማላከልኝ ፅቃዎች ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ አደርጋለሁ። ይህን እንደሚያደርግ አስቀድሜ አውቄያለሁ። እናም በሽተኛ ሆኖ የመጫወቱን ባህሪ በሚገባ ተወጥቼዋለሁ። አመሰግናለሁ ዋትሰን፣ ፖሊስ ጣቢያ መልስ ወደዚያ ወደምናውቀው ሬስቶራንት ጉራ ብለን ቀበቶአችንን ማጥበቅ አለብን።"

ተ ፈ ጸ መ



t.me/OLDBOOKSPDF

# ከውስጥ ገጾች

<< ሁላችንም በእንደዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ብንሆንና በሠርጋችን እለት ሚስትና ሃብትን የሚያሳጣ ድንገተኛ አጋጣሚ ቢፈጠርብን ራሳችንን አሁን በምናስበው አቂም ውስጥ አናገኘውም::>>

* * * *

<< ...ኧክ ፣እሀል ሠሃ ከእኔ ጋር ሲያገናኝህ አያፈቀርኩህ መጣሁ:: ስለልጂ ለእንተ ለመንገርም ፈራሁ:: እገዚር ይቅር ይበለኝ:: ላጣህ አችላለሁ የሚል ሥጋት በላደረብኝ ለእንተ ደፍሬ የመንገር ወኔ አጣሁ:: ከሁለት አንዳቷን መምረጥ ነበረብኝ:: የአሷን መኖር ለለስት ዓመታት ምሥጢር አየሆነ ያለኝት::>>

<<ኢፈ፣እኑ ጥሩ ነው አደረሰሁም:: ይሁን እንጅ አንቺ ይሆናል ብለሽ ከማታስቢኝ ነገሮች [illegible]>>

<<ለምን ጉሉ [illegible]>>

<<ሙጅ ዋችህ፡ እገ[illegible]ከ ሰው ነበ:: ሁልጊዜ ሠላን አርምኝ አ[illegible] ብዙርግጫች ምንም ሕጋዊ ማስረጃ አያ[illegible] ግለት ለክርክር የሚያበቃ ጉዳይ [illegible] ግለት ነው::

* * * *

<<የመድኃኒዓለም ንስሀ ምን ይሻለኛል?>> ቢለኝለተኛው በተቢዩ ተሰፋ ሥኝ:: <<ያ የሴትል ወሳ ሥድሲያ ያ ርኩስ ይብተራ አማንተዋታል ግለት ነው:: በእሠነት ጋደኞቹ ከሆናችሁ ኑ ተከተሉኝ:: አብረን ተባብረን ልጅቷን ከሁድ እናውጣት::>>

ዋጋው ብር 31.00

t.me/OLDBOOKSPDF